# ክፍል **1.** የቅድመ መደበኛ ትምህርት መሠረታዊ ሃሳቦች

## **1.1.** መግቢያ

በቅድመ አፀደ ሕፃናት ማለትም ከ3-4 የእድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናት እንዲያድጉና እንዲዳብሩ ከእድሜያቸውና ከደረጃቸው ጋር በተመጣጠነ መልኩ እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል። ሕፃናት ስለአካባቢያቸው መረጃ ሊሰበስቡና ሊማሩ የሚችሉት የስሜት አካላታቸዉን በመጠቀም ነው። የተለያዩ ተግባራዊ እንቅስቃሴዎችን እንዲያደርጉ እና አካባቢያቸውን በመፈተሸ እንዲማሩ በቂ የእንቅስቃሴ ነፃነት ያስፈልጋቸዋል። ከቁሳቁሶች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት የነገሮችን ምንነት እንዲያስተውሉ፣ በነገሮች መካከል ስላለው አንድነት እና ልዩነት ግንዛቤ እንዲኖራቸው፣ ነገሮችን የመያዝ፣ የመጨበጥ፣ የማንከባለል ፣የመጣል ፣ የማንሳት፣ የመክፈት ፣ የመዝጋት፣ የመፍታት፣ የመግጠም ወዘተ እድል እንዲያገኙ ማድረግ አስፈላጊ ሲሆን ለዚህም አካባቢን ማመቻቸት ያስፈልጋል።

ከላይ በአጭሩ የተቀመጠውን እውነታ የተገነዘቡ ሀገራት ከ3-4 ዓመት ላሉ ሕፃናት መርሀ ትምህርት በመቅረፅና መለኪያዎችን በማስቀመጥ በመንቀሳቀስ ህፃናቶቻቸው ለትምህርት ያላቸውን ዝግጁነት ለማሻሻል ችለዋል። በሀገራችንም ትምህርት ሚኒስቴር ከ3-4 ዓመት ያሉ ሕፃናትን ትኩረት በመስጠት ያዘጋጀው መርሀ ትምህርት ቢኖርም ሊከናወኑ የሚገባቸውን ተግባራት በተገቢው ደረጃ ማከናወን እንዲችሉ መምህራንን ለመርዳት ይቻል ዘንድ ይህ አጋዥ መጽሐፍ ተዘጋጅቷል።

> የቅድመ አፀደሕፃናት ዋና ዓላማ
>
> የሕፃናቱን ጤና መጠበቅና እንዲሁም በአካል፣ በአእምሮ፣ በማህበራዊ ሕይወት እና በስሜት ክንዋኔያቸው በእድሜያቸው ሊደርሱበት በሚችሉት የመዳበር ደረጃ ላይ እንዲደርሱ በማገዝ ለአፀደሕፃናት ማዘጋጀት ሊሆን ይገባል፡:

አጋዥ መጽሐፉ መርሀ ትምህርቱን በመከተል በአምስት ጭብጦች ላይ ትኩረት በማድረግ በየዘርፉ ሕፃናት ሊደርሱበት የሚገባውን የሚጠበቅ ውጤትና ብቃት ያመለክታል። መጽሐፉን በቀላሉ መጠቀም ይቻል ዘንድ የተግባር፣ የዓላማ፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ ተደርጎበታል። ከዚህ በተጨማሪም የየተግባሩን ምዘናና አጠቃላይ የመገምገሚያ ቅጽን አካቶ ቀርቧል።

## **1.2.** የቅድመ አፀደ ሕፃናት ምንነት

ቅድመ አጸደህፃናት ከ 3-4 እድሜ የሚገኙ ሕፃናትን በተገቢው ደረጃ በመንከባከብና እርስ በእርሳቸውና ከአዋቂ ሰዎች ጋር ግንኙነት በመፍጠር ማኅበራዊነትን እንዲያዳብሩ፣ አካባቢያቸውን እንዲለማመዱ፣ ጤናቸው እንዲጠበቅና በደረጃቸው ራሳቸውን ችለው የተለያዩ ተግባራትን በማከናወን የህይወት ክህሎቶችን እንዲለማመዱ በማድረግ ለአፀደ ሕፃናት የሚያዘጋጃቸው ተቋም ነው። በዚህ ተቋም የመሳተፍ እድል ያገኙ ሕፃናት በቤታቸው አካባቢ ከሚውሉት የተሻለ ንቃትና የተግባር ተሳትፎ እንደሚኖራቸው እሙን ነው። ምንም እንኳን ለእያንዳንዱ ሕፃን ወላጅ የሕይወቱ መሠረት ቢሆንም ከወላጅ ጋር አብሮና ተቀናጅቶ በመሥራት ህፃናት ለመጀመሪያ ጊዜ የሚገቡበትን ይህን ተቋም በቀላሉ እንዲላመዱትና እንዲጠቀሙበት ማድረግ ይገባል።

በአጠቃላይ ከ 3-4 ዓመት ያሉ ሕፃናት የሚገኙበት እድሜ ለቀጣዩ ደረጃ መዘጋጃና ወሳኝ በመሆኑ የሚሠራው ሥራ በሚከተሉት ነጥቦች ላይ ማተኮር ይኖርበታል።

- የሕፃናትን ሁለንተናዊ እድገት ታሳቢ ያደረጉ ተግባራትን መከወን
- የሚውሉበትን አካባቢ በቀላሉ መልመድ እንዲችሉና የሚደሰቱበት እንዲሆን የተመቻቸ ማድረግ
- ለአካል እና እንቅስቃሴ መዳበር ትኩረት በመስጠት መሠረታዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ራስን በሥርዓት የመጠበቅ ክህሎቶችን እንዲለምዱ የተመቻቸ ሁኔታ መፍጠር
- አካባቢያቸውን እንዲለዩ፣ እንዲረዱና እንዲያውቁ የስሜት አካላቶቻቸዉን የሚጠቀሙበትን ሁኔታ ማመቻቸት
- ራሳቸውን ችለው የመጫወት፣ አካባቢን የማስተዋልና የመፈተሽ እድል እንዲኖራቸው ማድረግ
- ከአካባቢያቸው ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ነገሮችን በቀናነት የሚመለከቱ እንዲሆኑ መርዳት
- በፈጠራ ሥራዎች የመሳተፍና ስሜታቸውን የመግለፅ አቅማቸውን ማጎልበት ያስፈልጋል።

## 1.3. ስለ ቅድመ አፀደሕፃናት አስተዳደግና ትምህርት ሊተኮርባቸው የሚገቡ ነጥቦች

1. ሕፃናት ሊዳብሩ የሚገባቸው ከሁለንተናዊ እድገት አንፃር ነው። ይህም ማለት የአካል፣ የአእምሮ፣ የቋንቋ፣ የማሕበራዊና ስሜታዊ እንዲሁም የፈጠራ እድገትን ያመለክታል።
2. ሕፃናት ሁሉ የሚያመሳስሏቸው ነገሮች ቢኖሩም እያንዳንዱ ሕፃን የተለየ መሆኑን መገንዘብ ይገባል። በተጨማሪም ልዩ ተሰጥኦና ልዩ ፍላጎት ያላቸው ሕፃናት ሊኖሩ እንደሚችሉ ማወቅ ይገባል።
3. ሕፃናት ተመሣሣይ በሆነ የእድገትና መዳበር ደረጃዎች የሚያልፉ ቢሆንም እያንዳንዱ ሕፃን የራሱ የሆነ የእድገት ፍጥነት እንዳለው መረዳት ያስፈልጋል።

4. ሕፃናት ስለአካባቢያቸው ግንዛቤ የሚጨብጡት በስሜት አካላታቸው አማካኝነት በመሆኑ የስሜት አካላታቸውን እንዲጠቀሙ ማበረታታት አስፈላጊ ነው።
5. ሕፃናት በንቃት ተሳትፎ በማድረግ አካባቢያቸውን ይቃኛሉ፣ ይፈትሻሉ፣ ነገሮችን ያዛምዳሉ በዚህም ችግር ፈቺ መሆንን ይለማመዳሉ ስለዚህ የመንቀሳቀስ ነፃነት ሊሰጣቸው ይገባል።
6. ሕፃናት አዲስ ነገርን የሚማሩት በመሞከር፣ በመሳሳትና በመታረም ስለሆነ ራሳቸውን ችለው አንዳንድ ተግባራትን እንዲያከናውኑ እድል ሊሰጣቸው ይገባል።
7. የሕፃናት ዋና ዝንባሌና መማሪያ መንገድ ጨዋታ ስለሆነ ተገቢው ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።
8. ሕፃናት የተሻለ የሚማሩት ከአቅማቸው ጋር የተመጣጠነና በራሳቸው የሚሸፍኑት ተግባር ሲሰጣቸው ሆኖ እገዛ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ እገዛ ማድረግ ተገቢ ነው።
9. ሕፃናት ከሌሎች ማለት ከአካባቢቸው ጋር ያላቸው ግንኙነት ለእድገትና መዳበራቸው በጣም አስፈላጊ ስለሆነ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል።

## **1.4.** ከ **3-4** ዓመት እድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናት ባህርይና የመዳበር ለውጦች

- በዚህ እድሜያቸው ሕፃናት የአካልና የእንቅስቃሴ መዳበራቸው እየተሻሻለ ስለሚመጣ አንዳንድ ተግባሮችን ራሳቸውን ችለው ማከናወን ይጀምራሉ።

- ከሌሎች ጋር አብሮ መጫወትን፣ ያላቸዉን ነገር መካፈልና ተራን ጠብቆ መጫወትን መለማመድ ይጀምራሉ።
- የእድሜ እኩዮቻቸውን ባህሪ በመመልከት መኮረጅና ማንፀባረቅ ይጀምራሉ።
- የምናብ ጨዋታ መጫወት እያስደሰታቸው ይመጣል።
- ለምን? እንዴት? የሚሉ ጥያቄዎችን መጠየቅ ይጀምራሉ።
- ተረቶችን በማዳመጥ በቀጣይ ምን ሊከሰት እንደሚችል ለመገመት ጥረት ያደርጋሉ።
- አዋቂ ሰዎችን በፈቃደኝነት መርዳት ይፈልጋሉ እድሉንም ካገኙ ደስታና ኩራት ይሰማቸዋል።
- መሠረታዊ ቀለሞችን ይለያሉ።
- በንግግር ሂደታቸው ገላጭ ቃላትን መጠቀም ይጀምራሉ።
- አጫጭር መልእክቶችን ማስተላለፍ ይችላሉ።
- በአንድ ተግባር ላይ ለረዥም ጊዜ ያለመቆየት ሁኔታ ይታይባቸዋል።

## **1.5.** የወላጆች ተሳትፎ በሕፃናት አስተዳደግና ትምህርት

ወላጆች የመጀመሪያዎቹ የሕፃናትን አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ስሜታዊና ማኅበራዊ ፍላጎቶችን የሚያሟሉ ከመሆናቸውም በተጨማሪ የመጀመሪያዎቹ አስተማሪዎችና በቀጣይ ሕይወታቸው ላይ ተፅዕኖ ፈጣሪዎች ናቸው። ምንም እንኳን የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ሕፃናትን ተንከባክበው በማሳደግና በማስተማር ለመደበኛ ትምህርትና ለቀጣይ ሕይወታቸው የማዘጋጀት ኃላፊነት ያለባቸው ቢሆንም ኃላፊነታቸውን በአግባቡ መወጣት የሚችሉት ግን ከሕፃናት ወላጆችና አሳዳጊዎች ጋር በጋራ በመሥራት መሆኑ ግልጽ ነው።

ወላጆችም ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ጋር አብረው ሲሰሩ ሕፃናቱ በትምህርት ብቻ ሳይሆን በወደፊት ሕይወታቸውም ውጤታማ ይሆናሉ፤ በራስ መተማመንን፣ ስለራሳቸው አዎንታዊ አመለካከትንና ጥሩ ባሕሪይን ያዳብራሉ፤ ጥሩ ማህበራዊ ልምድን
በመመሥረትም ደስተኛ ይሆናሉ። ወላጆችም ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ፕሮግራምጋር በመጠኑ ይተዋወቃሉ፤ ከሌሎች ወላጆች ጋር ልምድን ይለዋወጣሉ፤ በወሳኝ የመዳበር ወቅት ላይ አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግና ችግሮች ቢከሰቱ መፍትሄ የመፈለግ እድል ይኖራቸዋል።
የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራንም ወላጆች ሕፃናትን በማሳደግና በማስተማር ሥራ ላይ ከጎናቸው ሆነው ተባብረው የሚሠሩ ከሆነ በሥራቸው ውጤታማና ደስተኛ ይሆናሉ። ስለ ሕፃናት እድገትና መዳበር መረጃ ማግኘት ይችላሉ፤ ወላጆችን በማሳተፋቸው በሃሳብ፣ በእውቀት፣ በጉልበትና በቁሳቁስ ድጋፍ ያገኛሉ።

በመሆኑም ወላጆች ይህንን ተመልሶ ሊገኝ የማይችለውን የሕፃንነትን ወርቃማ ጊዜ በአግባቡ ለመጠቀም ከቅድም መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ጋር መልካም ግንኙነትን በመፍጠር በልጆቻቸው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ንቁ ተሳትፎ ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

ጥናቶች ወላጆችም ሆኑ የሕፃናት አሳዳጊዎች ከቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ጋር የሥራ አጋርነትን በመፍጠር በሕፃናት የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ላይ የሚሳተፉ ከሆነ ሶስቱም አካሎች (ሕፃናቱ፣ ወላጆችና መምህራን) ተጠቃሚ እንደሚሆኑ ይገልፃሉ።

ወላጆች በሕፃናት አስተዳደግ ትምህርት እንዲሳተፉ ለማበረታታት ጠቃሚ መንገዶች

- ወላጆች በልጆቻቸው የእድገትና የመማር ሂደት ላይ ተሳታፊ የመሆንና ልጆቻቸውን በትምህርት ቤት ጥሩ እንዲሆኑላቸው ያላቸውን ፍላጎት መረዳት
- ወላጆችን የሚደግፍና የልጆችን የመማር ሂደት ሊረዱ የሚችሉበትን ፕሮግራም መንደፍና መተግበር
- ቋሚ የሆነ ከወላጅ ጋር ግንኙነት መፍጠር /ሕፃኑን በመቀበያና በመሸኛ ሰዓት፣ በመገናኛ ደብተር፣ በስልክ፣ ወዘተ.../
- የተለያዩ የማንቂያና ግንዛቤ የማስጨበጫ ስልቶችን መንደፍ /የቡድን ውይይት በማካሄድ፣ አጫጭር ሥልጠናዎችን በማዘጋጀት፣ ወዘተ.../
- ወላጆች በሕፃኑ የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማበረታታት /እረፍት ሰዓት ሕፃናቱን እንዲያጫውቱ፣ ተረት እንዲተርቱ፣ በሽርሽር ወቅት እንዲረዱ በማድረግ፣ ወዘተ.../
- ወላጆች ዕለት በዕለት ከልጆቻቸው ጋር በሚኖራቸው ግንኙነት ስለተማሩት ነገር እንዲወያዩ ማድረግ
- የልጆቻቸውን የዕለት ተዕለት ለውጥና መሻሻል እንዲያጤኑ ማድረግ

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት በተለያዩ ፕሮግራሞች ሕፃናትን በመምራት የሚሳተፉት የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ቢሆኑም ከላይ እንደተገለጸው የወላጅ ሚና ከፍተኛ ነው። ስለዚህ ከተገለጸው በተጨማሪ ሕፃኑ/ኗን ስለቀን ውሎአቸው እንዲያወሩ ቤት በሚገባበት/በምትገባበት ጊዜ አብረው የሚሠሩትን /የሚያወሩበትን/ ሥራ በመስጠትና እንዳስፈላጊነቱ ስለሕፃኑ/ኗ ለመነጋገር ጊዜ በማመቻቸት ወላጅ አብሮ የሚሠራበትንና በሕፃናት አስተዳደግ ላይ በተገቢው አቅጣጫ የሚንቀሳቀሱበትን ሁኔታ ማመቻቸት ያስፈልጋል።

## 1.6. የመጽሐፉ አጠቃቀም

በዚህ አጋዥ መጽሐፍ ላይ የሚጠበቁ ውጤቶች፣ ብቃቶች፣ ዓላማ፣ ተግባር፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማና ምዘና በሚል ትኩረት እንዲያገኙ ምልክቶችና ደመቅ ብለው የተቀመጡ ሐረጎች በመጽሐፉ ውስጥ ይገኛሉ። የእነዚህ ምልክቶችና ሐረጎች ትርጉም በተጠቃሚዎቹ የቅድመመደበኛ ትምህርት ቤት መምህራን ሊታወቁ ይገባል። ትርጉማቸውም እንደሚከተለው ተቀምጦአል።

| ምልክቶች | በተጠቃሚዎች ሊታወቁ የሚገቡ ሐረጎች |
|---|---|
|  | የሚጠበቁ ውጤቶች፡- ሕፃናት በተጠቀሱት የብቃት ደረጃዎች ላይ ሲደርሱ በእነሱ ላይ ሊታዩ የሚገባቸው ለውጦች ናቸው። |
|  | ብቃቶች፡- ብቃቶች ሕፃናት የተለያዩ ተግባራትን በመተግበር ወይም በማከናውን ሊደርሱባቸው የሚገቡ የብቃት ደረጃዎችን ያመለክታሉ። |
|  | ተግባር፡- በአንድ ክፍለ ጊዜ ሊታቀዱና (lesson plan) ሊተገበሩ ለሚችሉ ተግባራት በርዕስነት የተቀመጠ ቃል ነዉ። ተግባራቱ በአንድ ክፍለ ግዜ እንዲከወኑ ታሳቢ ተደርገው የተዘጋጁ ተከታታይነት ያላቸው ክንውኖች ሲሆኑ በአንድ ብቃት ሥር ከአንድ በላይ ተግባር ሲኖር ተግባራቱ እንደየአስፈላጊነቱ ሊደጋገሙ እና ከአንድ ክፍለግዜ በላይ ሊተገበሩ ይችላሉ። |
|  | ዓላማ፡- ተግባራቱ ከተተገበሩ ወይም ክፍለ ጊዜው ከተጠናቀቀ በኋላ ሕፃናት ሊያገኙት የሚችሉትን ጥቅም ወይም ሊደርሱባቸው የሚችሉትን የብቃት ደረጃዎች የሚጠቁም ነው። የክፍለ ጊዜ ዕቅድ ዓላማ ሆኖም ሊያገለግል የሚችል ነው። |
|  | የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- ሕፃናት የሚፈለገው ብቃት ላይ እንዲደርሱ የሚከናወኑ ተግባራትን ለመደገፍ /ለማስተላለፍ/ ጥቅም ላይ መዋል ያለባቸውንና እገዛ ሊያደርጉ የሚችሉ መሣሪያዎችን ያመለክታሉ:: መሣሪያዎቹ እንደሚከናወነው ተግባር፣ እንደሕፃናት ዕድሜ እና የአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ የተለያዩሊሆኑ ይችላሉ። ከዚህም በተጨማሪ በመምህራን ሊታወቅ የሚገባው ነገር በዚህ ጽሁፍ ውስጥ የተጠቆሙት የመርጃ መሣሪያዎች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ከርዕሱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው መሣሪያዎችን መጠቀም እንደሚቻል ነው። መምህራን በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን እንደ መርጃ መሣሪያ አድርገው መጠቀም ይኖርባቸዋል። |
|  | የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-__በዚህ ሐረግ ሥር የተቀመጡት ሐሳቦች /ተግባራት/ ተግባሩን እንዴት ተግባራዊ ማድረግ እንደሚቻል ለመምህራን እንደ ጥቆማ የተቀመጡ ሲሆን ተግባር ላይ ለማዋል መምህራን ዕቅድን በማዘጋጀት የሕፃናትን ስሜት ማሰባሰቢያ፣ የክፍለ ጊዜውን ርዕስ ማስተላለፊያ መንገዶችንና በተግባሩ መጨረሻ የማጠቃለያ ዘዴዎችን በማካተት ሊጠቀሙ ይገባል። |
|  | ምዘና፡- ሕፃናቱ በየብቃቱ ሥር የተቀመጡትን ተግባራት በመተግበር ሂደቱና ከተገበሩ በኋላ የደረሱበትን ደረጃ ለመገምገም የሚረዳ ነው። |

| ምልክቶች | በተጠቃሚዎች ሊታወቁ የሚገቡ ሐረጎች |
|---|---|
| | የምልከታ መከታተያ ቅጽ፡- በዚህ አጋዥ ጽሁፍ በየመዳበር አቅጣጫዎቹ ወይም ጭብጦች መጨረሻ ላይ የምልከታ መከታተያ ቅጽ ተቀምጧል። ይህ ቅጽ በዓመት ውስጥ ሶስት ጊዜ /በዓመቱ መጀመሪያ፣ አጋማሽና መጨረሻ/ መሞላት ይኖርበታል። ሆኖም በቅድመ መደበኛ ትምህርት ፕሮግራም ላይ የሚገኙ ህጻናት የሚመዘኑት በተከታታይ ምዘና ሆኖ ምዘናው በየዕለቱ፣ በየሳምንቱና በወሩ መጨረሻ ላይ ሊደረግ ይገባል። በቅድመ መደበኛ ት/ቤት የሚካሄደዉ ተከታታይ ምዘና በየጊዜዉ በህጻናት ላይ የሚታየዉን አካላዊ፣ አእምሮአዊ፣ ማህበራዊ እና ስሜታዊ የመዳበር ለውጦችን በመከታተል መመዘን እንጂ በጽሁፍ ፈተና የሚከናወን ምዘና እንዳልሆነ መገንዘብ ለመምህራንም ሆነ ለወላጅ በጣም አስፈላጊ ነው። በዚህ አጋዥ ጽሁፍ ላይ በየጭብጡ መጨረሻ የተቀመጠዉ የምዘና ቅጽ የማጠቃለያ መሆኑን መምህራን ተገንዝበው የህጻናቱን እድገትና ለውጥ በየጊዜው መከታተልና መገምገም የሚኖርባቸው ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም በአባሪዉ ላይ የተቀመጡትን የምዘና ናሙና እና በመርሀ ትምህርቱ ላይ የተቀመጡትን የምዘና ጥቆማዎች መጠቀም ይቻላል። |
| | መዝሙሮች እና ተረቶች፡- በየተግባራቱ ስር የተጠቀሱት መዝሙሮች እና ተረቶች በመጽሀፉ መጨረሻ ገጾች ላይ አባሪ ተደርገዋል። |

## 1.7. የህጻናት አስተዳደግና ትምህርት እቅድ

በቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ለአስተዳደግና ትምህርት ስራ ሶስት ዓይነት ዕቅዶች ይታቀዳሉ። እነርሱም የዓመት፣ የወርና የዕለት ናቸው። ከዕለት ዕቅድ ጋር እንደ አባሪ ሆኖ የክፍለ ጊዜ ትምህርት ዕቅድ /Lesson plan/ ይዘጋጃል።

**የዓመት ዕቅድ**

- **የዓመት ዕቅድ፡-** ይህ የዕቅድ ዓይነት የቅድመ መደበኛ መርሀ ትምህርትን መሰረት በማድረግ የሚዘጋጅ ሲሆን በዓመት አንድ ጊዜ ለአስር ወራት ይዘጋጃል፡፡

**የወር ዕቅድ**

- **የወር ዕቅድ፡-** በወር ውስጥ የሚገኙትን ሳምንታት አጠቃሎ በየወሩ ለየወሩ የሚታቀድ ሲሆን የወር ዕቅድ ላይ የሚጠቀሱት በየዕለቱ የሚከናወኑት ዋና ዋና ፕሮግራሞች፣ ጭብጥና ርዕሶች ናቸው፡፡

**የዕለት ዕቅድ**

- **የዕለት ዕቅድ፡-** የዕለት ዕቅድ ለህጻናት አስተዳደግና ትምህርት በየዕለቱ የሚያከናወኑትን ተግባራት ህጻናትን ከመቀበያ ሰዓት እስከ መሸኛ ደረስ ያሉትን በሚከናወኑበት ሰዓት ቅድም ተከተል ይዞ የሚገኝ ሲሆን የዋና ዋናዎቹ ፕሮግራሞች ጭብጥና ርዕስ በቀጥታ ከወር ዕቅድ ላይ ተወስደው የሚሞሉ ናቸው፡፡ ሌሎች በየዕለቱ በተመሳሳይ ሁኔታ የሚታቀዱት የቁርስ፣ የእረፍት፣ የምሳ፣ የመኝታ እና የመሸኛ ሰዓታት በየእለቱ የሚታቀዱ ናቸው፡፡

የዕለት ዕቅድ ማቀጃ ፎርማት አራት ክፍሎች ሲኖሩት የመጀመሪያው ሰዓትን፣ ሁለተኛው የዕለቱን የስራ ይዘት፣ ሶስተኛው የክንውኑን ሂደት፣ አራተኛው ሊታረሙ የሚገባቸውን ማለትም በክንውኑ ሂደት ያጋጠሙ ሊስተካከሉ የሚገባቸው ነገሮች የሚጠቀስባቸው ናቸው። የዕለት ዕቅድ በየዕለቱ ምን መሰራት እንዳለበት፣ የታቀደው እንዴት እንደተሰራ እና በህጻናቱ ላይ ምን ለውጥ እንደመጣ በጊዜው ያለተሸፈነ ችግር ካለ ወደፊት የሚታረምበት ሁኔታ እንዲመቻች የሚጠቁም ስለሆነ በየዕለቱ የህጻናትን ለውጥ ለመከታተልና ችግሮቻቸውን ለመቅረፍ ስለሚጠቅም አስፈላጊ ነው።

የክፍለ ጊዜ ክንውን ዝግጅት፡- ይህ ሌሰን ፕላን በመባል የሚታወቀው ሲሆን በየዕለቱ ለሚከናወኑት ዋና ዋና ፕሮግራሞች የሚዘጋጅ ነው። ዝግጅቱ በህጻናት እድገትና መዳበር ላይ የተመሰረተና ዝርዝር አስፈላጊ ነጥቦችን የሚጠቁም ሊሆን ይገባል።

የክፍለ ጊዜ ክንውን /ትምህርት/ ዝግጅት ማዘጋጃ ፎርማት

<table>
<tr><td>ቀን</td><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>ቡድን</td><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>ፕሮግራም</td><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>ጭብጥ</td><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>ብቃት</td><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td>ርዕስ</td><td colspan="3"></td></tr>
<tr><td colspan="4">ዓላማ፡- ከዚህ ትምህርት /ጨዋታ/ በኋላ ህጻናት<br>1. ________________<br>2. ________________<br>3. ________________</td></tr>
<tr><td colspan="2">የመርጃ መሳሪያዎች</td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td colspan="2">የማስተማሪያ ዘዴዎች</td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td colspan="2">የፕሮግራሙ ዝርዝር ሂደት</td><td colspan="2"></td></tr>
<tr><td colspan="2">የመምህሩ ተግባር</td><td>ጊዜ</td><td>የህጻናቱ ተግባር</td></tr>
<tr><td colspan="2"></td><td></td><td></td></tr>
</table>

ቀን፣ ቡድን፣ ጭብጥና ርዕስ የሚወስደው ከዕለት ዕቅድ ውስጥ ሲሆን የክፍለ ጊዜ ትምህርት ዕቅዱ /ሊሰን ፕላን/ ለየትኛው እድሜ እንደተዘጋጀ እንዲታወቅ ነው።

ብቃት ፦ የሚወሰደው ከዓመት ዕቅድ ላይ ሲሆን ህጻኑ ሊደርስበት የሚገባውን የለውጥ ደረጃ የሚያመላክት ነው።

ዓላማ ፦ በክፍለ ጊዜው ህጻናቱን በማሳተፍ ከተከናወነ በኋላ ህጻናት የሚያሳዩትን ለውጥ የሚያመላክት ሲሆን ዓላማዎቹ ሲነደፉ በአንድ ክፍለ ጊዜ ተግባራዊ እንደሚሆኑ ታስቦ መዘጋጀት ይኖርባቸዋል። ከርእሱ ጋር መሄድ አለመሄዳቸው ትኩረት ሊሰጠውና ከህጻናቱ አቅም አንጻር ሊተገበሩ የሚችሉ፣ ከአካባቢው ተጨባጭ ሁኔታ ጋር ተጣጥመው ሊሰሩ የሚችሉ፣ ሊመዘኑ የሚችሉ እና ተገቢና ግልጽ መሆናቸውን በማሰብ ሊዘጋጁ ይገባል። በእቅድ ላይ ሲቀመጡም በተራ ቁጥር ተለይተው ቢቀመጡና ባይበዙ ለአፈጻጸም ምቹ ይሆናሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ፡- የመርጃ መሳሪያዎች ርዕሱን ከህጻናቱ ደረጃ አንጻር በቀላሉና ህጻናቱን ሊያሳትፉ፣ ሊያዝናኑና ሊያስደስቱ በሚችል መልኩ ለመተግበር እንዲቻል የምንመርጣቸው ሲሆኑ እንደአካባቢያችን ሁኔታ በቀላሉ ሊገኙ ከሚችሉ ቁሳቁሶች የተዘጋጁ ቢሆኑ ይመረጣል።

የማስተማሪያ ዘዴዎች ፡- ዓላማዎችን ለመተግበር የምንጠቀምባቸው ስልቶች ሲሆኑ የሚመረጡት ከህጻናት ዕድሜና ደረጃ፣ ከክፍለጊዜው ርዕስና ከአላማዎቹ አንጻር ሊሆን ይገባል። የክፍለ ጊዜ ትምህርት ዕቅድ /ሌሰን ፕላን/ ዘዴዎች ሲቀመጡ ግልጽ በሆነ መልኩ እንዴት ልንጠቀምባቸው እንደሆነ በሚጠቁም ሁኔታ ቢሆኑ ትምህርቱን ለሚያቀርበው ሰው ይጠቅማሉ።

የፕሮግራሙ ዝርዝር ሂደት ፡- ፕሮግራሙ እንዴት እንደሚጀመር፣ እንዴት ዓላማዎቹ እንደሚተገበሩ፣ እንዴት ፕሮግራሙ እንደሚጠቃለልና የመምህሩንና የህጻናቱን ተግባር የሚወስደው ጊዜም በዚሁ ላይ የሚቀመጥ ይሆናል።

ህጻናት ተማሪዎች ሳይሆኑ ለተማሪነት ህይወት የሚዘጋጁ እንደሆኑ ይታወቃል። ማንኛውም ፕሮግራም የህጻናቱን የማወቅ ፍላጎት የሚቀሰቅስ፣ መርጃ የሚያስጨብጥና ክህሎትን የሚያለማምድ ሊሆን ይገባል። ይህንን ለመተግበር የሚያስችለው ዕቅድ በመስራት ስለሆነ ስራዉን ለማሳለጥ ለዕቅድ ከፍተኛ ቦታ ልንሰጠው ይገባል።

# ክፍል 2. የመዳበር አቅጣጫዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

## 2.1. ለተገቢው ዕድገትና የአካል ጥንካሬ ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ

### 2.1.1 ማብራሪያ

የሕፃናት ዕድገትና መዳበር የሚጀምረው ከተፀነሱበት ጊዜ አንስቶ በመሆኑ እንክብካቤውም ከዚሁ ጊዜ ጀምሮ ትኩረት ሊያገኝ ይገባል። የአካል ዕድገትና መዳበር የአካል መጠን መጨመርን፣ ጥንካሬን፣ የእንቅስቃሴ ቅንጅትን ሲያመለክት የረቂቅና ጉልህ ጡንቻዎች መዳበር ከፍተኛ ቦታ የሚሰጠው ነው።

የሕፃናት የተመጣጠነ ምግብ መመገብና የጤናቸው መጠበቅ ለአካል መዳበር መሠረት ነው። ለጋ ሕፃናት መሠረታዊ እንቅስቃሴዎችን በተገቢው ጊዜ ማከናወን መቻል ይገባቸዋል። በዕቅድና በሥነ ሥርዓት የተመራ የአካል እንክብካቤና እንቅስቃሴ መዳበር ለአእምሮ መዳበር አስተዋጽኦ ያደርጋል። ለምሣሌ አካላቸው የዳበረ ሕፃናት አካበቢያቸውን የመፈተሽ፣ የማወቅ እና የመረዳት ፍላጐታቸው ይጨምራል። የእንቅስቃሴ መዳበር በማህበራዊነት መዳበርም የሚያበረክተው አስተዋጽኦ ከፍተኛ ነው። ለምሣሌ ከሌሎች ጋር ተባብሮ መጫወት፣ ራስን ተቆጣጥሮ እና ተስማምቶ መንቀሳቀስ፣ በራስ መተማመን የእንቅስቃሴ መዳበር ለማህበራዊነት መዳበር የሚያስገኛቸው ውጤቶች ናቸው። ስለዚህ ለተገቢው እድገትና የአካል ጥንካሬ ተገቢውን እንክብካቤ ማድረግ ይገባል። ይህም በቅድመ መደበኛ ትምህርት ተቋም ብቻ ሣይሆን በቤትም ትኩረት እንዲሰጠው ከወላጆች ጋር በጋራ መስራት ያስፈልጋል።

### 2.1.2 አጠቃላይ ዓላማዎች

1. ራሳቸውን ማወቅ፣ የአካል ክፍሎቻቸውንና ተግባራቸውን መለየት፣ ከሌሎች ጋር ተግባብቶ እና ተባብሮ መንቀሳቀስ እንዲችሉ አቅማቸውን ማዳበር
2. የስሜት አካላቸውን (ሕዋሳቶቻቸውን) እንዲለዩና አካላቸውን የመጠበቅ /የመንከባከብ/ ዝንባሌ እና ክህሎት እንዲኖራቸው ማድረግ
3. ጉልህና ረቂቅ ጡንቻዎቻቸውን ለማዳበርና የተለያዩ ተግባራትን የማከናወንና በነፃነት ፈጠራቸውን የመግለጽ አቅም እንዲኖራቸው ማድረግ

**2.1.3** የሚጠበቁ ውጤቶች እና ብቃቶች

1. ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመን እና ራስን የማክበር ስሜት መኖር
   1.1. ስማቸውን፣ ዕድሜአቸውን እና ፆታቸውን መናገር ይችላሉ
   1.2. አዲስ ጓደኛን ማፍራት እና መወዳጀት ይችላሉ
2. የሰውነት ክፍሎቻቸውን መለየት እና ተግባራቸውን መናገር
   2.1. የሰውነት ክፍሎቻቸውን መጥራት ይችላሉ
   2.2. በተለያዩ የስውነት ክፍሎቻቸው የሚከናወኑትን ተግባራት መናገር ይችላሉ
3. ዓይኖችን መንከባከብ
   3.1 . ዓይኖቻቸውን መንከባከብ ይችላሉ
4. ጆሮዎችን መንከባከብ
   4.1 . ጆሮዎቻቸውን መንከባከብ ይችላሉ
5. የማሽተት ስሜት አካልን መጠቀምና አፍንጫን መንከባከብ
   5.1 . በማሽተት የተለያዩ ነገሮችን ሽታ መለየት ይችላሉ
6. የመቅመስ ስሜት አካልን መጠቀምና አፍን መንከባከብ
   6.1 . የተለያየ ጣዕም ያላቸዉን ምግቦች መለየት እና መናገር ይችላሉ
   6.2 . አፉቸዉን በጥንቃቄ እና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ
7. በመዳሰስ ነገሮችንና ሁኔታዎች መግለጽ
   7.1 . ሙቀትን መለየት እና በመዳሰስ የተሰማቸዉን ስሜት መግለጽ ይችላሉ
8. ጤናን መጠበቅና የአመጋገብ ሥርዓቶችን መለማመድ
   8.1. የአመጋገብ ሥርዓትን ይለማመዳሉ
9. አካልን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ
   9.1. አካላቸውን መጠበቅና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ
10. ጉልህና ረቂቅ /ትላልቅና ትናንሽ/ ጡንቻዎችን መጠቀም
    10.1. የሰውነት ክፍሎቻቸውን ለተለያዩ ተግባራት መጠቀም ይችላሉ
11. በነፃነት ፈጠራን መግለጽ
    11.1. አካላቸዉን በመጠቀም ሃሳባቸዉን ይገልጻሉ

**2.1.4.** የሚጠበቁ ውጤቶች፣ ብቃቶች፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመን እና ራስን የማክበር ስሜት መኖር | 1.1. ስማቸውን፣ ዕድሜአቸውን እና ፆታቸውን መናገር ይችላሉ። |

## ተግባር አንድ ፡- ራስን ማስተዋወቅ

ዓላማ ፡- ሕፃናት ስማቸውን፣ዕድሜአቸውን እና ፆታቸውን በመናገር ራሳቸውን የማስተዋወቅ ክህሎት ያዳብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሕፃናት ፎቶግራፎች፣ ማጣበቂያ፣ሰፊ እና ወፍራም ወረቀት፣ አሻንጉሊት እና ሌሎችም

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-


- መምህር ለህፃናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመቆም ራስን ለህፃናት ማስተዋወቅ
- በመቀጠልም አሻንጉሊቷን ተናጋሪ በማስመሰል ራሷን ለህፃናቱ ስሟን፣ እድሜዋንና ፆታዋን በመናገር እንድታስተዋውቅ ማድረግ
- ሕፃናቱ በየተራ እየተነሱ ከጓደኞቻቸው ፊት በመቆም እና በትልቅ ሰፊ ወረቀት ላይ የተለጠፈውን የራሳቸውን ፎቶ በመጠቆም ስማቸውን፣ ዕድሜአቸውን እና ፆታቸውን እንዲናገሩ ማድረግ
- መናገር የሚቸግራቸውን ሕፃናት ስማቸውን በማስታወስ እንዲናገሩ ማነቃቃት እና ማገዝ
- <<እኔ ትንሽ ልጅ ነኝ>> የሚለውን መዝሙር ለአሻንጉሊቷ እንዲዘምሩላት ማነቃቃት

ምዘና፡- ስማቸውን፣ ዕድሜአቸውን እና ፆታቸውን መናገር መቻላቸውን ሲናገሩ በማዳመጥ መገምገም።


## ተግባር ሁለት ፡- ራስን በፆታ በመመደብ መጫወት

ዓላማ፡- ራሳቸውን በፆታ መድበው ይጫወታሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-



- ህፃናቱን ከክፍል ውጪ ባለ ሜዳ ላይ ይዞ በመውጣት ራሳቸውን በፆታ በመመደብ እጅ ለእጅ እንዲያያዙ ማድረግ
- በፆታ ራሳቸውን ችለው መደባቸውን በማየት ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ድጋፍ መስጠት
- <<ትንሹ ጎማ ትልቁ ጎማ ተሽከረከረ>> የተባለውን እንቅስቃሴያዊ ጨዋታ እንደብዛታቸው ትንሹን ወይም ትልቁን ጎማ ሴቶች ወይም ወንዶች ሆነው እንዲጫወቱ ማድረግ



ምዘና ፡- ራሳቸውን በቦታ መድበው መጫወታቸውን በመመልከት መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
| --- | --- |
| 1. ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመን እና ራስን የማክበር ስሜት መኖር | 1.2. አዲስ ጓደኛን ማፍራት እና መወዳጀት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ፡- አዲስ ጓደኛ ማፍራት

ዓላማ ፡- አዲስ ጓደኛ መተዋወቅ እና መወዳጀት ይጀምራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ‹‹እጅ ለእጅ ተያይዘን እንሽከረከራለን›› የተባለውን ጨዋታ በተለያዩ ተግባራት የሚቀራረቡ ሕፃናት እጅ ለእጅ ተያይዘው እንዲጫወቱ ማድረግ
- ከሌሎች ጋር እንዲተዋወቁ ማገዝና አዲስ ጓደኛ እንዲያፈሩ ማድረግ
- ቦታ በማቀያየር ከሌሎች ጋር ተያይዘው እየዘመሩ እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፡- አዲስ ጓደኛ መተዋወቅ እና መወዳጀት መጀመራቸውን መገምገም።

ተግባር ሁለት ፡- ጓደኛን መለየት

ዓላማ ፡- ጓደኞቻቻውን በመልክና በስም ይለያሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ እንቅስቃሴያዊ ጨዋታዎችን /መሐረቤን፣ አረንጓዴ፣ ሰብለወንጌል ወዘተ…/ በሕብረት ማጫወት
- አብረዋቸው የተጫወቱት የክፍል ጓደኞቻቸው ማን ማን እንደሆኑ ስማቸውን እንዲናገሩ እና በጣታቸው ጠቁመው እንዲያሳዩ ማድረግ

  ለምሳሌ ፡- ስማቸውን መጥራት ባይችሉ ተጠቃሚዎቹ ስማቸውን እንዲናገሩ እና እንዲጨብጧቸው ማበረታታት።

ምዘና ፡- ጓደኞቻቻውን በመልክና በስም መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር ሶስት ፡- የጓደኛን ስእል መቀባት ተግባር ሶስት፡- የጓደኛን ስእል መቀባት**

ዓላማ ፡- የጓደኛን ስእል ቀለም በመቀባት ስለጓደኛቸው የሚያውቁትን ለመናገር ይሞክራሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በወረቀት ላይ የተሳለ የህጻናት ምስል፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለሕፃናት ለእያንዳንቸው የሕፃን ስዕልን መስጠትና ከለር እንዲቀቡ ማድረግ
- ቀብተው ሲጨርሱ የቀቡት የማንን ወይም የየትኛውን ጓደኛቸውን ምስል እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- ስለጓደኞቻቸው የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት
- በመጨረሻም የህፃናቱን ስም በመፃፍ በሚታይ ቦታ ላይ መለጠፍ

> ማስታወሻ ፡- የህፃናት ስእልን ከመስጠታችን በፊት ጓደኛቸው ሴት ወይም ወንድ መሆናቸውን በመጠየቅ ሴት ከሆነች የሴት ምስል ወንድ ከሆነ የወንድ ምስል መስጠት ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- የጓደኛቸውን ስእልን ቀለም መቀባታቸውንና ስለጓደኛቸው የሚያውቁትን ለመናገር መሞከራቸውን ሲቀቡ በማየትና ሲናገሩ በማዳመጥ መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. የሰውነት ክፍሎችን መለየት እና ተግባራቸውን መናገር | 1.1. የሰውነት ክፍሎቻቸውን መጥራት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የሰውነት ክፍሎችን መለየት

ዓላማ ፡- ዋና ዋና የሰውነት ክፍሎችን ስም ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- አሻንጉሊት፣ የሕፃን ሙሉ ሰውነት ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የሰውነት ክፍሎችን ለማስተዋወቅ አሻንጉሊትን ተናጋሪ በማስመሰል ስሟን፣ ዕድሜዋን፣ ፆታዋን በመናገር እንድትተዋወቃቸው ማድረግ
- ዋና ዋና የሰውነት ክፍሎቿን በየተራ እያሳየች መጠሪያቸውን እንድትናገር ማድረግ
- አንዱን የሰውነት ክፍል አሳይታ ስም ስትጠራ እነርሱም የራሳቸውን በማሳየት ስም እንዲጠሩ ማድረግ
- ሕጻናት በየተራ ዋና ዋና የሰውነት ክፍላቸውን ለጓደኞቻቸው በማሳየት እንዲጠሩ ማድረግ
- በግድግዳ ለይ የተሰቀለ ስዕል በመጠቀም የሰውነት ክፍሎችን እንዲለዩ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- ሁሉም ሕጻናት ዋና ዋና የሰውነት ክፍላቸውን እያሳዩ መጥራት እንዲችሉ ማበረታታት።

ምዘና ፡- የተጠራውን የሰውነት ክፍላቸውን ማሳየታቸውን እና በስም መጥራታቸውን በማየት እና ሲናገሩ ትኩረት ሰጥቶ በማዳመጥ መገምገም።

ተግባር ሁለት፡- የሰውነት ክፍሎችን መጥራት

ተግባር ሁለት፡- የሰውነት ክፍሎችን መጥራት

ዓላማ ፡- ዋና ዋና የሰውነት ክፍሎችን በስም ይጠራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሰውነት ክፍሎችን የሚያሳይ ጎላ ብሎ የተሳለ ባለቀለም የሕፃን ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የሰውነት ክፍሎችን የሚያሳይ ስዕል በመጠቀም ስዕሉን እንዲመለከቱና ዋና ዋና የሰውነት ክፍሎችን እንዲጠሩ ማድረግ
- ከህፃናቱ ፊት በመቆም የራስን የሰውነት ክፍል በማሳየት ምን እንደሆነ መጠሪያውን እንዲናገሩ ማድረግ
- ህፃናቱ በየተራ እየተነሱ ከጓደኞቻቸው ፊት በመቆም የተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸውን በመንካት የሰውነት ክፍሎቻቸውን መለየት እና መጥራት እንዲችሉ ማለማመድ

ምዘና ፡- የተጠየቀውን የሰውነት ክፍል በትክክል መጠሪያ ስሙን መናገር መቻላቸውን ሲናገሩ በማዳመጥ መገምገም።

ተግባር ሦስት ፡- የአካል ክፍሎችን ፐዝል መገጣጠም

ዓላማ ፡- የአካል ክፍሎችን ይገጣጥማሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በመገጣጠም የሚሠራ የሰው ቅርፅ /ፐዝል/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በመገጣጠም የሚሠራ የሰው ቅርፅ ማዘጋጀት
- የተገጣጠመውን በሕፃናት ፊት በመለያየት እና በመገጣጠም ለሕፃናቱ ማሳየት
- የተገጣጠመውን መለያየትና እነርሱ እንዲገጣጥሙት መጋበዝ
- ህፃናቱ በግል መይም በጋራ የተለያዩትን የአካል ክፍሎች በቦታቸው እንዲያስገቡ ማድረግ
- ሲቸግራቸው ፍንጭ በመስጠት ማገዝ

ለምሳሌ፡- እጅ ወይም እግር የት አካባቢ ነው የሚገኘው በማለት መጠየቅ

ማስታወሻ፡- ህፃናቱ እንዲገጣጥሙ የሚሰጣቸው የሰውነት ክፍሎች ከሶስትና ከአራት ያልበለጡ እና ዋና ዋና የሰውነት ክፍሎችን የያዙ ሊሆኑ ይገባል።

ምዘና ፡- ሲገጣጥሙ በመከታተል የአካል ክፍሎችን መገኛ ቦታቸውን ለይተው በማወቅ በቦታው መግጠም መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- የሰውነት ክፍሎችን ቅርጽ መለየትና መለጠፍ

ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎችን ቅርጽ በመለየት በተገቢዉ ቦታ ላይ ይለጥፋሉ

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የሰውነት ክፍሎች ቅርጾች፣ ኮላ፣ ፊት የተሳለበት ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን ቅርፅ ከባለቀለም ወረቀት ላይ ቆርጦ በማውጣት ለእያንዳንዱ ሕፃን መስጠት
- በነጭ ወረቀት ላይ በተሳለ ፊት ላይ በተገቢዉ ቦታ እንዲለጥፉት ማድረግ
- የለጠፉት ምን እንደሆነ በመጠየቅ ትክክል መሆንና አለመሆናቸውን ጓደኞቻቸው እንዲያረጋግጡ ማድረግ
- ህፃናቱ የለጠፉትን የተሟላ የሰውነት ክፍል ያለውን ምስል በክፍል ውስጥ ለእይታ አመቺ በሆነ ቦታ ላይ መለጠፍ

ምዘና ፡- የሰውነት ክፍሎችን ቅርጽ መለየት መቻላቸውንና በትክክለኛ ቦታ ላይ መለጠፋቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፡- የሰውነት ክፍሎችን በመዝሙርና በጨዋታ መለየት

ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎቻቸውን እየዘመሩና እየተጫወቱ ይለያሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- “ የቱ ነው እጃችን? ” የሚለውን መዝሙር ማዘመር
- በየተራ የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን በመጠየቅ በመዝሙር እንዲለዩት ማድረግ

ለምሳሌ፡- መምህር የቱ ነው እጃችን? ሲሉ ይሄ ነው እጃችን በማለት እጃቸውን እያሳዩ በዜማ እንዲናገሩ ማድረግ፣ የቱ ነው ጆሮአችን? ይሄ ነው ጆሮአችን ወዘተ... በማለት የተነካውን የሰውነት ክፍል ተናገር/ተናገሪ በሚል ጨዋታን ማጫወት

- <<አረንጓዴ አረንጓዴ>> የሚባለውን ጨዋታ አጨዋወት በመከተል መምህር የሚጠሩትን የሰውነት ክፍል በመንካት እንዲጫወቱ መምራት

  ለምሣሌ ፡-እንቅስቃሴውን <<አረንጓዴ አረንጓዴ>> በማለት መምራት እና መምህር አፍንጫ ሲሉ ባሉበት ቦታ በመቆም አፍንጫን መንካት በዚህ መሠረት ህጻናት ዋና ዋና የሰውነት ክፍሎቻቸውን እየነኩ እንዲለዩ ማጫወት

ምዘና ፡- በመዝሙሩ እና በጨዋታው ሂደት የሰውነት ክፍሎቻቸውን መለየት መቻላቸውን በማየት መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. የሰውነት ክፍሎችን መለየት እና ተግባራቸውን መናገር | 1.2. በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው የሚያከናዉኑትን ተግባራት መናገር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት መተዋወቅ

ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት ይተዋወቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- አሻንጉሊት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- አሻንጉሊትን ተናጋሪ በማስመሰል የሰውነት ክፍሎቿን በየተራ እያሳየች በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው የሚከናወኑ ተግባራትን እንድትነግራቸው ማድረግ
- አሻንጉሊቷ አንዱን የሰውነት ክፍል አሳይታ ስም በመጥራት ተግባሩ ምን እንደሆነ እንድትጠይቃቸው ማድረግ
- እነርሱም የራሳቸውን በማሳየት በሰውነት ክፍሎቻቸው የሚከናወኑ ተግባራትን መናገር እንዲችሉ ማለማመድ

ማስታወሻ ፡- ህጻናቱም በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው የሚያከናውኑትን ተግባር እንዲናገሩ እድል መስጠት ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- በተለያዩ የአካል ክፍሎቻቸው የሚያከናውኑትን ተግባር መተዋወቃቸውን ሲናገሩ ትኩረት ሰጥቶ በማዳመጥ ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት መናገር

ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎችን ተግባራት ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡-ባለቀለም የሕፃንየሰውነት ክፍሎች ስዕል፣ የመዝሙር ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- "በምን ምን እናደርጋለን?" የተባለውን መዝሙር በመጠቀም የሰውነት ክፍሎቻቸውን እያሳዩ እንዲዘምሩ ማድረግ
- የሰውነት ክፍሎችን ስዕል በማሳየት በዓይናችን ምን እናደርጋለን**?**፣ በአፍንጫችን ምን እናደርጋለን**?**፣ በእግራችን ምን እናደርጋለን**?** ወዘተ… እያሉ በመጠየቅ የሰውነት ክፍሎችን እንዲለዩና እና ተግባራቸውን እንዲናገሩ ማለማመድ
- በመዝሙሩ ውስጥ የጠሯቸውን የሰውነት ክፍሎች ተግባር የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማወያየት

  ምዘና፡- የሰውነት ክፍሎቻቸው የሚያከናውኑትን ተግባራት መለየት እና መናገር መቻላቸውን በዜማ ለሚጠየቁት ጥያቄ ምላሽ ሲሰጡ ትኩረት ሰጥቶ በማዳመጥ መገምገም።

ተግባር ሶስት ፡- የሰውነት ክፍሎችን ቅርፅ መሥራትና ተግባራቸውን መናገር

ዓላማ ፡- የሰውነት ክፍሎችን ቅርጽ ይሰራሉ፣ ተግባራችውንም ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጭቃ፣ የተቦካ ወረቀት፣ አሸዋ**…**ወዘተ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናቱ ከተቦካ ጭቃ ወይም ወረቀት የተሰራ የሰውነት ክፍል በማሳየት ምን እንደሆነና ለምን ተግባር እንደሚጠቀሙበት በመጠየቅ ማነቃቃት
- ጠረጴዛቸውን ላስቲክ እንዲሸፍኑና የሹራብና የሸሚዛቸውን እጀታ እንዲያጥፉ ማድረግ

- ለእያንዳንዳቸው የተቦካ ጭቃ ወይም ወረቀት በመስጠት የተለያዩ የሰውነት ክፍሎችን እንዲሰሩ ማድረግ የማይችሉ ከሆነ ድጋፍ ማድረግ
- ሲጨርሱም የሰሯቸውን የሰውነት ክፍሎች ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ እና ተግባራቸውን እንዲናገሩ ማድረግ
- የሕጻናቱን ሥራዎች ማድነቅ  እና ለተወሰኑ ቀናት እንዲታዩ ፊት ለፊት ማስቀመጥ
- በመጨረሻም አካባቢያቸውን እንዲያጸዱና እጃቸውን በውሃና በሳሙና እንዲታጠቡ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- ይህንን ተግባር ከክፍል ውጪ ያለውን የአሸዋ ገንዳ በመጠቀም ማከናወን ይቻላል።

ምዘና ፡- የሰውነት ቁርጾችን በመሥራትና ተግባራቸውን መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
| --- | --- |
| 2. ዓይኖችን መንከባከብ | 2.1. ዓይኖቻቸዉን መንከባከብ ይችላሉ፡: |

ተግባር አንድ ፡- የዓይንን ጥቅም መናገር

ዓላማ ፡- የዓይንን ጥቅም ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የዓይን ስዕል፣አሻንጉሊት /ጉላጉላ ብለው የሚታዩ ዓይኖች ያሏት/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- አሻንጉሊቷን ወደ ህፃናቱ በማቅረብ እያየቻቸው እንደሆነ መንገር
- አሻንጉሊቷ እነሱን በምኗ እንዳየቻቸው እና እነሱም በምናቸው እንዳዩአት መጠየቅ
- ህፃናቱም ማየት የሚቻለው በአይን እንደሆነ እንዲረዱ ማድረግ
- ዓይኖቻቸውን እንዲጨፍኑ ማድረግ እና ሲጨፍኑ በአካባቢያቸው ያሉትን ነገሮች ማየት መቻል እና አለመቻላቸውን በመጠየቅ ማወያየት
- መልሳቸውን መሰረት በማድረግ አይን ለማየት እንደሚጠቅም እና ዓይናቸውን ከከለሉት ወይም ከጨፈኑት ማየት እንደማይችሉ ማስረዳት
- ደግመው በተግባር በእጃቸው እየከለሉ እና እየጨፈኑ እንዲያረጋግጡ ማድረግ

ምዘና ፦ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የአይንን ጠቀሜታ መረዳታቸውን ሲናገሩ በማዳመጥ ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ የዓይንን ቅርጽ መለየትና ቀለም መቀባት

ዓላማ

ተግባር ሁለት፦ የዓይንን ቅርጽ መለየትና ቀለም መቀባት

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በተለያየ ቅርፅ የተሰሩ /ሞላላ፣ ክብ ቅርፅ፣ ሶስት ማእዘን፣አራት ማዕዘን/፣ በወረቀት ላይ የተሰራ የአይን ምስሎች፣ ባለቀለም እርሳሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- የተለያዩ ሥዕሎችን በየጠረጴዛቸው በማደል በጋራ ሆነው የትኛው ሥዕል ትክክለኛ የዓይን ሥዕል እንደሆነ እንዲለዩ መጠየቅ
- የለዩትን ሥዕል እንዲያሳዩ ማድረግና የተሳሳተ ቡድን ካለ እገዛ ማድረግ
- የአይን ቅርፅ ሞላላ ሆኖ ውስጡ ነጭ ሆኖ መሀሉ ላይ ጥቁር እንደሆነ መግለፅ
- መምህር ጎላ ብሎ የተሳለ የአይን ስእል በማሳየት "ይሄ ምንድን ነው?" ሲሉ አንድ ላይ "ይህ የአይን ቅርፅ ነው።" በማለት እንዲናገሩ ማድረግ
- ለእያንዳንዳቸው በትክክል የተሰራ የአይን ስእል በመስጠት የመካከለኛውን ክፍል ብቻ ጥቁር ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- ሲጨርሱ በክፍል ውስጥ መለጠፍ

ምዘና ፦ ሁሉም የአይንን ቅርጽ መለየትና በተገቢው ሁኔታ ቀለም መቀባታቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፦ ዓይንን ከሚጎዱ ነገሮች መጠበቅ

ዓላማ ፦ ዓይናቸውን ሊጎዱ ከሚችሉ ነገሮች ይከላከላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የዓይን ስዕል፣ ዓይንን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- " ከእናንተ መሀል ዓይኑን ታሞ የሚያውቅ ልጅ አለ?" በማለት መጠየቅ

- መልሳቸውን መሰረት በማድረግ ዓይንን ሊያሳምሙ ወይም ሊጎዱ ስለሚችሉ ነገሮች እንደሚከተለው ማስገንዘብ፡-
    - እጅችን ሳይታጠቡ ዓይኖችን መንካት ወይም ማሸት እንደሌለባቸው
    - ሀይለኛ ብርሀንን ወይም አንፀባራቂ ነገርን መመልከት እንደሌለባቸው
    - አቧራ በሚቦንበት ጊዜ አይኖቻቸውን በእጆቻቸው መከለል
    - ኃይለኛ ብርሃን ሲኖር ዓይኖቻቸውን መጨፈን
    - ዝንቦች ፊታቸው ላይ ሲያርፉ ማባረር
    - ቴሌቪዥንን ለረጅም ጊዜ ተጠግቶ ማየት እንደሌለባቸው፣ ወዘተ... ማስገንዘብ
- "አቧራ" በሚል ስያሜ አረንጓዴ የሚባለውን እንቅስቃሴያዊ ጨዋታ እንደሚከተለው ማጫወት፡-
    - አቧራ ሄደ አቧራ ሄደ ሲባል መንቀሳቀስ /ዱብ ዱብ ማለት/
    - አቧራ መጣ ሲባል ቆሞ እጅን ዓይን ላይ መከለል
    - ዝንቦች ፊታችን ላይ አረፉ ሲባል በእጅ እሽ ማለት እና ማባረር
- በዚህ መልኩ በጨዋታ ዓይንን ከሚጎዱ ነገሮች መከለልን ማለማመድ

ምዘና **፡-** አይናቸውን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን ማወቃቸውን ጥያቄዎችን በመጠየቅና በጨዋታ አይናቸውን ዓይንን ከሚጎዱ ነገሮች መጠበቅ መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አራት ፡- ዓይንን መንከባከብ

ዓላማ ፡- ፊታቸውን በመታጠብ ዓይናቸውን መንከባከብ ይለማመዳሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የውሃ ጣሳ፣ ማስታጠቢያ፣ውሃ፣ንፁህ ፎጣ፣ሳሙና

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ጠዋት ከእንቅልፋቸው ሲነሱ ፊታቸውን ማን እንደሚያጥባቸው እና ለምን እንደሚታጠቡ በመጠየቅ ማወያየት
- መምህር መጀመሪያ ሁለት እጅን በውሃ እና በሳሙና በመታጠብ ቀጥሎም በውሃ ብቻ ፊትን በመታጠብ ማሳየት
- ሕፃናቱ ባዩት መሠረት በየተራ መጀመሪያ በሳሙና እጆቻቸውን ቀጥለውም ፊታቸውን በውሃ ብቻ እንዲታጠቡ ማድረግ

ምዘና ፡- ፊታቸውን በመታጠብ ዓይናቸውን መንከባከብ መቻላቸውን መከታተል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 4. ጆሮዎችን መንከባከብ | 4.1 ጆሮዎቻቸውን መንከባከብ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የጆሮን ምስል መቀባት

ዓላማ ፡- የጆሮን ምስል ቀለም ይቀባሉ እንዲሁም የቀቡትን ስእል ምንነት ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡-ጎላ ብሎ የተሳለ የጆሮ ስዕል (ፎቶግራፍ)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናቱ በደምብ ሊያዩት የሚችሉትን የጆሮ ስዕል (ፎቶግራፍ) በማሳየት ምን እንደሆነ መጠየቅ
- ከላይ የተጠቀሰውን ስዕል ሁሉም ሕፃናት በቅርበት እንዲያዩት ማድረግ
- ስዕሉ ላይ የተመለከቱትን የሚመስል የሰውነት ክፍል አላችሁ ወይስ የላችሁም? የቱጋ ይገኛል? በማለት መጠየቅ
- መልሳቸውን መሰረት በማድረግ ሁለቱንም ጆሮዎቻቸዉን በእጆቻቸው በመንካት ‹‹እነዚህ ጆሮዎቼ ናቸው›› በማለት እንዲናገሩ ማበረታታት
- አጠገባቸው የተቀመጡትን ጓደኞቻቸውን በመመልከት እርስ በእርስ ጆሮአቸውን እንዲነካኩ ማድረግ
- የጆሮን ስእል በመስጠት ደስ ያላቸውን ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- ሲጨርሱም የቀቡት ስእል ምን እንደሆነ በመጠየቅ ማጠቃለል

ምዘና ፡- የጆሮን ስእል ቀለም መቀባታቸውን በማየትና የስእሉን ምንነት ሲጠየቁ መናገር መቻላቸውን በማዳመጥ መገምገም።

ተግባር ሁለት ፡- ድምጽን መለየት እና አስመስሎ ማውጣት

ዓላማ ፡- የተለያዩ ድምጾችን ይለያሉ እንዲሁም ለማስመሰል ይሞክራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የውሻ፣ የድመት፣ ወዘተ... ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- **"**ማን እንዴት ይጮሃል**?"** ጨዋታን እንደሚከተለው ማጫወት፡-
  ለምሳሌ ፡- መምህር የውሻ ስዕልን በማሳየት **"**ማነው**?** እንዴት ይጮሃል**?"** በማለት ሲጠይቁ ሕፃናት እንደ ውሻ በመጮህ መልስ እንዲሰጡ በማድረግ ወዘተ**...**
- በአካባቢያቸው ምን ምን ነገሮችን ሰምተው ያውቁ እንደሆነ በመጠየቅ የሰሙትን ድምፅ አስመስለው በማውጣት ለጓደኞቻቸው እንዲያሰሙ ማበረታታት
- ከከበዳቸው ፍንጭ መስጠት ለምሳሌ መኪና ሲሄድ፣ በር ሲንኳኳ፣ ህፃን ልጅ ሲያለቅስ ወዘተ በማለት መጠየቅ
- እነዚህን ሁሉ ድምፆች በምናቸው እንደሰሙ በመጠየቅ የጆሮን ጥቅም እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- የተለያዩ የድምፅ ምንጮችን መለየት እና አስመስለው ማውጣት መሞከራቸውን ትኩረት ሰጥቶ በማድመጥ ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- የጆሮ ጥቅምና ሊደረግለት የሚገባ እንክብካቤን መናገር

ዓላማ ፡- የጆሮ ጥቅምና ሊደረግለት ስለሚገባ እንክብካቤ ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጎላ ብሎ የተሳለ የጆሮ ስዕል፣ የመዝሙር ካሴት፣ የተረት መጽሐፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ህፃናት ፀጥ እንዲሉና በአካባቢያቸው ምን እንደሚሰሙ ትኩረት ሰጥተው ለተወሰኑ ሰከንዶች እንዲያዳምጡ ማድረግ
- ምን ምን ድምፆችን እንደሰሙ እንዲናገሩ ማድረግ፣ በመቀጠልም በጠቋሚ ጣታቸው ከውጪ ጆሮአቸውን ጫፍ ደፍነው ለትንሽ ሰከንድ እንዲያዳምጡ ማድረግ
- ለምን ድምፅ እንዳልተሰማቸው በመጠየቅ የጆሮን ጥቅም እንዲረዱ ማድረግ

- ጆሮ የተለያዩ ነገሮችን ለማዳመጥ እንደሚረዳ በጥያቄና መልስ ከተወያዩ በኋላ ጆሮ እንክብካቤ ሊደረግለት እንደሚገባ መግለፅ
    - ጆሮ ቆሻሻ እንዳይሆን ውጪው መታጠብ እና መጠረግ እንዳለበት ማስገንዘብ
    - በጆሮ ውስጥ ውሃ እንዳይገባ ተጠንቅቀው ጆሮአቸውን የሚያጥቡትም ወላጆች እንደሆኑ ማስገንዘብ
    - ህጻናት ጆሮዎቻቸው ውስጥ ምንም ነገር መክተት እንደማይገባቸውና ድንገት የሆነ ነገር የገባ ከመሰላቸው በፍጥነት አጠገባቸው ላለ ትልቅ ሰው/ወላጅ፣ መምህር፣ ሞግዚት ወዘተ/ መንገር እንዳለባቸው ማስገንዘብ
    - ለጆሮ ሊደረግለት የሚገባውን እንክብካቤ በጥያቄና መልስ ማወያየት
- “አምስቱ የስሜት አካላት” መዝሙርን የጆሮውን ስዕል እያሳዩ እንዲዘምሩ መምራት

ምዘና ፡- የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የጆሮን ጥቅምና ጆሮን እንዴት መንከባከብ እንደሚችሉ መገንዘባቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
| --- | --- |
| 5. የማሽተት የስሜት አካልን መጠቀምና አፍንጫን መንከባከብ | 5.1 በማሽተት የተለያዩ ነገሮችን ሽታ መለየት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የአፍንጫን ጥቅም መናገር

ዓላማ ፡- ስለ አፍንጫ ጥቅምና ስለተያያዥ ሽታዎች ይናገራሉ። ተግባር አንድ ፡- የአፍንጫን ጥቅም መናገር

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጎላ ብሎ የተሳለ የአፍንጫ ስዕል ወይም ፎቶግራፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የአፍንጫ ስዕል (ፎቶግራፍ) በማሳየት ምን እንደሆነ መጠየቅ
- ስዕሉ ላይ የተመለከቱትን የሚመስል የሰውነት ክፍል አላችሁ ወይም የላችሁም በማለት መጠየቅ
- መልሳቸውን መሠረት በማድረግ አፍንጫቸውን በእጃቸው በመንካት “ይህ አፍንጫዬ ነው።” እንዲሉ ማበረታታት
- አፍንጫቸው ለምን እንደሚጠቅማቸውና በአፍንጫቸው ምን ምን /ደስ የሚል ጠረን ያላቸውንና የሌላቸውን ነገሮች/ ነገሮች አሽተው ወይም ሸቷቸው እንደሚያውቅ፣ በአካባቢያቸው ያሉ የተለያዩ ነገሮች ሲሸቷቸው ምን ስሜት እንደሚሰማቸው በመጠየቅ ማወያየት

- አየር ወደውስጥ በማስገባትና በማስወጣት እንዲተነፍሱ በማድረግ አፍንጫ ለመተንፈስና ሽታን ለመለየት እንደሚረዳ በደረጃቸው እንዲረዱ ማድረግ
- መልሳቸውን መሰረት በማድረግ ስለ አፍንጫ ጥቅምና በአካባቢያቸው ስላሉ ጥሩ እና መጥፎ ሽታዎች እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፦ ስለ አፍንጫ ጥቅምና ስለተለያዩ ሽታዎች ለመናገር መሞከራቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ አፍንጫን የሚጎዱ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፦ አፍንጫቸውን የሚጎዱ ነገሮችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ጎላ ብሎ የተሳለ የአፍንጫ ስዕል ወይም ፎቶግራፍ ዶቃዎች፣ እርሳስ፣ እስክርቢቶ፣ ጥራጥሬዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- አጠገባቸው የተቀመጡትን ጓደኞቻቸውን በማየት ሰንት አፍንጫና ስንት የአፍንጫ ቀዳዳዎች እንዳላቸው በማየት እንዲናገሩ ማድረግ
- አፍንጫቸው ለምን እንደሚጠቅማቸው በመጠየቅ ማነቃቃት
- አፍንጫ በጥንቃቄ ካልተያዘ ሊጎዳ እንደሚችል በመግለፅ አፍንጫ ውስጥ የተለያዩ ነገሮችን / ዶቃዎችን፣ ጥራጥሬዎችን፣ ወረቀቶችን፣ እርሳስ፣ እስክሪብቶ ወዘተ... / መክተት ጎጂ እንደሆነና እንደዚሁም አፍንጫን በእጅ ጣት መጎርጎር እንደሌለባቸው ማስገንዘብ
- በአጋጣሚ አፍንጫቸው ውስጥ የሆነ ነገር ቢገባባቸው ቶሎ አጠገባቸው ላለ ሰው /ለወላጅ፣ለመምህር፣ ለሞግዚት...ወዘተ/ መንገር እንዳለባቸው እንጂ እነሱ ለማውጣት መሞከር እንደሌለባቸው አፅንኦት ሰጥቶ መንገር

ማስታወሻ ፦ ህፃናቱ በእለት ተእለት ህይወታቸው አፍንጫን የሚጎዱ ነገሮችን ተረድተው አፍንጫቸውን ሊጎዱ ከሚችሉ ነገሮች መጠበቅ መቻላቸውን ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል።

ምዘና ፦ አፍንጫን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን መለየታቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

## ተግባር ሦስት ፡- ሽታን መለየት

ተግባር ሦስት፡- ሽታን መለየት

ዓላማ ፡- ነገሮችን በሽታቸው መለየት ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቅማ ፡- እጣን፣ ሰንደል፣ ሽቶ፣ ሽታን መለያ ጣሳ /ጠርሙስ/፣ የተለያዩ ሽታ ያላቸው ነገሮች ለምሳሌ፡- ሎሚ፣ሙዝ፣ነጭ ሽንኩርት ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቅማ፡-

- በወቅቱ ከሚገኙ የፍራፍሬና የአትክልት የተወሰኑትን በማቅረብ ምንነታቸውን መጠየቅ ለምሳሌ፡- ሙዝ፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ወዘተ…
- ሽታን መለያ ጣሳ ውስጥ የተለያየ ሽታ ያላቸው ነገሮችን መጨመር
- የተከተተውን /የተጨመረውን/ ሽታ ያለው ነገር ሳያዩ እንደተከደነ በቀዳዳ እንዲያሸቱ ማድረግ
- የምን ሽታ እንደሸተታቸው እንዲናገሩ በማድረግ ሽታን መለየት ማለማመድ
- ያሸተቱትን ነገር በትክክል ማወቅና አለማወቃቸውን ከሽታ መለያ ጣሳ ውስጥ በማውጣት ማሳየት

ማስታወሻ ፡- ይህንን ተግባር ሽታ ያለውን ነገር በሽታ መለያው ዕቃ ከትቶ ጥቂት ጊዜ ማቆየት እና ማውጣት ባዶውን ዕቃ ምን ነበረበት በማለት መጠየቅም ይቻላል። የሽታ መለያ ጣሳ ካላገኘን የህፃናቱን አይን በጨርቅ ላላ አድርጎ በማሰር አፍንጫቸው አጠገብ የሚሸተውን ነገር በማምጣት አሽተው እንዲለዩ ማድረግም ይቻላል።

ምዘና ፡- ነገሮችን በሽታቸው መለየት መሞከራቸውን በማየት መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 6. የመቅመስ ስሜት አካልን መጠቀምና አፍን መንከባከብ | 6.1 የተለያዩ ጣዕም ያላቸውን ምግቦች መለየት እና መናገር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፦ የምላስን ስእል ቀለም መቀባት መለየት

ዓላማ ፦ ምላስ የት እንደሚገኝ ይናገራሉ እንዲሁም የምላስን ስእል ተገቢውን ቀለም ይቀባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ጎላ ብሎ የተሳለ የምላስ ስዕል ወይም ፎቶግራፍ፣ ባለቀለም እርሳሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- በትልቅ ወረቀት ላይ የተሳለ የአፍ እና የምላስ ስዕል በማሳየት ምን እንደሆነ እና የት እንደሚገኝ መጠየቅ
- መልሳቸውን መሰረት በማድረግ በምስሉ ላይ የተመለከቱትን የሰውነት ክፍል አላችሁ ወይስ የላችሁም በማለት መጠየቅ
- ከዚያም ምላሳቸውን በጣታቸው እንዲጠቁሙ ማበረታታት
- የተሳለ የአፍ ስእልን በመስጠት ምላስን ብቻ ቀይ ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- ሲጨርሱ ከቀቡት ግርጌ ስማቸውን በመፃፍ ክፍሉ ውስጥ መለጠፍ

ምዘና ፦ ምላስ የት እንደሚገኝ ማወቃቸውንና የምላስን ስእል ተገቢውን ቀለም መቀባታቸውን በማየት መገምገም።

ተግባር ሁለት ፦ በመቅመስ ጣዕምን መለየትና መናገር

ዓላማ ፦ በመቅመስ የምግቦችን ጣእም ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ጎላ ብሎ የተሳለ የምላስ ስዕል ወይም ፎቶግራፍ፣ የተለያየ ጣዕም ያላቸው ምግቦች፣ የተለያዩ የምግብ ስዕሎች፣ ዓይንን መሸፈኛ ንፁህ ጨርቅ ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- “ቀምስህ ዕወቅ” የሚለውን ጨዋታ በሚከተለው መንገድ ማጫወት
    - የተለያዩ ጣዕም ያላቸውንና ሊበሉ የሚችሉ ነገሮችን ማዘጋጀት

      ለምሳሌ፦ ስኳር፣ ጨው፣ሙዝ፣ ሎሚ፣ ብስኩት፣ ዳቦ፣ ወዘተ**...**
    - ሁለት ሕፃናትን ከሕፃናት ፊት እንዲቆሙ በማድረግ ዓይኖቻቸውን ላላ አድርጎ በጨርቅ ማሰር
    - ለሕፃናቱ ምላሳቸው ላይ ትንሽ ስኳር በማድረግ እንዲያጣጥሙ እና ጣዕሙን እንዲናገሩ ማድረግ

- ቀጥሎም ትንሽ ጨው ምላሳቸው ላይ በማድረግ በፊት ከቀመሱት ጋር አንድ መሆኑን እና አለመሆኑን እንዲናገሩ መጠየቅ
- የቀመሱት ጣዕም ምን እንደሆነ መጠየቅ
- ጣዕሙን በምናቸው እንዳወቁት እንዲናገሩ በማድረግ የምላስን ጠቀሜታ እንዲረዱ ማድረግ
- ምላሳቸው ላይ ምግብ በትንሹ በማድረግ እንዲቀምሱና ሳያዩ ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ

- ጣዕሙን ይጣፍጣል፣ ጨው ጨው ይላል፣ ይመራል፣ ይኮመጥጣል በማለት እንዲለዩ ማበረታታት
- ከቀመሱት ምግብ ውስጥ የትኛው ጣፋጭ፣ የትኛው መራራ፣ የትኛው ኮምጣጣ እንደነበር እንዲናገሩ እድሉን መስጠት

ምዘና ፦ በመቅመስ ምግቦችን መለየትና ጣእማቸውን መናገር መቻላቸውን በማቅመስ እና በመጠየቅ ማረጋገጥ።

**ተግባር ሦስት ፦ ምላስን የሚጎዱ ነገሮችን መለየት**

ዓላማ ፦ ምላሳቸውን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን ይለያሉ እንዲሁም ሊጎዱት ከሚችሉ ነገሮች መከላከል ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የትኩስ መጠጥ ስዕል፣ የስለታም ነገሮች ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ምላሳቸውን እሚቸው ያውቅ እንደሆነና ምን ሆነው እንዳመማቸው በመጠየቅ ማወያየት
- ምላሳችንን ትኩስ ነገር ሊያቃጥለው እንደሚችል እና ስለት ነገርም ሊቆርጠው እና ሊጐዳው እንደሚችል በሚከተለው መልኩ ማስገንዘብ
  - በቁርስ ሰዓት ወይም በመክሰስ ሰዓት ሻይ ወይ ወተት ሲጠጡ ማብረድ እንዳለባቸው፤
  - ምላሳቸውን እንደ ማስቲካ እያኘኩ መጫወት
  - ምላሳቸውን ስለት ባለው ነገር መንካት ወይም መቧጠጥ እንደሌለባቸው፤
  - ምላስን አውጥቶ መሮጥ ወይም መጫወት እንደሌለባቸው፤

ማስታወሻ ፦ ህፃናቱ በእለት ተእለት ህይወታቸው ምላስን የሚጎዱ ነገሮችን ተረድተው ምላሳቸውን ሊጎዱ ከሚችሉ ነገሮች መጠበቅ መቻላቸውን ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል።

ምዘና፡- ምላሳቸውን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን መለየታቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 6. የመቅመስ ስሜት አካልን መጠቀምና አፍን መንከባከብ | 6.2 አፋቸዉን በጥንቃቄ እና በእንክብካቤ መያዝን ይለማመዳሉ። |

## ተግባር አንድ ፡- የጥርስ ጥቅምን መናገር

ዓላማ ፡- ጥርስን ይተዋወቃሉ። ጥቅሙን ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የጥርስ ሰእል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በትልቅ ወረቀት ላይ የተሳለ የአፍን እና የጥርስን ስዕል ለሕፃናቱ በማሳየት ምን እንደሆነ እና የት እንደሚገኝ መጠየቅ
- መልሳቸውን መሰረት በማድረግ በምስሉ ላይ የተመለከቱትን የሰውነት ክፍል አላችሁ ወይስ የላችሁም በማለት መጠየቅ
- ጥርሳቸውን እያመለከቱ "ይህ ጥርሴ ነው።" እንዲሉ ማበረታታት
- ሁሉም ሕፃናት እርስ በእርሳቸው አጠገባቸው ለተቀመጡ ልጆች ጥርሳቸውን እንዲያሳዩና ያዩትን እንዲናገሩ በጥያቄ ማወያየት
- ጥርሳቸው ለምን እንደሚጠቅማቸው በመጠየቅ መልሳቸውን ካዳመጡ በኋላ የጥርስን ጥቅም መግለፅ

ምዘና ፡- ጥርስን መተዋወቃቸውንና የጥርስን ጥቅም ማወቃቸውን ሲናገሩ በማዳመጥ ማረጋገጥ።

## ተግባር ሁለት ፡- ጥርስን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፡- ጥርስን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ብስኩት፣ ስኳር፣ ከረሜላ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለሕፃናት ብስኩት፣ ከረሜላ፣ ስኳር በማሳየት ምን እንደሆኑ መጠየቅ
- ሕፃናት አዘውትረው እነዚህን ጣፋጭ ምግቦች የሚመገቡ ከሆነ ጥርሳቸው ሊበላሽ እንደሚችል መንገር እና ማወያየት
- ሕፃናት ጥርሳቸው እንዳይበላሽ ሁልጊዜ ከምግብ በኋላ አፋቸውን መጉመጥመጥ እንዳለባቸው ማስገንዘብ
- ካልተጉመጠመጡ ግን አፋቸው ሊሸት እንደዚሁም ጥርሳቸውም ሊበላሽ እንደሚችል መንገር

> ማስታወሻ ፦ ሁልጊዜ በአፀደ ሕፃናት ውስጥ ሕፃናት ከምግብ በኋላ እንዲጉመጠመጡ በማስታወስ ክትትል እና ድጋፍ በማድረግ ልምድን እንዲያዳብሩ ማስቻል ያስፈልጋል።

ምዘና ፦ ጥርስን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን መለየታቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፦ ስለጥርስ እንክብካቤ መረዳት

ዓላማ ፦ ጥርሳቸውን እንዴት ማጽዳት እንደሚችሉ ይረዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- “ጥርስን መፋቅ እንደዚህ ነው።” የሚለውን መዝሙር መዘመር
- በአካላዊ እንቅስቃሴ ከላይ ወደ ታች እና ከታች ወደላይ እጆችን በማንቀሳቀስ ማሳየት
- ሕፃናቱም መዝሙሩን አብረው እንዲዘምሩ እና እጃቸውን ከላይ ወደታች እና ከታች ወደላይ በማንቀሳቀስ እንዲለማመዱ ማድረግ
- የጥርስ ብሩሽ እና የመፋቂያ እንጨት ለሕፃናት በማሳየት ምን እንደሆነ እና ለምን እንደሚጠቅም እና ተጠቅመውበት ያውቁ እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- መምህርም የጥርስ ብሩሽ እና የጥርስ ሣሙናን እንዴት መጠቀም እንደሚቻል በተግባር ማሳየት
- የጥርስ ሳሙና ለአንድ ጊዜ አተር የምታክል መጠን በቂ እንደሆነ መንገር
- የጥርስ ሣሙና መዋጥ እንደሌለበት መንገር

- ለመፋቂያነት የሚሆኑ የእንጨት አይነቶችን መጠቀም
- በመፋቂያ እንጨትም እንዴት ማጽዳት እንደሚቻል ማሳየት
- ሕፃናቱ ገና ለጋ ስለሆኑ በጥርስ ብሩሽና በመፋቂያ እራሳቸው ሳይሆኑ ወላጆቻቸው ጥርሳቸውን እንደሚያፀዱላቸው መንገር
- ሕፃናት ጠዋት እና ማታ ከምግብ በኋላ ጥርሳቸውን በውሃ በመጉመጥመጥና ምላሳቸውን በማንቀሳቀስ ማፅዳት እንዳለባቸው እና የሌሎችን የጥርስ ብሩሽም ሆነ የእንጨት መፋቂያ መጠቀም እንደሌለባቸው ማሳሰብ ያስፈልጋል።

ማስታወሻ ፡- ለወላጆቻቸው/ለአሳዳጊዎቻቸው በቃል በመንገር ወይንም ማስታወሻ በመላክ በቤት ውስጥም ክትትልና ድጋፍ በማድረግ ሕፃናቱ ከምግብ በኋላ የመጉመጥመጥ ልምድ እንዲያዳብሩ ድጋፍ እንዲያደርጉላቸው ማድረግ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- ጥርሳቸውን እንዴት ማጽዳት እንደሚችሉ መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 7. በመዳሰስ ነገሮችን እና ሁኔታዎችን መግለጽ | 7.1 ሙቀትን መለየት እና በመዳሰስ የተሰማቸውን ስሜት መግለጽ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ሙቀት እና ቅዝቃዜ መለየት

ዓላማ ፡- ሙቀት እና ቅዝቃዜን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የውሃጣሳዎች፣ ለብ ያለ ውሃ፣ ቀዝቃዛ ውሃ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሁለት የውሃ መያዣ ጣሳዎችን በመጠቀም በአንደኛው ለብ ያለ ውሃ በሌላኛው ደግሞ ቀዝቃዛ ውሃ ማድረግ

- ሁሉም ሕፃናት በየተራ እጃቸውን በጣሳዎቹ ውስጥ በመክተት የተሰማቸውን ስሜት በመጠየቅ፤‹‹ይሄ ይሞቃል፣ ይሄ ደግሞ ይቀዘቅዛል›› በማለት እንዲናገሩ ማበረታታት
- በየትኛው የሰውነት ክፍላቸው እንዳወቁ እና እንዴት ሊያውቁ እንደቻሉ በመጠየቅ የእጃቸውን ጥቅም እንዲረዱ ማድረግ

ማስታወሻ ፦ ለዚህ ተግባር የምንጠቀምበት ውሃ ሙቀት ተመጣጣኝ እንዲሆን እና ልጆች ቤት ውስጥ በምንም አይነት ሁኔታ የፈላ ውሃ ውስጥ እጃቸውን መክተት እንደሌለባቸው ማስገንዘብ አስፈላጊ ነው።

ምዘና ፦ ሙቀት እና ቅዝቃዜን መለየት መጀመራቸውን ተግባሩን ሲያከውኑ በማየት እና በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ በመዳሰስ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፦ በመዳሰስ የነገሮችን ምንነት ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በአካባቢ የሚገኙ ትናንሽ ቁሳቁሶች፣ ዓይንን መሸፈኛ ጨርቅ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የሚጠቀሙባቸውን ቁሳቁሶች ከሕፃናቱ ፊት ጠረጴዛ ላይ ማስቀመጥ
- እያንዳንዱን በማንሳት ምን እንደሆነ እና ለምን ተግባር እንደሚያገለግል በመጠየቅ ማወያየት
- “ተዓምረኛው ከረጢት” ጨዋታን በሚከተለው መንገድ ማጫወት
  - የሚያውቋቸውን ቁሳቁሶች በማሳየት ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ
  - ቁሶቹን በከረጢት ውስጥ መክተት
  - በፈቃደኝነት በማስነሳት አይኖቻቸውን ላላ አድርጎ በጨርቅ ማሰር
  - እጃቸውን ከረጢት ውስጥ በመክተት አንድ አንድ ዕቃ እንዲያወጡ ማድረግ
  - በመዳሰስ ያወጡትን ዕቃ ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ፣

- ○ ከዛም ጨርቁን ፈትቶ ትክክል መሆን አለመሆናቸውን እራሳቸው እንዲያረጋግጡ በማድረግ ማጫወት

ምዘና ፡- በመዳሰስ የነገሮችን ምንነት መለየታቸውን በጨዋታ ወቅት በማየት ማረጋገጥ።

**ተግባር ሶስት ፡- ለስላሳ እና ሸካራ ነገሮችን መለየት**

ዓላማ ፡- በመዳሰስ ለስላሳ እና ሸካራ ነገሮችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡ - የብርጭቆ ወረቀት፤ለስላሳ ጨርቅ ወይም በአካባቢ የሚገኙ ለስላሳ እና ሸካራ ነገሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሸካራና ለስላሳ ነገሮችን ጠረጴዛቸው ላይ መደርደር
- በመዳሰስ መልክ እንዲነኩአቸው ማድረግ
- የትኛው ሸካራ የትኛው ለስላሳ እንደሆነ መጠየቅ
- ሲዳስሱአቸው የተሰማቸውን ስሜት መጠየቅ

ማስታወሻ ፡- በመዳሰስ ሊለዩ የሚችሉ በአካባቢያቸው ያሉ ነግሮችን እየዳሰሱ እንዲለዩ ማበረታታት።

ምዘና ፡- በመዳሰስ ለስላሳ እና ሸካራ ነገሮችን መለየታቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ዉጤት | ብቃት |
|---|---|
| 8. ጤናን መጠበቅና የአመጋገብ ሥርዓቶችን መለማመድ | 8.1 የአመጋገብ ሥርዓትን ይለማመዳሉ። |

ዓላማ ፡- ተገቢ የሆነ የአመጋገብ ሥርዓትን ይተዋወቃሉ።

የመርጃ መሳረያዎች ጥቆማ ፡- የውሃ ኩባያ፣ ሰሃኖች

**ተግባር አንድ ፡- ተገቢ የአመጋገብ ሥርዓትን መተዋወቅ**

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሕፃናት ምግብን በሚመገቡበት ሰዓት ማወቅ እና መልመድ የሚገባቸው የአመጋገብ ሥርዓቶች እንደሚከተለው ማስረዳት
    - ምግብ መጥኖ መጉረስ
    - አፍ ውስጥ ምግብ ይዞ አለማውራት
    - ሲያኝኩ ድምጽ አለማሰማት
    - በአፍ ያለ ምግብን ሳይውጡ ሌላ አለመጉረስ
    - ምግብ በምንመገብበት ወቅት ውሃ በኩባያ ማቅረብ
    - ምግባቸው ከተንጠባጠበ ከመሬት አንስተው መብላት እንደሌለባቸው እና የመሣሡሉትን ማስረዳት እና በተግባር ማሳየት
- እነዚህን ምግብ በሚመገቡበት ሰዓት እንዲለማመዱ ማድረግ

> ማስታወሻ ፦ እነዚህ ክህሎቶች ለአንድ ጊዜ ብቻ የሚተገበሩ ሳይሆኑ ዕለት ተዕለት ሕይወታቸው መለማመድ እና ማድረግ የሚገባቸዉ በመሆኑ ሁልጊዜም መተግበራቸዉን መከታተል።

ምዘና ፦ ተገቢ የዓመጋገብ ሥርዓትን መተዋወቃቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

**ተግባር ሁለት፦ የሹካ እና ማንኪያ አጠቃቀም**

ዓላማ ፦ ሹካ እና ማንኪያ አያያዝ እና አጠቃቀምን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ሹካ፣ ማንኪያ፣ ዶቃዎች፣ የዛፍ ፍሬዎች፣ ጥራጥሬዎች ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሕፃናት አዘውትረው የሚመገቧቸውን ምግቦች ስም በመጥራት በምን ሊመገቡ እንደሚችሉ መጠየቅ
- በተለያዩ ሰሃኖች ሹካና ማንኪያ፣ ጥራጥሬዎች፣ዶቃዎች ወዘተ...መስጠት።
- ማንኪያዎቹን በመጠቀም ጥራጥሬዎቹን ከአንድ ሰሃን ወደ ሌላ ሰሃን እንዲሰፍሩ ማድረግ

> ማስታወሻ ፦ ይሄን ተግባር ቁርሳቸዉን ወይም ምሳቸዉን በሚበሉበት ጊዜ ማድረግ ይቻላል።

ምዘና ፡- የሹካ እና የማንኪያ አያያዝና አጠቃቀማቸውን በማየት መገምገም።

ተግባር ሶስት ፡ - እጅን መታጠብ

ዓላማ ፡- እጃቸዉን በተገቢው ሁኔታ መታጠብ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዝሙር ካሴት፣በጣሳ ውሃ፣ ፎጣ፣ ሣሙና ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- “እጅን መታጠብ እንደዚህ ነው” የሚለውን መዝሙር ከሕፃናት ፊት በመቆም መዘመር
- እጅን ስንታጠብ የእጃችንን የውስጥ እና የውጪኛውን ክፍል እንዲሁም የእጅ ጣቶቻችን መካከል በማሸት መታጠብ እንዳለብን ማሳየት
- ባዩት መሠረት መዝሙሩን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት እንዲዘምሩ ማድረግ
- እጅን ለመታጠብ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን በማቅረብ እጃቸውን እንዴት እንደሚታጠቡ እና እንደሚያደርቁ እየተናገሩ ማሳየት
- ሁሉም በየተራ እንዲለማመዱ እድሉን መስጠት

> ማስታወሻ ፡- ሁልጊዜ ከምግብ በፊት እና በኋላ እጃቸዉን መታጠብ እንደዚሁም አፍን መጉመጥመጥ መርሳት እንደሌለባቸው ማስገንዘብ ክትትልም ማድረግ።ይሄን ተግባር የት/ቤቱን እጅ መታጠቢያ በመጠቀም ማከናወን ይቻላል።

ምዘና ፡- እጃቸውን በተገቢው ሁኔታ መታጠብ መጀመራቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 9. አካልን በጥንቃቀቄ መያዝ እና መንከባከብ | 9.1. አካላቸውን መጠበቅ እና በእንክብካቤ መያዝን ይችላሉ:: |

ተግባር አንድ ፡- አካላቸውን ሊጎዱ የሚችሉ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፡- አካላቸውን ሊጎዱአቸው የሚችሉ ነገሮችን ይለያሉ

የመርጃ መሳርያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሀፍ፣ ምላጭ፣ መርፌ፣ የተሰባበሩ ጠርሙሶች፣ ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መምህር የተለያዩ ገጠመኞችን በመንገር ከአደገኛ እና ሊጎዱአቸው ከሚችሉ ነገሮች እንዲጠበቁ ማስረዳት

  ለምሳሌ ፡- የሚከተለውን ገጠመኝ ለህፃናቱ መንገር፡-

  "ዛሬ ጠዋት ወደ እናንተ ስመጣ በመንገድ ላይ አንድ ትንሽ ልጅ ቁጭ ብሎ ሲያለቅስ አየሁት እና ‹ምን ሆነህ ነው የምታለቅሰው›? ብዬ ጠየቅኩት። እርሱም ‹የወደቀ ምላጭ አግኝቼ ሳር ልቆርጥበት ስል ምላጩ ጣቴን ቆረጠኝ›; አለና የተቆረጠውን ጣቱን አሳየኝ። እኔም በሁኔታው አዝኜ ቀረብ ወዳለ ጤና ጣቢያ ይዤው ሄድኩኝ። እዛም ያለቸው ሐኪም የልጁ ደም እጁን እንዳይነካት ጓንት አጥልቃ አከመችው። እኔም ‹ሁለተኛ የወደቀ ምላጭ እንዳታነሳ›; ብዬ መከሬው ወደ እናንተ መጣሁ።"

- እነሱ በህፃኑ ቦታ ቢሆኑ እንደሱ ያደርጉ እንደነበር እና እንዳልነበር በመጠየቅና ማወያየት
- መርፌ፣ ምላጭ፣ የተሰባበረ ጠርሙስ፣ የዛገ ምስማር፣ ሽቦ የመሳሰሉትን ቁሶች ህፃናት መንካት እንደሌለባቸው በመንገር ጎጂነታቸውን እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፡- የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ በአካላቸው ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- የአልባሳትን እና የጫማ ጥቅምን መገንዘብ

ዓላማ ፡- የአልባሳትን እና የጫማ ጥቅምን ይገነዘባሉ።

የመርጃ መሳርያዎች ጥቆማ ፡- የልጆች ዩኒፎርም፣ የልጆች ጫማዎች፣ የአሻንጉሊት ልብስ እና ጫማ፣ ከእንጨት ፍሬም የተዘጋጀ ልብስ ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ስለ "አየለ ሞኙ" ታሪክ እንደሚከተለው መናገር፡-

በዱሮ ጊዜ አንድ አየለ ሞኙ የሚባል ልጅ ነበር። አየለ ጠዋት ከእንቅልፉ ይነሳና እናቱን እማዬ እጀቴን እንዳይበርዳቸው ካልሲ ላድርግ ብሎ ያደርጋል እንደገና ደግሞ እማዬ እራሴን እንዳይበርደኝ ቁምጣዬን ላድርግ ብሎ ቁምጣውን ራሱ ላይ ያደርጋል... በማለት ሕፃናት አየለ ለምን ሞኝ እንደተባለና ካልሲ ምን ላይ እንደሚደረግ በመጠየቅ ማወያየት

- ሰውነታችንን እንዳይበረደው ልብስ መልበስ እንዳለብን
- እንቅፋት እግራችንን እንዳይመታን ጫማ ማድረግ እንዳለብን
- የጫማ ማሰሪያዎች ሁልጊዜ በትክክል መታሰር እንዳለባቸው በመንገር

ምዘና ፡- የአልባሳት እና የጫማ ጥቅምን መገንዘባቸዉን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ መገምገም።

ተግባር ሶስት ፡- አካልን በንፅህና የመያዝ አስፈላጊነት

ዓላማ ፡- በደረጃቸው አካልን በንፅህና የመያዝ አስፈላጊነትን ይናገራሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጎላ ብሎ የተሳለ ሰዎች ፊታቸውን፣ እጃቸውን፣ እግራቸውን፣ ፀጉራቸውን ወዘተ ሲታጠቡ የሚያሳይ ስእል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናት እይታ አመቺ ቦታ ላይ ስእሉን በመለጠፍ ህፃናቱን የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ በስእሉ ላይ ስላዩት ነገር እንዲናገሩ እድሉን መስጠት
- እነሱም በስእሉ ላይ እንዳዩት ንፅህናቸውን በመታጠብ መጠበቅ እንዳለባቸው መንገር

- ከምግብ በፊትና በኋላ፣ ከመፀዳጃ ቤት መልስ እጃቸውን በሳሙና መታጠብ እንዳለባቸው
- በየቀኑ ጠዋትና ማታ ፊታቸውን መታጠብ እንዳለባቸው
- በየቀኑ ከትምህርት ቤት መልስ እግራቸውን መታጠብ እንዳለባቸው
- በየጊዜው ፀጉራቸውንና ሰውነታቸውን መታጠብ እንዳለባቸው
- ጥፍራቸው በየጊዜው መቆረጥ እንዳለበት

- ከላይ በተገለፀው መንገድ የአካላቸውን ንፅህና ካልጠበቁ ግን ለተለያዩ በሽታዎች እንደሚጋለጡ ሊገባቸው በሚችል ግልፅ በሆነ መንገድ መግለጽ

ማስታወሻ ፡- እለት በእለት ህፃናቱ የግል ንፅህናቸውን መጠበቅና አለመጠበቃቸውን መከታታልና ወላጅ የህፃናቱ አካል ንፅህና በተገቢው ሁኔታ እንዲጠብቅ ማንቃት ያስፈልጋል፡፡

ምዘና ፡- የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አካልን በንፅህና የመያዝ አስፈላጊነትን መገንዘባቸውን በማዳመጥ ማረጋገጥ፡፡

ተግባር አራት ፡- እጅን እና ፊትን መታጠብ

ዓላማ ፡- እጃቸዉን እና ፊታቸዉን መታጠብ ይለማመዳሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የውሃ ጣሳ፣በአፀደ ህጻናት ቅጥር ግቢ ውስጥ የሚገኙ ቧንቧዎች፣ የተለያዩ ሳሙናዎች (እጃክስ፣የፊት/የገላ፣ የልብስ)፣ፊት እና እጅን መጥረጊያ ሊሆኑ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመቆም መምህር የጓዋናቸውን እጅጌ ወደላይ በማጠፍ ሁለቱንም እጆች በሳሙና እና በውሃ በመታጠብ ለህፃናቱ ማሳየት
- በመቀጠልም ፊትን በውሃ ብቻ በመታጠብ በንፁህ ጨርቅ ማድረቅ
- በተመሳሳይ ልጆቹ በየተራ መምህር ባሳዩአቸው መሰረት የሹራብና የሸሚዛቸውን እጅጌ ወደላይ በመሰብሰብ እጃቸውን በሳሙናና በውሃ፣ ፊታቸውን ደግሞ በውሃ ብቻ እንዲታጠቡ ማድረግ

- ሕፃናት በሳሙና ፊታቸውን መታጠብ እንደሌለባቸው አጽንኦት ሰጥቶ መንገር
- የሳሙናዎችን ልዩነት እና አገልግሎቶች ማስረዳት

ለምሳሌ ፡- የእቃ፣ የልብስ፣ የእጅና የገላ ሳሙና ለምን እንደሚየገለግሉ በመግለፅ ባገኙት ሳሙና እንዳይታጠቡ መንገር ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- እጃቸዉን እና ፊታቸዉን መታጠብ መለማመዳቸዉን በማየት መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 10. ጉልህና ረቂቅ /ትላልቅና ትናንሽ/ ጡንቻዎችን መጠቀም | 10.1. የሰውነት ክፍሎቻቸውን ለተለያዩ ተግባራት መጠቀም ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የሰዉነት ሚዛንን ጠብቆ መራመድ

ዓላማ ፡- የሰዉነት ሚዛናቸውን ጠብቀው ይራመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሰፋ ባለ ቦታ ላይ/ በክፍል ወይም በግቢ ውስጥ/እጅ የመዘርጋት ያህል ተራርቀው ወደ ጎን እንዲቆሙ ማድረግ
- ዓይንን ጨፍኖ እንዴት መራመድ እንደሚቻል በተግባር ማሳየት
- እያንዳንዳቸው በየተራ አይናቸውን ጨፍነው አምስት ያህል እርምጃ እንዲራመዱ ማድረግ
- ዓይናቸውን በመግለጥ ዞረው ወደ ቦታቸው እንዲመለሱ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- አካባቢው ህፃናቱን ጉዳት ላይ የሚጥሉ ነገሮች የሌሉበት ሊሆን ይገባል።

ምዘና ፡- የሰውነት ሚዛናቸዉን ጠብቀዉ መራመዳቸውን መገምገም።

ተግባር ሁለት ፡- የሰውነት ሚዛንን ጠብቆ በመስመር ላይ መራመድ

ዓላማ ፡- የሰውነት ሚዛናቸውን ጠብቀው ከመስመር ሳይወጡ ይራመዳሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፦ ጠመኔ /ቾክ/፣ ሲባጎ /ገመድ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ወገባቸውን ይዘው ቀጥ ብለው እንዲቆሙ ማድረግ
- መነሻ እና መድረሻቸውን በቾክ ምልክት በማድረግ እንዲያዩት ማድረግ
- ከመነሻ እስከመድረሻቸው ሲባጎ ወይም ገመድ መሬት ላይ መዘርጋት (ገመድ ጠልፎ እንዳይጥላቸው ጥንቃቄ ማድረግ ይገባል)
- ወገባቸውን ይዘው ሚዛናቸውን ጠብቀው እንዲሄዱ ማድረግ

ምዘና ፦ ሚዛናቸዉን ጠብቀዉ ከመስመሩ ሳይወጡ መራመዳቸውን መመዘን።

ተግባር ሶስት ፦ የሰውነት ሚዛንን ጠብቆ በመስመር ውስጥ መሮጥ

ዓላማ ፦ የሰውነት ሚዛናቸውን ጠብቀው ከመስመር ሳይወጡ ይሮጣሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፦ ጠመኔ/ ቾክ/፣ ሲባጎ/ገመድ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ከክፍል ውጩ ሴቶችና ወንዶች በሁለት ረድፍ እንዲሰለፉ ማድረግ
- ከፊት ለፊታቸው 50-60 ሴ.ሜ ርቀት ሁለት የተለያዩ መስመሮችን ማስመር በረድፍ በመጀመሪያ እጃቸውን ዘርግተው ቀጥለውም ወገባቸውን ይዘው ከተሰመረው መስመር ሳይወጡ እንዲሮጡ ማለማመድ

ምዘና ፦ የሰውነት ሚዛናቸውን ጠብቀው ከመስመር ሳይወጡ መሮጥ መቻላቸዉን መገምገም።

ተግባር አራት ፦ የሰውነት ሚዛንን ጠብቆ መዝለል

ዓላማ ፦ የሰውነት ሚዛናቸውን ጠብቀው በሁለት እግራቸው ይዘላሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፦ ገመዶች/ሲባጎ ወይም ቾክ/ጠመኔ ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከክፍል ውጩ ሴቶችና ወንዶች በሁለት ረድፍ እንዲሰለፉ ማድረግ
- በመካከላቸው ከ 30-40 ሴ.ሜ አራርቆ ሁለት ገመዶችን በትይዩ በመሬት ላይ መዘርጋት
- በሁለት እግር ገመዱን ሳይረግጡ እንዴት እንደሚዘለል ማሳየት
- በየተራ እንዲዘሉ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- ወገብን ይዞ መዝለል እጅን ዘርግቶ ከመዝለል ከበድ ስለሚል መምህር ህፃናቱን ሲያለማምዱ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርባቸዋል፡፡ እንደዚሁም ሕፃናቱ የሚሮጡበት እና የሚዘሉበት አካባቢ ምቹ መሆኑን አስቀድሞ ማረጋገጥ ያስፈልጋል፡፡

ምዘና ፡- የሰውነት ሚዛናቸዉን ጠብቀዉ በሁለት እግራቸው መዝለል መቻላቸውን መከታተል፡፡

ተግባር አምስት ፡- ኳስ በመወርወር ኢላማን መምታት መለማመድ

ዓላማ ፡- ኳስ በመወርወር ኢላማን መምታትን ይለማመዳሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ትናንሽ ኳሶች፣ ጎማዎች /ቱቦዎች/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከቅርብ ርቀት ትንሽ ኳስ በመወርወር በተተከለ ጎማ ውስጥ ማሾለክን ማሳየት
- ሁሉም ህፃናት በየተራ ባዩት መሠረት እንዲጫወቱ ማድረግ
- ለመወርወር የሚቸገርን ሕፃን መለየትና እያያዝና አወራወር ማሳየት

ምዘና ፡- ኳስ በመወርወር ከቅርብ ርቀት ኢላማ መምታትን መለማመዳቸዉን የጨዋታውን ሂደት በማየት መገምገም፡፡

ተግባር ስድስት ፡- መሽሎክሎክ

ዓላማ ፡- በተለያዩ ነገሮች ውስጥ መሽሎክሎክ ይለማመዳሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ትናንሽ ጎማዎች /ቱቦዎች/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በግቢ ውስጥ መሬት ላይ በግማሽ በተተከሉ ወይም በተቀበሩ ትላልቅ ጎማዎች/ ቱቦዎች/ ፊት ለፊት በረድፍ እንዲቆሙ ማድረግ
- በተተከለው ጎማ ወይም ቱቦ ሲሽልኩ ጭንቅላታቸውን እንዳይመታቸው ጎንበስ ማለት እንዳለባቸው አስቀድሞ መግለፅ
- በየተራ እንዲሽሎከሎኩ ማድረግና ጉዳት እንዳይደርስባቸው መቆጣጠር

ምዘና ፡- በተለያዩ ነገሮች ውስጥ መሹሎክሎክ መቻላቸውን የጨዋታውን ሂደት በማየት ማረጋገጥ።

**ተግባር ሰባት ፡- መሰላል መውጣት እና መንሸራተት**

ዓላማ ፡- መሰላል መውጣት እና መንሸራተት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- መሰላል፣ ሸርተቴ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በግቢ ውስጥ ባሉ መሰላል ፊት ለፊት በረድፍ ሴቶች ለብቻ ወንዶች ለብቻ እንዲሰለፉ ማድረግ
- መሰላል በመውጣትና በመውረድ ሂደት ላይ በሁለት እጃቸው መሰላሉን መያዝ እንዳለባቸው ማስጠንቀቅ
- ተራቸውን ጠብቀው መሰላልን መውጣት እና መውረድን እንዲለማመዱ ማበረታታት
- በመሰላል ወጥተው መንሸራተትን ማለማመድ
- የሚፈሩ ሕፃናትን ማደፋፈር
- አንዱ ህፃን ተንሸራቶ ሳይወርድና ከታች ሳይነሳ ሌላ ህፃን መንሸራተት እንደሌለበትና ቢንሸራተት ሊከሰት የሚችለውን አደጋ ሊገባቸው በሚችል መልኩ ማስገንዘብ

> ማስታወሻ ፡- መሰላል ሲወጡና ሲወርዱ አጠገባቸው መሆን የሚያስፈልግ ሲሆን መሰላል ላይ መውጣት ያልፈለገን ህፃን ማስገደድ አያስፈልግም።

ምዘና ፡- መሰላል መውጣት እና መንሸራተት መለማመዳቸዉን መከታተል።

**ተግባር ስምንት ፡- ጎማ ማንከባለል**

ዓላማ ፡- ኳሷ ማንከባለል ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ትናንሽ ኳሷዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከህፃናቱ ፊት ለፊት ትንሽ ራቅ ብሎ በመቆም ቀስ አድርጎ ትንሽ ኳሷን በሁለት እጅ በማፈራረቅ እያንከባለሉ ህጻናቱ ወደቆሙበት በማንከባለል ማሳየት
- ወንዶች በሁለት ረድፍ ሴቶችም በሁለት ረድፍ እንዲሰለፉ ማድረግና ከፊት ላሉት ህፃናት ትናንሽ ኳሷዎችን አንዳንድ በመስጠት ከተሰመረላቸው መነሻ በመነሳት መድረሻው ድረስ በማንከባለል እንዲጫወቱ ማድረግ
- ኳሷዎች ሲያንከባልሉ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ተጠጋግተው እንዳያንከባልሉ ማድረግ

ምዘና ፡- ኳሷ ማንከባለል መቻላቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር ዘጠኝ ፡- ሚዛን ጠብቆ በፍጥነት መንቀሳቀስ

ዓላማ ፡- ሚዛናቸውን ጠብቀው በፍጥነት መንቀሳቀስ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ትንሽ ጨርቅ/መሀረብ/፣ ከገመድ ወይም ከልጥ የተሰራ ጅራፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናት እጅ ለእጅ በመያያዝ ክብ በመስራት ቁጭ ብለውመሀረቤን ያያችሁ ጨዋታን እንዲጫወቱ ማድረግ
- ፈጣኑ ባቡር (ሰለሜ ሰለሜ) መስመራቸውን እና ሚዛናቸውን ጠብቀው በንቃት የመረውን እንቅስቃሴ በማስተዋል ከአንዱ ወደ ሌላው አቅጣጫ እየተዘዋወሩ እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፡- ሚዛናቸውን ጠብቀው በፍጥነት መንቀሳቀስ መለማመዳቸዉን መከታተል።

**ተግባር አስር ፡- ቀለል ያሉ የአካል እንቅስቃሴዎችን መሥራት**

ዓላማ ፡- ቀለል ያሉ የሰውነት ማጎልመሻ እንቅስቃሴዎችን ይሠራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የወረቀት አበባ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ህፃናቱ በ አምስት ወይም በስድስት ረድፍ እንዲሰለፉ ማድረግ
- በእጆቻቸዉ ላይ የወረቀት አበባ ማስያዝ
- መምህር ከህጻናቱ ፊት ለፊት በመቆም ሁለት እጆችን በማንሳት ወደ ግራ ወደ ቀኝ፣ ወደ ላይ ወደ ታች፣ወደፊት ወደ ኋላ በማድረግ ሰውነትን አብሮ በትንሹ በማንቀሳቀስ እንቅስቃሴውን በመስራት ማሳየት
- ህፃናት እያንዳንዱን እንቅስቃሴ መምህርን በመከተል ከመመህር ጋር አብረው እንዲሰሩ በማድረግ ማበረታታት

ማስታወሻ ፡- መምህር እንቅስቃሴውን ሲያሰሩ አቅጣጫውን አብረው መናገር ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- ቀለል ያሉ የሰውነት ማጎልመሻ እንቅስቃሴዎችን መስራት መቻላቸዉን መገምገም።

**ተግባር አስራ አንድ ፡- የአካል እንቅስቃሴዎችን መስራት**

ዓላማ ፡- የተለያዩ የአካል እንቅስቃሴዎችን ይሰራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ዱብ ዱብ ብለው ሰውነታቸውን እንዲያሟሙቁ ማድረግ
- እግሮቻቸዉን ትንሽ ከፊት አድርገዉ እጃቸዉን በወገብ አድርገዉ እንዲቆሙና እና ወደፊት ጎንበስ በማለት ጉልበቶቻቸዉን በእጆቻቸዉ ነክተዉ እንደመለሱ ማድረግ
- የተወሰነ ጊዜ በመደጋገም እንዲሰሩ ማድረግ
- አቋቋማቸዉ ከላይ እንደተጠቀሰዉ ሆኖ

  - አንድ ሲባል እጃቸዉን ወደ ላይ እንዲያነሱ
  - ሁለት ሲባል እንዲያጨበጭቡ ማድረግ

- ህጻናት እግራቸዉን ወደፊት ዘርግተዉ ወገባቸዉን ይዘዉ በወለል ላይ እንዲቀመጡ ማድረግ
  - አንድ ሲባል እጆቻቸዉን ወደፊት እንዲዘረጉ
  - ሁለት ሲባል የእግር ጣቶቻቸዉን እንዲነኩ
  - ሶስት ሲባል ወደነበሩበት አቀማመጥ እንዲመለሱ በማድረግ ማለማመድ

ማስታወሻ ፦ መምህር እነዚህን የሰውነት ማጎልመሻ እንቅስቃሴዎች በእርጋታ እንዲሰሩ ማሳሰብ እና አንዳንድ እንቅስቃሴዎችን የማይችሉ ሕፃናትን አለማስገደድ አስፈላጊ ነው፡፡

ምዘና ፦ የተለያዩ ቀለል ያሉ የአካል እንቅስቃሴዎችን መስራት መቻላቸዉን መከታተል፡፡

ተግባር አስራ ሁለት ፦ ክር ዶቃዎች ውስጥ መክተት

ዓላማ ፦ በሰፋፊ ዶቃዎች ውስጥ መክተትን ይለማመዳሉ

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያየ ቀለም እና ሰፋፊ ቀዳዳ ያላቸው ዶቃዎች

የአተገባበር ጥቆማ፦

- የተለያየ ቀለም እና ሰፋፊ ቀዳዳ ያላቸዉ ትላልቅ ዶቃዎች ዉስጥ እንዴት ክር መክተት እንደሚቻል ማሳየት
- ለእያንዳንዱ ህጻን ሶስት ሶስት የተለያየ ቀለም ያላቸዉ ዶቃዎች እና ሲባጎ /ክር/ በመስጠት ባዩት መሠረት ክሩን በሶስቱም ዶቃዎች ውስጥ እንዲያስገቡ ማድረግ
- በየጠረጴዛቸዉ እየተዘዋወሩ በማየት ለከበዳቸዉ ፍንጭ መስጠት
- የሰሩትን በጓደኞቻቸዉ ፊት ወጥተዉ እንዲያሳዩ እና ቀለማቱን እንዲናገሩ ማበረታታት
- ይህን ለመተግበር በቀላሉ የእስከሪፕቶ ቀፎዎችን በተለያየ መጠን በመቁረጥ ወይም የፕላስቲክ የውሃ መያዣ መክደኛዎችን ሰፋ አድርጎ በመብሳት መጠቀም ይቻላል

ማስታወሻ ፦ ዶቃዎቹን ወደ አፋቸዉ፣ አፍንጫቸዉ፣ ጆሮአቸዉ እና ኪሳቸዉ ዉስጥ መክተት እንደሌለባቸዉ በማስጠንቀቅ መንገር እና መከታተል ያስፈልጋል፡፡

ምዘና ፦ ዶቃዎች ዉስጥ ክር መክተት መቻላቸውን በማየት መገምገም፡፡

ተግባር አሥራ ሶስት ፦ ወረቀት ላይ መሞነጫጨር

ዓላማ ፦ እጃቸውን ወደፈለጉበት ቦታ በማንቀሳቀስ ወረቀት ላይ ይሞነጫጭራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያየ መጠን ያላቸው ወረቀቶች፣ እርሳስ (ባለቀለም እርሳስ ቢሆን ይመረጣል)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ነጭ ወረቀትና እርሳስ ለሕፃናቱ ማደል
- በነፃነት ወረቀቱ ላይ እንዲጽፉ ወይም እንዲሞነጫጭሩ ማድረግ
- የሳሉት ወይም የሞነጫጨሩት ነገር ትርጉም እንዳለው መጠየቅ

ምዘና ፦ ወረቀት ላይ መሞነጫጨር ወይም ስእል መሳል መጀመራቸውን መከታተል።

**ተግባር አስራ አራት ፦ የእርሳስ አያያዝ እና አጠቃቀም**

ዓላማ ፦ እርሳስ አያያዝን እና አጠቃቀምን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያየ መጠን ያላቸው ወረቀቶች፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ከህፃናቱ ፊት ለፊት በመቆም ትልቅ ባለቀለም እርሳስን በመጠቀም የተለያዩ ቀላል የሆኑ መሠረታዊ መስመሮችን በመስራት ማሳየት
- ወረቀትና እርሳስ በመስጠት መምህር ባሳዩአቸው መሠረት እርሳስ እንዲይዙ ማድረግና የተለያዩ ቀላል የሆኑ መሠረታዊ መስመሮችን በማሳየት ባየት መሠረት እነሱም በተሰጣቸው ወረቀት ላይ እንዲሰሩ ማድረግ
- ሲጨርሱም በሰሩት ስራ ግርጌ ስማቸውን በመፃፍ ለእይታ አመቺ በሆነ ቦታ ላይ በክፍል ውስጥ መለጠፍ

ምዘና ፦ የእርሳስ አያያዝ እና አጠቃቀምን መለማመድ መጀመራቸዉን መከታተል።

**ተግባር አስራ አምስት ፦ ስዕል መሳልና መቀባት**

ዓላማ ፡- ስዕል ይስላሉ እንዲሁም ይቀባሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ መጠን ያላቸው ወረቀቶች፣ እርሳሶች፣ ባለቀለም እርሳሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ግማሽ ወረቀቶችን በማጣጠፍ ለእያንዳንዱ ህፃን ትናንሽ መጽሀፎችን አስቀድሞ መስራት
- በመጀመሪያው ገጽ ላይ የህፃናቱን ስም ጎላ አድርጎ በመጻፍ ስማቸውን እየጠሩ ለህፃናቱ የሰሩላቸውን መፅሐፍ መስጠት አሰቀድሞ የመፅሀፉን አገላለጥ ማሳየትና የመፅሀፉን ገፆች መቅደድ እንደማይቻል መንገር
- በመፅሀፉ ጥቂት ገፆች ላይ /2 ወይም 3/ የፈለጉትን ነገር እንዲስሉና ቀለም እንዲቀቡ እድሉን መስጠት
- ህጻናት በያንዳንዱ ገፅ ላይ የሳሉትንና የቀቡትን ስዕል እንዲመለከቱ እና ምን እንደሆነ እንዲገልጹ ማበረታታት
- ሲጨርሱ መፅሀፋቸውን መሰብሰብና ሌላ ጊዜም በተቀሩት ገፆች ላይ እንደሚሰሩ በመንገር ማጠቃለል

ማስታወሻ ፡- ይህ ተግባር በአንድ ክፍለጊዜ ሁሉንም ገጾች ላይ መሳልና መቀባት ስለማይቻል በተለያየ ጊዜ ማከናወን ያስፈልጋል።

ም[illegible] ።

ተግባር አስራ ስድስት ፡- ቅርጻ ቅርጾችን መስራት

ዓላማ ፡- ቀላል ቅርጻ ቅርጾችን ይሰራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ጭቃ ወይም የተቦካ ወረቀት፣ ጠረጴዛ መሸፈኛ ላስቲኮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናት በ “ህ” ቅርጽ እንዲቀመጡ ማድረግ
- ከሕፃናቱ ፊት በመቆም የጋዋንን እጇታ ወደላይ በማጠፍ የተቦካ ጭቃ ወይም ወረቀትን በመጠቀም በቀላሉ ሊሠሩ የሚችሉ እንደ ኳስ፣ ስኒ የመሣሠሉትን በመሥራት ማሳየት
- ህፃናቱ የሹራባቸውን ወይም የሸሚዛቸውን እጇታ ወደላይ እንዲያጥፉ ማድረግ

- በመቀጠልም ጠረጴዛቸው እንዳይቆሽሽ የሚያነጥፉት ቁራጭ ላስቲክ እና የተቦካ ጭቃ ወይም ወረቀት መስጠት
- ኳስ፣ ስኒ፣ ማንኪያ፣የመሣሠሉትን እንዲሠሩ ማድረግ
- ሰርተው ሲጨርሱም ምን እንደሰሩና እንዴት እንደሠሩት ማወያየት
- በመጨረሻም የሰሩትን ቅርጽ ስማቸው በተፃፈበት ወረቀት ላይ በማስቀመጥ ሊደርቅ የሚችልበት ቦታ ላይ እንዲያስቀምጡት ማድረግ

ማስታወሻ ፦ የአሰራር ቅደም ተከተልን በእርጋታ በማሳየት በአንድ ጊዜ አንድ ነገር እንዲሰሩ ማድረግ ይገባል።

ምዘና ፦ ቀላል ቅርጻ ቅርጾችን መስራት መቻላቸዉን በማየት መገመግም።

ተግባር አስራ ሰባት ፦ ተገጣጣሚ ነገር (ፐዝል) መገጣጠም

ዓላማ ፦ ተገጣጣሚ ነገር (ፐዝል)ይገጣጥማሉ፣ የገጣጠሙትንም ምንነት ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ 3 ወይም 4 ቦታ የተቆራረጡ ተገጣጣሚ ነገሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የሚያውቁትን እንሰሳ ወይም ቁሳቁስ በማሳየት ምን እንደሆነ በመጠየቅና ማወያየት
- ከ 3-4 ቦታ የተቆራረጠውን ተገጣጣሚ በማሳየት እንዴት ሊገጣጠም እንደሚችልና ሲገጣጠም ምን ዓይነት ምስል እንደሚሰጥ እንዲመለከቱ ማድረግ
- ፈቃደኛ የሆኑ ሁለት ሕፃናትን ማስወጣትና ለሁለቱም ሕፃናት እኩል 3 ወይም 4 ቦታ የተቆራረጡ ተገጣጣሚዎችን በመስጠት እንዲገጣጥሙ ማድረግ
- የገጣጠሙት ምን እንደሆነ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማድረግ
- ሁሉም ሕፃናት በየተራ ወጥተው በመገጣጠም እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፦ መገጣጠም መቻላቸውንና የገጣጠሙትን ምንነት መናገራቸውን በማየትና በማዳመጥ ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ ስምንት ፦ ነገሮችን በቀለማቸው መመደብ

ዓላማ ፦ የተለያዩ ነገሮችን በቀለማቸው ይመድባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቀማ ፦ ቀይ፣ ሰማያዊ እና ቢጫ የተቀቡ ቆርኪዎች/ቀይ ሰማያዊ እና ቢጫ ቀለም ያላቸው ሌሎች ነገሮች/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለሕፃናቱ በየጠረጴዛቸው ላይ ሶስቱን መሠረታዊ ቀለማት፦ ቀይ፣ ሰማያዊ እና ቢጫ የተቀቡ ቆርኪዎችን ወይም የውሃ መያዣ ፕላስቲክ ክዳኖችን መስጠት
- ቆርኪዎቹን በየቀለማቸው እንዲመድቡ እና ቀለማቸዉን እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፦ የተለያዩ ነገሮችን በቀለማቸው መመደብና ቀለማቸውን መናገር መቻላቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ ዘጠኝ ፦ የእህል ዘሮችን በዓይነታቸው መመደብ

ዓላማ ፦ የእህል ዘሮችን በዓይነታቸው በመለየት ይመድባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ባቄላ፣ በቆሎ፣ አደንጓሬ፣ ሽምብራ፣ ቦሎቄ፣ ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የተደባለቁ የእህል ዘሮችን ለእንዳንዱ ህፃን ሕፃናቱ በየጠረጴዛቸው ላይ መስጠት
- የእህል ዘሮቹን በዓይነታቸው እንዲመድቡ ማድረግ
- መድበው ሲጨርሱ ለመምህር እንዲያሳዩ በማድረግ ማበረታታት
- ልክ መሆንና አለመሆናቸውን በጠረጴዛቸው ዙሪያ ያሉ ህፃናት እንዲያረጋግጡ እድሉን መስጠት

ምዘና፦ የእህል ዘሮችን በዓይነታቸው መለየትና መመደብ መቻላቸዉን የሰሩትን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር ሃያ ፦ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን መመደብ


ዓላማ ፦ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን በመለየት ይመድባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ከወፍራም ካርቶን የተሰሩ የተለያየ ቀለም ያላቸው የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርፆች /ክብ፣ ጐነ ሶስት፣ ካሬ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ከወፍራም ካርቶኒ የተሰሩ የጂኦሜትሪ ቅርጾችን በማሳየት መጠሪያ ስማቸውን መጠየቅ
- እነዚህ የተለያየ ቀለም ያላቸው ቅርፆች በየጠረጴዛቸው እንደሚሰጣቸውና ሳይጣሉ ክቦቹን አንድ ላይ፣ ጎነሶስቶቹን አንድ ላይ እንዲሁም ካሬዎቹን አንድ ላይ መመደብ እንዳለባቸው መንገር
- ቅርፆቹን ለህፃናቱ በየጠረጴዛቸው በመስጠት ተመሳሳይ ቅርፅ ያላቸውን የጂኦሜትሪ ቅርፆች በመለየት በቅርፃቸው እንዲመደቡ ማድረግ
- መድበው ሲጨርሱ ለመምህር በማሳየት የትኞቹ ክብ፣ የትኞቹ ጐነ ሶስት፣ የትኞቹ ካሬ እንደሆኑ እንዲናገሩ ማበረታታት

ለምሳሌ፦



ምዘና ፦ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን በመለየት መመደብ መቻላቸዉን ተግባሩን ሲያከውኑ በማየት መገምገም።

ተግባር ሃያ አንድ ፦ ወረቀቶችን መቦጫጨቅ እና መለጠፍ

ዓላማ ፦ ወረቀቶችን ቦጫጭቀው ይለጥፋሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያዩ መጠንና ቀለም ያላቸው ወረቀቶች፣ የማጣበቂያ ኮላ ወይም ከእህል ዘር የተዘጋጀ ሙቅ፣ ትልቅ ነጭ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለህጻናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመቆም የተለያዩ መጠንና ቀለም ያላቸው ወረቀቶችን ሶስት ቦታ በተለያየ መጠን በመቦጫጨቅ ለሕፃናቱ ማሳየት
- ለእያንዳንዱም ህጻን ባለቀለም ወረቀቶችን በመስጠት ባዩት መሠረት ሶስት ቦታ እንዲቦጫጭቁ ማድረግ
- የማጣበቂያ ኮላ ወይም ከእህል ዘር የተዘጋጀ ሙቅን በመጠቀም ትልቅ ነጭ ወረቀትን መለቅለቅ
- የተቆራረጡትን ባለቀለም ወረቀቶች በትልቁ ወረቀት ባዶ ቦታ ላይ እንዲለጥፉበት ማድረግ
- ሲደርቅ ክፍላቸው ግርግዳ ላይ መለጠፍ

ምዘና ፡- ወረቀቶችን መቦጫጨቅ እና መለጠፍ መቻላቸውን ተግባሩን ሲያከውኑ በማየት ማረጋገጥ።

**ተግባር ሀያ ሁለት ፡- የስጦታ ካርድ መስራት**


ዓላማ ፡- የስጦታ ካርድ መስራት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ክላሰሮች፣ማጣበቂያ ኮላ፣ ባለቀለም ወረቀቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በትልቅ ክላሰር የተዘጋጀ የስጦታ ካርድን በማሳየት ለጓደኛ፣ ለወላጅ በስጦታ መልክ የሚሰጥ መሆኑንና መምህር እንደሰሩት በመንገር ህፃናቱም ለመስራት ያላቸውን ፍላጎት መቀስቀስ
- ለሕፃናቱ የተቆራረጡ ባለቀለም ወረቀቶችን በመስጠት እንዲቦጫጭቁ ማድረግ
- ቦጫጭቀው ሲጨርሱ እንደ ስጦታ ካርድ ታጥፈው የተዘጋጁትን ትናንሽ ክላሰሮችን ማጣበቂያ ኮላ በመለቅለቅ ለህፃናቱ መስጠት
- የቦጫጨቁትን ማጣበቂያ የተለቀለቀው ላይ እንዲለጥፉ ማድረግ
- በመጨረሻም ወደቤታቸው ወስደው ለወላጆቻቸው በስጦታ መልክ እንዲያበረክቱ ማድረግ

  ለምሳሌ፡-



ማስታወሻ ፡- ይህንን ተግባር በተለያየ ጊዜ በማከናወን በእናቶች ቀንና በአባቶች ቀን ለወላጆቻቸው እንዲሁም ለወንድም፣ ለእህትና ለጓደኞቻቸው የልደት በዓልም በስጦታ መልክ እንዲሰጡ ማለማመድ ይቻላል።

ምዘና ፡- የስጦታ ካርድ መስራት መለማመዳቸዉን በተግባር ሲሰሩ በማየት ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 11. በነፃነት ፈጠራን መግለጽ | 11.1. አካላቸውን በመጠቀም ሃሳባቸውን ይገልፃሉ:: |

**ተግባር አንድ ፡- መዝሙርን በእንቅስቃሴ መግለጽ**

ዓላማ ፡- መዝሙርን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት ይዘምራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሸረሪት ስዕል፣ መዝሙር ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የሸረሪትን ስዕል ለሕፃናቱ በማሳየት ምን እንደሆነች እና አይተዋት ያውቁ እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- “ቀስ በቀስ ሸረሪቷ” የሚለውን መዝሙር ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት መዘመር
- ሸረሪቷ እንዴት እንደምትንቀሳቀስ /ፍጥነቷን/፣ ንፋስ ሲመጣ ንፋሱ እንዴት እንደሚያወዛውዛት እና ዝናብ ሲዘንብ እንዴት እንደምትወድቅ ማሳየት
- ሕፃናቱም የመምህሯን እንቅስቃሴ በማየት እንዲዘምሩ ማድረግ
- የተለያዩ ነገሮችን /እንሰሳትን፣ ነገሮችን ዕቃዎችን ወዘተ.../ እንቅስቃሴ በመንገር እና በማሳየት ሕፃናቱ አብረው እንቅስቃሴውን እንዲያሳዩ ማለማመድ

ለምሣሌ፡- እንደ ዛፍ እወዛወዛለሁ

እንደ ወፍ እበራለሁ

እንደ ፌንጣ እዘላለሁ ወዘተ.....

እንደ አሳ እዋኛለሁ

ምዘና ፡- መዝሙርን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት መዘመር መቻላቸውን ሲዘምሩ በማየት ማረጋገጥ።

**ተግባር ሁለት ፡- የሙብረር እንቅስቃሴን በአካል ማሳየት**

ዓላማ ፡- የሙብረር እንቅስቃሴን አካላቸውን በመጠቀም በመዝሙር ይገልፃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የወፍ እና የቢራቢሮ ስዕል፣ የመዝሙር ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የወፍንና የቢራቢሮን ስዕል በማሳየት ምን እንደሆኑ፣ የት እንደሚኖሩ እና እንዴት እንደሚኖሩ በመጠየቅ ማወያየት
- <<ወፊቷን እሆናለሁ>> የሚለውን መዝሙር ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት ከሕፃናት ጋር አብሮ መዘመር

ምዘና ፦ የመብረር እንቅስቃሴን አካላቸው በመጠቀም በመዝሙር መግለፅ መቻላቸውን ሲዘምሩ በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፦ ምትን ተከትሎ መንቀሳቀስ

ዓላማ ፦ ምትን ተከትለው ይንቀሳቀሳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ለታምቡርነት የሚያገለግል ቆርቆሮ ወይም ጣሳ፣ ለመምቻነት የሚያገለግል ዱላ/እንጨት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሕፃናት በግቢ ውስጥ ባለው ሜዳ ላይ በቦታቸው በሁለት ረድፍ እንዲሰለፉ ማድረግ
  - ጣሳ ወይም ቆርቆሮ ሳህን እንደታንቡር በመጠቀም ምቱን ተከትለው በመጫወቻ ሜዳቸው ላይ በሰልፍ እንዲጓዙ ማድረግ
  - ምቱ በሚቆምበት ጊዜ ባሉበት እንዲቆሙና ምቱ ሲቀጥል እንዲንቀሳቀሱ በማድረግ ማለማመድ

ምዘና ፦ ምትን ተከትለው መንቀሳቀስ መቻላቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፦ በአካላዊ እንቅስቃሴ የሚሰጡ ትእዛዞችን ማከናወን

ዓላማ ፦ በአካላዊ እንቅስቃሴ የሚሰጣቸውን ትእዛዝ ለመረዳትና ለማከናወን ይሞክራሉ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- "ማን ቀድሞ ያውቃል?" የሚለውን ጨዋታ ለማጫወት ሁለት ሕፃናትን በማስወጣት ከመምህር አጠገብ እንዲቆሙ ማድረግ
- መምህር ድምጽ ሳያሰሙ በአካላዊ እንቅስቃሴ ብቻ የተለያዩ ትዕዛዞችን በማዘዝ ህፃናቱ በተግባር እንዲፈፅሙ ማድረግ
  - ለምሳሌ ህፃናቱ ከመምህር ትንሽ ራቅ ብለው እንዲቀመጡ ማድረግ መምህር በአካላዊ እንቅስቃሴ ተነሱ፣ ሩጡ፣ ኑ፣ ተቀመጡ በማለት በማዘዝ ህፃናቱ በተግባር ትእዛዙን ተረድተው እንዲተገብሩ ማለማመድ
- ሁሉም ህፃናት በጨዋታው ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ

ምዘና ፦ ያለ ድምጽ የተሰጡ የተለያዩ ትእዛዛትን ተረድተው በአካል እንቅስቃሴ መተግበራቸውን በማየት ማረጋገጥ።

### ተግባር አምስት ፦ በስዕል ሃሳብን መግለጽ

ዓላማ ፦ በስዕል ሃሳባቸውን መግለጽ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ እርሳስ፣ ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለሕፃናት ወረቀትና እርሳስ በመስጠት ደስ ያላቸውን ነገር እንዲስሉ ማድረግ
- ምን እንደሳሉ ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ እና እንዲናገሩ ማድረግ
- የሳሉትን ስእል ከግርጌው ስማቸውን በመፃፍ በክፍል ውስጥ በመለጠፍ ህፃናቱ እንዲመለከቱት ማድረግ

ምዘና ፦ የመረጡትን ስእል በመሳል ሃሳባቸውን መግለጽ መጀመራቸውን መገምገም።

### ተግባር ስድስት ፦ መስሎ ጨዋታ መጫወት

ዓላማ ፦ መስሎ ጨዋታ በመጫወት ሃሳባቸውን መግለጽ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመስሎ ጨዋታ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለመስሎ መጫወት ጨዋታ የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶችን ማሟላት
- ህፃናቱ የፈለጉትን ጨዋታና የመረጡትን ሚና ወስደው እንዲጫወቱ ማነቃቃት
- ለሕፃናቱ በቂ የጨዋታ ጊዜ በመስጠት እንዲጫወቱ ማድረግ
- በጨዋታው ሂደት ህፃናቱን ሳይረብሹ መከታተል

ምዘና ፡- መስሎ ጨዋታዉን ሲጫወቱ ሃሳባቸውን በቃልና በድርጊት መግለጽ መለማመዳቸዉን መከታተል።

## 2.1.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም ----------------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም ------------------------------------------- ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም --------------------------------------------- ዓመተ ምሕረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡-

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ ------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት ------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | የዓመቱ መጀመሪያ | የዓመቱ አጋማሽ | የዓመቱ መጨረሻ |
| **1.** ራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመንና ራስን የማክበር ስሜት መኖር | | | |
| 1.1. ስማቸውን ዕድሜአቸውንና ፆታቸውን መናገር ይችላሉ | | | |
| 1.2. አዲስ ጓደኛን ማፍራትና መወዳጀት ይችላሉ | | | |
| **2.** የሰውነት ክፍሎችን መለየትና ተግባራቸውን መናገር | | | |
| 2.1. የሰውነት ክፍሎቻቸውን መጥራት ይችላሉ | | | |
| 2.2. በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው የሚከናወኑትን ተግባራት መናገር ይችላሉ | | | |
| **3.** ዓይኖችን መንከባከብ | | | |
| 3.1. ዓይኖቻቸውን መንከባከብ ይችላሉ | | | |
| **4.** ጆሮዎችን መንከባከብ | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 4.1. ጆሮዎቻቸውን መንከባከብ ይችላሉ | | | |
| **5.** የማሽተት ስሜት ሕዋስን መጠቀም አፍንጫን መንከበካብ | | | |
| 5.1. በማሽተት የተለያዩ ነገሮችን ሽታ መለየት ይችላሉ | | | |
| **6.** የመቅመስ ስሜት ሕዋስን መጠቀምና አፍንጫን መንከባከብ | | | |
| 6.1. የተለያየ ጣዕም ያላቸውን ምግቦች መለየትና መናገር ይችላሉ<br>6.2. አፋቸዉን በጥንቃቄ እና በእንክብካቤ መያዝን ይለማመዳሉ | | | |
| **7.** በመዳሰስ ነገሮችንና ሁኔታዎችን መግለጽ | | | |
| 7.1. ሙቀትን መለየትና በመዳበስ የተሰማቸውን ስሜት መግለጽ ይችላሉ | | | |
| 8. ጤናን መጠበቅና የአጠባበቅ ሥርዓቶችን መለማመድ | | | |
| 8.1. የአመጋገብ ሥርዓትን ይለማመዳሉ | | | |
| 9. አካልን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ | | | |
| 9.1. አካልን መንከባከብና በጥንቃቄ መያዝ ይችላሉ | | | |
| 10. ጉልህና ረቂቅ /ትላልቅና ትናንሽ/ ጡንቻዎችን መጠቀም | | | |
| 10.1. የሰውነት ክፍሎቻቸውን ለተለያዩ ተግባራት መጠቀም ይችላሉ | | | |
| 11. በነፃነት ፈጠራን መግለጽ | | | |
| 11.1. አካላቸውን በመጠቀም ሃሳባቸውን ይገልፃሉ | | | |

## 2.2 ተቀባይነት ባለው መልኩ ከሌሎች ጋር ግንኙነት መፍጠር

### 2.2.1 ማብራሪያ

ይህ ርዕስ ከማህበራዊና ስሜታዊ ክህሎት መዳበር ጋር የተያያዘ ነው። የማህበራዊነት መዳበር መነሻው በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያላቸውን ከሰው ጋር የመግባቢያ ሥርዓቶች መረዳትና መተግበር ነው። ከሕፃናት የተሚላ ስብዕና መዳበር አቅጣጫዎች አንዱ የማህበራዊነት መዳበር ሲሆን አንድ ሕፃን ከወላጆቹ፣ከመምህራን፣ ክትትል ከሚያደርጉላቸውና ከዕድሜ እኩዮቻቸው ጋር የሚኖራቸው ግንኙነት በመልካም ሁኔታ እንዲዳብር ሁኔታዎች ከተመቻቹላቸው ሕፃናት ለራሳቸውና ለሌሎች ምቹ የሆነ ማህበራዊ ሕይወት እንዲኖራቸውና የስሜት መረጋጋት እንዲያገኙ ይረዳቸዋል።

ከሕፃንነቱ ጀምሮ ጥሩ የማኅበራዊ ሕይወት መሠረት ያልተጣለለትና የተረጋጋ ስሜት ይዞ ካላደገ ሕፃኑ ለድብርት፣ ለብስጭት፣ በፍርሃት የሚሸማቀቅ ለመሆንና ለአሉታዊ አመለካከት የተጋለጠ ይሆናል።

ስለዚህ የማኅበራዊ ሕይወት መዳበርና የስሜት መረጋጋት ገና ከጠዋቱ ትኩረት ሊሰጠው ይገባል። መምህር ስለእያንዳንዱ ሕጻን ባህርይ ከወላጆቹ ጋር በዝርዝር በመወያየት ስለማኅበራዊና ስሜታዊ ክህሎት ጠቅለል ያለ ግንዛቤ መያዝ ይኖርባቸዋል።

> በሕፃንነታቸው ጥሩ የሆነ ማህበራዊ ትስስርና የስሜት መረጋጋት ያላቸው ሕፃናት በወደፊት ሕይወታቸው ስኬትና በትምህርት ቤትም ጥሩ ተሳትፎ ይኖራቸዋል።
> የተረጋጋ ሕይወት የሚመሰረተው ከሕፃንነት ጀምሮ እርጋታ ባለው እንክብካቤና በጥሩ ማኅበራዊ መስተጋብር ውስጥ ማደግ ሲቻል ነው።

### 2.2.2 አጠቃላይ ዓላማዎች

1. ሕፃናት በአካባቢያቸው ያሉ ሰዎችን የማወቅ፣ የመግባባትና የመተባበር ባህሪ እንዲኖራቸው ለማድረግ
2. ጓደኞቻቸውንና በሚውሉበት አካባቢ ጥንቃቄ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች ለይተው እንዲያውቁና ከሰዎች ጋር ባላቸው ግንኙነት በማህበረሰቡ ተቀባይነት ያላቸውን ባህርያት የመልመድና የማንፀባረቅ ዝንባሌ ኖሮአቸው ዋና ዋና ሥርዓቶችን እንዲለምዱ ለማድረግ
3. ከሌሎች ሰዎችና ጓደኞቻቸው ጋር አብሮ የመጫወት፣ የመስራት፣ ያላቸውን ነገር የማካፈል፣ በቡድን ተግባራት በተገቢው ሥርዓት የመሳተፍ ዝንባሌን እንዲያዳብሩ ለማድረግ

### 2.2.3 የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች

1. በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት ለማወቅ ፍላጎት ማሳደርና መለየት
   - 1.1. አብረዋቸው የሚጫወቱትን እና በዙሪያቸው የሚያገኙአቸውን ሰዎች፣ ወላጆችንና የሚንከባከቧቸውን ሰዎች በስም መጥራት ይችላሉ
   - 1.2. ተቀባይነት ያለውን ባህሪ ማሳየትና አብረው መጫወት ይችላሉ
   - 1.3. ስለጓደኞቻቸውና አብረው ስለሚውሏቸው ሰዎች መግለፅ ይችላሉ
2. ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየትና እንዴት እንደሚንከባከቧቸው ማወቅ
   - 2.1 . ስለሚጠነቀቁላቸውና ስለሚንከባከቧቸው ሰዎች መናገር ይችላሉ
3. ሌሎችን መንከባከብና ያለንን ነገር ማካፈል
   - 3.1. በቡድን ሥራ ውስጥ መሳተፍ ይችላሉ

### 2.2..4 የሚጠበቁ ውጤቶች፣ ብቃቶች፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት፣ ለማወቅ ፍላጎት ማሳደር እና መለየት | 1.1. አብረዋቸው የሚጫወቱትን እና በዙሪያቸው የሚያገኙአቸውን ሰዎች በስም መጥራት እና በመልክ መለየት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፦ አብረዋቸው የሚጫወቱትን ህፃናት በመልክና በስም መለየት

ዓላማ ፦ አብረዋቸው የሚጫወቱትን ህፃናት በመልክና በስም ይለያሉ በዙርያቸው ያሉ ሰዎችን ያውቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የመዝሙር ካሴት፣ መሀረብ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- በሕብረት የተለያዩ እንቅስቃሴያዊ ጨዋታዎችን እንዲጫወቱ ማድረግ

  ለምሳሌ፦ «መሐረቤን አያችሁ ወይ»፣ «አረንጓዴ አረንጓዴ»፣ «ስምሽ ማነው? ሱብለወንጌል» ወዘተ...
- ከጨዋታ በኋላ አብረዋቸው የተጫወቱ የክፍል ጓደኞቻቸው ማን ማን እንደሆኑ እንዲናገሩና በጣታቸው ጠቁመው እንዲያሣዩ ማድረግ

- ስማቸውን መጥራት ባይችሉ ተጠቋሚዎቹ ስማቸውን እንዲናገሩና እንዲጨብጧቸው ማበረታታት

ምዘና ፡- አብረዋቸው የሚጫወቱትን ህፃናት በመልክና በስም መለየታቸውን ሲናገሩ በማዳመጥና ሲጠቁሙ በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- የወላጆቻቸውን ስምና ፆታ መናገር

ዓላማ ፡- የወላጆቻቸውን ስምና ፆታ ይናገራሉ፡

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መምህር የራሳቸውን ወላጅ ስምና ፆታ ለህፃናቱ በመንገር ማስተዋወቅ
- ህፃናቱም በየተራ እየተነሱ ለክፍል ጓደኞቻቸው የእናታቸውና የአባታቸው ስም ማን እንደሆነ፣ ፆታቸውንም ጭምር እንዲናገሩ ማበረታታት
- ፆታቸውን መግለፅ ከከበዳቸው አስታውሰው እንዲናገሩ ድጋፍ ማድረግ
- ህጻናቱ የወላጆቻቸውን ስም ካላወቁ አለማስጨነቅ ለቀጣይ ጠይቀው እንዲመጡ ማድረግ

ምዘና ፡- ወላጆቻቸውን ስምና ፆታ መናገር መቻላቸውን ትኩረት ሰጥቶ በማዳመጥ ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት፡- የክፍል ጓደኛን በድምፅ መለየት

ዓላማ ፡- የክፍል ጓደኞቻቸውን በድምጻቸው እና በመልካቸው ይለያሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- አንድ ፈቃደኛ የሆነ ህፃን በማስነሳት ከህፃናቱ ፊት እንዲቆምና አብረውት ከሚጫወቱት የክፍል ጓደኞቹ መካከል ሶስቱን በስም እንዲጠራና ህጻናቱም ስማቸው ሲጠራ እሱጋ መጥተው እንዲቆሙ ማድረግ

- በስም ለይቶ ካላወቃቸው አጠገባቸው በመሄድ እየነካ ሲያሳይ ተነስተው ከህፃናቱ ፊት እንዲቆሙ በማድረግ
- በመቀጠልም ህፃናቱ ስማቸውን ሌሎች ህፃናት እንዲሰሚቸው ድምፃቸውን ከፍ አድርገው እንዲናገሩ በማድረግ ማበረታታትና በሚከተለው መንገድ “የጠራህን ዕወቅ” የሚለውን ጨዋታ ማጫወት
- መጀመሪያ በፈቃደኝነት የወጣው ህፃን ፊቱን ወደ ግርግዳ በማዞር እንዲቆም ማድረግ
- መምህር ከሰስቱ ጓደኞቹ አንዱን ስሙን ሳይጠሩ በጣታቸው በመጠቆም ብቻ ወደግርግዳ ፊቱን ያዞረውን ህፃን ስም እንዲጠራ ማድረግ
- ወደ ግርግዳ ፊቱን አዙሮ የቆመው ህፃን ፊቱን ወደ ጓደኞቹ በመመለስ ከጓደኞቹ መካከል ማን እንደጠራው እንዲናገር ወይም ስሙን ካላወቀው እንዲጠቁም ማድረግ

- ህጻኑ ጓደኛውን በድምፅ ለይቶ ማወቅና አለማወቁን ሌሎች ህጻናት እንዲያረጋግጡ በማድረግ ሁሉም ህፃናት በጨዋታው እንዲሳተፉ ማድረግ

ምዘና ፡- የክፍል ጓደኞቻቸውን በድምጻቸው እና በመልካቸው መለየት መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር አራት ፡- በትምህርት ቤት ያሉ ሙያተኞችን መተዋወቅ

ላማ ፡- በትምህርት ቤታቸው ያሉ ሙያተኞችን በስም ይለያሉ።

ኣተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መምህር ከህፃናቱ ፊት ለፊት በመቆም "እኔ ማነኝ?" በማለት ህጻናቱን በመጠየቅ የመምህራቸውን ስም እንዲናገሩ ማድረግ
- በክፍል ውስጥ ያሉትን መምህርና ሞግዚት ከህጻናቱ ፊት እንዲቆሙ በማድረግ ማን እንደሆኑ መጠየቅ
- የመምህራናቸውንም ሆነ የሞግዚታቸውን ስም ካላወቁ ስማቸውን በመንገር የትኛዋ እንደሆነች እንዲያሳዩ ማድረግ
- በመቀጠልም የሚማሩበት አፀደ ሕፃናት በር ላይ ሆኖ የሚጠብቀው ማን እንደሆነ?፣ ክፍላቸውን የሚያፀዳላቸው ማን እንደሆነ ? በመጠየቅ በአፀደ ህጻናቱ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችን በስም እንዲያውቋቸው ማድረግ

- በጨዋታ እና በተለያዩ ተግባራት ሕፃናት ለረዳት መምህራናቸው ቀላል መልእክቶችን እንዲያደርሱ ማድረግ

> ማስታወሻ ፦ በጨዋታና በተለያዩ ተግባራት ወቅት ሕፃናት ለመምህራኖቻቸውና ለሞግዚቶቻቸው ቀላል መልእክትን እንዲያደርሱ በማድረግ መምህራኖቻቸውንና ሞግዚቶቻቸውን በስምና በመልክ ለይተው እንዲያውቁ ማለማመድ ያስፈልጋል።

ምዘና ፦ በትምህርት ቤታቸው ያሉ ሙያተኞችን በመልክና በስም መለየታቸውን ማረጋገጥ።

## ተግባር አምስት ፦ የሚፈልጉትን ሰው መሳል

ዓላማ ፦ የሚፈልጉትን ሰው ይስላሉ፣ ስለሳሉት ሰው ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀቶች፣ ባለቀለም እርሳሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለእያንዳንዱ ህፃን አንዳንድ ወረቀትና የሚፈልገውን ባለቀለም እርሳስ በመስጠት የሚፈልገውን ሰው እንዲስል ማነቃቃት
- ህፃኑ ስሎ ሲጨርስ የሳለውን ስእል ለክፍል ጓደኞቹ በማሳየት ማንን እንደሳለ እንዲናገር ማበረታታት
- በመጨረሻም ከስእሉ ስር ህፃኑ የሳለውን ሰው ስም እና ከስእሉ ግርጌ ደግሞ የህፃኑን ስም በመጻፍ ለእይታ አመቺ ቦታ ላይ መለጠፍ

ምዘና ፦ ደስ ያላቸውንና መሳል የሚፈልጉትን ሰው መሳላቸውና ስለሳሉት ሰው ማንነት መናገር መቻላቸውን በማየትና በመጠየቅ መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት፣ ለማወቅ ፍላጐት ማሳደር እና መለየት | 1.2. ተቀባይነት ያለውን ባህሪይ ማሳየት እና አብረው መጫወት ይችላሉ:: |

**ተግባር አንድ ፡- ተገቢ የአነጋገር ሥርዓትን መከተል**

ዓላማ ፡- ተገቢ የአነጋገር ሥርዓትን ተከትለዉ መናገር ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በትምህርት ቤታቸው ግቢ ውስጥ በጉብኝት መልክ እንዲዘዋወሩ ማድረግ
- ከጉብኝት መልስ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እጃቸውን በማውጣት መልስ መስጠትን እንዲለማመዱ ማነቃቃት

  ለምሳሌ፡- ከክፍል ወጥተን ጉብኝት የሄድነው የት ነበር? ምን ምን ነገሮችን አየን?
- ጥያቄ ሲጠይቁአቸው ተገቢውን ሥርዓት ጠብቀው እንዲናገሩ ማለማመድ
- በንግግር ወቅት እጅን ማሻሸት፣ ጣትን አፍ ውስጥ ማስገባት እንደማይገባ ማስገንዘብ

ምዘና ፡- ሀሳባቸውን በሚገልፁበት ወቅት ተገቢ የአነጋገር ሥርዓት ተከትለው መናገር መለማመዳቸውን በማየት ማረጋገጥ።

**ተግባር ሁለት ፡- መሠረታዊ የጨዋታ ህጎችን መተዋወቅ**

ዓላማ ፡- በጨዋታ ሂደት ሊተገብሩ የሚገባቸውን መሠረታዊ የጨዋታ ህጎችን ይተዋወቃሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- በጨዋታ ሂደት ሊያከብሩ የሚገቡ የጨዋታ ሕጐችን ያውቁ እንደሆነ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ማወያየት
- መልሳቸውን ካዳመጡ በኋላ ከሌሎች ጋር በሚጫወቱበት ወቅት ጓደኞቻቸውን መሳደብ፣መምታት፣መገፍተር፣ እንዳይጫወቱ መከልከል፣ መጫወቻዎችን መንጠቅ ወዘተ እንደሌለባቸው አፅንኦት ሰጥተው ልጆቹ እንዲገነዘቡ ማድረግ
- እነሱ መጫወት እንደሚፈልጉ ሁሉ ጓደኞቻቸውም መጫወት እንደሚፈልጉ በመንገር እንዲረዱ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- በእለት ተእለት እንቅስቃሴያቸው የጨዋታ ህጎችን ተከትለው ለመጫወት ሙከራ ማድረጋቸውን በማየት ማበረታታት ያስፈልጋል።

ምዘና ፦ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ በጨዋታ ሂደት ሊጠብቋቸው የሚገቡ መሠረታዊ ህጎችን መረዳታቸዉንና እንዲሁም ሲጫወቱ ህጎቹን መተግበራቸዉን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፦ ተቀባይነት ያላቸውን ባህሪያት መለየት

ዓላማ ፦ ተቀባይነት ያላቸውን ባህሪያት ይለያሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፦ የተረት መፅሃፍት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ተቀባይነት ያላቸውን ባህሪያት ለምሳሌ ይቅርታ ጠያቂነትን፣ አለመዋሸትን፣ እውነተኛነትን፣ ምስጋና መስጠትን ወዘተ... ሊያስተምሩ የሚችሉ አጫጭር ተረቶችን መተረክ
- ከተረቱ በኋላ በተረት ውስጥ ካሉ ገፀባህርያት ማንን እንደወደዱ እና ለምን እንደወደዱ መጠየቅ
- በተረቱ ውስጥ ጥሩ ባህሪ የነበራቸውን ገፀባህሪያት ላይ በመወያየት ተቀባይነት ያላቸውን ባህሪያት እንዲለዩ እገዛ ማድረግ

ማስታወሻ ፦ ተቀባይነት ያላቸውን ባህሪያት በሙሉ በአንድ ክፍለጊዜ ሳይሆን በተለያየ ክፍለ ጊዜ ማስተዋወቅ ያስፈልጋል።

ምዘና ፦ ተቀባይነት ያላቸውን ባህሪያት መለየታቸውን ጥያቄዎች በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፦ ተቀባይነት የሌላቸውን ባህሪያት መለየት

ዓላማ ፦ ተቀባይነት የሌላቸውን ባህሪያት ይለያሉ፣ ለማስወገድም ሙከራ ያደርጋሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መልካም ያልሆኑና ተቀባይነት የሌላቸውን ባህሪያት እነማን እንደሆኑ ገጠመኞችን በመንገር እንዲለዩአቸው ማድረግ
- በንግግር ወቅት ተገቢ ያልሆኑ ባህርያት ምን ምን እንደሆኑ በመጠየቅ ማወያየት
- በንግግር ወቅት ተገቢ ያልሆኑ የሰውነት እንቅስቃሴዎች

  ለምሳሌ፡- እጅ ማሻሸት፣ጣት እየጠቡ ጥፍርን እየበሉ ማውራት፣የልብስ ኮሌታን እያኘኩ ማውራት ወዘተ... እንደሌለባቸው ማስተማር
- በጨዋታ ግዜ ተገቢ ያልሆኑ ባህርያት ምን ምን እንደሆኑ በመጠየቅ ማወያየት

  ለምሳሌ፡- ጓደኞቻቸውን መሳደብ፣ መምታት፣ መገፍተር፣ መጫወቻ መንጠቅ ወዘተ...

ማስታወሻ፡- ከላይ የተጠቀሱትን ተቀባይነት የሌላቸውን ባህሪያት በእለት ተእለት ከሌሎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ላለማሳየት መሞከራቸውን መከታተልና አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ እና መምህርም ከላይ የተጠቀሱትን አላስፈላጊ ቃላቶችንና ባህርያትን ባለመናገርና ባለማሳየት አርአያ ሆኖ መገኘት ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- ተቀባይነት ያላቸውን ባህሪያትን መለየታቸዉን እና መተግበር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት፣ ለማወቅ ፍላጐት ማሳደር እና መለየት | 1.3. ስለጓደኞቻቸው እና አብረዋቸው ስለሚውሉ ሰዎች መግለጽ ይችላሉ:: |

ተግባር አንድ ፡- የቤተሰብ አባላትን መለየት እና መግለፅ

ዓላማ ፡- የቤተሰብ አባላቶችን ይለያሉ፣ በቤት ውስጥ የሚያከናውኑትን ተግባር ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቤተሰብ አባላትን የሚያሳይ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የቤተሰብ አባላትን የሚያሳይ ስዕልን በማሳየት ስእሉ ላይ ስላዩት ነገር መጠየቅ የቤተሰብ አባላት የሚባሉት እነማን እንደሆኑ መግለፅ
- በቤታቸው ከማን ጋር አብረው እንደሚኖሩ በመጠየቅ ስለቤተሰባቸው በዝርዝር እንዲናገሩ ማነቃቃት

  ለምሣሌ፡- ቤታችሁ ከእናንተ ጋር አብረዋችሁ በጋራ የሚኖሩት የቤተሰብ አባላት ማን ማን ናቸው?፣ቤታችሁ ውስጥ ስራ ይሰራሉ ወይ?፣ ምን አይነት ስራ ይሰራሉ? ወዘተ... በማለት በመጠየቅ ስለቤተሰብ አባላት እንዲናገሩ ማበረታታት
- መልሶቻቸውን ካዳመጡ በኋላ የቤተሰብ አባላት በአንድ ቤት ውስጥ አብረው የሚኖሩ ሲሆን በቤት ውስጥ የተለያዩ ስራዎችን በመስራትና በመተጋገዝ የሚኖሩ መሆኑን መግለፅ

ምዘና ፡- የቤተሰብ አባላትን መለየት እና መግለጽ መቻላቸውን የተለያዩ ጥያቄዎች በመጠየቅ መገምገም።


ተግባር ሁለት ፡- ሰዎችን በፆታ እና በእድሜ መለየት

ዓላማ ፡- ሰዎችን በፆታ እና በእድሜ ይለያሉ።

የመርጃ መሳርያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ የሰዎች ምስል እና የልብስ ዓይነቶችን የያዘ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ጎላ ብለው የተሳሉ የተለያዩ የሰዎች ምስል በማሳየትና የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ በፆታቸውና በእድሜያቸው እንዲለዩአቸው ማድረግ
- በመቀጠልም የተለያዩ የልብስ ዓይነቶችን የያዘ ስዕል በመስጠት የልብስ ዓይነቶቹን ሊለብሷቸው ከሚችሉ የሰዎች ስእል ጋር በጨዋታ መልክ እንዲያዛምዱ መርዳት





- የተለያዩ የሰዎች እንደዚሁም የአልባሳት እና የጫማዎች ስዕሎችን በማሳየት ይህ ጫማ ለማን ይሆናል? ይህ ሸሚዝ ትልቅ ነው ወይንስ ትንሽ? ለማን ይሆናል? ወዘተ…በማለት ጥያቄ መጠየቅ
- ስለትንሽ እና ስለ ትልቅ የአሻንጉሊት አልባሳትን በመጠቀም ማስተማር

ምዘና ፡- አልባሳትን እና ጫማዎችን ከሰዎች እድሜ እና ጾታ ጋር በማዛመድ ሰዎችን መለየት እና መግለፅ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- በስራ ላይ አብረዋቸው የተሳተፉ ሰዎችን መለየት

ዓላማ ፡- በስራ ላይ አብረዋቸዉ የሰሩ የክፍል ጓደኞቻቸዉን ይለያሉ።

የመርጃ መሳርያዎች ጥቆማ ፡- የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በአፀደ ሕፃናት ቅጥር ግቢያቸው እና ክፍላቸው ውስጥ ቅጠሎችን፣ ወረቀቶችን ወዘተ… በቡድን ሆነው እንዲለቅሙ ማድረግ
- የለቀሙትን ቆሻሻ የተዘጋጀው ማጠራቀሚያ ውስጥ እንዲያስቀምጡ ማሳየት
- ሲጨርሱ እጃቸውን በውሃ እና በሳሙና በደንብ እንዲታጠቡ ማድረግ
- በመጨረሻም መምህር አብረዋቸው ቆሻሻዎቹን ሲለቅሙ የነበሩትን የቡድናቸውን አባላት ስም እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ከሌሎች ጋር በጋራ ሲሰሩ አብረዎቸው የሰሩትን የክፍል ጓደኞቻቸዉን እነማን እንደሆኑ መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

## ተግባር አራት ፡- አብሮ በመስራት ጥሩ ስነምግባርን ማዳበር

ዓላማ ፡- አብሮ በመስራት በማኅበረሰቡ ተቀባይነት ያለው ሥነ-ምግባርን ያዳብራሉ።

የመርጃ መሳርያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መምህር በትልቅ ወረቀት ላይ የተሳለች የጽጌረዳ አበባን ረጋ ብለው ደማቅ ቀለም በመቀባት
- የአቀባብ ሂደቱን ለህፃናቱ ማሳየት
- ለእያንዳንዳቸው ህፃናት በትንሽ ወረቀት ላይ የተሳለች የፅጌሬዳ አበባንና፡በየጠረጴዛቸው ላይ በህብረት የሚጠቀሙበት ባለቀለም እርሳስ መስጠት
- ባለቀለም እርሳስ እየተዋዋሱ በሚቀቡበት ወቅት ጓደኞቻቸውን ባለቀለም እርሳስ እንዲሰጧቸው ሲጠይቁ “እባክህ ቀይ ባለቀለም እርሳስ ስጠኝ?፤ እባክሽ ሮዝ ባለቀለም እርሳስ ስጪኝ?›› ብለው እንዲጠይቁ ማለማመድ
- የቀቡትን የአበባ ስእል ለጓደኛቸው ወይንም አብሮአቸው ለተቀመጠ ልጅ እንዲሰጡ ያድርጉ
- ስጦታ ተቀባዩ አመስግኖ እንዲቀበል/እንድትቀበል ያስተምሩአቸው
- መስጠት እና መቀበልን እንደዚሁም አክብሮትን እንዲለማመዱ ያስተምሩአቸው

ምዘና፡- አብሮ በመስራት በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያለው ስነምግባርን ማዳበር መጀመራቸውን መከታተል።

## ተግባር አምስት ፡- ስለሚወዷቸው ሰዎች እና ነገሮች መዘመር

ዓላማ ፡- ስለሚወዷቸው ሰዎች እና ነገሮች በመዘመር ተቀባይነት ስላለው ስነምግባር ይገነዘባሉ።

የመርጃ መሳርያዎች ጥቆማ ፡- የመዝሙር ካሴቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከዚህ በፊት የተተዋወቋቸውን ስለሚወዷቸው ሰዎችና ነገሮች የሚገልፁ መዝሙሮችን ከመምህር ጋር አብረው እንዲዘምሩ ማድረግ

ለምሳሌ ፦ “አሻንጉሊቴ” “እናት አባቴን እወዳለሁ” "ትንሿ ቦርሳዬ" እና መሰል መዝሙሮችን ማዘመር

- ዘምረው ሲጨርሱ የመዝሙሩ ይዘት በጥያቄና መልስ እንዲያስታውሱ በማድረግ የመዝሙሮቹን ዋና ፍሬ ሀሳብ እንዲረዱት ማድረግ

ምዘና ፦ ስለሚወዷቸው ሰዎች እና ነገሮች በመዘመር ተቀባይነት ስላለው ስነምግባር መገንዘባቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ስድስት ፦ ምክርንና ትእዛዝን የማዳመጥ ጠቀሜታ

ዓላማ ፦ የአዋቂዎችን ምክርና ትእዛዝን ማዳመጥ ጠቀሜታ እንዳለው ለመረዳት ይሞክራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተረት መጽሐፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

ስለ “ትንሿ አይጥ” ተረት ተገቢውን የአተራረክ ሂደት በመከተል ለህፃናቱ መተረክ

<u>ትንሿ አይጥ</u>

ውሮ ጠዋት ተነስቶ ውጪውን ሲመለከት ፀሐይ ወጥታ ደስ የሚል ሙቀት እየሰጠች ነው። ውሮ ከቤቱ በራፍ ላይ ጋደም ብሎ ፀሐይ መሞቅ ጀመረ ሙቀቱም ደስ አለው ከተኛበት ቤት ግድግዳ ስር ኮሽ-ኮሽ የሚል ድምፅ ሰማና ቀና ብሎ ሲያይ ትንሽ ቀዳዳ ከግድግዳው ስር ተመለከተ ግን ቀዳዳው አካባቢ ምንም አላየም ተመልሶ ጋደም አለ አሁንም ኮሽ-ኮሽ የሚል ድምጽ ሰማና ቀና ብሎ ሲመለከት አንዲት ትንሽ አይጥ ከቤቱ ግድግዳ ሥር ባለው ትንሽ ቀዳዳ አንገቷን አውጥታ ውጪውን ታያለች ውሮ ሊይዛት ብድግ ሲል ጉድጓዱ ውስጥ ግብት አለች። ውሮ ተናደደ "ቆይ እንደገና ትመጫለሽ" በማለት ዛተና ጋደም ብሎ መጠበቁን ቀጠለ። ትንሷ አይጥ ከጉድጓድ ውጪ ያለውን ማየት ስለፈለገች እንደገና ብቅ አለች ውሮም በፍጥነት ሊይዛት ተነሳ ትንሷ አይጥ ፈጥና ወደጉድጓዱ ዘላ ስትገባ በጉድጓዱ ጫፍ ላይ የነበረ ድንጋይ እግሯን መታት፣ እያነከሰች ወደ ጉድጓድ ውስጥ ገባች፣ ስታነክስ ጉድጓዱ ውስጥ ያለችው እናቷ አየቻትና "ልጄ ምን ሆነሽ ነው የምታነክሺው? ወደ ውጪ ወጣሽ እንዴ? ውሮ ይበላሻል ወደ ውጪ አትውጪ አላልኩሽም? የእናት ትዕዛዝ አለመስማት ጥሩ አይደለም" ስትላት ትንሷ አይጥ በማዘን "እናቴ ይቅርታ አድርጊልኝ ሁለተኛ አልወጣም ምክርሽን እፈጽማለሁ" ብላ ጐንበስ ብላ ይቅርታ ስትጠይቅ እናቷ እቅፍ አድርጋ የተመታውን እግሯን አሻሸችና አስተኛቻት እግሯም ቀስ እያለ ዳነላት ከዛ ቀን ጀምሮ ትንሷ አይጥ የእናቷን ምክር በደንብ ማዳመጥና መፈፀም ጀመረች ይባላል።

ተረቱን መልሱ አፎን በዳቦ አብሱ።

- በጥያቄና መልስ የተረቁን ይዘት ከተረዱ በኋላ የተረቱ መልእክት እንዲረዱ ማድረግ

ለምሳሌ ፦ የወላጅን ምክር እና ትዕዛዝን አለማዳመጥ ለአደጋ ሊያጋልጥ እንደሚችል እንዲገነዘቡ፤ ሲያጠፉ ደግሞ ይቅርታ መጠየቅ እንዳለባቸው፤ ወዘተ…

| ማሳሰቢያ ፦ መምህር የሚያውቁትን ተረት በመጠቀም መልካም ሥነ ምግባርን ማስተማር ይችላሉ። |
|---|

ምዘና ፦ የወላጅን ምክርና ትእዛዝ ማክበር ጠቀሜታ እንዳለው መረዳታቸውን ጥያቄ በመጠየቅ ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየትና እንዴት እንደሚንከባከቧቸው ማወቅ | 2.1. ስለሚጠነቀቁላቸው እና ስለሚንከባከቧቸው ሰዎች መናገር ይችላሉ:: |

ተግባር አንድ ፦ ስለሚንከባከቧቸውን ሰዎች መናገር

ዓላማ ፦ ስለሚንከባከቧቸውን ሰዎች ይናገራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፦ ወላጆች ህፃናትን ሲንከባከቡ፣ መምህራን ህፃናትን ሲያስተምሩና ሲያጫውቱ የሚያሳዩ ስዕሎች ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ወላጆችና መምህራን ህፃናትን ሲንከባከቡ የሚያሳዩ ስዕሎችን በማሳየት ስላዩት ነገር እንዲናገሩ ማበረታታት

- የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የእነሱ ወላጆችና መምህራን እንዴት እንደሚንከባከቧቸው እንዲናገሩ ማድረግ
- መልሶቻቸውን ካዳመጡ በኋላ ወላጆች ልጆቻቸውን በመመገብ፣ በማልበስ፣ በመውደድ አስተማሪዎቻቸው ደግሞ በማስተማር፣ በማጫወት እንደሚንከባከቧቸው ማስረዳት

ምዘና ፦ ወላጆቻቸውና መምህሮቻቸው እንዴት እንደሚንከባከቧቸው ሲናገሩ በማዳመጥ መገምገም።

ተግባር ሁለት ፦ ቤተሰብ የሚያደርግላቸውን ጥንቃቄ መረዳት

ዓላማ ፦ ቤተሰቦቻቸው የሚያደርጉለቸውን ጥንቃቄ ይረዳሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፦ የመዝሙር ካሴቶች፣ ለመስሎ መጫወት የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- "እናት አባቴን እወዳለሁ" የሚለውን መዝሙር እንዲዘምሩ ማድረግ
- የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እናትና አባታቸው ስለሚያደርጉላቸው ጥንቃቄ እና እንክብካቤ እንዲናገሩ ማነቃቃት
- ቤተሰብ ለልጆች በቤት ውስጥና ከቤት ውጪ የሚያደርጉትን ጥንቃቄና እንክብካቤ መግለፅ
- በመስሎ መጫወት በተለይ በቤተሰብ ጨዋታ ላይ የወላጅ ሚናን በመወከል አሻንጉሊትን በመመገብ፣ በማጠብ፣ በማጫወት ወዘተ እንዲሳተፉ ማበረታታት

ማስታወሻ ፦ የጨዋታ ማዕዘናት ለሁሉም ሕፃናት ላይበቁ ስለሚችሉ ያልተጫወቱ ሕፃናት የሚጫወቱበትን ሁኔታ በየጊዜው በማመቻቸት ሌሎች በመስሎ መጫወት ጨዋታው ተሳታፊ ያልሆኑ ልጆች በትምህርታዊ፣ በግንባታ ወዘተ...ጨዋታዎችን እንዲጫወቱ ማመቻቸት።

ምዘና ፦ ቤተሰቦቻቸው እነሱን እንዴት እንደሚንከባከቡአቸው እና እንደሚጠነቀቁላቸው መገንዘባቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- የሚጠነቀቁላቸውና የሚንከባከቧቸውን ሰዎች ስእል ቀለም መቀባትና መናገር

ዓላማ ፡- የሚጠነቀቁላቸውና የሚንከባከቧቸውን ሰዎች ስእል ቀለም ይቀባሉ፣ እንዴት እንደሚንከቢከቧቸውና እንደሚጠነቀቁላቸው ይናገራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የአባት፣ የእናት፣የመምህር፣ የሀኪም ስዕል፤ባለቀለም እርሳስ/ከለር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የአባት፣ የእናት፣ የመምህር፣ የሀኪም ስዕልን ከለር እንዲቀቡ መስጠት
- ቀለም ቀብተው ሲጨርሱ የምን ስእልን ቀለም እንደቀቡና ወላጆች፣ መምህራኖችና ሀኪሞች እንዴት እንደሚንከባከቧቸውና እንደሚጠነቀቁላቸው ጥያቄ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማድረግ
- መልሳቸውን ካዳመጡ በኋላ አባት፣ እናት፣ መምህር፣ ሀኪም እነሱን እንደሚወዷቸው፣ እንደሚንከባከቧቸውና አደጋ እንዳይደርስባቸውና እንዳይታመሙ እንደሚጠነቀቁላቸው በመንገር ማጠቃለል

ምዘና ፡- የሚጠነቀቁላቸውና የሚንከባከቧቸውን ሰዎች ስእል ቀለም በመቀባት ስለቀቡት ሰዎች መናገራቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- በእረፍት ቀን ወላጆቻቸው ያደረጉላቸውን መናገር

ዓላማ ፡- በእረፍት ቀናቸው ቅዳሜና እሁድ ወላጆቻቸው ያደረጉላቸውን ነገር አስታውሰው ለመናገር ይሞክራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ቅዳሜና እሁድ እቤታቸው ሲውሉ ወላጆቻቸው ምን እንዳደረጉላቸው የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አስታውሰው እንዲናገሩ ማድረግ
- ወላጆቻቸው ገላቸውን እንደሚያጥቧቸው፣ ዘመድ ቤት ሽርሽር እንደሚወስዷቸው ወዘተ በመንገር ወላጆቻቸው ብዙ ነገር እንደሚያደርጉላቸው መንገር

- እነሱም በቤት ውስጥ ወላጆቻቸው በአቅማቸው መርዳትና ወላጅ የሚላቸውን መስማት እንዳለባቸው መንገር

ምዘና ፡- በእረፍት ቀናቸው ቅዳሜና እሁድ ወላጆቻቸው ያደረጉላቸውን ነገር አስታውሰው ለመናገር መሞከራቸውን በማዳመጥ ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3. ሌሎችን መንከባከብ እና ያለንን ነገር ማካፈል | 3.1 . በቡድን ስራ ውስጥ መሳተፍን ይለማመዳሉ። |

ዓላማ ፡- ከሌሎች ጋር አብሮ መስራት ይለማመዳሉ።

ተግባር አንድ ፡- ከሌሎች ጋር በጋራ መስራት

የመርጃ ... ም እርሳሶች/ከለሮች ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለሚወዷቸው ሰዎች ስጦታ እንደሚያዘጋጁ በመንገር የተሳለ ግን ቀለም ያልተቀባ አበባን መስጠት
- ቀለም በቡድን እየተነጋገሩ እንዲቀቡ ማድረግና የቀቡትን ስዕል ለማን እንደሚሰጡ በመጠየቅ ማወያየት
- ስዕሉን ለፈለጉት ሰዉ እንዲሰጡ ማበረታታት

ምዘና ፡- ከሌሎች ጋር በጋራ ተስማምቶ መስራት መቻላቸዉን መከታተል።

ተግባር ሁለት ፡- ከሌሎች ጋር አብሮ መጫወት

ዓላማ ፡- ከሌሎች ጋር ተስማምተው በነፃነት መጫወት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በክፍል ውስጥ የሚገኙ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከክፍል ውጪ ህፃናቱ የፈለጉትንና የመረጡትን የህብረት ጨዋታ እንዲጫወቱ ማድረግ
- እርስ በእርሳቸው ተስማምተው መጫወታቸውን በቅርብ ርቀት መከታተል
- አላስፈላጊ ባህሪያትን ሲያሳዩ ወዲያውኑ እርማት መስጠት
- ከጨዋታ በኋላ ከማን ጋር ምንና እንዴት እንደተጫወቱ በመጠየቅ በጥሩ ሁኔታ የተጫወቱትን በማድነቅና በማበረታታት እውቅና መስጠት፣አላስፈላጊ ባህሪያትን በቀጣይ ማሻሻል እንዳለባቸው ምክር መስጠት
- ከሌሎች ጋር ተስማምቶ መጫወትን እንዲለማመዱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት

ምዘና ፡- ከሌሎች ጋር ተስማምተው በነፃነት መጫወታቸውን በመከታተል መገምገም።

ተግባር ሶስት ፡- ትእዛዝ ተቀብሎ መተግበር

ዓላማ ፡- ትእዛዝን ተቀብለው ይተገብራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ፡- በክፍል ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በክፍላቸው ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶችን እንዲያስተካክሉ በተለያየ ጊዜ ትዕዛዝ መስጠት
- ቀላል ሥራዎችን ያለ አጋዥ ማከናወን እንዲለማመዱ ማድረግ

  ለምሣሌ፡- የተጫወታችሁበትን መጫወቻ ለቅማችሁ ካርቶን ውስጥ አስገቡ በማለት ማዘዝ እና የታዘዙትን ሲያደርጉ መከታተልና ሲጨርሱ ማሞገስ፣

ምዘና ፡- ትእዛዝ ተቀብለው መተግበራቸውን መከታተል።

ተግባር አራት ፡- መገልገያ ቁሳቁሶችን እና ክፍልን በአግባቡ መያዝ

ዓላማ ፡- መገልገያ ቁሳቁሶቻቸዉን፣መጫዎቻቸዉን እና ክፍላቸውን በአግባቡ መያዝን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- መጫወቻዎች፣ የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት፣ የምሳ ዕቃ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- መጫዎቻዎችና የክፍል ውስጥ ቁሳቁሶች በስርዓት እና በሚያምር መልኩ የተቀመጡበትን የክፍል ማዕዘን ማሳየት
- ቀጥሎም በተገቢው መልኩ ያልተሰናዳ ማዕዘንን ማሳየት
- ሲያዩት ስለተሰማቸው ስሜት እንዲናገሩ «ደስ ይላል ወይ?፤ ምኑ ነው ደስ የሚለው?» በማለት መጠየቅና ማወያየት
- ደስ ያላቸው ሁሉም ነገር በስርዓት ተቀምጦ ስላዩት መሆኑን፤ ስርዓት የያዘው ደግሞ ሕፃናት ተጫውተው ሲጨርሱ መጫወቻዎችን ወደቦታቸው ስለመለሱ እንደሆነ ማስገንዘብ
- በተቃራኒው የተበታተኑ መጫወቻዎችና ቁሳቁሶች ያሉበትን ማዕዘን ሲያዩ የተሰማቸውን መጠየቅና ማወያየት
- የተዘበራረቀው ለምን እንደሆነ እንዲረዱ በማድረግ ማጠቃለል

ምዘና ፦ መገልገያ ቁሳቁሶቻቸዉን እና የመጫወቻ ዕቃዎቻቸውን በአግባቡ መጠቀም እና በተገቢው ቦታ ማስቀመጣቸውን መከታተል።

## **2.2.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም -----------------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም ------------------------------------------- ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም --------------------------------------------- ዓመተ ምሕረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፦

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ -----------------------------------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት -----------------------------------------------------------------

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት ------------------------------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | የዓመቱ መጀመሪያ | የዓመቱ አጋማሽ | የዓመቱ መጨረሻ |
| **1.** በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት ለማወ... | | | |
| 1.1 . አብረዋቸው የሚጫወቱትን እና በዙ... ሰዎች/ጓደኛን ወላጆችንና የሚንከ... | | | |
| 1.2 . ተቀባይነት ያለውን ባህሪ ማሳየት... | | | |
| 1.2. ስለጓደኞቻቸውና አብረው ስለሚኖ... | | | |
| **2.** ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላ... | | | |
| 2.1. ስለሚጠነቀቁላቸውና ስለሚንከባከ... | | | |
| **3.** ሌሎችን መንከባከብና ያለንን ነገር ... | | | |
| 3.1. በቡድን ሥራ ውስጥ መሳተፍን ይለ... | | | |

ቋንቋ ሥርዓት ባለው መልክ ለመግባባት፤ ሃሳብን፣ ስሜትን፣ ፍላጎትን፣ ወዘተ… ለሌላው ለመግለጽ የሚያስችል መሣሪያ ነው። ቋንቋ በጣም ጠቃሚ የሆነ የቅድመ ልጅነት ግኝት ሲሆን ሕፃናት በአካባቢያቸው ያሉ ሰዎች የሚናገሩትን እንዲረዱና እነሱም ሃሳባቸውን፣ ፍላጎታቸውንና ስሜታቸውን እንዲገልፁ ከመርዳቱም በተጨማሪ ስለሚኖሩበት አካባቢ መረጃ እንዲያገኙ አካባቢያቸውን በይበልጥ እንዲያውቁና ምናባቸውን እንዲያሰፉ ይረዳቸዋል።

ሕፃናት በመጀመሪያው ዓመታቸው የመጀመሪያዎቹን ቃላት ማውጣት ይጀምራሉ። እነዚህም ቃላቶች በምግባቸው፣ በመጫወቻዎቻቸው በቅርብ ከሚያገኟቸውና ከሚያዩአቸው ሰዎችና ቁሳቁሶች ጋር የተያያዙ ይሆናሉ።

**ቋንቋ...**

**2.3.1** ማብራሪያ

ሕፃናት በሁለት ዓመት ... ዕድሜያቸው ላይ ቃላትን አገጣጥመው ሀረግን በመጠቀምና ቃላትን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት ፍላጐታቸውንና ሐሳባቸውን መግለጽ ይጀምራሉ። ሶስት ዓመት አካባቢ ሲሆናቸው ከዕድሜ እኩዬቻቸውና ከአዋቂዎች ጋር በሚኖራቸው ግንኙነትና አካባቢያቸውን ለማወቅ በሚያደርጉት ጥረት /ጥያቄዎችን በመጠየቅ/ ከዕለት ወደ ዕለት የቃላት ክምችታቸው እየጨመረ ከመምጣቱም ባሻገር ቃላትን ገጣጥመውና ሰዋሰዋዊ አገባብን ለመከተል በመሞከር ሃሳባቸውን ለመግለጽ ጥረት ያደርጋሉ።

ይህ ከላይ በአጭሩ የተጠቆመው የሕፃናት ቋንቋ ከዕድሜያቸው፣ ከአካባቢ ጋር ካላቸው መስተጋብርና ከሚደረግላቸው ድጋፍ የተነሳ ደረጃ በደረጃ እየዳበረ ይመጣል። በመሆኑም ሕፃናት ቃልን ለማውጣትና የማዳመጥ ዕድል ሊኖራቸው የሚገባ ሲሆን ንግግርን እንዲለማመዱ ያዳመጡትን በቃላት የማውጣት፣ ስሜታቸውን የመግለጽና ማነቃቂያ የማግኘት ዕድል ሊኖራቸው ይገባል።

የቋንቋ መዳበር ከአስተሳሰብ መዳበር፣ ከማህበረሰቡ ጋር በሚኖር ግንኙነትና ከአካባቢ ከሚደረግ እገዛ ጋር የተያያዘ መሆኑን በመገንዘብ ሕፃናት በተገቢው ዕድሜና ደረጃ የቋንቋ ክህሎቶችን እንዲያዳብሩ አስፈላጊው እገዛ ሊደረግላቸው ይገባል። ይህም እገዛ ከአቅማቸው /ከሚገኙበት ደረጃ/ ጋር የተመጣጠነና ሊደርሱበት የሚገባውን ደረጃ ከትኩረት ውስጥ ያስገባ ሊሆን ይገባል።

### **2.3.2** አጠቃላይ ዓላማዎች

1. ትኩረት ሰጥቶ የማዳመጥ ክህሎትንና ሃሳባቸውን በንግግር የመግለጽ ልምድን እንዲያዳብሩ ለማድረግ፤
2. የቃላት ክምችታቸው እንዲጨምር ለማድረግ፤
3. ቀላል ትዕዛዞችንና መመሪያዎችን አዳምጠው ምላሽ የመስጠት ልምድን እንዲያዳብሩ ለማድረግ፤
4. በደረጃቸው ለንባብና ለጽሁፍ ዝግጁ እንዲሆኑ ለማድረግ፤

### **2.3.3** የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች

1. መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት
   1.1. ለተለያዩ ድምፆችና ትዕዛዞች ምላሽ መስጠት ይችላሉ
   1.2. የተለያዩ ድምፆችን በማዳመጥ መለየትና አቅጣጫዎችን መጠቆም ይችላሉ
   1.3. አጫጭር ተረቶችንና መዝሙሮችን በማዳመጥ መልሰው መናገርና መዘመር ይችላሉ
2. በተለያዩ ሁኔታዎች በራስ በመተማመን በተገቢውና ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ንግግርና የምልክት ቋንቋ መግባባት
   2.1. ቀላል ትዕዛዞችንና መመሪያዎችን መከተል ይችላሉ
3. በማንበብ መደሰት ዕውቀት ማግኘትና መረዳት
   3.1. ስዕሎችንና ቅርፆችን በማየት መለየት ይችላሉ
4. የዓይንና የእጅ እንቅስቃሴ ቅንጅትን በማዳበር ለጽሁፍ መዘጋጀት
   4.1. የዓይንና የእጃቸውን እንቅስቃሴ ማቀናጀትን ይለማመዳሉ

2.3.4 የሚጠበቁ ውጤቶች፣ ብቃቶች፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|

| | |
|---|---|
| 1. መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት | 1.1 . ለተለያዩ ድምፆችና ትዕዛዞች ምላሽ መስጠት ይችላሉ:: |

ተግባር አንድ ፡- ድምጽ ሰምቶ ማስመሰል

ዓላማ ፡- የሰሙትን ድምፅ አስመስለው ያወጣሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ሕፃናትን በግማሽ ክብ ወይም በ ‘ሀ’ ቅርጽ እንዲቀመጡ ማድረግ
- ከሕፃናት ፊት ለፊት በመቆም የተለያዩ ድምፆችን ለሕፃናት ማሰማት
- የሰሙትን ድምጽ በሕብረት እንዲያወጡ ማበረታታት
- የድምጽ አወጣጣቸውን በማየት ድምጽን በትክክል ያላወጣ ሕፃን ካለ መልሶ እንዲያወጣ ማበረታታት
  ለምሣሌ፡- ሃሃሃ፣ ቡም ቡም ቡም ፣ላ ላ ላ፣ ድርን ድርን ድርን ወዘተ...
- አጫዋች መሆን የሚፈልግ ሕፃን ካለ በመጠየቅ እሱም እንደመምህር እንዲያጫውት ዕድሉን መስጠትና ሲያጫውት ማበረታታት

| |
|---|
| ማሳሰቢያ ፡- ሕፃናት ከፍተኛ ድምጽ በማውጣት ጉሮሮና ጆሮአቸውን እንዳይጎዱ የተመጠነ ድምጽ እንዲያወጡ ማድረግ ያስፈልጋል። |

ምዘና፡- የሰሙትን ድምፅ አስመስለው ማውጣት መቻላቸዉን ትኩረት ሰጥተው በማዳመጥ ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት፡- የድምፅ አይነትን መለየት እና ማስመሰል

ዓላማ ፡- የተለያዩ የድምጽ አይነቶችን ይለያሉ እንዲሁም ድምጾቹን አስመስለው ያወጣሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የቤት እንስሳት፣ የነፍሳቶችንና የአእዋፍን ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ የእንስሳትን፣ነፍሳትንና አእዋፍን ምስል በማሳየት ምን እንደሆኑ መጠየቅ፤
- የእንስሳቱን ስም እንዲናገሩ ማድረግና ከከበዳቸው ፍንጭ መስጠት
- መምህር የእንስሳቱን ድምጽ አስመስለው በማውጣት ሕፃናቱ የየትኛው እንስሳ፣ነፍሳትና አእዋፍ ድምጽ እንደሆነ እንዲገምቱ ማድረግ
- ሕፃናቱ የድምፁን የተጠየቁትን እንስሳ/ነፍሳት/አእዋፍ ድምፅን አስመሰለው እንዲያወጡ በመጠየቅ ማበረታታት

ምዘና ፡- የሰሙትን ድምፅ/ የእንስሳቱን፣ የአእዋፍና፣ የነፍሳቶቹን/ መለየታቸውን እና ድምጾቹን አስመስለው ማውጣታቸውን መገምገም።

ተግባር ሶስት ፡- መዝሙር ማዳመጥ እና መልሶ መዘመር

ዓላማ ፡- የሰሙትን መዝሙር መልሰው ይዘምራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዝሙር ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ አጫጭር የሕፃናት መዝሙሮችን ተገቢውን አካላዊ እንቅስቃሴ በመጠቀምና ዜማዉን በመከተል መዘመር
- ህፃናቱ የሰሙትን መዝሙር መልሰው ዜማዉን በመከተል እንዲዘምሩ እና እንዲንቀሳቀሱ ማድረግ

ለምሳሌ ፡- ቀስ በቀስ ሸረሪቷ፣ ወፊቱን እሆናለሁ ወዘተ...

ምዘና ፡- የሰሙትን መዝሙር ምቱን ተከትለው መልሰው መዘመር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- ተረት አዳምጦ መረዳት

ዓላማ ፡- ተረት አዳምጠዉ ከተረቱ ለወጡ ጥያቄዎች ተገቢዉን ምላሽ ይሰጣሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሐፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የህፃናቱን አቀማመጥ ማስተካከል/ በ << ሀ >>ቅርፅ ወንበር ላይ ወይም መሬት ምንጣፍ ላይ እንዲቀመጡ ማድረግ/
- ዕድሜያቸውን የሚመጥን ተረትን አስፈላጊውን የድምፅ አወጣጥን፣ የፊት ገፅታንና አካላዊ እንቅስቃሴ በመጠቀም ገፀባህሪውን ተላብሶ መተረክ
- ከትረካው በኋላ ከተረቱ የወጡ ጥያቄዎችን በቅደም ተከተል መጠየቅ
- የተረቱን ይዘትና መልእክት እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ተረት አዳምጠው ከተረቱ ለሚወጡ ጥያቄዎች በትክክል ምላሽ መስጠታቸውንና የተረቱን ይዘትና መልእክት መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት፡- ትዕዛዝን አዳምጦ መተግበር

ዓላማ ፡- ቀለል ያሉ ትእዛዛትን ተቀብለው ይተገብራሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በክፍል ውስጥ ያሉ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- አጫጭር ትዕዛዞችንና መልእክቶችን ለሕፃናት በቃል በመንገር
- ትዕዛዞችን ሰምተው እንዲፈጽሙና መልእክትም እንዲያስተላልፉ ማበረታታት

  ለምሳሌ፡- ቦርሳዬን አምጣልኝ፣ ይሄንን ለመምህር ....... ስጠዉ፣ መምህር ....... ነይ ብለሽ ጥሪያት ወዘተ...

ምዘና ፡- ቀለል ያሉ ትእዛዛትን ተቀብለው መተግበር መቻላቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር ስድስት ፡- ድርጊትን በንግግር መግለፅ

ዓላማ ፡- ድርጊት ገላጭ ስእሎችን በመመልከት ያዩትንና የተረዱትን በንግግር ይገልፃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ሰዎች የተለያዩ ድርጊቶች ሲያከናውኑ የሚያሳዩ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሰዎች የተለያዩ ድርጊቶችን ሲያከናውኑ የሚያሳዩ ስዕሎችን ማሳየት
- በስዕሉ ላይ ሰዎች ምን እንደሚያደርጉ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት
- ከከበዳቸው ትንሽ ፍንጭ መስጠት

ለምሳሌ፦ «ልጁ ምኑን እየታጠበ ነው?››፣ ሴትየዋ ምንድን ነው የያዘችው?» ወዘተ...

ምዘና ፦ የተለያዩ ድርጊቶችን በመመልከት በንግግር መግለፅ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር ሰባት ፦ ድምጾችን ከስእሎች ጋር ማዛመድ**

ዓላማ ፦ የሰሟአቸውን ድምጾች ከስእሎቹ ጋር ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የቤት እንሰሳት፣ የአእዋፍ፣ የነፍሳት ስእል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የተለያዩ የቤት እንሰሳትን ምስል ለሕፃናቱ ማደል
- መምህር የቤት እንሰሳቱን ድምጽ ሲያወጡ የሰሙትን ድምጽ ምስል የያዙ ህፃናት እየተነሱ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ ማድረግ
- በሂደትም ፈቃደኛ የሆኑ ህፃናት የመምህርን ቦታ ተክተው የእንሰሳቱን ድምፅ እንዲያወጡ በማድረግ ማሳተፍ

ምዘና ፦ የሰሟአቸውን ድምጾች ከትክክለኛው ስእል ጋር ማዛመድና አስመስለው ማውጣት መቻላቸውን ትኩረት ሰጥቶ በማየትና በማዳመጥ ማረጋገጥ።

**ተግባር ስምንት ፦ ቀለም የመለየት ጨዋታን መጫወት**

ዓላማ ፦ ትዕዛዛትን ተከትለው ይጫወታሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ቀይ፣ ሰማያዊና ቢጫ ቀለም ያላቸው ሪቫኖች /ጨርቅ/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሕፃናትን በክብ ማስቀመጥ
- እጃቸው ላይ ቀይ፣ ሰማያዊ ወይም ቢጫ ጨረቅ /ሪቫን/ ማሰር
- የጨዋታውን ህግና ሂደት አስቀድሞ መንገር

- <<ቢጫ ጨርቅ ያሰራችሁ ተነሱና አጨብጭቡ>>፣ <<ቀይ ጨርቅ ያሰራችሁ ዝለሉ>>፣ <<ሰማያዊ ጨርቅ ያሰራችሁ ወገባችሁን ያዙ>> በማለት የተለያዩ ትእዛዞችን በመስጠት ማጫወት

ማስታወሻ ፡- ሕፃናት በእርጋታ ሊያዳምጡ የሚችሉት የሚያዳምጣቸው ሰው ካገኙና ሌሎች ሰዎች በጥሞና ትኩረት ሰጥተው ሲያዳምጧቸው ስለሆነ መምህር በማንኛውም ሰዓት ሕፃናት በሚናገሩበት ጊዜ ትኩረት ሰጥቶ በጥሞና በማዳመጥ፣ ሲናገሩ ዓይን ዓይናቸውን በማየት እያዳመጧቸው መሆኑን በፊት ገጽታና በአካላዊ እንቅስቃሴ በመግለጽ፣ የሚሰሩትን ሥራ አቁመው በማዳመጥና የሕፃናቱን ንግግር ባለማቋረጥ ጥሩ ሞዴል ሊሆኑአቸው ይገባል።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት | 1.2. የተለያዩ ድምፆችን በማዳመጥ መለየትና አቅጣጫውን መጠቀም ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ድምፅን መለየትና መናገር

ተግባር አንዱ፡- ድምፅን መለየትና መናገር

ዓላማ ፡- የሰሙትን ድምፅ በመለየት ይናገራሉ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡ -

- "በድምጽ ለይተህ ዕወቅ" የሚለውን ጨዋታ በሚከተለው መንገድ ማጫወት
- አንድ ሕፃን ከሕፃናት ፊት ወጥቶ ፊቱን ወደ ግርግዳ አዙሮ እንዲቆም ማድረግ
- ስሙን ከክፍል ጓደኞቹ መካከል አንዱ እንዲጠራው ማድርግ
- ማን እንደጠራው እንዲገምት ማድረግ
- በትክክል የጠራውን ሰው እንዲያውቅ ማገዝ
- በሂደትም በማጨብጨብ፣ በማስነጠስ፣ በማሳል፣ ጠረጴዛን በማንኳኳት ወዘተ ያዳመጠውን ድምፅ እንዲለይና እንዲናገር ማድረግ
- ሁሉም ሕፃናት እንዲጫወቱ ማነቃቃት

ምዘና ፡- በጨዋታ መልክ ድምጾችን መለየታቸውንና የለዩትን ድምፅ ምንነት መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- የድምፅን አቅጣጫ በመከተል ነገሮችን ማግኘት

ዓላማ ፡- የድምፅን አቅጣጫ በመከተል ነገሮችን ፈልገው ያገኛሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- አሻንጉሊት፣ ዓይን መሸፈኛ ጨርቅ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- “አሻንጉሊቷን ፈልገህ አግኝ” የሚለውን ጨዋታ በሚከተለው መንገድ ማጫወት
  ሕፃናት በክብ እንዲቀመጡ ማድረግ
- ከመካከላቸው በፈቃደኝነት አንድ ልጅ በማስነሳት ጨዋታውን እንዲጀመር ማድረግ
- የሕፃኑን ዓይን ላላ አድርጎ በጨርቅ ማሰርና በዳበሳ መሬት ላይ የተቀመጠች አሻንጉሊት እንዲፈልግ ማድረግ
- ሕፃኑ አሻንጉሊቷ ወዳለችበት አቅጣጫ ሲሄድ መምህር በማጨብጨብ ልክ መሆኑን መግለጽ
- ከዛም አሻንጉሊቷን ፈልጎ ሲያገኛት ማስጨብጨብ ሌላ ተጨዋች ልጅ እንዲመርጥ እድሉን መስጠት

| |
|---|
| ማስታወሻ ፡- ሁሉም ህፃናት በጨዋታው ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ ያስፈልጋል። |

ምዘና ፡- በጨዋታው ወቅት የድምፅን አቅጣጫን በመከተል ነገሮችን ለማግኘት መሞከራቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- የድምፅን አቅጣጫ መለየት

ዓላማ ፡- የድምፆችን አቅጣጫ ይለያሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናትን ወደ ሜዳ ይዞ በመውጣት በዙሪያቸው ያሉ ድምፆችን እንዲያዳምጡ ማድረግ

- የሰሙት ድምፅ የምን ድምፅ እንደሆነና ከየት በኩል እንደሰሙ በመጠየቅ የድምጽን አቅጣጫ መለየት እንዲችሉ ማለማመድ
- ህፃናት በሜዳ ውስጥ በአራቱም አቅጣጫ በቡድን በመመደብ እንዲቆሙ ማድረግ
- ከአንዱ ቡድን አንድ ህፃን በመምረጥ በሜዳው መሀል ላይ ፊቱን በእጆቹ ሸፍኖ እንዲቆም ማድረግ
- ከአራቱ ቡድን አንዱ ቡድን በፍጥነት ሶስት ጊዜ እንዲያጨበጭብ ማድረግ ህፃኑ ጭብጨባው ሲያቆም ጭብጨባውን ወደሰማበት ቦታ ሮጦ ሄዶ ከቡድኑ ጋር እንዲቀላቀል ማድረግ
- በዚህ አይነት ሁኔታ ሁሉም ህፃናት በጨዋታው ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ

ምዘና ፡- ህፃናቱ የድምፆችን  አቅጣጫ መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር አራት፡- የድምፅን አቅጣጫ መለየትና መናገር**

ዓላማ ፡- የድምፆችን  አቅጣጫ በመለየት ይናገራሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የድምጽ ሳጥኖች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናት በ ‹ሀ› ቅርጽ እንዲቀመጡ ማድረግ
- ሶስት ሕፃናት በመምረጥ ለሶስቱም ህፃናት የተለያዩ ቦታዎች ላይ እንዲቆሙ በማድረግ  አንድ ዓይነት ድምጽ የሚሰጡ የድምጽ ሳጥኖችን መስጠት
- አንድ ህፃን በማስነሳት የድምጽ ሳጥን የያዙትን ሕፃናት የቱ ጋር እንደቆሙ እንዲያያቸው ማድረግ
- በመቀጠልም ሕፃኑ ፊቱን ወደ ግድግዳ አዙሮ እንዲቆም ማድረግ
- ከሶስቱ አንዱ የድምጽ ሳጥኑን በማወዛወዝ ድምጽ እንዲያሰማ ማድረግ
- ወደ ግድግዳ የቆመው ሕፃን ፊቱን ወደ ክፍል ጓደኞቹ በማዞር ከየት በኩል ድምጹን እንደሰማ በእጁ እንዲጠቁም እና እንዲናገር ማድረግ
- ለሎችም ሕፃናትም በየተራ እንዲጫወቱ እድሉን መስጠት

ምዘና ፡- የድምፆችን  አቅጣጫ መለየትና መናገር መቻላቸዉን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|

| | |
|---|---|
| 1. መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት | 1.3. አጫጭር ተረቶችንና መዝሙሮችን በማዳመጥ መልሰው መናገርና መዘመር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ተረት አዳምጦ መረዳት

ዓላማ ፡- ከተረቱ ለወጡ ጥያቄዎች ምላሽ ይሰጣሉ እንዲሁም የተረቱን ይዘት ይረዳሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሐፍት፣ የጥንቸል እና የኤሊ ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የጥንቸል እና የኤሊን ስዕል በማሳየት ምን እንደሆኑ እና የት እንደሚኖሩ በመጠየቅ ማወያየት
- ስለእንስሳቱ የሚተርክ ተረት ማዳመጥ እንደሚፈልጉ በመጠየቅ የማዳመጥ ፍላጎታቸውን መቀስቀስ
- የጥንቸልና የኤሊን ተረት ገጸባህሪውን ተላብሶ መተረክ
- ተረቱን ተርከው ሲጨርሱ ሕፃናቱን ተረቱ እንዳስደሰታቸውና ማንን እንደወደዱ በመጠየቅ ማወያየት
- በመቀጠልም በቅደም ተከተል ጥያቄ በመጠየቅ የተረቱን ይዘትና መልእክት እንዲረዱ ማድረግ
- “ጥንቸል ጉረኛው” የሚለውን መዝሙር እንዲዘምሩ በማድረግ ማጠናከር

ምዘና ፡- ተረት አዳምጠዉ ከተረቱ ለወጡ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠታቸውንና የተረቱን ይዘትና መልእክት መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- ተረት አዳምጦ መልሶ መተረክ

ዓላማ ፡- ያዳመጡትን ተረት መልሰው ለመተረክ ይሞክራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የተረት መጽሐፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለሕፃናት ዕድሜ የሚመጥን ተረት ከሕፃናቱ ፊት በመቆም ረጋ ብሎ የፊት ገጽታና አካላዊ እንቅስቃሴን በመጠቀም መተረት
- ተረቱን ተርከው ሲጨርሱ ሕፃናቱን ተረቱ እንዳስደሰታቸውና ማንን እንደወደዱ በመጠየቅ ማወያየት
- በመቀጠልም በቅደም ተከተል ጥያቄ በመጠየቅ የተረቱን ይዘትና መልእክት እንዲረዱ ማድረግ
- በተደጋጋሚ የሰሙትን ተረት በመምህር እርዳታ እንዲተርቱ በማድረግ ማበረታታት

ምዘና ፦ ተረት አዳምጠው ከተረቱ ለወጡ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ መስጠታቸውንና በመምህር እርዳታ መልሰው ለመተረክ መሞከራቸውን ትኩረት ሰጥቶ በማዳመጥ መገምገም።

ተግባር ሶስት ፦ መዝሙር መዘመር

ዓላማ ፡- እርስ በእርስ የመደማመጥ ክህሎታቸውን ያዳብራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፦ የመዝሙር ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሕፃናትን በቡድን በመከፋፈል የተዋወቋቸውን የተለያዩ የሕፃናት መዝሙሮችን በየተራ እንዲዘምሩ ማድረግ
- አንዱ ቡድን ሲዘምር ሌላው ቡድን ፀጥ ብሎ ማዳመጥ እንዳለበት፣ በጣም ጮክ ብለው መዘመር እደሌለባቸው ወዘተ አስቀድሞ መንገር
- ዘምረው ሲጨርሱ ጥሩ አድርገው እንደዘመሩና እንዳልዘመሩ ፀጥ ብለው ያዳመጡትን ቡድን በመጠየቅ አስተያየት እንዲሰጡ ማድረግ

ምዘና ፦ በየተራ በመዘመር እርስ በእርስ የመደማመጥ ክህሎትን ለማዳበር መሞከራቸውን ትኩረት ሰጥቶ በማየትና በማዳመጥ ማረጋገጥ።

ተግባር አራት፡ - የጠዋት ሪፖርት ማቅረብ

ዓላማ ፡- በእረፍት ቀናቸው ያደረጉትን አስታውሰው ለመናገር ይሞክራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- መምህር ቅዳሜና እሁድ የእረፍት ቀናቸውን እንዴት እንዳሳለፉት ለህፃናቱ አጠር አድርገው መንገር
- በመቀጠልም ሕፃናት ከጓደኞቻቸው ፊት በመቆም በእረፍት ቀናቸው ምን ምን ነገር እንዳደረጉ መምህር የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ አስታውሰው እንዲናገሩ ማበረታታት
- ህፃኑ ተናግሮ ሲጨርስ ምን እንደተናገረ ሌሎቹን በመጠየቅ አስተውለው የማዳመጥ ልምድን እንዲያዳብሩ ማድረግ

ምዘና ፡- አስታውሶ የመናገር እና ሌሎች ሲናገሩ ለማዳመጥ መሞከራቸውን በማዳመጥና በማየት መገምገም።

**ተግባር አምስት ፡- ተከታታይነት ያላቸው ስእሎችን መረዳት እና መግለጽ**

ዓላማ ፡- ተከታታይነት ያላቸውን ስዕሎች በማየት የተረዱትን ይገልጻሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- ተከታታይነት ያላቸው የተለያዩ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ተከታታይነት ያላቸው ስዕሎችን ለሕፃናት ዕይታ አመቺ ቦታ ላይ በቅደም ተከተል ማስቀመጥ
- በቅደም ተከተል የተቀመጡትን ስዕሎች እያንዳንዱን በማሳየት ስእሉ ላይ ያዩትን እንዲናገሩ ዕድል በመስጠት በጥያቄና መልስ ማወያየት

  ለምሳሌ፡- «ሴትየዋ ምን ገዛች?፤ ምን አደረገች?» ወዘተ…
- ስእሎቹን በቅደም ተከተል በማስቀመጥ ታሪኩን በመተረክ ማወያየት
- በመጨረሻም በቅደም ተከተል ስእሎቹን በማስቀመጥ ህፃናቱ ስእሎቹን በማየት የተረዱትን እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- ተከታታይነት ያላቸው የተለያዩ ስዕሎችን ተረድተው መግለጽ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር ስድስት ፡- ተረትን በድራማ ማቅረብ**

ዓላማ ፡- ገፀባህሪውን ተላብሰው ድራማውን ለማቅረብ ይሞክራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቀማ ፡- ለድራማ የሚያስፈልጉ አልባሳት እና ቁሳቁሶች፤የተረት መጽሐፍት፤ ተረቶቹ ላይ ያሉ ገፀ ባህርያት ስእሎች፤ ጭንብል /ማስክ/ ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ህፃናቱ በተደጋጋሚ የሰሙትን ተረት መልሶ በመተረክ ገፀባህሪያቱን ተላብሰው መጫወት እንደሚፈልጉ በመጠየቅ በድራማው ላይ ተሳታፊ የመሆን ፍላጎታቸውን ማነሳሳት
- አስፈላጊውን አልባሳት እና ጭንብል /ማስክ/ መስጠት
- ሕፃናት የተሰጣቸውን ገፀ ባህሪ ተላብሰው እንዲጫወቱ ማለማመድ

ማስታወሻ ፡- በተረቱ ላይ ገፀባህርያቱ ብዙ ከሆኑ መቀነስ ይቻላል ለምሣሌ ከቤቷ የጠፋችው ውሮን 2 ወይም 3 ገፀ ባህርይ ብቻ በመጠቀም ድራማውን ማዘጋጀት ይቻላል።

ምዘና ፡- ገፀባህሪያቱን ተላብሰው ድራማውን ለመተወን መሞከራቸውን በማየት ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 2. በተለያዩ ሁኔታዎች በራስ በመተማመን በተገቢዉ እና ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ንግግር ወይም የምልክት ቋንቋ መግባባት | 2.1. ቀላል ትዕዛዞችንና መመሪያዎችን መከተል ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- በአካላዊ እንቅስቃሴ የታጀቡ መዝሙሮችን መዘመር

ዓላማ ፡- አጫጭር መዝሙሮችን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት ይዘምራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዝሙር ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናቱ እይታ አመቺ ቦታ በመቆም “ቀስ በቀስ ሽረረቷን”፣ “ወፊቷን እሆናለሁ”፣ “አሻንጉሊቴ” የመሳሰሉ አጫጭር የሕፃናት መዝሙሮችን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት መዘመር
- መምህር መዝሙሩን ስንኝ በስንኝ በመዘመር ህፃናቱ ከመምህር በኋላ በመዘመር እንዲለማመዱ ማድረግ
- ሕፃናቱም መዝሙሩን መልሰው ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር አቀናጅተው እንዲዘምሩ ማለማመድ

ማስታወሻ ፦ በሚዘምሩበት ጊዜ አካላዊ እንቅስቃሴያቸዉ ከሚዘምሩት መዝሙር ቃላት /ሀረግ/ ጋር አብሮ እኩል መሄድ አለመሄዱን ትኩረት መስጠትና በተደጋጋሚ መዝሙሩን ማለማመድ ያስፈልጋል።

ምዘና ፦ አጫጭር መዝሙሮችን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት መዘመር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ መሠረታዊ ቀለማትን መለየት

ዓላማ ፦ መሰረታዊ ቀለማትን በቀለማቸውና በስማቸው ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ቀይ፣ ቢጫ እና ሰማያዊ የቀለም ሰሌዳዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የቀለም ሰሌዳዎቹን በማሳየት መጠሪያ ስማቸውን ማስተዋወቅ
- ሰሌዳዎቹን በማሳየት ስማቸውን እንዲናገሩ ማድረግ
- ህፃናቱ በክፍላቸው ውስጥ ቀይ፤ ቢጫ እና ሰማያዊ ቀለም ያለው ወይም የተቀባ ምን እንዳለ እንዲመለከቱና እንዲናገሩ ማበረታታት ከከበዳቸው ፍንጭ መስጠት

  ለምሳሌ፦ «ግርግዳችን ላይ የተለጠፈችው መኪና ምን ዓይነት ቀለም ነው የተቀባችው?» ወዘተ… በማለት በመጠየቅ ማነቃቃት

ማስታወሻ፦ ህጻናቱ መሠረታዊ ቀለማትን ከተዋወቁ በኋላ ዩኒፎርም በማይለብሱበት ቀን ማን ቀይ፣ ማን ቢጫ፣ ማን ሰማያዊ እንደለበሰ በመጠየቅ ማጠናከር ያስፈልጋል።

ምዘና ፦ መሰረታዊ ቀለማትን መለየት እና መጠሪያቸዉን ማወቃቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፦ መሰረታዊ ቀለማትን ከስእሎች ጋር ማዛመድ

ዓላማ ፦ ተመሳሳይ ቀለም ያላቸውን ስእሎች ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ቀይ፣ ቢጫ እና ሰማያዊ ቀለም ያላቸው ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለእያንዳንዱ ሕፃን መሰረታዊ ቀለም የተቀባ አንድ አንድ ስዕሎችን በነፍስ ወከፍ መስጠት/ለምሳሌ ቢጫ መኪና፣ ቀይ መኪና፣ ሠመያዊ መኪና ወዘተ…
- መምህር ቀይ ሲሉ ሕፃናት ቀይ ቀለም የተቀቡ ስዕሎችን እንዲያሳዩ፤ ቢጫ ሲሉ ቢጫ ቀለም የተቀቡ ስዕሎችን እንዲያሳዩ ወዘተ… ማድረግ
- ሕፃናትን በየተራ በማስነሳት መምህር የማራከሻ ድምጽን እያሰሙ ቀይ ቀይ ሲሉ ሕፃናቱ በፍጥነት በክፍላቸው ውስጥ ተንቀሳቅሰው ቀይ ቀለም ያለውን ዕቃ እንዲያሳዩ ወዘተ… በማድረግ ማጠናከር

ምዘና ፦ ተመሳሳይ ቀለም የተቀቡ ስእሎችን ማዛመድ መቻላቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፦ ራስን መግለጽ

ዓላማ ፦ ስለራሳቸዉ ይናገራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- አንድ ሕፃን በፈቃደኝነት በማስነሳት እና ከሕፃናት ፊት እንዲቆም/እንድትቆም በማድረግ ስሙን/ስሟን፣ የእናቱን/የእናቷን እና የአባቱን/የአባቷን ስም፣ ዕድሜውን/እድሜዋን፣ ምን እንደሚወድ ወዘተ… የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ ስለራሱ እንዲገልጽ ማድረግ
- ሌሎች ሕፃናትም በንቃት እንዲያዳምጡ እና ተራቸው ሲደርስ እነሱም ወጥተው እንደጓደኛቸው እንዲናገሩ ዕድሉን መስጠት

ምዘና ፦ ስለራሳቸዉ መናገር መቻላቸውን በማዳመጥ ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፦ የስሜት መግለጫዎችን መለየት

ዓላማ ፡- የሰዎችን የተለያዩ የስሜት መግለጫዎች በመለየት ለመናገር ይሞክራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመደሰት፣ የመከፋት፣ የመናደድ ወዘተ… ስሜትን የሚያሳዩ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ ስሜቶችን የሚገልፁ ስእሎችን በየተራ በማሳየት በስዕሉ ላይ ያዩትን የሰዎችን ስሜት እንዲናገሩ ማበረታታት
- ሕፃናት ምን ሲሆኑ እንደሚደሰቱ /እንደሚስቁ/ ምን ሲሆን እንደሚከፉ /እንደሚያለቅሱ/ በመጠየቅ ማወያየት
- "ደስተኛ የሆነ" የሚለውን መዝሙር ከአካላዊ እንቅስቃሴ እና ከድርጊት ጋር በማቀናጀት መዘመር እና መልሰው ባዩት መሠረት እንዲዘምሩ ማለማመድ

ምዘና ፡- የሰዎችን የተለያዩ የስሜት መግለጫዎች ለመለየት እና ለመናገር መሞከራቸውን በማዳመጥ ማረጋገጥ።

ተግባር ስድስት ፡- ድርጊትን በቃላት መግለፅ

ዓላማ ፡- ድርጊቶችን በቃላት ይገልጻሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- "ምን እያደረግሁ እንደሆነ ተናገር" የሚለውን ጨዋታ በሚከተለው መንገድ ማጫወት፤
- መምህር ከሕፃናት ፊት በመቆም አንድን ድርጊት በማሳየት/ ፊትን የሚታጠብ በማስመሰል/ ምን እያደረጉ እንደሆነ ሕፃናቱን በየተራ መጠየቅ
- ህፃናቱ በህብረት ሳይሆን እጅ አውጥተው እንዲመልሱ ማድረግና ተግባሩን መልሰው እነሱም እንዲሞክሩት ማበረታታት
- ሕፃናቱም በየተራ የጨዋታው መሪ ሆነው እንዲጫወቱ ማድረግ
- "እጅን መታጠብ እንደዚህ ነው" የሚለውን መዝሙር ከአካላዊ እንቅስቃሴ እና ከድርጊት ጋር በማቀናጀት መዘመርና ሕፃናቱም አብረው እንዲዘምሩ ማነቃቃት

ማስታወሻ ፡- ተግባራቱ ህፃናቱ እለት በእለት የሚያከናውኑትና በአቅራቢያቸው ያሉ ሰዎች ሲያከናውኑ የሚገልጹ ሊሆኑ ይገባል።

ምዘና ፡- የተለያዩ ድርጊቶችን በቃላት መግለጽ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሰባት ፡- "እያ ጅብ አለህ?" ጨዋታን መጫወት

ዓላማ ፡- የጨዋታውን ሂደት ተረድተው ለመጫወት ይሞክራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ህፃናቱን ከክፍል ውጭ ይዞ በመውጣት እጅ ለእጅ በመያያዝ በክብ እንዲቆሙ በማድረግ ምን እንደሚጫወቱና እንዴት እንደሚጫወቱ ለህጻናቱ በሚገባቸው መንገድ ረጋ ብሎ መግለፅ
- መምህር ከህፃናቱ ጋር እጅ ለእጅ በመያያዝ መዝሙሩን ከዜማው ጋር አጣጥሞ በመዘመር ህፃናቱም አብረው እንዲዘምሩ ማድረግ
- መምህር በክቡ መሀል በመሆን የእያጅቦን ገፀባህሪን በመላበስ ከህፃናቱ ጋር አብሮ መጫወት

ምዘና ፡- የጨዋታውን ሂደት ተከትለው መጫወት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ስምንት ፡- ቃላትንና አካላዊ እንቅስቃሴ በማቀናጀት መንቀሳቀስ

ዓላማ ፡- ቃላትንና አካላዊ እንቅስቃሴን በማቀናጀት ይንቀሳቀሳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- ህፃናቱ ከክፍል ውጭ ይዞ በመውጣት በግማሽ ክብ እንዲቆሙ ማድረግ፤
- መምህር "እኔ ዛፍ ነኝ" የሚለውን እንቅስቃሴያዊ ጨዋታ በሚከተለው መንገድ ተጫውቶ ማሳየት

<u>እኔ ዛፍ ነኝ</u>

እኔ ዛፍ ነኝ

እነዚህ ቅርንጫፎች ናቸው /እጆችን መዘርጋት/

ንፋሱ ሲነፍስ

እንደዚህ እንደዚያ /እጆቻቸውን ያንቀሳቅሱአቸዋል/

እንደዚህ እንደዚያ /በማለት ወደ መሬት ይወድቃሉ፤ እጆቻቸውን ወደታች ያደርጋሉ/

- ህጻናቱ መምህርን በመከተል እንቅስቃሴውን ከቃላት ጋር በማቀናጀት እንዲያከናውኑ ማበረታት

ምዘና ፡- ቃላትን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር ማቀናጀት መሞከራቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር ዘጠኝ ፡- ተመሳሳይ ስእሎችን ማዛመድ**

ዓላማ ፡- ተመሳሳይ ስእሎችን በመለየት ማዛመድ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ጥንድ ቁሳቁሶች እና እንሰሳት ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለእያንዳንዱ ህፃን በነፍስ ወከፍ አንድ አንድ ሰዕሎች ለሕፃናት መስጠት
- መምህር የዕቃውን ወይም የእንሰሳቱን ስዕል እያሳዩ <<ልትወጣ ነው ልትወጣ ነው ወጣች» ሲሉ ያንን ዕቃ ወይም እንሰሳት ስዕል የያዙ ህፃናት በሕፃናቱ ፊት ወጥተው እንዲያሳዩ ማድረግ
- ሕፃናት ትክክል መሆናቸውንና አለመሆናቸውን መምህር ከያዙት ጋር በማስተያየት ራሳቸው እንዲያረጋግጡ በማድረግ የስእሉን መጠሪያ ስም መጠየቅና ካላወቁት በመንገር ማጫወት

ምዘና ፡- ቁሳቁሶችን በመለየት ማዛመድ መቻላቸውን በማየት ማረጋገጥ።

**ተግባር አስር ፡- ቁሳቁሶችን በስማቸው መለየት**

ዓላማ ፡- የተለያዩ ቁሳቁሶችን በስማቸው ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ካርቶን፣ ማንኪያ፣ ኩባያ፣ ትንሽ ኳስ፣ አሻንጉሊት ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በአንድ በኩል ክፍት የሆነ መካከለኛ መጠን ያለው ካርቶን ከሕፃናት ፊት በሚገኝ ጠረ â?ዛ ላይ በማድረግ ክፍቱን ወደ መምህሩ ድፍን ሆኖ ትንሽ ክፍተት ያለውን ወደ ሕፃናቱ በማድረግ ማስቀመጥ
- ከካርቶኑ ጀርባ ሕፃናት እንዲያዩት ማንኪያ፣ ኩባያ፣ ትንሽ ኳስ፣ አሻንጉሊት ወዘተ… ማስቀመጥ
- መምህር በእነሱ በኩል ባለው ትንሽ የእጅ ማሾለኪያ እጅዎን አውጥተው "እከሌ እጄ ባዶ ነው ኩባያ ይፈልጋል፣ እጄን ኩባያ አስይዘው/ዥው/>> በማለት እያንዳንዱ ልጅ እየተነሳ የጠየቁትን ዕቃ በእጅት እንዲያስይዞት ያድርጉ

ማስታወሻ፡- ሁሉም ዕቃዎች ተራ በተራ በመምህር እጅ እስኪገቡ ድረስ ጨዋታውን መቀጠል ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- የተለያዩ ቁሳቁሶችን በስማቸው መለየታቸውን መገምገም።

ተግባር አስራ አንድ ፡- የቁሳቁሶችን ስያሜ እና አገልግሎት መናገር

ዓላማ ፡- የቁሳቁሶችን ስያሜ እና አገልግሎታቸውን ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ዘወትር ክፍል ውስጥ የሚያዩአቸው እና የሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ቁሳቁሶች (እርሳስ፤ ደብተር፤ ማንኪያ የጽህፈት መሣሪያዎችንና የተለያዩ ዕቃዎች ወዘተ...)

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መምህር ከህፃናቱ ፊት በመቆም አንድ እቃ በመያዝ ምን እንደሆነና ለምን እንደሚጠቅም አገልግሎቱን መንገር

  ለምሣሌ፡- ማንኪያ፣ ሻይ ለመጠጣት፣ ቅንጬ ለመብላት ወዘተ

- አምስት ህፃናትን በመምረጥ ከክፍል ጓደኞቻቸው ፊት እንዲቆሙ በማድረግ ለእያንዳንዳቸዉ አንድ አንድ ቁስ መስጠት
- ህፃናቱ በየተራ የተሰጣቸው እቃ ምን እንደሆነና ለምን እንደሚያገለግል ጥያቄ በመጠየቅ ለክፍል ጓደኞቻቸው እንዲናገሩ ማድረግ
- የተናገሩት ትክክል መሆንና አለመሆኑን ሌሎቹ እንዲያረጋግጡ ማድረግ

ምዘና ፡- የቁሳቁሶችን ስያሜ እና አገልግሎታቸውን መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3. በማንበብ መደሰት፣ እውቀትን ማግኘት እና መረዳት | 3.1. ስዕሎችን እና ቅርፆችን በማየት መለየት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ተመሳሳይ ነገሮችን ማዛመድ

ዓላማ ፡- ተመሳሳይ ነገሮችን ይለያሉ እንዲሁም ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በጥንድ የተዘጋጁ ቁሳቁሶች፣ የተለያዩ እና ተመሳሳይ የፍራፍሬዎች እና የእንስሳት ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በጥንድ የተዘጋጁ ቁሳቁሶችን፣ የእንስሳት እና የፍራፍሬ ባለቀለም የተለያዩ እና ተመሳሳይ ስዕሎችን ለሕፃናት በየጠረጴዛቸው ላይ ማስቀመጥ
- ተመሳሳዮችን እና አንድ አይነቶችን በመፈለግ እንዲያዛምዱ ማድረግ

ለምሳሌ፡-




- “ተመሳሳዩን አግኙ” የሚለውን ጨዋታ እንደሚከተለዉ ማጫወት
    - ለሕፃናቱ የተለያዩ ስዕሎችን በነፍስ ወከፍ በመስጠት ልጆቹ የተሰጣቸውን ስዕል ለማንም ሳያሳዩ በደንብ እንዲመለከቱ ማድረግ
    - ለልጆቹ እርስዎ የሰጧቸውን ስዕል ተመሳሳይ በየተራ በማውጣት ማሳየት
    - ተመሳሳዩን ስዕል የያዘ/ች ሕፃን ጋር በመምጣት የስዕሉን መጠሪያ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ተመሳሳይ ነገሮችን መለየት እና ማዛመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

## ተግባር ሁለት ፡- ልዩነትን መፈለግ

ዓላማ ፡- በነገሮች መካከል ያሉ ልዩነቶችን ይናገራሉ።

የመርጃ መሣርያዎች ጥቆማ ፡- የፍራፍሬዎች እና የእንስሳት የተለያዩ እና ተመሳሳይ የሆኑ ስዕሎች



የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለዕይታ አመቺ ቦታ ላይ ሶስት ጎላ ጎላ ያሉ ተመሳሳይ ስዕሎችን ማስቀመጥ
- ሕፃናቱ አስተውለው ስዕሎቹን እንዲመለከቱ እና ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ ማድረግ
- በመቀጠልም ከሶስቱ የትኛው የተለየ እንደሆነ እንዲናገሩ ዕድሉን መስጠት
- ከከበዳቸው ልዩነቱን ሊጠቁም የሚችል ፍንጭ መስጠት
- ለሕፃናቱ ሶስት ሶስት ተመሳሳይ ስዕሎችን በመስጠት የትኛው የተለየ እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- በነገሮች መካከል ያሉ ልዩነቶችን መናገር መቻላቸውን መመዘን።

<u>ተግባር ሶስት ፡- የተቆራረጡ እንጨቶችን መገጣጠም</u>

ዓላማ ፡- የተቆራረጡ እንጨቶችን በመገጣጠም ምስሉን ይሞክራሉ።

የመርጃ መሣርያዎች ጥቆማ ፡- ፐዝሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መምህር ለህፃናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመቆም ሶስት ቦታ የተቆራረጡ እንጨቶችን በመገጣጠም ማሳየትና ሲገጣጠም የተገኘው ስእል ወይም ቅርፅ ምን እንደሆነ ህፃናቱን በመጠየቅ ማነቃቃት
- ለሕጻናት ሶስት አራት ቦታ የተቆራረጡ እንጨቶችን ወይም ካርቶኒዎችን ላይ በመስጠት በየተራ እንዲገጣጥሙ ማድረግ
- ሕፃናቱ ገጣጥመው ሲጨርሱ ምን እንደሆነ እንዲናገሩ እድሉን መስጠት ማድረግ

ምዘና ፡- የተቆራረጡ እንጨቶችን በመገጣጠም ያገኙትን ምስል መናገራቸውን በማየትና በማዳመጥ መገምገም።

<u>ተግባር አራት ፡- ነጠብጣቦችን በመገጣጠም መናገር</u>


ዓላማ ፦ ነጠብጣቦችን ለመገጣጠም ይሞክራሉ የገጠሙትንም ስዕል ምንነት ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ሕፃናት የሚያውቋአቸው ጎላ ጎላ ያሉ በነጠብጣብ የተሳሉ ስእሎች፣ እርሳሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- መምህር ጎላ ብሎ በነጠብጣብ የተሳለ ስዕልን ለዕይታ አመቺ ቦታ ላይ መለጠፍ
- ቀስ ብለው ነጠብጣቦቹን በመገጣጠም እያደመቁ ለሕጻናት ማሳየት
- ሲጨርሱ እርስዎ የገጣጠሙት ነጠብጣብ ምስል ምን እንደሆነ መጠየቅ
- ሕጻናት ባዩት መሰረት ነጠብጣቦቹን ቀስ ብለው እንዲገጣጥሙ ማድረግ
- ነጠብጣብ ተከትለው የገጣጠሙትን ምስል በጓደኞቻቸው ፊት ወጥተው እንዲያሳዩ እና እንዲናገሩ ማበረታታት

ለምሳሌ፦ ይህን ስዕል ይጠቀሙ



ምዘና ፦ ነጠብጣቦችን በመገጣጠም ስዕሎችን እና ቅርፆችን መለየት መቻላቸውን መከታተል።

ተግባር አምስት ፦ ስዕሎችን መሳልና ስያሜ መስጠት

ዓላማ ፦ ስእሎችን በመሳል የሳሉትን ስእል ምንነት ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ባለቀለም እርሳሶች /ከለሮች፣ ጎላ ጎላ ያሉ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- መምህር ከህፃናቱ ፊት በመቆም በትልቅ ወረቀት ላይ ጐላ አድርጎ ስእል በመሳል ለህጻናቱ ማሳየትና ምን እንደሆነ በመጠየቅ የህፃናቱን መልስ ካዳመጡ በኋላ ትክክለኛውን መናገር
- ለህፃናቱ በነፍስ ወከፍ ወረቀትና እርሳስ በመስጠት ደስ የሚላቸውን ነገር እንዲስሉ ማድረግ
- ስዕሎቹን ሲሰሩ እየተዘዋወሩ መመልከትና ማበረታታት አስፈላጊውን ድጋፍ መስጠት
- ሲጨርሱም የሳሉትን ስእል ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ ማድረግና ከስእሉ ስር መጠሪያ ስሙን መፃፍ
- የሁሉንም ስእል ሊታይ በሚችል ቦታ ላይ በመለጠፍ ሁሉም ህፃናት እንዲመለከቱ ማድረግ

ምዘና ፦ የፈለጉትን ነገር መሳል እና ለሳሉት ስእል ስያሜ መስጠታቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር ስድስት ፡- ተከታታይነት ያላቸው ስእሎችን በመመልከት መተረክ**

ዓላማ ፦ ተከታታይነት ያላቸው ስእሎችን በመመልከት መተረክን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ተከታታይነት ያላቸው ስዕሎችን የያዘ የሕፃናት የተረት መጽሀፍ ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የሕፃናት የተረት መጽሐፍን በመጠቀም ስዕሎቹን እያሳዩ መተረክ
- ያዩትን እና የሰሙትን እያስታውሱ መልሰው እንዲተርኩ ዕድሉን መስጠት
- በዚህ ዓይነት ስለተለያዩ ፎቶዎች/ ስዕሎች/ እያዩ እንዲተርኩ ማበረታታት
- እየደጋገሙ በየዕለቱ ይህን መሰል ተግባር እንዲያከናውኑ ማለማመድ

ምዘና ፦ ተከታታይነት ያላቸው ስእሎችን በመመልከት መተረክ መሞከራቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር ሰባት ፡- የመፅሃፍት አጠቃቀም እና አያያዝ**

ዓላማ ፡- መጽሐፍትን በስርዓት መያዝን እና መጠቀምን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሳርያዎች ጥቆማ ፦ የመጽሐፍ ማዕዘን /ኮርነር/፣ የተለያዩ የተረት መፅሃፍት፣ ደብተሮች፣ ጋዜጣ ወዘተ..

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መምህር ጎላ ጎላ ያሉ ባለቀለም ስዕሎች ያሏቸውን የሕፃናት መጽሐፍት በመጠቀም ከቀኝ ወደ ግራ መግለጥ እንዳለባቸው በእርጋታ ለህፃናቱ ማሳየት
- ሕፃናቱ በየተራ እየወጡ መጽሐፍን ከቀኝ ወደግራ እንዴት እንደሚገለጥ ማለማመድ
- መጽሐፍት በአግባቡ ካልተያዙ ሊገነጠሉ፣ ሊቆሽሹ እና ሊቀደዱ እንደሚችሉ ማስረዳት
- ሕፃናት በቀላሉ ሊያዩት እና በቀላሉ ሊደርሱበት የሚችሉበት የመጽሐፍ ማዕዘን ማመቻቸት፤
- የሕፃናቱን የእድሜ እርከን እና ባህላቸውን ያገናዘቡ በአመዛኙ ባለቀለም የስዕል ይዘት ያላቸው የተለያዩ የተረት መጽሐፍቶችን፣ ወዘተ... ማስቀመጥ

ማስታወሻ ፡- ሕፃናቱ በፈለጉት ጊዜ መጽሐፍቶችን አንስተው የሚያገላብጡበትን ሁኔታ መፍጠር ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- መጽሐፍትን በስርዓት መያዝንና መጠቀም መለማመዳቸዉን በመከታተል መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 4. የዓይንና የእጅ እንቅስቃሴ ቅንጅትን በማዳበር ለጽሁፍ መዘጋጀት | 4.1. የዓይን እና የእጃቸውን እንቅስቃሴ ማቀናጀትን ይለማመዳሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ወረቀቶችን መቦጫጨቅ እና መለጠፍ

ዓላማ ፡- ወረቀቶቹን በመቦጫጨቅ እና በመለጠፍ የእጅ እና የጣት ጡንቻዎቻቸዉን ያዳብራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ መጠንና ቀለም ያላቸው ወረቀቶች፣ ማጣበቂያ ኮላ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ወረቀቶቹን በተለያየ መጠን በመቦጫጨቅ ማሳየት
- ሕፃናቱም ወረቀቶቹን እንዲቦጫጭቁ ዕድሉን መስጠት
- የቦጫጨቁትን ወረቀት ማጣበቂያ ኮላ ተለቅልቆ በተቀመጠ ትልቅ ወረቀት ላይ እንዲለጥፉ ማድረግ
- ሲጨርሱም በክፍላቸው ውስጥ በመለጠፍ ለክፍል ማስዋቢያነት መጠቀም

ምዘና ፡- ወረቀቶቹን በመቦጫጨቅ እና በመለጠፍ የእጅ እና የጣት ጡንቻዎቻቸዉን ማዳበር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- መሞነጫጨር

ዓላማ ፡- በመሞነጫጨር የአይንና የእጅ እንቅስቀሴ ቅንጅታቸውን ያዳብራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለምእርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለሕፃናት ለእያንዳንቸው ወረቀት እና እርሳስ በመስጠት እጃቸውን በማንቀሳቀስ እንደፈለጉ እንዲሞነጫጭሩ ማድረግ
- ሲጨርሱ የሰሩትን ለክፍል ጓደኞቻቸው እና ለመምህራቸው እንዲያሳዩ ማድረግ
- ከሰሩት ስራ ስር ስማቸውን በመጻፍ ለእይታ አመቺ ቦታ ላይ በክፍል ውስጥ መለጠፍ

ምዘና ፦ የአይንና የእጅ እንቅስቃሴያቸውን በማቀናጀት መሞነጫጨር መቻላቸውንና የሰሩትን መናገራቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፦ ስእልን ቀለም መቀባት

ዓላማ ፦ ስዕሎችን ቀለም በመቀባት የቀቡትን ስእል ይናገራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፦ ጐላ ብሎ የተሳለ ስዕል፤ ስዕል የተሳለባቸዉ ትናንሽ ወረቀቶች፣ ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ጐላ ብሎ የተሳለዉን ስዕል በባለቀለም እርሳስ ከላይ ወደ ታች ወይም ከግራ ወደ ቀኝ ቀስ ብሎ ከመስመር ሳይወጡ በመቀባት ማሳየት
- ስዕል የተሳለባቸዉን ትናንሽ ወረቀቶች ለሕፃናቱ በመስጠት ባዩት መሰረት ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- በመጨረሻም የቀቡት ስዕል ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፦ ስዕሎችን ቀለም በመቀባት የቀቡትን ስእል ምንነት መናገራቸውን በማዳመጥ መገምገም።

ተግባር አራት ፦ ህትመትን መለማመድ

ዓላማ ፦ በውሃ ቀለሞች እጃቸውን ያትማሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያዩ የውሃ ቀለሞች፣ ስፖንጅ፣ ወረቀቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የስፖንጁን ጫፍ የውሃ ቀለም ውስጥ መንከር
- መምህር የግራ እጅ መዳፍዎን በመለቅለቅ እጅዎን በነጭ ወረቀት ላይ ማተም

- ለሁሉም ሕፃናት ወረቀት በማዘጋጀት ካሉት ቀለሞች መርጠው መዳፋቸዉን እንዲያትሙ ማድረግ
- ወረቀቱ ግርጌ ላይ ስማቸዉን እና ቀኑን በመፃፍ ወረቀቱ ሲደርቅ በክፍል ውስጥ መለጠፍ

ምዘና ፡- በውሃ ቀለሞች እጃቸውን ማተም መቻላቸውን በማየት መገምገም።

## ተግባር አምስት ፡- በተቦካ ጭቃ ወይም ወረቀት ቅርፆችን መስራት

ዓላማ ፡- በጭቃ ወይም በተቦካ ወረቀት /ፔፐር ማሼ/ ቀለል ያሉ ቅርፆችን ይሰራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- ጭቃ ወይም የተቦካ ወረቀት፣ የጠረጴዛ ላስቲክ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ጭቃዉን ወይም ወረቀቱን በመጠቀም ቀለል ያሉ ቅርፆችን በመስራት ማሳየት
  ለምሳሌ፡- እንደ ኳስ፣ ድስት፣ ሳህን ወዘተ…
- ጠረጴዛቸው እንዳይቆሽሽ ላስቲክ እንዲያለብሱ ማድረግ
- የሹራባቸውን ወይም የሸሚዛቸውን እጅታ ወደላይ እንዲያጥፉ ማድረግ
- ለሁሉም ሕፃናት በየጠረጴዛቸው ላይ ጭቃ ወይም የተቦካ ወረቀት በመስጠት ባዩት መሰረት እንዲሰሩ ማድረግ
- ሲጨርሱም ምን እንደሰሩ መጠየቅ እና እንዲናገሩ ማበረታታት
- የተሰሩት ቅርፆች ሊደርቁ የሚችሉበት ቦታ ላይ ማስቀመጥ
- እጃቸውን በሳሙናና በውሃ እንዲታጠቡ ማድረግ

ምዘና ፡- በጭቃ ወይም በተቦካ ወረቀት ቀለል ያሉ ቅርፆችን መስራታቸውንና የሰሩትን ምን እንደሆነ መናገራቸውን በማዳመጥ መገምገም።

## ተግባር ስድስት ፡- መሠረታዊ መስመሮች መስራት መለማመድ

ዓላማ ፡- መሰረታዊ መስመሮችን መስራት ይለማመዳሉ።


የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- “ማነው ጉበዝ ሰዓሊ?” የሚለውን ጨዋታ በሚከተለው መንገድ ማጫወት

- መምህር ከሕፃናት ፊት ለፊት በመቆም በአመልካች ጣት አግድም መስመርን በአየር ላይ በመፃፍ ማሳየት እና እነሱም ባዩት መሠረት መሠረታዊ መስመሮችን በአየር ላይ እንዲሰሩ ማበረታታት
- የተለያዩ መሠረታዊ መስመሮችን በወረቀት ላይ ሰርቶ በመስጠት እንዲያደምቁት ማድርግ
- መሠረታዊ መስመሮችን በነጠብጣብ ሰርቶ በመስጠት ነጠብጣቦቹን በማገጣጠም መስመሮቹን እንዲሰሩ ማድረግ

ለምሳሌ፡-



ምዘና ፡- መሰረታዊ መስመሮችን ለመስራት መሞከራቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር ሰባት ፡- በአሸዋ የተለያዩ ቅርጾችን መስራት

ዓላማ ፡- በአሸዋ የተለያዩ ቅርጾችን ይሰራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የአሸዋ ሳጥን፣ አሸዋ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናቱ የአሸዋ ሳጥንን እንዴት መጠቀም እንዳለባቸው አስቀድሞ ገለፃ ማድረግ
- አስቀድመው ሹራባቸውን ወደላይ ማጠፍ፣ አሸዋ በሌሎች ላይ መበተን እንደማይቻል፣ አሸዋውን ከአሸዋ ሳጥን ውጭ መድፋት እንደማይቻል ወዘተ…
  - የአሸዋ ሳጥንን በመጠቀም ሕፃናት ጣቶቻቸውን በማንቀሳቀስ የተለያዩ ቅርፆችን እንዲሰሩ ማበረታታት
  - ሰርተው ሲጨርሱ ለመምህር እንዲያሳዩና ምን እንደሰሩ እንዲናገሩ ማድረግ፤
  - የሰሩትን ስራ በማየት ማበረታታት

ምዘና ፡- በአሸዋ የተለያዩ ቅርጾችን መስራታቸውንና የሰሩትን መናገራቸውን በማየትና በማዳመጥ መገምገም።

ተግባር ስምንት ፡- ቁሶችን በቀለማቸው በመመደብ መጫወት

ዓላማ ፡- ቁሶችን በቀለማቸው በመመደብ ይጫወታሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ ቀለም ያላቸው ቁርጥራጭ እንጨቶች ወይም ካርቶኒዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያየ ቀለም ያላቸውን ቁርጥራጭ እንጨቶች ለሕፃናት በየጠረጴዛቸው መስጠት
- በቀለማቸው እንዲለዩአቸው በማድረግ በለዩአቸው ቁርጥራጭ እንጨቶች የተለያዩ ነገሮችን በመስራት እንዲጫወቱ ማድረግ
- ምን ምን ነገሮችን እንደሰሩ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- ቀለማትን መለየት መቻላቸውንና በተመሳሳይ ቀለማት የተለያዩ ነገር መስራታቸውን በማየት ማረጋገጥ።

**ተግባር ዘጠኝ ፡- ቁሶችን በቁመት እና በቅርጽ መመደብ**


ዓላማ ፡- የተለያዩ ነገሮችን በቁመታቸዉና በቅርጻቸዉ ይመድባሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጽ ያላቸው ቁርጥራጭ እንጨቶች፣ በቁመታቸዉ የተለያዩ የእንጨት ሽመሎች፣ እርሳሶች፣ ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በቁመታቸዉ የተለያዩ ነገሮችን በመስጠት በቁመታቸዉ እንዲመድቧቸው ማድረግ
- በቅርፃቸው የተለያዩ ነገሮችን በመስጠት በቅርፃቸው እንዲመድቧቸው ማድረግ

ለምሳሌ፡-



ምዘና ፡- የተለያዩ ነገሮችን በቁመታቸዉና በቅርጻቸዉ መመደብ መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

**ተግባር አስር ፡- የተለያዩ ቅርፆችን መስራት**


ዓላማ ፡- የተለያዩ ቅርፆችን መስራት ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የክብሪት እንጨቶች፣ የእንጨት ሽመሎች፣ እርሳሶች ወዘተ**...**

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የመርጃ መሳሪያዎቹን በመጠቀም መምህር ቀለል ያሉ ቅርፆችን በመስራት ያሳዩዋቸዉ፤
- የመርጃ መሳሪያዎቹን ለሕፃናት በየጠረጴዛቸው ላይ በማደል የተለያዩ ቅርጾች እንዲሰሩ ማበረታታት፤

  ለምሳሌ፡-



- ሲጨርሱም ምን ምን እንደሰሩ እንዲናገሩ እድሉን መስጠት

ምዘና ፡- ቁርጥራጭ እንጨቶችን በመገጣጠም የተለያዩ ቅርፆችን ለመስራት መሞከራቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር አስራ አንድ ፡- ክርን በቀዳዳ ማስገባትን መለማመድ


ዓላማ ፡- ክር በሰፊ ቀዳዳ ውስጥ ያስገባሉ ቁሶችን በቀለማቸውና በቅርፃቸው ይለያሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- ክር፣ ሰፋፊ ቀዳዳ የተዘጋጀላቸው የውሃ መያዣ ፕላስቲክ ክዳኖች፣ በተለያየ ቅርጽ ተቆራርጠዉ በእያንዳንዱ መካከል ሰፊ ቀዳዳ ያለቸዉ ወፍራም ካርቶኒዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-


- ክር እና ክዳኖቹን በመጠቀም በቀዳዳ ውስጥ ክር እንዴት ማስገባት እንደሚቻል ማሳየት
- ክር እና ክዳኖቹን በየጠረጴዛቸው ላይ በመስጠት በቀዳዳ ውስጥ ክሩን ማስገባት ማለማመድ

ለምሳሌ፡-



- በመቀጠልም ክዳኖቹን በቀለማቸው ካርቶኒዎቹን በቅርፃቸው በመለየት ተመሳሳይ የሆኑትን እየመረጡ እንዲከቱ ማድረግ

ለምሳሌ፡-



ምዘና ፡- ክር በማስገባት ሂደት የዓይንና የእጅ ቅንጅታቸዉን ማዳበራቸዉን ማረጋገጥ።

**ተግባር አስራ ሁለት ፡- ጫማ ማሰርና መፍታትን መለማመድ**

ዓላማ ፡- ቀለል ያሉ የጫማ ፍሬሞችን ማሰርና መፍታትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- ዘለበትና ማጣበቂያ ያላቸው ንፁህ ጫማዎች ወይም የጫማ ማሰሪያ ፍሬሞች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ጫማዎቹን ወይም ፍሬሙን በመጠቀም ጫማ ማሰር እንዴት እንደሚቻል በእርጋታ ማሳየት
- ሁሉም ሕፃናት በመጀመሪያ በመምህር እርዳታ በመቀጠልም በራሳቸዉ እንዲለማመዱ ዕድሉን መስጠት

ምዘና ፡- ጫማዎችን ማሰርና መፍታት መለማመዳቸውን በማየት ማረጋገጥ።

**ተግባር አስራ ሶስት ፡- የልብስ ቁልፎችን መቆለፍ እና መፍታትን መለማመድ**

ዓላማ ፡- የልብስ ቁልፎችን መቆለፍ እና መፍታትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- ትላልቅ ቁልፍ ያላቸው ሸሚዞች ወይም የቁልፍ ፍሬሞች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ፍሬሙን በመጠቀም የልብስ ቁልፍ እንዴት መቆለፍና መፍታት እንደሚቻል ማሣየት
- ሕፃናቱም በየተራ እየወጡ ፍሬሙን በመጠቀም መቆለፍ እና መፍታትን እንዲለማመዱ ማድረግ
- ሕፃናቱ ለሁለት ቡድን ተከፍለዉ በትይዩ እንዲቆሙ ማድረግ
- ለአንዱ ቡድን ቢጫ ለሌላኛዉ ቡድን ደግሞ ቀይ ቀለም ያለዉ ጨርቅ/ሪቫን በእጃቸው ላይ ማሰር
- በመጀመሪያ ቢጫ ጨርቅ/ሪቫን የታሰረላቸው ቀይ ሪቫን የታሰረላቸውን ልጆች ሸሚዝ ቁልፍ ረጋ ብለው እንዲፈቱ እና መልሰው እንዲቆልፉ ማድረግ
- በመቀጠልም እንደዚሁ ቀይ ጨርቅ/ሪቫን ያሰሩ ልጆች ቢጫ ሪቫን ያሰሩ ልጆችን የሸሚዝ ቁልፍ ፈትተው መልሰው እንዲቆልፉ በማድረግ ማለማመድ
- ሕፃናት የአሻንጉሊቶቻቸውን ሸሚዝ እና ሹራብ ቁልፍ በመፍታት እንዲያወልቁ እና በትክክል እያለበሱ ቁልፉን በመቆለፍ እንዲጫወቱ ዕድሉን መስጠት

ምዘና ፡- የልብስ ቁልፎችን መቆለፍና መፍታትን መለማመዳቸውን በማየት ማረጋገጥ።

## ተግባር አስራ አራት ፡- መሰረታዊ መስመሮችን መስራት

ዓላማ ፡- መሰረታዊ መስመሮችን ይሰራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- ወረቀት፣ እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በትልቅ ነጭ ወረቀት ላይ የተለያዩ መሰረታዊ መስመሮችን በየተራ እየሰሩ ለሕፃናት ማሳየት
- ለህጻናት ወረቀትና እርሳስ በመስጠት ባዩት መሠረት እንዲሰሩ ማበረታታት

ማስታወሻ ፡- እነዚህን መሰረታዊ መስመሮች በአንድ ክ/ጊዜ እንዲሰሯቸው ሳይሆን በተለያየ ክ/ጊዜ እንዲለማምዷቸው ሲሆን የሕፃናቱ የእጅ ጡንቻዎች እስኪጠነክሩ ድረስ ይህንን ተግባር በተደጋጋሚ ማለማመድ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- መሰረታዊ መስመሮችን በመስራት ለጽሁፍ መዘጋጀታቸዉን ማረጋገጥ።

### 2.3.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም ---------------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም --------------------------------------------- ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም ----------------------------------------------- ዓመተ ምሕረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡-

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ ---------------------------------------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት ----------------------------------------------------------------------

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት -----------------------------------------------------------------------

ማሳሰቢያ ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | የዓመቱ መጀመሪያ | የዓመቱ አጋማሽ | የዓመቱ መጨረሻ |
| **1.** መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት | | | |
| 1.1. ለተለያዩ ድምፆችና ትዕዛዞች ምላሽ መስጠት ይችላሉ | | | |
| 1.2. የተለያዩ ድምፆችን በማዳመጥ መለየትና አቅጣጫዎችን መጠቆም ይችላሉ | | | |
| 1.3. አጫጭር ተረቶችንና መዝሙሮችን በማዳመጥ መልሰው መናገርና መዘመር ይችላሉ | | | |
| **2.** በተለያዩ ሁኔታዎች በራስ በመተማመን በተገቢውና ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ንግግር እና የምልክት ቋንቋ መግባባት | | | |
| 2.1. ቀላል ትዕዛዞችንና መመሪያዎችን መከተል ይችላሉ | | | |
| **3.** በማንበብ መደሰት፤ ዕውቀት ማግኘትና መረዳት | | | |
| 3.1. ስዕሎችንና ቅርፆችን በማየት መለየት ይችላሉ | | | |
| **4.** የዓይንና የእጅ እንቅስቃሴ ቅንጅትን በማዳበር ለጽሁፍ መዘጋጀት | | | |
| 4.1. የዓይንና የእጃቸውን እንቅስቃሴ ማቀናጀትን ይለማመዳሉ | | | |

## 2.4. በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ የሂሣብ ስሌትንና ፅንሰ ሐሳብን መጠቀም

### 2.4.1 ማብራሪያ

የሂሣብ ጽንሰ ሐሳቦች ማለትም የስፍራ፣ የጊዜ፣ ቁሳቁሶችን በመጠን፣ በቀለምና በቅርጽ መለየት፣ ቁሰቁሶችን መቁጠር፣ ወዘተ ሲሆን በደረጃ ቀስ በቀስ እየዳበረ የሚሄድና ከሌሎች የዕለት ተዕለት ተሞክሮዎቻቸውና እንቅስቃሴዎች ጋር የተያያዘ ነው። ስለዚህ የሂሣብ ትምህርት የሕፃናትን አዕምሮ የሚያዳብርና በደስታ የሚሳተፉበት እንዲሆን እንቅስቃሴው ተግባራዊና ከዕለት ተዕለት ክንውኖችና ሌሎች ትምህርታዊ ፕሮግራሞች ጋር ተያይዞና ተደጋግፎ የሚሰጥ ሊሆን ይገባል።

ከላይ እንደተጠቀሰው ሕፃናት በቁሳቁሶች በበለፀገ አካባቢ መማር አለባቸው። ይህ እንዲሆን አስገዳጁ ሁኔታም ሕፃናት ማሰብ የሚችሉት ከተግባራዊ ክንውን ጋር መሆኑ ነው። ይህ ከ3-4 ዓመት ያለው ዕድሜ ሕፃናት በአፀደ ሕፃናት ተሳትፎ የሚጀምሩበት ጊዜ ስለሆነ ለቀጣዩ ደረጃ መሰረት መጣያ እንዲሆን ከፍተኛ ትኩረት ተሰጥቶ ሊሰራበት ይገባል።

ሂሣብ በሁሉም የሕይወት መስስስክ የሚገኝ ሲሆን የለጋ ሕፃናት የዕለት ተዕለት ገጠመኝም ከሂሣብ ጋር የተያያዘ ነው።
ሂሣብ በአብዛኛው በአዕምሮ ስራ ላይ ያተኮረ ስለሆነ ሕፃናት ሂሳባዊ ፅንሰ ሐሳቦችን እንዲረዱ በቁሳቁሶች በበለፀገ አካባቢ ቁሳቁሶችን እየተጠቀሙ፣ በራሳቸው አቅም እየተንቀሳቀሱ አካባቢአቸውን እንዲፈትሹና እንዲማሩ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል። ይህ ከተከናወነ ሕፃናት ራሳቸውን ችለው ማሰብ የሚችሉ፣ ችግር የመፍታት ዝንባሌ ያላቸው፣ የሂሣብ ትምህርትን በመዝናናት፣ በደስታና በጨዋታ መንፈስ የሚማሩ ሊሆኑ ይችላሉ።

### 2.4.2 አጠቃላይ ዓላማዎች

1. ነገሮችን በዓይነት፣ በአንድነትና ልዩነት እንዲሁም ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ማስቀመጥ እንዲችሉ ለማድረግ
2. የአንድ ለአንድ ግንኙነትን ማሳየት፣ ቁሳቁሶችን በቃል መቁጠርና ብዛትን መጨመርና መቀነስ እንዲችሉ ለማድረግ እና ሳንቲምንና ብርን ለማስለየት
3. በሁለት ቁሶች መካከል ያለ የመጠን ልዩነትን መናገር እንዲችሉ ለማድረግ

4. በጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየት፣ ሰዎችንና ነገሮችን መሰረት በማድረግ ቦታንና ርቀትን መግለጽ እንዲችሉ ለማድረግ

### 2.4.3 የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች

1. የቁሳቁሶችን ባህሪ መፈተሽ መረዳትና መለየት
   1.1. ነገሮችን በዓይነትና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ይችላሉ
2. ነገሮችን በባህሪያቸው መሰረት ማወዳደር
   2.1. በነገሮች መካከል ያለ ዝምድናን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ማሳየት ይችላሉ
3. ቁጥሮችን ማስተዋወቅ፣ መግለጽ፣ ዝምድናቸውን መረዳት እና ቀላል ስሌቶችን መስራት
   3.1. የአንድ ለአንድ ግንኙነትን ማሳየት ይችላሉ
   3.2. ቁሳቁሶችን መቁጠር ይችላሉ
   3.3. ብዛትን መጨመርና መቀነስ ይችላሉ
4. በተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢ የሆኑ የመለኪያ መስፈርቶችንና መሳሪያዎችን መጠቀም
   4.1. በሁለት ቁሶች መካከል የሚታዩ የመጠን ልዩነቶችን መናገር ይችላሉ
5. የጊዜ ፅንሰ ሐሳብ መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም
   5.1. በጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየትና መከተል ይጀምራሉ
6. የቦታ ጽንሰ ሐሳብ መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም
   6.1. ሰዎችንና ነገሮችን መሰረት በማድረግ ቦታንና ርቀትን መግለጽ ይችላሉ
7. ገንዘብን መተዋወቅ፣ መለየት፣ መግለጽና መጠቀም
   7.1. ሳንቲምና ብርን ይለያሉ

## 2.4.4 የሚጠበቁ ውጤቶች፣ ብቃቶች፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1.የቁሳቁሶችን ባህሪ መፈተሽ፣ መረዳት እና መለየት | 1.1.ነገሮችን በአይነት እና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የጂኦሜትሪ ቅርፆችን በስም መለየት

ዓላማ ፡- የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጾችን በስም መለየት ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ባለ ቀለም ወረቀት፣ ኮላ፣ መቀስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ጐን ሶስት፣ ካሬ እና ክብ ቅርጽን ከባለ ቀለም ወረቀት ቆርጦ ማውጣትና መጠሪያ ስማቸውን በመንገር ማስተዋወቅ
- ለእያንዳንዱ ሕፃን ተቆርጦ የወጡ ቅርጾችን በመስጠት በነጭ ወረቀት ላይ እንዲለጥፉ ማድረግ
- ለጥፈው ሲጨርሱ ምን ዓይነት ቅርጽን እንደለጠፉ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጾችን መጠሪያ ስም ማወቃቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- ተመሳሳይ ቅርፆችን ማዛመድ

ዓላማ ፡- በቅርፃቸውና በቀለማቸው ተመሳሳይ የሆኑ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ መሠረታዊ ቀለማት የተቀቡ በርከት ያሉ ቅርፆች ለምሳሌ፡- ካሬ፣ ክብ፣ ጐን ሶስት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያየ ቀለም የተቀቡ ተመሳሳይ ቅርፆች አደባልቆ መስጠት

ለምሳሌ፡- ክብ ፣ ካሬ፣ ጐን ሶስት

- መምህር አንዱን ቅርጽ አንስተው ሲያሳዩ ህጻናቱ ተመሳሳዩን ቅርጽና ቀለም አንስተው እንዲያሳዩና ቅርፁ ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ
- ትክክል መሆንና አለመሆናቸውን ሌሎች ህጻናት እንዲያረጋግጡ ማድረግ

ምዘና ፡- በቅርፃቸውና በቀለማቸው ተመሳሳይ የሆኑ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን ማዛመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- ቅርፆችን በቦታቸው መክተት

ዓላማ ፡- የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጾችን ቅርፃቸውን መሰረት አድርገው በቦታቸው ይከታሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ተፈልፍለው የወጡ የጂኦሜትሪ ቅርፆች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመሆን የተለያየ መጠን ያላቸው የጂኦሜትሪ ቅርፆችን ተፈልፍለው በወጡበት ትክክለኛ ቦታ እንዴት መክተት እንደሚቻል ማሳየት
- በአንድ ጠረጴዛ ላይ ሁለት ሆነው በየተራ መክተትን እንዲለማመዱ ማበረታታት
- ትክክል በቦታው መክተታቸውን ሌሎች እንዲያረጋግጡ ማድረግ

ምዘና ፡- የተለያዩ የጂኦሜትሪ ቅርጾችን ተፈልፍለው በወጡበት ቦታ በትክክል መክተታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- የቅርፆችን መጠሪያ ስም መለየት

ዓላማ ፡- ቅርፆችን በስም ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ኳስ፣ ቾክ/ጠመኔ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ‹‹በቅርፁ ውስጥ ኳስን ክተት››የሚባለውን እንቅስቃሴያዊ ጨዋታ እንደሚከተለው ማጫወት
- በግቢ ውስጥ ወይም በክፍል ውስጥ በምድር ላይ ወይም በወለል ላይ በቾክ የተለያዩ ትልልቅ ቅርፆችን መስራት
- የተሰራውን ቅርጽ ከበው እንዲቆሙ ማድረግ እና መጫወቻ ኳስ መስጠት
- የቅርፁ ስም ሲጠራ የተሰጣቸውን መጫወቻ በተጠራው ቅርፅ ውስጥ እንዲከቱ መጠየቅ

ምዘና ፡- ቅርፆችን በስምና በቅርፅ መለየታቸውን መገምገም።

**ተግባር አምስት ፡- ተመሳሳይ ነገሮችን መለየት**

ዓላማ ፡- ተመሳሳይ ቀለም እና ቅርፅ ያላቸውን ነገሮች ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ መሠረታዊ ቀለማት የተቀቡ በርከት ያሉ ቅርፆች፣ ሰፋ ያለ ካርቶን ወይም የፕላስቲክ ገንዳ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሰፋ ባለ ካርቶን ወይም የፕላስቲክ ገንዳ ውስጥ ተመሳሳይ የሆኑ ነገሮችን በጥንድ መክተት
  ለምሳሌ፡- ጥንድ ጎን አራት፣ ላጲስ፣ ትንሽና ትልቅ ጥንድ እርሳሶች፣ መሰረታዊ ቀለማትን የተቀቡ የክብሪት ፓኮዎች እና የመሳሰሉት
- የሚከተቱት ነገሮች ሕፃናትን ሊማርኩ እንዲችሉ ንፁህና ቀለም የተቀቡ እንደሆኑ ትኩረት መስጠት ያስፈልጋል
- እያንዳንዱን ከመካከል እያወጡ ማሳየት
- ተመሳሳይ የሆነውን ሕፃናት በየተራ ፈልገው እንዲያወጡ ማድረግ
- በመቀጠል ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ተመሳሳይ ቀለምና ቅርፅ ያላቸውን ነገሮች ማዛመዳቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር ስድስት ፡- ቁሶችን በቀለም እና በቅርፅ መመደብ**

ዓላማ ፡- ተመሳሳይ ቅርፅ እና ቀለም ያላቸውን ቁሶች በአንድ ላይ ይመድባሉ

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በቀለም፣ በቅርጽ፣ በባህሪ፣ በመጠን የተለያዩ ቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በሕፃናት ጠረጴዛ ላይ በቀለም፣ በቅርጽ፣ በመጠን የተለያዩ ቁሶች ማስቀመጥ
- ደረጃ በደረጃ ጥያቄን በማቅረብ በዓይነታቸው እንዲለዩ ማድረግ
  ለምሣሌ ፡- በፊታቸው ካሉት ነገሮች መካከል ቀይ የተቀቡ ቆርኪዎችን ለይተው እንዲያወጡ መጠየቅ፣ ቢጫ የተቀቡ ክቦችን ለይተው እንዲያወጡ ማድረግ ወዘተ...

ምዘና ፡- ተመሳሳይ ቅርፅና ቀለም ያላቸውን ቁሶች በአንድ ላይ መመደብ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሰባት ፡- የተለያዩ ነገሮችን መገንባት

ዓላማ ፡- የግንባታ ቁሳቁሶችን/ብሎኮችን በመጠቀም የተለያዩ ነገሮችን ይገነባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡-የተለያየ መጠን ያላቸውን ብሎኮች ወይም ቁርጥራጭ እንጨቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያየ መጠንና ቅርፅ ያላቸውን የግንባታ ብሎኮች ወይም ቁርጥራጭ እንጨቶችን በመጠቀም የተለያዩ ቅርፆችን በመገንባት ለህፃናት ሰርቶ ማሳየት
- በየጠረጴዛቸው ቁሳቁሶቹን በመስጠት የተለያዩ ነገሮችን በመገንባት እንዲጫወቱ ማነቃቃት
- ገንብተው ሲጨርሱ በምን እንደገነቡ ምን እንደገነቡ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- የግንባታ ቁሳቁሶችን/ብሎኮችን በመጠቀም የተለያዩ ነገሮችን መገንባት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ስምንት ፡- የጂኦሜትሪ ቅርፆችን በእጅ ቀዶ ማውጣት

ዓላማ ፡- የጂኦሜትሪ ቅርፆችን መስመራቸውን ተከትለው በእጃቸው ቀደው ቅርፁን ያወጣሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በወረቀት ላይ የተሳሉ የጂኦሜትሪ ቅርፆች/ ክብ፣ ካሬና ጎነ ሶስት/ ባለቀለም እርሳሶች/

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በትልቁ የተሳለ የጂኦሜትሪ ቅርጽን ለህፃናቱ በማሳየት መስመሩን ጡብቆ ቀስ ብሎ በእጅ ቀዶ ቅርፁን በማውጣት ለህጻናቱ ማሳየትና ቅርፁ ምን እንደሆነ መጠየቅ
- ህፃናቱም ቅርፁን ቀደው ማውጣት ይፈልጉ እንደሆነ በመጠየቅ የመስራት ፍላጎታቸውን ማነሳሳት
- ለእያንዳንዱ ህፃን በደማቁ የተሳለ የጂኦሜትሪ ቅርፆችን በመስጠት ባዩት መሠረት ቀደው እንዲያወጡ ማድረግ
- ሲጨርሱም ምን ምን ቅርፆችን ቀደው እንዳወጡ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- ቅርፆቹን ቀደው ማውጣታቸውንና ያወጡትን ቅርጽ መናገራቸውን በማየትና በማዳመጥ ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|

| | |
|---|---|
| 2. ነገሮችን በባህርያቸው መሰረት ማወዳደር | 2.1. በነገሮች መካከል ያለ ዝምድናን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ማሳየት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የቁሶችን መጠን መለየት

ዓላማ ፡- ቁሶችን በመጠናቸው ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በመጠን ጎላ ያለ ልዩነት ያላቸው አንድ አይነት ቅርፆች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በመጠን ጐላ ያለ ልዩነት ያላቸውን ሁለት አንድ ዓይነት ቁሶች በማቅረብ ምን እንደሆኑ መጠየቅ
- በመቀጠልም ሁለቱንም በተለያየ እጅ በማንሳት የትኛው ትልቅ፣ የትኛው ትንሽ እንደሆነ እንዲገምቱ ማድረግ
- እያንዳንዱን ህፃን መምህርጋ እንዲመጣ በማድረግ ትልቁን አንሳና ስጠኝ፣ ትንሹን አንሳና ስጠኝ፣ ለአከሌ ትንሹን ስጥ፣ ለእከሌ ትልቁን ስጥ በማለት ልዩነታቸውን እንዲያውቁ ማለማመድ

ምዘና ፡- ቁሶችን በመጠናቸው መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- ቁሶችን በክብደታቸው መለየት

ዓላማ ፡- ቁሶችን በክብደታቸው በማወዳደር ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ትልቅ ድንጋይ፣ ትልቅ ስፖንጅ፣ ትንሽ ድንጋይ. ትንሽ ስፖንጅ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናቱ በየጠረጴዛቸው ላይ ትልቅ ስፖንጅና ትንሽ ድንጋይ በማስቀመጥ ምን እንደሆነ መጠየቅ
- በመቀጠልም በእጃቸው ሳይነኩ በአይናቸው ብቻ በማየት የትኛው ትልቅ የትኛው ትንሽ እንደሆነ መጠየቅና ከሁለቱ የትኛው እንደሚከብድ አይተው ብቻ እንዲናገሩ ማነቃቃት
- በመቀጠልም በየተራ ሁለቱንም በሁለቱ እጃቸው ይዘው የትኛው እንደሚከብድና የትኛው እንደሚቀል እንዲፈትሹ ማድረግ

- የህፃናቱን መልስ ካዳመጡ በኋላ አንድ እቃ ትልቅ ስለሆነ ይከብዳል ትንሽ ስለሆነ ይቀላል ማለት እንደማይቻል እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ቁሶችን በእጃቸው ላይ አድርገው በማወዳደር ቀላልና ከባድ ቁሶችን ለመለየት መሞከራቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- ቁሶችን በብዛታቸው ማወዳደር

ዓላማ ፡- ቁሶችን በብዛታቸው ማወዳደር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡-የዛፍ ፍሬዎች፣ ኮርኪዎች፣ ጠጠሮች፣ ወዘተ.......

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመሆን በአንድ በኩል በርካታ ጠጠሮች በሌላ በኩል ደግሞ ጥቂት ጠጠሮችን በማስቀመጥ የትኛው ብዙ የትኛው ጥቂት እንደሆነ በመጠየቅ ማነቃቃት
- ለህፃናቱ ለእያንዳንዳቸው በየጠረጴዛቸው ላይ በርካታ ቆርኪዎችን፣ ጠጠሮችንና የዛፍ ፍሬዎችን በመስጠት በአንድ በኩል ብዙ በሌላ በኩል ጥቂት እንዲያደርጉና ሲጨርሱም ለመምህር የትኛው ብዙ የትኛው ጥቂት እንደሆነ እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- የተለያየ ብዛት ያላቸውን ቁሶች በማወዳደር ብዙና ጥቂትን መለየት መቻላቸውን በማየትና በማዳመጥ ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- ቁመትን /ርዝመትን/ ማወዳደር

ዓላማ ፡- የተለያዩ ቁመት/ ርዝመት/ ያላቸውን ነገሮች በማወዳደር ረዥም አጭር በማለት ይገልፃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ረዥም እና አጭር ጥብጣቦች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከወፍራም ክላሰር ወይም የስዕል ወረቀት ረዣዥምና አጫጭር የሆኑ ሶስት ጥብጣቦችን ከ 3 ሴ.ሜ ባላነሰ ልዩነት ቆርጦ ማዘጋጀት
- ጥብጣቦቹን ከረጅሙ ጀምሮ ወደ አጭሩ፤ ከአጭሩ ወደ ረጅሙ እኩል በመደርደር ማሳየት
- ራሳቸው እንዲደረድሩ በማድረግ ረጅምና አጭሩን እንዲለዩ መርዳት
- የመደርደር ጥረታቸውን ማበረታታት

ለምሣሌ ፡-



ምዘና ፡- የተለያዩ ቁመት/ ርዝመት/ ያላቸውን ነገሮች ማወዳደር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር አምስት ፡- ቁሶችን ቅደም ተከተል ጠብቆ መቁጥር**

ዓላማ ፡- ቁሶችን ቅደም ተከተል ጠብቆ በመቁጠር ብዛታቸውን ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቅማ ፡- ከአምስት ያልበለጡ ኮርኪዎች ወይም ጠጠሮች ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በአካባቢ የሚገኙ ተቆጣሪ ነገሮችን በመጠቀም በቅደም ተከተል በመደርደር ድምፅን ከፍ በማድረግ ቁሱን በጣት እየነኩ ከአንድ ጀምሮ እስከ አምስት በመቁጠር ለህፃናቱ ማሳየት
- ለእያንዳንዱ ህፃን ከአምስት የማይበልጡ ቁሳቁሶችን በመስጠት በረድፍ እንዲደረድሩ ማድረግና ከመምህር ጋር አብረው የሚቆጠረውን በጣት እየነኩ እንዲቆጥሩ ማበረታታት
- የተደረደረውን በቅደም ተከተል በመቁጠር ማሳየት እና ባዩት መሰረት እንዲቆጥሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ቁሶችን በቅደም ተከተል በመደርደር እስከ አምስት ድረስ መቁጠር መቻላቸውን በማየት ማረጋገጥ።

**ተግባር ስድስት ፡- ከ 1- 10 በቃል መቁጠር**

ዓላማ ፡- ጣቶቻቸውን በመጠቀም ከ 1-10 በቃል ይቆጥራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የቀኝና የግራ ጣቶችን በማፈራረቅ በጠቋሚ ጣት የጣቶችን ጫፍ በመንካት ከ 1-10 ድምፅን ከፍ አድርጎ በመቁጠር ማሳየት
- ህፃናቱም ባዩት መሠረት መምህርን ተከትለው ጣቶቻቸውን እንዲቆጥሩ ማለማመድ
- 3-4 ህፃናትን በመጋበዝ በጓደኞቻቸው ፊት ወጥተው እንዲቆጥሩ ማድረግና ሌሎችም በቡድን በመሆን በየተራ እንዲቆጥሩ ማድረግ

ምዘና፡- ጣቶቻቸውን በመጠቀም ከ 1-10 በቃል መቁጠር መቻላቸዉን መገምገም።

## ተግባር ሰባት ፦ መዝሙር መዘመር

ዓላማ ፦ የመዝሙሩን ዜማና ስንኝ ተከትለው መዘመርን ይለማመዳሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- <<ቁጥር መቁጠር ደስ ይላል>> የሚለውን መዝሙር ከህፃናቱ ፊት በመቆም ረጋ ብሎና ድምፅን ከፍ አድርጎ መዘመር
- መምህር የመዝሙሩን ስንኝ ዜማውን በጠበቀ ሁኔታ መዘመር እና ህጻናቱም ከመምህር በኋላ ስንኙን እንዲለማመዱ ማድረግ
- በመጨረሻም መዝሙሩን ከመምህር ጋር አብረው በመዘመር እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፦ የመዝሙሩን ዜማ ተከትለው ለመዘመር መሞከራቸውን በማዳመጥ ማረጋገጥ።

## ተግባር ስምንት ፦ አካላዊ እንቅስቃሴን በመጠቀም መዝሙር መዘመር

ዓላማ ፦ አካላዊ እንቅስቃሴን በመጠቀምና የስሜት አካላቶቻቸውን እየጠቆሙ ከ 1-5 በመቁጠር ይዘምራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- <<አምስቱ የስሜት ህዋሳት>> የሚለውን መዝሙር ከቁጥሮች ጋር በማያያዝ በሚከተለው መንገድ ለህፃናት መዘመር፡-

አምስቱ አምስቱ የስሜት ሕዋሳት ሕዋሳት
ዓይን፣ አፍንጫ፣ ምላስ፣ጆሮና እጃችን ናቸው
አንድ፣ ሁለት፣ ሶስት ፣ አራት፣ አምስት ናቸው።

- መዝሙሩ መጨረሻ ላይ ያለውን ስንኝ እየቆጠርን ስንዘምር የስሜት ህዋሳትን በመንካት መዘመር
- መምህር የመዝሙሩን ስንኝ ዜማውን በጠበቀ ሁኔታ መዘመር እና ህጻናቱም ከመምህር በኋላ ስንኙንና አካላዊ እንቅስቃሴውን እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- የመዝሙሩን ዜማ ተከትለው አካላዊ እንቅስቃሴን በመጠቀምና የስሜት ህዋሳታቸውን በመንካት ከ 1-5 መቁጠራቸውን በማዳመጥና በማየት ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3. ቁጥሮችን መተዋወቅ፣ መግለጽ፣ ዝምድናቸውን መረዳት እና ቀላል ስሌቶች መስራት | 3.1 የአንድ ለአንድ ግንኙነትን ማሳየት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ተመሳሳይ ነገሮችን ማዛመድ

ዓላማ ፡- ተመሳሳይ ነገሮችን ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- ቆርኪዎች፣ ፍሬዎች፣ ጠጠሮች ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በእያንዳንዱ ጠረጴዛ ላይ ከሁሉም አይነት አንድ አንድ አይነት በመስጠት እንዲደረድሩ ማድረግ
- በመቀጠልም የደረደሩትን ቁሶች ማዛመጃዎችን በጠረጴዛቸው ላይ ማስቀመጥና ህጻናቱ ከተመሳሳዩ አጠገብ እንዲያስቀምጡ ማነቃቃት
- ምን ምን ነገሮች አንድ አይነት ሆነው እንዳዛመዱ በጣታቸው እየጠቆሙ እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ተመሳሳይ ነገሮችን ማዛመድ መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ሁለት ፡- በማዛመጃ ሰሌዳ መጫወት


ዓላማ ፡- ተመሳሳይ ነገሮች በማዛመድ ይጫወታሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- ተቆራርጠው የወጡ ስዕሎች፣ ሎቶዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የቤት እንስሳት ስዕል፣ የዱር እንስሳት ስዕል፣ የፍራፍሬ፣ የአትክልት፣ የቤት ቁሳቁሶች ማዛመጃ ሰሌዳ /ሎቶ/ በማቅረብ /ከተጠቀሱት የተገኘውን ዓይነት/ እንዴት ሊዛመድ እንደሚችል በተግባር ማሳየት
- በግል ወይም ከ 2-4 አባላት ባሉት ቡድን የማዛመጃ ሰሌዳውን በመስጠት የማዛመድ ጨዋታን እንዲጫወቱ ማድረግ
- አንድ ለአንድ ማዛመድ መቻላቸውን መከታተልና አስፈላጊውን እገዛ በማድረግ ማበረታታት





ምዘና ፡- ተመሳሳይ ነገሮችን በማዛመድ መጫወት መቻላቸውን በማየት መገምገም።


ተግባር ሶስት ፡- ተመሳሳይ ነገሮችን ቀለም በመቀባት ማዛመድ

ዓላማ ፡- ተመሳሳይ ነገሮችን ቀለም በመቀባት ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፦ የቤት እንስሳት ስዕል፣ የዱር እንስሳት ስዕል፣ የአበባ ስዕል፣ የፍራፍሬ ስዕል፣ ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ጥንድ ጥንድ የሆኑ የተሳሉ አበባዎች፣ ፍራፍሬዎችና ሌሎች መሰል ነገሮችን ቆርጦ ማውጣት
- ለእያንዳንዱ ህፃን አንድ ጥንድ በመስጠት አንድ ዓይነት ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- ቀብተው ሲጨርሱ እርስ በእርስ እያገናኙ እንዲያስቀምጡና ምን እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ ለምሳሌ፦



ምዘና ፡- ተመሳሳይ ነገሮችን ቀለም በመቀባት ማዛመድ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- ተመሳሳይ ነገሮችን መለየት እና መቁጠር

ዓላማ ፡- ተመሳሳይ ነገሮችን ለይተው መቁጠር ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- ፍሬዎች፣ ቆርኪዎች፣ ጠጠሮች፣ ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ፍሬዎች፣ ቆርኪዎች፣ ጠጠሮች በመጠቀም ከተደባለቁት ውስጥ እንዴት ለይቶ ማውጣት፣መደርደር እና መቁጠር እንደሚቻል ማሳየት
- ለሕፃናት በየግላቸው ከ1ዐ ያልበለጡ ተደባልቀው የሚገኙ የተለያዩ ነገሮችን ማደል እና ለቅመው በዓይነት እንዲለዩ፣ እንዲደረድሩ እና እንዲቆጥሩ ማድረግ

ምዘና ፡- ተመሳሳይ ነገሮችን ለይተው መቁጠር መጀመራቸውን በማየት ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3. ቁጥሮችን መተዋወቅ፣ መግለጽ፣ ዝምድናቸውን መረዳት እና ቀላል ስሌቶችን መስራት | 3.1. ቁሳቁሶችን መቁጠር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- መዝሙር መዘመር

ዓላማ ፡- ከ 1 -1 ያሉትን ቁጥሮች በመዝሙር በቅደም ተከተል ይቆጥራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የመዝሙር ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- "ትንሽ ትንሽ ወፎች" መዝሙርን በመዘመር 1-10 እንዲቆጥሩ ማለማመድ
- መዝሙሩን ለማጀብ ትናንሽ ተስለውና ተቆራርጠው የወጡ የወፎች ምስሎችን መጠቀም
- ሕፃናት በቃል ሲቆጥሩ የወፎቹን ምስል በማሳየትና በመምራት ማነቃቃት

ምዘና ፡- ከ 1 -10 ያሉትን ቁጥሮች በቅደም ተከተል መቁጠር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- አንድ ለአንድ ማዛመድ

ዓላማ ፡- ነገሮችን አንድ ለአንድ ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- አምስት ከረሜላዎች፣ አምስት አሻንጉሊቶች፣ የፕላስቲክ ውሃ መያዣዎች እና ክዳናቸው ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- አምስት ከረሜላዎችና አምስት አሻንጉሊቶች ማዘጋጀት
- እያንዳንዱ ልጅ በየተራ ወደ መምህር በመቅረብ ለአሻንጉሊቶቹ ከረሜላ እንዲያድል በማድረግ
- አንድ ለአንድ ማገናኘትን ማለማመድ
- ተመሳሳይ ተግባርን የፕላስቲክ ውሃ መያዣዎችን እና ክዳናቸውን ለብቻ በማስቀመጥ አንድ ለአንድ እንዲያገናኙ ማበረታታትና ማለማመድ

ምዘና ፡- አንድ ለአንድ ማዛመድ መቻላቸውን በማየት መገምገም።

ተግባር ሶስት ፡- ቁሳቁሶችን መቁጠር

ዓላማ ፡- ከ 1 -5 ያሉ ቁሶችን ቀጥረው መጠኑን ይናገራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያየ ቀለም ያላቸው የውሃ ኮዳ ክዳኖች፣ ቆርኪዎች፣ጠጠሮች ወዘተ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለእያንዳንዱ ህጻን በየጠረጴዛቸው ከ አምስት ያልበለጡ የተለያዩ ቁሶችን በመስጠት ከፊት ለፊታቸው እንዲደረድሩ ማድረግ

- ደርድረው ሲጨርሱ በመምህር መመሪያ መሠረት ከተሰጣቸው ቁሶች ውስጥ እየቆጠሩ እንዲያወጡ ማድረግ
- ለምሳሌ መምህር ሶስት ሲል ሶስት ቁሶችን ብቻ ቆጥረው እንዲያወጡ ሁለት ሲል ሁለት ቁሶችን እንዲያወጡና ሁሉም በአንድነት እያንዳንዱን ቁስ በጣታቸው እየነኩ ቆጥረው እንዲናገሩ ማነቃቃት
- ከከበዳቸው አስፈላጊውን ድጋፍ በማድረግ ማበረታታት

ምዘና :- ቁሶችን በመቁጠር መጠናቸውን መለየትና መናገር መቻላቸውን በማየትና በማዳመጥ መገምገም።

ተግባር አራት :- ከ 1 -10 በተቆጣሪዎች መቁጠር

ዓላማ :- ከ 1 -10 ተቆጣሪዎችን በመጠቀም መቁጠር ይችላሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ :- ቾክ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ :-

- ከ 1 0 ያልበለጡ ሕፃናት ወጥተው በጓደኞቻቸው ፊት እንዲቆሙ ማድረግ
- የወጡትን ሕፃናት በክፍል ውስጥ በቾክ በተሰራ ክብ ውስጥ እንዲቆሙ ማድረግ፤,
- ከሕፃናቱ መካከል አንዱን በመጥራት በክብ ውስጥ ካሉት ልጆች መካከል 3 ወይም 4 ልጅ ቆጥሮ እንዲያወጣ እና በመምህር ፊት እንዲያቆማቸው ማድረግ
- በትክክል ቆጥሮ ማውጣቱን ወይም አለማውጣቱን ሌሎች እንዲያረጋግጡ በማድረግ ማጫወት

ምዘና :- ከ 1 -10 ያሉትን ቁጥሮች መቁጠር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3. ቁጥሮችን መተዋወቅ፣ መግለጽ፣ ዝምድናቸውን መረዳት እና ቀላል ስሌቶችን መስራት | 3.3 ብዛትን መጨመር እና መቀነስ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ :- መጨመርን መለማመድ

ዓላማ :- በደረጃቸው የመጨመርን ጽንሰ ሀሳብ ለመረዳት ይሞክራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ :-

- በክፍሉ ውስጥ ካሉት ሕፃናት መካከል 2 ወንዶች እና 4 ሴቶች በማስወጣት ለየብቻ በቡድን እንዲቆሙ ማድረግ
- ሕፃናቱ ሰንት ወንዶችና ስንት ሴቶች እንደሆኑ ቆጥረው እንዲናገሩ ማድረግ
- ቆጥረው ሲጨርሱ «የትኞቹ ብዙ ናቸው? ሴቶች ወይስ ወንዶች?» በማለት መጠየቅ
- በመቀጠልም ሌላ ሶስት ወንዶችን በማምጣት ከወንዶቹ ጋር እንዲቀላቀሉና አሁን ደግሞ የትኞቹ ብዙ እንደሆኑና ለምን ብዙ እንደሆኑ በመጠየቅ የመጨመርን ፅንሰ ሀሳብ በደረጃቸው እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- በደረጃቸው የመጨመርን ፅንሰ ሀሳብን መረዳት መጀመራቸውን በማየትና በማዳመጥ መገምገም፡፡

ተግባር ሁለት ፡- መቀነስን መለማመድ

ዓላማ ፡- በደረጃቸው የመቀነስን ጽንሰ ሀሳብ ለመረዳት ይሞክራሉ፡፡

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- አምስት የአረንጓዴ ጠርሙስ ስዕሎች፣ የውሃ ፕላስተር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መምህር ለህፃናት እይታ አመቺ ቦታ ላይ ከወፍራም አረንጓዴ ክላሰር ላይ የተቀረፁ አምስት የወረቀት ጠርሙሶችን በውሃ ፕላስተር መለጠፍ
- አምስት አረንጓዴ ጠርሙሶች በግርግዳ ላይ ድንገት አንዱ ወድቆ ቢሰበር አራት ይቀራል በማለት በየተራ አንድ አንድ የወረቀት ጠርሙሱን ከግርግዳ ላይ በማላቀቅ ወደመሬት መጣል
- ህፃናቱም አብረው ከመምህር ጋር በመደጋገም መዝሙሩን እንዲዘምሩ በማድረግ በደረጃቸው የመቀነስ ጽንሰ ሀሳብን እንዲረዱ ማድረግ
- አባከስን በመጠቀም በየተራ በቅደም ተከተል መቁጠርን መጨመር እና መቀነስን እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- በደረጃቸው የመቀነስን ፅንሰ ሀሳብን መረዳት መጀመራቸውን በማየትና በማዳመጥ መገምገም፡፡

ተግባር ሶስት ፡- መጨመርና መቀነስን መለማመድ

ዓላማ ፡- ተቆጣሪ ነገሮችን በመጠቀም መጨመርና መቀነስን ይለማመዳሉ፡፡

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፦ አባከስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለህፃናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመሆን አበከስን በመጠቀም በአንድ አቅጣጫ ያሉትን የአበከስ ጠጠሮችን/ዶቃዎችን ከመምህር ጋር አብረው እንዲቆጥሩ ማድረግ
- ቆጥረው ሲጨርሱ ስንት እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግና በቆጠሩት ላይ ሌላ ተጨማሪ የአበከስ ጠጠሮችን/ዶቃዎችን በመጨመር መጠኑን ቆጥረው እንዲናገሩ በማድረግ መጨመርን እንዲለማመዱ ማድረግ
- በመቀጠልም የተወሰኑ የአበከስ ጠጠሮችን/ዶቃዎችን በአንድ አቅጣጫ በማድረግ ከህፃናቱ ጋር አብሮ መቁጠር
- በመቀጠልም ከተቆጠሩት ውስጥ አንድ ወይም ሁለት በመቀነስ እንደገና መልሶ በመቁጠር ስንት እንደቀሩ እንዲናገሩ በማድረግ መቀነስን እንዲለማመዱ ማድረግ

> ማስታወሻ ፦ ህፃናቱ የሚገኙበት የዕድሜ ደረጃ ስለማይፈቅድ ደምሩ ቀንሱ ብሎ መጫን ተገቢ አይሆንም፤ በተቻለ መጠን ከቁሳቁሶች ጋር የሚያደርጉት ተግባር የጨዋታ መንፈስ ሊኖረው ይገባል።

ምዘና ፦ አበከስን በመጠቀም መጨመርና መቀነስን መለማመዳቸውን በማየትና በማዳመጥ ማረጋገጥ።

**ተግባር አራት ፦ ወንበር ሽሚያ ጨዋታን መጫወት**

ዓላማ **፦** በጨዋታው በአንድ የማነስን እና የመብለጥን ፅንሰ ሀሳብ ለመረዳት ይሞክራሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ፦ በክፍል ውስጥ ያሉ ወንበሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ **፦**

- የወንበር ሽሚያ ጨዋታን እንደሚከተለው ማጫወት በሚከተለው መንገድ መጫወት፡-
  - 5 በክፍል ውስጥ ያሉ ወንበሮች በክብ ቅርፅ መደርደር
  - 6 ተማሪዎችን በፍላጎት ማስወጣት
  - መምህር ሲያጨበጭቡ ህፃናቱ በወንበሩ ዙሪያ እየተሽከረከሩ እንዲሮጡ ማድረግ

o ጭብጨባው ሲቆም ህፃናቱ ወንበሮቹን ተሻምተው እንዲቀመጡ በማድረግ በአንድ የማነስ እና የመብለጥን ፅንሰ ሀሳብ እንዲያስተውሉ ማለማመድ

ማስታወሻ፡- በወንበር ሽምያው ወቅት ህፃናቱ ጉዳት እንዳይደርስባቸው ጥንቃቄ ማድረግ፡፡

ምዘና፡- በአንድ የማነስን እና የመብለጥን ፅንሰ ሀሳብ መረዳት መቻላቸዉን ማረጋገጥ፡፡

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 4. በተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢ የሆኑ የመለኪያ መስፈርቶች እና መሣሪያዎችን መጠቀም | 4.1. በሁለት ቁሶች መካከል የሚታዩ የመጠን ልዩነቶችን መናገር ይችላሉ፡፡ |

ተግባር አንድ ፡- የመጠን ልዩነትን መረዳት

ዓላማ ፡- የመጠን ልዩነትን ይለያሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በቤት እና በክፍል ዉስጥ በየዕለቱ የሚጠቀሙባቸው ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከቁሳቁሶቹ መካከል ትንሽ እና ትልቅን ለይተው እንዲያወጡ ማድረግ

  ለምሣሌ፡- ትልቅ እና ትንሽ መቀሶች፣ ደውሎች ወዘተ…

- በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው የሚያጋጥሟቸውን እና የሚጠቀሙባቸውን ቁሶች በማንሳት ትንሽና ትልቅን እንዲያወዳድሩ ማድረግ

  ለምሣሌ፡- «በምንድነው ቁርስ የበላሽው? /ሽው/››፤ ሳህኑ ትልቅ ነው ትንሽ?»


  ወዘተ…ብለው የተለያዩ ጥያቄዎችን ማንሳት


ምዘና ፡- በቁሳቁሶች መካከል ያለውን የመጠን ልዩነትን መረዳታቸውን ማረጋገጥ፡፡

ተግባር ሁለት ፡- ትንሽ እና ትልቅ መለየት

ዓላማ ፡- የተመሳሳይ ቁሶችን መጠን ትንሽ እና ትልቅ በማለት ይለያሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቀማ ፡- የተለያዩ ስዕሎች





የአተገባበር ዘዴ ጥቀማ ፡-

- ከህፃናቱ ፊት ለፊት ባለው ጠረጴዛ ላይ በጥንድ ያሉ በመጠን ግን የሚለያዩ በርካታ ስዕሎች በማስቀመጥ ህጻናቱ በየተራ እየወጡ ተመሳሳይ ቁሶቹን እንዲመርጡና እንዲያወጡ ማድረግ
- በመቀጠልም ምን እንደሆነና የትኛው ትልቅ፣ የትኛው ትንሽ እንደሆነ ለጓደኞቻቸው በማሳየት እንዲናገሩ ማበረታታት
- ሁሉም ህፃናት በተግባሩ ላይ ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ

ምዘና ፡- ተመሳሳይ ቁሶችን በመምረጥ ትንሽ እና ትልቅ በማለት መለየታቸውን በማየትና በማዳመጥ ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- ረጅም እና አጭር መለየት

ዓላማ ፡- ረጅም እና አጭር ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቀማ ፡- የቁመት ልዩነት ያላቸው ልምጮች፣ እርሳሶች፣ ወረቀቶች ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቀማ ፡-

- በጥንድ ያሉ የቁመት ልዩነት ያላቸውን ልምጮችን ፣እርሳሶችን፣ወረቀቶችን ወዘተ.... ለእያንዳንዱ ህፃን መስጠት
- የተሰጣቸው ቁስ ምን እንደሆነና የትኛው ረዥም፣ የትኛው አጭር እንደሆኑ ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩና እንዲናገሩ ማበረታታት

- ከከበዳቸው ድጋፍ ማድረግ እና ማበረታታት

ምዘና ፦ የቁሶችን መጠን ረጅም እና አጭር በማለት መግለጽ መቻላቸውን በማየትና በማዳመጥ መገምገም።

ተግባር አራት ፦ አሸዋ መስፈር

ዓላማ ፦ በመስፈር ብዙና ጥቂትን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ትልልቅና ትንንሽ ኩባያዎች /ጣሳዎች/ እና የአሸዋ ሳጥን

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ከክፍል ውጭ ያለውን የአሸዋ ሳጥን በመጠቀም በትልቅና በትንሽ ኩባያዎች በመስፈር ሁለት ቦታ ላይ በማድረግ የትኛው ብዙ፣ የትኛው ጥቂት እንደሆነ መጠየቅና ለምን እንደዛ እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- በመቀጠልም ህጻናቱ በመስፈሪያዎቹ በመስፈርና ከአንዱ ወደ አንዱ በማገላባበጥ በመጫወት ብዙና ጥቂትን እንዲለዩ ማድረግ

ምዘና ፦ የብዙ እና የጥቂትን ልዩነት መረዳታችውን በማየትና በማዳመጥ ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፦ የተለያ መጠን ያላቸውን ነገሮች መገንባት

ዓላማ ፦ የተለያየ መጠን ያላቸውን ነገሮች ይገነባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያየ መጠንና ቅርጽ ያላቸው የመገንቢያ ብሎኮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፦

- ለህፃናት እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመሆን አንድ ትልቅና አንድ ትንሽ ቤትን ገንብቶ ለህጻናት በማሳየት ምን እንደሆነና የትኛው ትልቅ፣ የትኛው ትንሽ ቤት እንደሆነ በመጠየቅ ማነቃቃት
- ለህፃናቱ የመገንቢያ ብሎኮችን በመስጠት ትልቅና ትንሽ የሆኑ ነገሮችን እንዲገነቡ እድሉን መስጠት
- ተነቃቅተው የመጫወት ሀሳብ እንዲመጣላቸው «ምን ትገነቢያለሽ /ህ?፣ መንገድ ነው? ቤት ነው?፣ ትልቅ ነው ትንሽ?›› ወዘተ… በማለት መጠየቅ እና መርዳት

ምዘና ፦ ትልቅና ትንሽ መጠን ያላቸውን ነገሮች ሲገነቡ በማየትና ሲናገሩ በማዳመጥ መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| **5.** የጊዜ ጽንሰ ሐሳብን መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም | 5.1. በጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየት እና መከታተል ይጀምራሉ። |


ተግባር አንድ ፦ በየእለቱ ስለሚከናወኑ ተግባራት መናገር

ዓላማ ፦ ስእልን በማየት በየእለቱ ስለሚያከናወኑ ተግባራት ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በተለያየ ጊዜ የሚከናወኑ ተግባራትን የሚያሳይ ስዕል፣ የሰዓት ስዕል፤ወዘተ...

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ህፃናት የተለያየ ተግባራትን ሲያከናውኑ የሚያሳይ ጎላ ብሎ የተሳለ ስእልን በማሳየት ልጆቹ ምን እያደረጉ እንደሆነ እንዲናገሩ ማነቃቃት



ለምሳሌ፡- ልጁ ምን እያደረገ ነው**?** ልጆቹስ? በማለት መጠየቅና እነዚህን ተግባራት በእለቱ አከናውነው እንደሆነና የት እንዳከናወኑና እንዲሚከናወኑ በመጠየቅ ምላሽ እንዲሰጡ ማበረታታት

- አንዳንድ ህጻን በማስነሳት መምህር በእለቱ የሚከናወኑ ተግባራትን ሲናገሩ ህፃናቱ ስእሉን እንዲያሳዩ ወይም እንዲጠቁሙ ማድረግ
- ህጻኑ በትክክል የተባለውን ተግባር ማሳየትና አለማሳየቱን ሌሎች ህጻናት እንዲያረጋግጡ በማድረግ በትኩረት እንዲከታተሉ ማነቃቃት

ማስታወሻ፡- ለልጆች የሚቀርቡ ስዕሎች ጉልህ የሆኑ ብሩህ ቀለም ያላቸው እና የሚስቡ እንዲሆኑ ያስፈልጋል፡፡

ምዘና ፡- ስእልን በማየት በእለት የሚከናወኑ ተግባራትን መናገር መቻላቸውን በማየትና በማዳመጥ ማረጋገጥ፡፡

<u>ተግባር ሁለት ፡- ጠዋትና ማታ የሚከናወኑ ተግባራትን መናገር</u>

ዓላማ ፡- ጠዋትና ማታ የሚከናወኑ ተግባራትን በመለየት ይናገራሉ፡፡

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ፀሀይ ስትወጣ ብርሀን ሆኖ የሚያሳይ ስእልና ሲመሽ ጨለማ ሆኖ ጨረቃ ወጥታ የሚያሳይ ስእል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ስእሉን በየተራ በማሳየት መቼ ጠዋትን መቼ ማታን እንደሚገልጽ በመጠየቅ ማነቃቃት
- ጠዋት የምንለው መቼ እንደሆነ፣ማታ የምንለው መቼ እንደሆነ በመግለፅ ምን ምን ተግባራትን እነሱ በቤታቸው እንደሚያከናወኑ በመጠየቅ ከልምዳቸው በመነሳት እንዲናገሩ ማድረግ
- መምህር ጠዋት የሚከናወኑ ተግባራትን ስትናገር ህፃናቱ ጠዋት ብለው እንዲናገሩ ማታ የሚከናወኑ ተግባራትን ስትናገር ማታ ብለው እንዲናገሩ በማድረግ ማጠናከር

ምዘና ፡- ህፃናቱ ጠዋትና ማታ የሚከናወኑ ተግባራትን በመለየት መናገራቸውን መገምገም፡፡

<u>ተግባር ሶስት ፡- በቀን ውስጥ የሚያከናወኑ ተግባራትን መለየት</u>

ዓላማ ፡- በቀን ውስጥ የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ይለያሉ፡፡

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መዝሙሩን ድምፅ ከፍ በማድረግ መዘመርና ህጻናቱም መዝሙሩን ለመዘመር እንደሚፈልጉ በመጠየቅ ማነቃቃት
- መምህር እያንዳንዱን የመዝሙሩን ስንኝ ዜማውን በመጠበቅ ረጋ ብሎ በመዘመር ህጻናቱ ከመምህር በኋላ እንዲዘምሩ በማድረግ ማለማመድ

<u>ሁልጊዜ ጠዋት ስንነሳ</u>

ሁልጊዜ ጠዋት ስንነሳ
ፊታችንን እንታጠባለን
ቁርሳችን እንመገባለን
ደግሞም ትምህርት ቤት እንሄዳለን

እዛም እንማራለን፣ እንጫወታለን፣
ሲመሽ ደግሞ እግራችንን ታጥበን
አልጋችን ላይ እንተኛለን
ሁልጊዜ ይህን እናደርጋለን

- በመጨረሻም እለት በእለት በጊዜ ውስጥ የሚያከናውኗቸው ተግባራትን ምን ምን እንደሆኑ በመጠየቅ ማጠናከር

ምዘና ፡- ዜማውን ተከትለው መዝሙሩን ለመዘመር መሞከራቸውን በማዳመጥና በእለት ተእለት ህይወታቸው የሚያከናውኗቸውን ተግባራት መለየታቸውን በመጠየቅ መገምገም።

ተግባር አራት ፡- በተለያየ ጊዜ የሚያከናውኑትን ተግባራትን መግለጽ

ዓላማ ፡- በተለያየ ጊዜ ያከናወኗቸውንና ወደፊት የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ተገቢውን ቃላት በመጠቀም ለመናገር ይሞክራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መምህር ከህጻናቱ ፊት ለፊት በመቆም ጠዋት ምን እንዳደረጉ በመናገር ህፃናቱም ቤታቸው ያደረጉትን አስታውሰው እንዲናገሩ ማነቃቃት
- ቀጥሎም አሁን ምን እያደረጉ እንደሆነና በኋላ ምን እንደሚያደርጉ መናገርና ህጻናቱም ምን እያደረጉ እንደሆነና በኋላ ወደቤታቸው ሲሄዱ ምን እንደሚያደርጉ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማድረግ
- ለከበዳቸው ህጻናት ፍንጭ በመስጠት ድጋፍ በማድረግ ያደረጉትን፣ እያደረጉ ያሉትንና በኋላ የሚያደርጉትን እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- በእለቱ ያከናወኗቸውን፣ እያከናወኑ ያሉትንና በኋላ ላይ የሚያከናውኑትን ተግባራት ተገቢውን ቃላት በመጠቀም ለመናገር መሞከራቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፦ የሰዓት ስእልን ቀለም መቀባት

ዓላማ ፦ የሰዓት ስእልን ቀለም ይቀባሉ እንዲሁም በደረጃቸው የሰዓትን ጥቅም ያውቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተሳሉ የእጅ ሰዓት ስእሎች፣ የእርሳስ ቀለሞች፣ ደማቅ ቀለም የተቀባ ትልቅ የእጅ ሰአት ስእል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- መምህር ለህፃናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመቆም ደማቅ ቀለም የተቀባውን የሰዓት ስእልን በማሳየት ምን እንደሆነ፣ ምን ላይ እንደሚታሰር፣ ለምን እንደሚጠቅም ወዘተ በመጠየቅ ስለ እጅ ሰዓት ያላቸውን ቀደምት እውቀት በመጠየቅ ማነቃቃት
- በመቀጠልም እንዴት ቀለም እንደሚቀቡ እጅን ከላይ ወደታች ወይም ከግራ ወደ ቀኝ በማንቀሳቀስ ረጋ ብሎ እንዴት እንደሚቀባ ማሳየት
- ለእያንዳንዱ ህጻን ያልተቀባ የሰዓት ስእል በመስጠት ባዩት መሠረት የፈለጉትን ቀለም እንዲቀቡ ማበረታታት
- ሲጨርሱ ምን እንደቀቡና ምን አይነት ቀለም እንደቀቡ ለጓደኞቻቸው በማሳየት እንዲናገሩ ማድረግ

ምዘና ፦ የሰዓትን ስእል ቀለም መቀባታቸውን በማየትና የሰዓትን ጥቅም ማወቃቸውን ሲናገሩ በማዳመጥ መገምገም።

ተግባር ስድስት ፦ መኪና በመንዳት መጫወት

ዓላማ ፦ እጃቸውን እንደ መኪና በማሰብ በተለያየ ፍጥነት ያሽከረክራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- መምህር ከህጻናቱ ፊት በመቆም ህፃናቱ መኪና መንዳት እንደሚፈልጉ በመጠየቅ ለመንዳት ያላቸውን ፍላጎት ማነቃቃት
- እጃቸውን መምህርን የሚያደርጉትን በማየትና የሚናገሩትን በማዳመጥ ከመምህር ጋር አብረው በቀስታ፣ በፍጥነት መንዳትና ማቆምን መለማመድ
- በመቀጠልም መምህር መኪና የሚነዳ ሰው መቼ በፍጥነት መንዳት እንደሚችል መቼ በቀስታ መንዳት እንዳለበት ከመንገድ አጠቃቀም ጋር በማዛመድ ለህፃናቱ ማስረዳት

- በመቀጠል መምህር የመኪና መንገድ ላይ ምንም አይነት እግረኛ የለም ስትል በፍጥነት መንዳት፣ መንገዱ ላይ እግረኛ ከሩቅ ይታያሉ ስትል በቀስታ መንዳት፣ እግረኛ መንገድ እያቋረጠ ነው ስትል በማቆም እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፦ ህጻናቱ እጃቸውን በታዘዙት መሠረት በፍጥነት፣ በቀስታ ማንቀሳቀስ እና እንቅስቃሴውን ማቆም መቻላቸውን በማየት ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 6. የቦታ ጽንሰ ሐሳብን መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም | 6.1. ሰዎችንና ነገሮችን መሰረት በማድረግ ቦታና ርቀትን መግለጽ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ፦ ላይ እና ታችን/ስርን/ መለየት

ዓላማ ፦ በታን ገላጭ ቃላት ላይ እና ታችን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተለያዩ ቁሳቁሶች፣ ደብተር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሕፃናትን በግማሽ ክብ ማስቀመጥ
- ከፊት ለፊታቸው ሁለት ጠረጴዛ በማቅረብ አንደኛው ጠረጴዛ ላይ በርካታ ቁሳቁሶችን ማድረግ በሌላኛው ላይ አንድ ደብተር ብቻ ማስቀመጥ
- መምህር ከቁሳቁሶቹ አንድ እቃ በማንሳት ጠረጴዛ ላይ በማስቀመጥ ምን እቃን ምን ላይ እንዳስቀመጡ ህጻናቱ በማየት እንዲናገሩ ማድረግ
- በመቀጠልም ህፃናቱን በየተራ እየጠሩ የተነገራቸውን ቁስ በታዘዙት ቦታ ላይ እንዲያስቀምጡ ማዘዝ ለምሳሌ፦ "አቤል እርሳሱን ከጠረጴዛው ታች/ስር/ አስቀምጥ" በማለት ማዘዝ
- ልክ መሆንና አለመሆኑን የት እንዳስቀመጡትም እንዲናገሩ በመጠየቅ ትኩረት ሰጥተው እንዲከታተሉ ማድረግ

ምዘና ፦ በታን ገላጭ ቃላትን ላይ እና ታች መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ ፊት እና ኋላን መለየት

ዓላማ ፡- ቦታን ገላጭ ፊት እና ኋላን ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ መጫወቻዎች፣ ወንበር፣ አሻንጉሊት፣ወዘተ....

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናት ከሚገኙበት ቦታ አንፃር የቁስን መገኛ እንዲናገሩ ከፊታቸው ምን እንዳለ ከኋላቸው ምን እንዳለ በመጠየቅ እንዲናገሩ ማለማመድ

  ለምሣሌ፡- ከፊት ምን አለ? /ጥቁር ሰሌዳ /

  ከኋላስ ማን አለ? /እነ ..........አሉ/ ወዘተ...

- ዕቃ ለእያንዳንዱ ልጅ በመስጠት ከፊታቸው ከኋላቸው እንዲያስቀምጡ ማዘዝ
- ከራሳቸው መገኛ አንፃር ቁሶች የሚገኙበትን ቦታ /አቀማመጥ/ እንዲያስተውሉ እና እንዲገነዘቡ ማድረግ

ምዘና ፡- ቦታን ገላጭ ቃላትን ፊት እና ኋላን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- "ፈልገህ አግኝ" ጨዋታን መጫወት

ዓላማ ፡- በጨዋታው ሂደት ቦታን ገላጭ ቃላትን ይጠቀማሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- አሻንጉሊት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የጨዋታውን ህግና ሂደት ህፃናቱ ሊረዱት በሚችሉት መልክ መግለፅ
- በየተራ ህጻናትን በመምረጥ ፊታቸው ወደግድግዳ አዙረው እንዲቆሙ በማድረግ አሻንጉሊቷን በተለያየ ቦታ በማስቀመጥ ፈልገው እንዲያገኙ ማድረግ
- ሲገኙም አሻንጉሊቷን የት እንዳገኟት በተሟላ አረፍተ ነገር እንዲናገሩ በማበረታታት ማጫወት

ምዘና ፡- የጨዋታውን ህግ አክብረው በተገቢው ሁኔታ መጫወታቸውን በማየትና በጨዋታው ሂደት ቦታን ገላጭ ቃላትን በተገቢው ሁኔታ መጠቀም መቻላቸውን በማዳመጥ መገምገም።

ተግባር አራት ፡- ወረቀቶችን ከቦታ አንጻር ማስተካከል

ዓላማ ፡- ወረቀቶችን በተለያየ አቅጣጫ ማጠፍ፣ መዘርጋትን፣ መጠምዘዝ፣ መወርወር ይችላሉ እንዲሁም በታንና አቅጣጫን ገላጭ ቃላቶችን በተግባር ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- አገልግሎት ላይ የዋሉ ባለቀለም ወረቀቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለእያንዳንዱ ህጻን አገልግሎት ላይ የዋሉ ባለቀለም ወረቀት በመስጠት ወደፊት ወደኋላ ማጣጠፍ፣ መዘርጋት፣ መጠምዘዝ እንዴት እንደሚሠራ ማሳየት
- ባዩት መሠረት እንዲሰሩ በማድረግ ወደፊት፣ ወደኋላ፣ ወደላይ፣ ወደታች የሚሉትን ቦታን ገላጭ ቃላቶች በተግባር እንዲለማመዱ ማድረግ

ምዘና ፡- ወረቀቶችን በተለያየ አቅጣጫ በማጣጠፍ፣ በመዘርጋት ወዘተ ከፊት፣ ከኋላ፣ ከላይ፣ከታች የሚሉትን ቦታንና አቅጣጫን ጠቋሚ ቃላቶችን በተግባር መረዳታቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 7. ገንዘብን መተዋወቅ መለየት መግለጽና መጠቀም | 7.1. ሣንቲምና ብርን ይለያሉ። |

ተግባር አንድ ፡- ሣንቲም እና ብርን መተዋወቅ

ዓላማ ፡- ሣንቲም እና ብርን ይተዋወቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ብር፣ ሣንቲሞች፣ ከካርቶን የተዘጋጁ የሣንቲም ምስሎች፣ በወረቀት ላይ ኮፒ የተደረገ ብር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-_

- የብር ኖቶችን እና ሳንቲሞችን በማሳየት ምን እንደሆኑ መጠየቅና የቱ ብር? የቱ ሣንቲም? እንደሆነ መጠየቅ
- የትኛው ሣንቲም፣ የትኛው ብር እንደሆነ በማሳየት ማስረዳት
- ስስ በሆነ ካርቶን በማስመሰል የተዘጋጁ የ 5፣የ 1 0፣የ 25፣የ 5 0 ሣንቲሞችን በየጠረጴዛ ላይ መስጠት
- ተመሳሳዮቹን በአንድ ላይ እያስቀመጡ እንዲጫወቱ ማድረግ

ምዘና ፡- ሣንቲም እና ብርን መለየታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- የብር ኖቶችን እና የሳንቲሞችን መገለጫ መናገር

ዓላማ ፡- የብር ኖቶችን እና የሳንቲሞችን መገለጫ ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ብር፣ ሣንቲሞች፣ ከካርቶን የተዘጋጁ የሣንቲም ምስሎች፣ በወረቀት ላይ ኮፒ የተደረገ ብር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ የብር ኖቶችን ፎቶ ኮፒ በማድረግ በእያንዳንዱ ብር ላይ የሚያዩትን ስእል እንዲናገሩ ማድረግ
- የብር ኖቶች በተሳለባቸው ስእል እንደሚለያዩ እንዲገነዘቡ ማድረግ
- ሳንቲሞቹ ክብ እንደሆኑና የማይቀደዱ፣ የማይሰበሩ እንደሆነ ብርን ግን በቀላሉ ሊቀደድ እንደሚችል እንዲረዱ ማድረግ
- ሰዎች ገንዘባቸውን እንዴት መያዝ እንዳለባቸውና የት ማስቀመጥ እንዳለባቸው የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና፡- የብር ኖቶችን እና ሳንቲሞችን መገለጫቸውን መናገር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት፡- የገንዘብ ጥቅምን መናገር

ዓላማ ፡- የገንዘብን ጥቅም ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ብር፣ ሣንቲሞች፣ ከካርቶን የተዘጋጁ የሣንቲም ምስሎች፣ በወረቀት ላይ ኮፒ የተደረገ ብር

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- "ብርና ሣንቲሞች ለምን ይጠቅማሉ? ምን ይደረግባቸዋል?" በማለት ማወያየት
- ቤተሰቦቻቸው ምን ምን እንደገዙላቸው መጠየቅ እና በምን እንደገዙላቸው እንዲናገሩ ማድረግ
- መልሳቸውን ካዳመጡ በኋላ ገንዘብ እነሱ የለበሱት ልብስ፣ ጫማ፣ ቦርሳቸው፣ ምግባቸው ሁሉ በገንዘብ እንደሚገዛ እንዲረዱ ማድረግ
- ሰዎች ገንዘብን ከየት እንደሚያመጡ በመጠየቅ ማወያየትና ገንዘብ የሚገኘው ስራ ሲሰራ መሆኑን እንዲረዱ ማድረግ
- ለመስሎ መጫወት ጨዋታ የተዘጋጁ የብር ኖቶችንና ሳንቲሞችን ለህፃናቱ በመስጠት ሱቅ ሱቅ ጨዋታ ላይ ገዢና ሻጭ በመሆን መጫወትን እንዲለማመዱ ማነቃቃትና ማበረታት

ምዘና ፡- የገንዘብ ጥቅምን መናገር መቻላቸውን መገምገም።

## **2.4.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም -------------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም ------------------------------------------ ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም -------------------------------------------- ዓመተ ምሕረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ ፡-

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ ---------------------------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት ----------------------------------------------------------

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት ------------------------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | የዓመቱ መጀመሪያ | የዓመቱ አጋማሽ | የዓመቱ መጨረሻ |
| 1. የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ | | | |
| 1.1. ስለመኖሪያ ቤታቸውና በቤታቸው ስላሉ ቀሳቁሶች መናገር ይችላሉ | | | |
| 1.2. በቤታቸውና በቅርብ አካባቢያቸው ያሉትን ሰዎች፣ እንስሳቶች፣ አትክልቶች፣ ቁሳቁሶችን ፣ ነፍሳቶችን ሌሎች ነገሮችን መለየት ይችላሉ | | | |
| 1.3.በቅ/መ/ት/ቤት የሚገኙትን ሰዎች መጫወቻዎችና ሌሎች ነገሮች መለየት ይችላሉ | | | |
| **2.** በአካባቢ የሚገኙትን አስፈላጊ ቦታዎች ማወቅና ማድነቅ | | | |
| 2.1. በአካባቢያቸው ስለሚገኙት አስፈላጊ ቦታዎች መናገር ይችላሉ | | | |
| | | | |
| **3.**አካባቢን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ማወቅና መንከባከብ | | | |
| 3.1 . ቤታቸውንና አካባቢያቸውን የማፅጃ መንገዶችን መጠቆም ይችላሉ | | | |
| **4.** በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየትና ጥንቃቄ መውሰድ | | | |
| 4.1. በአካባቢ ያሉ አደገኛ ነገሮችና ሁኔታዎችን መለየት ይችላሉ | | | |
| **5.** የእንቅስቃሴን ጽንሰ ሃሳብ መረዳትና ሙከራ ማካሄድ | | | |
| 5.1. በአካባቢ ስለሚገኙ ነገሮች እንቅስቃሴ መግለጽ ይችላሉ | | | |
| **6.** በስነ ስዕልና ቅርፃ ቅርጽ የተለያዩ ነገሮችን መፍጠር ማድነቅና ራስን መግለጽ | | | |
| 6.1. የዓይንና የእጆቻቸውን እንቅስቃሴ በማቀናጀት የተለያዩ ነገሮች መሥራትን ይለማመዳሉ | | | |

## 2.5 ከአካባቢ ጋር በሚፈጠር መስተጋብር አካባቢን ማጥናትና በአግባቡ ማጣጣም

### 2.5.1 ማብራሪያ

ከ 3-4 ዓመት ዕድሜ ክልል የሚገኙ ሕፃናትም ከስሜት ሕዋሳቶቻቸው በተጨማሪ ምልክትንና ቋንቋን በመጠቀም አካባቢያቸውን ማወቅና መረዳት አዳዲስ ጽንሰ ሃሳቦችን መተዋወቅ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ለሚከሰቱና በአካባቢያቸው ስላሉ ነገሮች ባህሪ መረዳት የነገሮችን መንስኤ መፈለግ የሚጀምሩበት ዕድሜ ነው።

አካባቢን የማጥናት፣ የመፈተሽና የመረዳት ክህሎት በአንድ ጊዜ የሚከናወን ተግባር ሳይሆን ሕፃናት ከተወለዱበት ጊዜ ጀምሮ የስሜት ሕዋሳቶቻቸውን በመጠቀም ያከናውናሉ።

በመሆኑም ይህንን ሕፃናት የሚኖሩበትን ዓለም የማወቅ ከፍተኛ ጉጉታቸውንና ተነሳሺነታቸውን በመረዳት ደረጃቸው በሚፈቅድ መጠን በአካባቢያቸው ስላሉ ተጨባጭ ሁኔታዎችና ነገሮች በማሳየትና በማስረዳት አካባቢያቸውን እንዲያውቁ በማድረግ፣ አካባቢያቸውን አስተውለው እንዲመለከቱና እንዲፈትሹ ምቹ አካባቢን በመፍጠርና ዕድሉን መስጠት፣ እንዲሁም ለሚጠይቁት ጥያቄ ሳይሰላቹ በወቅቱ ተገቢውን ምላሽ መስጠትና አስፈላጊውን ሁሉ ድጋፍ በማድረግ አካባቢያቸውን አስተውለው እንዲመለከቱ እንዲፈትሹና እንዲያውቁ ማድረግ ያስፈልጋል።

### 2.5.2 አጠቃላይ ዓላማዎች

1. በቅርብ አካባቢያቸው ስለሚገኙ ሰዎች፣ ቁሳቁሶች፣ እንስሳቶች፣ አትክልቶች፣ ነፍሳቶች፣ ወዘተ... መጠነኛ ግንዛቤ እንዲኖራቸው ለማድረግ
2. በአካባቢያቸው የሚገኙ አስፈላጊ ቦታዎችን መጠሪያ ስምና የሚሰጡትን አገልግሎት በደረጃቸው እንዲገነዘቡ ለማድረግ
3. ቤታቸውንና አካባቢያቸውን በንጽህና የመያዝ ዝንባሌን እንዲያዳብሩ በአካባቢያቸው ያሉ አደገኛ ነገሮችንና ሁኔታዎችን በመገንዘብ በአቅማቸው ራሳቸውን ከአደጋ እንዲጠብቁ ለማድረግ

4. የፈጠራ ችሎታቸውን በመጠቀም የተለያዩ ነገሮችን የመስራት ዝንባሌን እንዲያዳብሩና በደረጃቸው የተለያዩ ሙከራዎችን በማከናወን የነገሮችን ባህሪ እንዲረዱ ለማድረግ

### 2.5.3 የሚጠበቁ ውጤቶችና ብቃቶች

1. የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ
    1.1. ስለመኖሪያ ቤታቸውና በቤታቸው ስላሉ ቀሳቁሶች መናገር ይችላሉ
    1.2. በቤታቸውና በቅርብ አካባቢያቸው ያሉትን ሰዎች፣ እንሰሳቶች፣ አትክልቶች፣ ቁሳቁሶችን፣ ነፍሳቶችን ሌሎች ነገሮችን መለየት ይችላሉ
    1.3. በቅ/መ/ት/ቤት የሚገኙትን ሰዎች መጫወቻዎችና ሌሎች ነገሮች መለየት ይችላሉ
2. በአካባቢ የሚገኙትን አስፈላጊ ቦታዎች ማወቅና ማድነቅ
    2.1. በአካባቢያቸው ስለሚገኙት አስፈላጊ ቦታዎች መናገር ይችላሉ
3. አካባቢን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ማወቅና መንከባከብ
    3.1. ቤታቸውንና አካባቢያቸውን የማፅጃ መንገዶችን መጠቀም ይችላሉ
4. በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየትና ጥንቃቄ መውሰድ
    4.1. በአካባቢ ያሉ አደገኛ ነገሮችና ሁኔታዎችን መለየት ይችላሉ
5. የእንቅስቃሴን ጽንሰ ሃሳብ መረዳትና ሙከራ ማካሄድ
    5.1. በአካባቢ ስለሚገኙ ነገሮች እንቅስቃሴ መግለጽ ይችላሉ
6. በስነ ሥዕልና ቅርፃ ቅርጽ የተለያዩ ነገሮችን መፍጠር ማድነቅና ራስን መግለጽ
    6.1. የዓይንና የእጆቻቸውን እንቅስቃሴ በማቀናጀት የተለያዩ ነገሮች መስራትን ይለማመዳሉ

2.5.4 የሚጠበቁ ውጤቶች፣ ብቃቶች፣ የመርጃ መሣሪያዎችና የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1. የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ | 1.1. ስለመኖሪያ ቤታቸውና በቤታቸው ስላሉ ቁሳቁሶች መናገር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ፡ - የመኖሪያ ቤት አይነቶችን መለየት

ዓላማ ፡- የተለያዩ የቤት አይነቶችን መጠሪያ ስም ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ቤቶች ስዕሎች፣ የእርሳስ ከለሮች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ የመኖሪያ ቤት ስዕሎችን ለህፃናት እይታ አመቺ ቦታ ላይ መለጠፍ

  ለምሳሌ፡- ጐጆ ቤት፣ ቪላ ቤት፣ ፎቅ ቤት፣ ኮንዲሚኒየም
- እያንዳንዱን ስእሎች በመጠቆም ምን እንደሆኑና ማን እንደሚኖርበት በመጠየቅ ማወያየት
- የትኞቹ ቤቶች ከላይ ሰው መኖር እንደሚችል የትኞቹ ከላይ ሰው የማይኖርባቸው እንደሆኑ መጠየቅ
- የሕፃናቱን መልስ ካዳመጡ በኋላ ቤቶቹ በቅርፃቸውም እንደሚለያዩ በመግለፅ ጎጆ ቤትና ቪላ ቤት ከላይ ሰው የሚኖርባቸው አለመሆኑን፣ ፎቅ ቤትና ኮንዲሚኒየም ግን ከላይ ሰው እንደሚኖርባቸው ማለትም መኖሪያ ቤቶች ወይም ክፍሎች እንዳሉት በሚገባቸው መንገድ መግለፅ

ምዘና ፡- የተለያዩ የቤት አይነቶች በመጠሪያ ስማቸውና በቅርፃቸው መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- የመኖሪያ ቤቶችን ማድመቅና ቀለም መቀባት

ዓላማ ፡- የመኖሪያ ቤቶችን ማድመቅና ከመስመር ሳይወጡ መቀባትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በወረቀት ላይ በነጠብጣብ የተሳሉ ቤቶች፣ መሠረታዊ ቀለማት ያላቸው ባለቀለም እርሳሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በነጠብጣብ የተሳሉ ስእሎችን በማሳየት እንዴት ነጠብጣቡን ተከትሎ ማድመቅና ቀለም መቀባት እንደሚቻል ማሳየት
- ለህጻናቱም አንድ አንድ በነጠብጣብ የተሳለ ስእል በመስጠት ባዩት መሠረት እንዲያደምቁና የፈለጉትን ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- ሲጨርሱም ምንን እንዳደመቁና ምን አይነት ቀለም እንደቀቡ ለጓደኞቻቸው እንዲያሳዩ ማበረታታት
- በመጨረሻም በእያንዳንዱ ህጻን ወረቀት ስር ስሙን በመፃፍ ለእይታ አመቺ ቦታ በመለጠፍ ሁሉም ህፃናት እንዲመለከቱት ማድረግ

ምዘና ፡- የተለያየ ቅርጽ ያላቸውን የቤት አይነቶች አድምቀው ከመስመር ሳይወጡ መቀባታቸውንና የቤቱን ዓይነት ለይተው መናገራቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- ቤቴ ቤቴ በምን ያማረ ነው መዝሙርን መዘመር

ዓላማ ፡- የቤትን ዋና ዋና ገፅታዎች ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በካርቶን የተሰራ ቤት፣ የመዝሙር ካሴት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በካርቶን የተሰራ የቤት ናሙናን ማሳየት
- የቤቱ ግርግዳ፣ ወለል እና ጣሪያው ምን አይነት ቀለም እንደተቀባ በመጠቆም ማሳየት
- "ቤቴ ቤቴ በምን ያማረ ነው?" የሚለውን መዝሙር ድምፅን ከፍ አድርጎ መዘመር
- መምህር ስንኙን በመዘመር ሕፃናቱ ከመምህር ኋላ እንዲዘምሩ ማድረግ
- ከተለማመዱ በኋላ ከመምህር ጋር በህብረት መዘመር
- በሚዘምሩበት ጊዜ በትክክል የቤቱን ጣሪያ ግርግዳ፣ ወለል ወዘተ ማሳየት፡

ምዘና ፡- መዝሙር ሲዘምሩ የቤት ዋና ዋና ገፅታዎችን መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- የመኖሪያ ቤት ክፍሎችንና በውስጡ የሚገኙ ቁሶችን መለየት

ዓላማ ፡- የመኖሪያ ቤት ክፍሎች እና በውስጣቸው ያሉ ቁሶችን ይለያሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የቤት ክፍሎችን የሚያሳይ ስዕል፣ በቤት ውስጥ የሚገኙ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የቤት ክፍሎችን የሚያሳዩ ስዕሎችን ማሳየት
- በክፍሉ ውስጥ የሚገኙትን ቁሳቁሶች በማየት ምን እንደሆኑ እንዲናገሩ ዕድሉን መስጠት

- በመቀጠልም በቤት ውስጥ ስለሚገኙ የተለያዩ ክፍሎች፣በውስጣቸው ስለሚገኙ ቁሳቁሶችና ጥቅማቸውን በመጠየቅ ማወያየት

  ለምሳሌ፡- መኝታ ቤት፣ እንግዳ ማረፊያ /ሳሎን/፣ ማድቤት

- ቁሳቁሶቹ በየትኛው የመኖሪያ ክፍል ውስጥ እንደሚገኙ ምርጫ በመስጠትና በመጠየቅ ቁሳቁሶቹ የሚገኙበትን ክፍል እንዲለዩ ማድረግ

  ለምሣሌ፡- አልጋ የሚገኘው በመኝታ ክፍላችን ውስጥ ነው ወይስ በምግብ ማብሰያ ክፍል? ወዘተ...

ምዘና ፡- የመኖሪያ ቤት ክፍሎች እና በውስጣቸው ያሉ ቁሶችን መለየታቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

### ተግባር አምስት ፡- የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶችን ጥቅም መናገር

ዓላማ ፡- የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሳቁሶችን በስም በመጥራት ጥቅማቸውን ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ መገልገያ ቁሶች ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በቤት ውስጥ የሚገኙ ዕቃዎችን በስዕል ማሳየት
- ስማቸውን እንዲናገሩና ለምን አገልግሎት እንደሚውሉ መጠየቅ
- ለእያንዳንዱ ህፃን የቤት ቁሳቁስ ስእልን በመስጠት ምን እንደሆነና ለምን አገልግሎት እንደሚጠቅም እንዲናገር ማበረታታት
- ህፃኑ ትክክል መሆንና አለመሆኑን ሌሎች ህፃናትን በመጠየቅ ትኩረት እንዲሰጡ ማድረግ

ምዘና ፡- በመኖሪያ ቤት የሚገኙ ቁሶችን በስም መጥራትና ጥቅማቸውን መናገር መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

### ተግባር ስድስት ፡- የመኖሪያ ቤትን መገንባት

ዓላማ ፡- የግንባታ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የመኖሪያ ቤትን አስመስለው ይገነባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የግንባታ መጫወቻ መሣሪያዎች፣ የቀለም ሰሌዳዎች፣ አሻንጉሊት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በእነሱ ተወዳጅ የሆነችው አሻንጉሊት የክፍሉ ሕፃናት አዲስ ቤት እንዲሰሩላት እንደፈለገች በማስመሰል በግንባታ መሣሪያዎች ቤት የመሥራት ፍላጐታቸውን ማነሳሳት
- በበቂ ሁኔታ የግንባታ መጫወቻ መሣሪያዎችን መስጠት
- ለአሻንጉሊቷ ቤት እንዲሰሩላት ማድረግ
- በሚሰሩበት ጊዜ መምህር አሻንጉሊቷን በመያዝ እየተዘዋወሩ የሕፃናቱን ስራ አሻንጉሊቷ እንደወደደችው በመንገር ማበረታታት

ምዘና ፡- የግንባታ ቁሳቁሶችን በመጠቀም የመኖሪያ ቤትን መገንባት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 1.የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ | 1.1. በቤታቸውና በቅርብ አካባቢያቸው ያሉትን ሰዎች፣ እንስሳቶች፣ አትክልቶች፣ ቁሳቁሶች፣ ነፍሳቶችና ሌሎች ነገሮች መለየት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- አብረዋቸው የሚኖሩ ሰዎችን መለየት

ዓላማ ፡- በቤታቸው አብረዋቸው የሚኖሩ ሰዎች በስም ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ሁለት የሶፍት ካርቶንዎች፣ ባለቀለም ወረቀት

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሁለት የሶፍት ካርቶኖችን በባለቀለም ወረቀት ወይም ባለቀለም ወረቀት በመሸፈን እንደ ድምጽ ማጉያ መጠቀም
- በመጀመሪያ መምህር በቤት ውስጥ ከማን ጋር እንደሚኖሩ እና አብረዋቸው የሚኖሩትን ሰዎች ስም በመናገር ማስተዋወቅ
- ፈቃደኛ የሆነ አንድ ሕፃን በማስነሳት አንዱን የድምጽ ማጉያ መስጠት
- ከዚያም የተለያዩ ጥያቄዎችን መጠየቅ

ለምሣሌ፡- «እናንተ ቤት ማን ማን ይኖራል? እከሌ ምንህ ነው? ምንህ ናት?» ወዘተ...

- ሲጨርስም ሕፃኑን በማመስገን ወደ ቦታ እንዲመለስ ማድረግ
- ሕፃኑ/ የተናገረውን ጠቅለል አድርጎ በመናገር ለተረኛ ሕፃን ዕድሉን መስጠት

ማስታወሻ፡- ሁሉም ሕፃናት ወጥተው እንዲናገሩ ዕድሉን መስጠትና ማበረታታት ያስፈልጋል።

ምዘና ፦ በቤታቸው አብረዋቸው የሚኖሩ ሰዎችን በስም መጥራት መቻላቸዉን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ ሰዎችን በፆታና በእድሜ በመለየት መመደብ

ዓላማ ፦ ስእሎችን በማየት ሰዎችን በፆታና በእድሜ በመለየት ይመድባሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የሴት፣ የወንድ፣ የህፃን፣ የአዋቂ ሰዎችን የያዙ ፍላሽ ካርዶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- መምህር ከህፃናቱ ፊት በመቆም የሴትና የወንድ ስእልን በማሳየት የትኛው ወንድ፣ የትኛዋ ሴት፣ የትኛው አዋቂ/ትልቅ ሰው፣ የትኛው ህፃን እንደሆነ በመጠየቅ ማነቃቃት
- መምህር ከእነሱ መካከል ሴቶች የሆኑ እጃቸውን እንዲያወጡ፣ ቀጥሎም ወንዶች፣ በመቀጠልም ህጻናት የሆኑ እንዲያወጡና አዋቂ ሲባል መምህርና በክፍል ውስጥ ያሉ መምህራንና ሞግዚትም እንዲያወጡ በማድረግ ማጠናከር
- ለእያንዳንዱ ህፃን አንድ አንድ ካርዶችን በመስጠት መምህር ህጻን ስትል ህጻን ልጅ ካርድ የያዘ መምህር ጋ መጥቶ እንዲቆምና በህብረት የምን ስእል እንደሆነ እንዲናገሩ ማድረግ
- በዚህ አይነት መልኩ ሁሉም ህጻናት የያዙት ካርድን የሚወክል የጋራ መጠሪያ ስም ሲጠራ መምህርጋ መጥተው እንዲቆሙ በማድረግ ሰዎችን በፆታና በእድሜ እንዲለዩ ማድረግ

ምዘና ፦ ሰዎችን በፆታና በእድሜ መለየት መቻላቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፦ የቤት እንስሳትን መለየት

ዓላማ ፡- በቤታቸው አካባቢ የሚኖሩ የቤት እንስሳትን በአኗኗራቸው፣ በጥቅማቸውና በአመጋገባቸው ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የውሻ፣ የድመትና የዶሮ ስዕሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ የቤት እንስሳትን ምስል ማሳየት
- ምን እንደሆኑ፣ የት እንደሚኖሩ፣ ምን እንደሚመገቡና ለምን እንደሚጠቅሙ የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ እንዲረዱ ማድረግ
- የተዋወቋቸውን እንስሳት ድምጽ አስመስሎ ማውጣትና የየትኛው እንስሳ ድምጽ እንደሆነ መጠየቅ
- በወረቀት ላይ የተሳሉ የቤት እንስሳት ስዕሎችን በመስጠት ምን እንደሆነና እንዴት ዓይነት ድምጽ እንዳለው በመጠየቅ ለተጠየቁት ምላሽ እንዲሰጡ ማበረታታት

ምዘና ፡- በቤታቸው አካባቢ የሚኖሩ የቤት እንስሳትን በአኗኗራቸው፣ በጥቅማቸውና በአመጋገባቸው መለየታቸውን በማዳመጥ ማረጋገጥ።

**ተግባር አራት ፡- የቤት እንስሳትን ቀለም መቀባት**

ዓላማ ፡- የቤት እንስሳትን ቀለም በመቀባት የቀቡትን እንስሳና ቀለሙን ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የድመት፣ የውሻና የዶሮ ስዕሎች፣ ባለቀለም እርሳስ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለእያንዳንዱ ልጅ አንዳንድ የቤት እንስሳትን ስዕል በመስጠት የመረጡትን ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- ቀብተው ሲጨርሱ የቀቡት ምን እንደሆነና ምን አይነት ቀለም እንደቀቡት እንዲናገሩ ማበረታታት
- ከከበዳቸው አስፈላጊውን ድጋፍ ማድረግ

ምዘና ፡- የቤት እንስሳትን ቀለም መቀባታቸውንና የቀቡትን እንስሳና ቀለሙን መናገራቸውን በማየትና በማዳመጥ ማረጋገጥ።

**ተግባር አምስት ፡- የጓሮ አትክልቶችን መለየት**

ዓላማ ፦ የሚመገቧቸውን የጓሮ አትክልቶች በስማቸው እና በቅርፃቸው ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ የጓሮ አትክልቶች/ ሽንኩርት፣ ቃሪያ፣ ቲማቲም፣ ጎመን፣ድንች፣ ካሮት/ እና ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሕፃናት በሚኖሩበት አካባቢ ሊገኙ የሚችሉት አዘውትረው ለምግብነት የሚጠቀሟቸውን የተለያዩ የጓሮ አትክልቶችን እንደ ጐመን፣ድንች፣ ካሮት፣ ቃሪያ፣ ቀይ ሽንኩርት ወዘተ... የመሳሰሉትን በክፍል ውስጥ በማምጣት ማሳየት
- ምን እንደሆኑና በልተው ያውቁ እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- ለእያንዳንዱ ልጅ የጓሮ አትክልቶችን ስዕል መስጠት
- ለክፍል ጓደኞቹ በማሳየት መጠሪያ ስሙን እንዲናገር ማበረታታት

| |
|---|
| ማስታወሻ ፦ የጓሮ አትክልቶቹን በሙሉ በአንድ ክ/ጊዜ ሳይሆን በተለያየ ክ/ጊዜ ማስተዋወቅ ያስፈልጋል። |

ምዘና ፦ የሚመገቧቸውን የጓሮ አትክለቶች በስማቸው እና በቅርፃቸው መለየት መቻላቸውን መገምገም።

## ተግባር ስድስት ፦ ፍራፍሬዎችን መለየት

ዓላማ ፦ ፍራፍሬዎቹን በቅርጽ፣ በጣዕም እና በቀለም ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ፍራፍሬዎች/ብርቱካን፣ ሙዝ፣ ሎሚ/፣ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሕፃናት ሊያገኟቸውና ሊመገቧቸው የሚችሉትን የተለያዩ ፍራፍሬዎች ከተቻለ በክፍሉ ውስጥ በማምጣት ካልተቻለ ስዕሉን ማሳየት ምን እንደሆነ ፣ምን ዓይነት ቀለም እንዳለው፣ በውስጡ ፍሬ መኖር አለመኖሩን፣ ተልጦ መበላት አለመበላቱን፣ ሲበላ መጣፈጥ አለመጣፈጡን በመጠየቅ ማወያየት
- ለእያንዳንዱ ህጻን የፍራፍሬዎችን ስእል በመስጠት የፍራፍሬውን ስም ሲናገሩ ያንን ስእል የያዘ ህፃን ከፍ አድርጎ እንዲያሳይ በማድረግ ፍራፍሬውን በስም እንዲለዩ ማድረግ
- በመቀጠልም እንቆቅልሽ በማጫወት ማጠናከር

ለምሳሌ፡-

እኔ ከፍራፍሬዎች ዘር አንዱ ነኝ

ቀለሜ ቢጫም፣አረንጓዴም ነው

ስበላ እኮመጥጣለሁ፣ አልጣፍጥም

እኔ ማነኝ በማለት በመጠየቅ ማጠናከር

ምዘና ፡- የሚበሉ ፍራፍሬዎችን በቅርጽ፣ በጣዕም እና በቀለም መለየታቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ሰባት ፡- የጓሮ አትክልቶችንና ፍራፍሬዎችን በማሽተት መለየት

ዓላማ ፡- የጓሮ አትክልቶችን ሳያዩ በማሽተት ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ የጓሮ አትክልቶች፣ ፍራፍሬዎች፣ የጓሮ አትክልትና የፍራፍሬዎች ስዕል፣ ዓይን መሸፈኛ ጨርቅ፣

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- “አሽትተህ ዕወቅ” ጨዋታን በሚከተለው መንገድ ማጫወት
- ቃሪያ ፣ ነጭ ሽንኩርት፣ ብርቱካን፣ ሎሚ፣ ሙዝን ለሕፃናቱ ማሳየት እና ምን እንደሆነ መጠየቅ
- አንድ ሕፃን በማስነሳት ከሕፃናቱ ፊት እንዲቆም/እንድትቆም ማድረግ
- በመቀጠልም ዓይኑን/ዓይኗን በጨርቅ ላላ አድርጐ ማሰር
- ወደ አፍንጫው/ዋ አንዱን ፍራፍሬ ወይም የጓሮ አትክልት ቀረብ በማድረግ እንዲያሸተውና ምን እንደሆነ እንዲናገር በመጠየቅ ማበረታታት
- በዚህ መልኩ ሁለም ሕፃናት በጨዋታው ተሳታፊ እንዲሆኑ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- ቃሪያ በእጃቸው ነክተው ዓይናቸውን እንዳይነኩና እንዳያቃጥላቸው ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- የጓሮ አትክልቶችን በማሽተት መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር ስምንት ፡- ነፍሳቶችን መለየት**

ዓላማ ፡- ነፍሳቶችን በስማቸውና በመልካቸው ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የደረቁ ነፍሳቶች/ ዝንብ፣ ጉንዳን፣ ሸረሪት፣ ቢራቢሮ/፣ ስእሎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- መጀመሪያ የደረቁትን ነፍሳቶች በማሳየት ምን እንደሆኑና አይተዋቸው ያውቁ እንደሆነና የት እንዳያቸው በመጠየቅ ማወያየት
- ለህጻናቱ አንድ አንድ ስእል በመስጠት መምህር የነፍሳቱን ስም ሲጠሩ ስእሉን የያዘ ህፃን ከፍ አድርጎ እንዲያሳይ በማድረግ ነፍሳቶቹን በስምና በመልካቸው እንዲለዩ ማድረግ

> ማስታወሻ ፡- ሕፃናት በግቢ ውስጥ ጉብኝት እንዲያደርጉና ግቢ ውስጥ ያሉትን ነፍሳቶችን እንዲመለከቱ ማድረግና የሚያዩዋቸውን ነፍሳቶች መጠሪያ ስም እንዲናገሩ ማበረታታት።

ምዘና ፡- ነፍሳቶችን በስማቸውና በመልካቸው መለየታቸውን በማየትና በማዳመጥ መገምገም።

**ተግባር ዘጠኝ ፡- መዝሙር መዘመር መለማመድ**

ዓላማ ፡- ቢራቢሮን ሳያት መዝሙር ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት መዘመርን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በትልቁና በደማቅ ቀለም የተሳለ የቢራቢሮ ስእል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- የቢራቢሮን ስእል በማሳየት ምን እንደሆነች? ምን አይነት ቀለም እንዳላት? እንዴት እንደምትንቀሳቀስ በመጠየቅ ማነቃቃት

- ህፃናቱ ስለምታምረው ውቧ ቢራቢሮ የተዘመረላትን መዝሙር ያውቁት እንደሆነና ለመዘመር ፍላጎት እንዳላቸው በመጠየቅ ማነቃቃት
- መዝሙሩን ረጋ ብሎ ድምጽን ከፍ በማድረግና በአካላዊ እንቅስቃሴ በመታጀብ መዘመር
- ከመምህር በኋላ እያንዳንዱን የመዝሙሩን ስንኝ ዜማውን ጠብቀው እንዲዘምሩ ማለማመድ
- ከመምህር ጋር መዝሙሩን አብረው በመዘመር መለማመድ

ምዘና ፦ ህጻናቱ የመዝሙሩን ዜማ ጠብቀውና አካላዊ እንቅስቃሴን ተጠቅመው ለመዘመር መሞከራቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር አስር ፦ መዝሙር መዘመር መለማመድ

ዓላማ ፦ ቀስ በቀስ ሸረሪቷ መዝሙርን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት መዘመርን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ በትልቁና ጠቆር ባለ እርሳስ ቀለም የተሳለ የሸረሪት ስእል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የሸረሪትን ስእል በማሳየት ምን እንደሆነች እና የት አይተዋት እንደሚያውቁ በመጠየቅ ማነቃቃት
- ስለ ሸረሪቷ የተዘመረውን መዝሙር ያውቁ እንደሆነና እንደማያውቁ በመጠየቅ መዝሙሩን ለማዳመጥ ያላቸውን ፍላጎት መቀስቀስ
- የሸረሪቷን ታሪክ በሚከተለው መንገድ አጠር አድርጎ መግለፅ፦
  ከእለታት አንድ ቀን አንድ ሸረሪት ነበረች፣ በግርግዳ ላይ ቀስ ብላ ወደላይ መውጣት ፈልጋ ስትወጣ ሀይለኛ ንፋስ መጣና አወዛወዛት። ከዛ ደግሞ ሀይለኛ ዝናብ ሲዘንብ ወደታች ጣላት በማለት መንገር
- መዝሙሩን ረጋ ብሎ ድምጽን ከፍ በማድረግና በአካላዊ እንቅስቃሴ በመታጀብ መዘመር
- ከመምህር በኋላ እያንዳንዱን የመዝሙሩን ስንኝ ዜማውን ጠብቀው እንዲዘምሩ ማለማመድ
- በመቀጠልም ከመምህር ጋር መዝሙሩን አብረው በመዘመር እንዲለማመዱ ማድረግ

ማስታወሻ፦ ከመምህር ጋር መዝሙሩን አብረው ሲዘምሩ ተገቢውን አካላዊ እንቅስቃሴ እንዲጠቀሙ ማበረታታት።

ምዘና ፦ መዝሙርን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት መዘመር መሞከራቸውን በማየትና በማዳመጥ ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|

| | |
|---|---|
| 1. የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ | 1.3. በቅ/መ/ት/ቤት የሚገኙትን ሰዎች፣ መጫወቻዎችና ሌሎች ነገሮች መለየት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፦ አጸደ ህፃናታቸውን. መማሪያ ክፍላቸውን መለየት

ዓላማ ፦ የሚማሩበትን አፀደ ህፃናትና መማሪያ ክፍላቸውን በስምና በማየት ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ክፍላቸው በር ላይ የተለጠፈውን መለያ ምልክት ስእል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ህፃናቱ የሚማሩበት አጸደ ህጻናት ስም ያውቁ እንደሆነ በመጠየቅ ማነቃቃት
- መልሳቸውን ካዳመጡ በኋላ የአፀደ ህፃናቸውን ስም መንገርና በህብረት መልስው እንዲናገሩ ማድረግ
- የተሳሳተ ስም በመጠቀም አፀደ ህፃናታችን ስሙ እንደዚህ ነው በማለት በመጠየቅ ስሙን ማስታወስና አለማስታወሳቸውን ማረጋገጥ
- ሁሉም ህፃናት አንድ ክፍል እንደሚማሩና እንደማይማሩ በመጠየቅ ሁሉም ልጆች በተለያየ ክፍል እንደሚማሩና ሲጫወቱ ግን አንድ ላይ እንደሚጫወቱ መንገር
- የእነሱ ክፍል በር ላይ ምን ምልክት እንዳለ በመጠየቅ መልሳቸውን ካዳመጡ በኋላ በራቸው ላይ የተለጠፈውን ወይም የተሳለውን ስእል የሚመስለውን ስእል በማሳየት እንዲለዩት ማድረግ
- ይህንንም ለማረጋገጥ በሩን በመክፈት ስእሉን እንዲያዩ ማድረግ

ምዘና ፦ የሚማሩበትን አፀደ ህፃናትና መማሪያ ክፍላቸውን በስምና በማየት መለየት መቻላቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፦ በቅርብ አካባቢያቸው የሚገኙ ሰዎችን በስም እና በመልክ መለየት

ዓላማ ፦ በቅርብ አካባቢያቸው የሚገኙ ሰዎችን በስም እና በመልክ ይለያሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- መምህር ከሕፃናቱ ሞግዚት ጋር ከሕፃናት ፊት ለፊት በመቆም
- “እኔ ማነኝ ?”፣ “ስሜ ማነው?” በማለት መጠየቅና ካላወቁ መንገር
- አብራ የቆመችውን ሞግዚት ስም በመጠየቅ እንዲናገሩ ማድረግና ካላወቁ መንገር
- አንድ ሕፃን በመጋበዝ ከሕፃናቱ ፊት እንዲቆም/እንድትቆም ማድረግ
- መምህር በስም የምትጠራውን ሕፃን ስም የት እንደሚገኝ በጣቱ በመጠቆም እንዲያሳይ ማድረግ

- በዚህ ዓይነት ሁሉም ሕፃናት እንዲሳተፉ ማድረግ

ምዘና ፡- በቅርብ አካባቢያቸው የሚገኙ ሰዎችን መጠሪያ ስም እና መልክ ማወቅ መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፦ በክፍል ውስጥ ያሉ ህፃናትን በስምና በመልክ መለየት

ዓላማ ፦ በክፍላቸው ውስጥ ያሉትን ህፃናት በስምና በመልክ ይለያሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ትናንሽ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- አንድ ፈቃደኛ ሕፃን በመምረጥ ከሕፃናት ፊት ወጥቶ/ወጥታ እንዲቆም/እንድትቆም ማድረግ
- ከጠረጴዛው ላይ አንድ ዕቃ በማንሳት "ይሄን ለእከሌ ስጥ/ስጪ" በማለት ማዘዝ
- ዕቃውን ለተባለው/ለተባለችው ልጅ ከሰጠ ለምን እንደሰጠ በመጠየቅ እንዲናገር ማበረታታት
- የተሰጠው/ጣት ልጅ ደግሞ ሌላ ዕቃ ለሌላ ልጅ እንዲሰጥ/ትሰጥ ማድረግ
- በሂደት ሁለት ዕቃን ለሁለት ልጆች እንዲሰጡ ማዘዝ
- በዚህም አብረዋቸው የሚውሉትን ሕፃናት በመልክና በስም እንዲለዩ ማድረግ

ምዘና ፦ በክፍላቸው ውስጥ ያሉትን ህፃናት በስም እና በመልክ መለየታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፦ ጓደኞቻቸውን በመልክ መለየት

ዓላማ ፡- አብረዋቸው የሚማሩ ህፃናትን በመልክ ይለያሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- "ማን ተቀየረ" የሚለውን ጨዋታ በሚከተለው መንገድ ማጫወት
- ሶስት ሕፃናትን ከህፃናት ፊት ወጥተው እንዲቆሙ ማድረግ
- ከመካከላቸው አንዱን/ዷን አጫዋች በማድረግ የሁለቱን ሕፃናት ስም እንዲናገር መጠየቅ
- አጫዋቹ ፊቱን ወደ ግርግዳ እንዲያዞር ማድረግ
- ከሁለቱ ተጫዋቾች አንዱን ወደ ቦታው ሄዶ እንዲቀመጥ እና በእሱ ቦታ ሌላ ልጅ እንዲገባ ማድረግ
- አጭዋቹ ፊቱን ወደ ልጆቹ በማዞር ማን በማን እንደተቀየረ እንዲናገር ማድረግ
- በዚህ ዓይነት ሁኔታ ሁሉም ህፃናትን በጨዋታው ማሳተፍ

ምዘና ፡- አብረዋቸው የሚማሩ ህፃናትን በመልክ መለየታቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፡- መጫወቻዎችን መጠቀም እና በአግባቡ ማስቀመጥን መለማመድ

ዓላማ ፡- መጫወቻዎችን መጠቀም እና በአግባቡ ማስቀመጥ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የክፍል ውስጥ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናት በክፍል ውስጥ ባሉ መጫወቻዎች እንዲጫወቱበት ማድረግ
- ሲጨርሱም የተጫወቱበትን መጫወቻ ወደ ቦታው እንዲመልሱ ማድረግ
- በጨዋታው ሂደት ላይ ምን እየተጫወቱ እንደሆነና የሚጫወቱት በምን እንደሆነ በመጠየቅ ማነቃቃት፣ ካላወቁት መንገር ፍንጭ በመስጠት እንዲናገሩ ማበረታታት

ምዘና ፡- በምን እንደተጫወቱ ማወቃቸውን እና በአግባቡ ማስቀመጥ መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር ስድስት ፡- በውጭ መጫወቻዎች መጫወት

ዓላማ ፡- የተጫወቱበትን መጫወቻና ከማን ጋር እንደተጫወቱ ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ ትናንሽ ቁሳቁሶች፣ በግቢ ውስጥ ያሉ መጫወቻዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናት በግቢ ውስጥ ባሉ መጫወቻዎች እንዲጫወቱ ማድረግ
- ከጨዋታውም በኋላ ወደ ክፍል ሲገቡ ማን ምን እንደተጫወተ እና በምን እንደተጫወተ መጠየቅ
- የጨዋታውን መጠሪያ፣ የመጫወቻውን ስም በመጥራት ሕፃናቱ የተጫወቱትን ጨዋታ እንዲለዩ ማድረግ

ምዘና ፡- ምን፣ በምን እና እንዴት እንደተጫወቱ መናገር መቻላቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|

| | |
|---|---|
| 1. በአካባቢ የሚገኙ አስፈላጊ ቦታዎች ማወቅና ማድነቅ | 2.1. በአካባቢያቸው ስለሚገኙት አስፈላጊ ቦታዎች መናገር ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- በአካባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን መለየት

ዓላማ ፡- ሕፃናቱ በአካባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን በስማቸውና በሚሰጡት አገልግሎት ይለያሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- የተለያዩ አገልግሎት ሰጪ ቦታዎች ስዕል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በሕፃናቱ መኖሪያ አካባቢ የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን /ሱቅ፣ ት/ቤት፣ ሐኪም ቤት፣ ቤተክርስትያን፣ መስጊድ፣ ፖሊስ ጣቢያ/ ስዕል ለሕፃናቱ ማሳየት
- በስዕሉ ላይ ያዩትን ተቋማት ወይም አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን መጠሪያ ስም እንዲናገሩ ማበረታታት
- ወደእነዚህ ቦታዎች ሄደው ያውቁ እንደሆነና ከማን ጋር እና ለምን እንደሄዱ በመጠየቅ ማወያየት
- የተለያዩ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የእነዚህን አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን መጠሪያ ስም እና አገልግሎት በደረጃቸው እንዲገነዘቡ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- እነዚህን የአገልግሎት ሰጪ ቦታዎች በአንድ ክ/ጊዜ ለሕፃናቱ ማስተዋወቅ ከባድ ስለሚሆን በተለያየ ክፍለ ጊዜ ማስተዋወቅ ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- በአካባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን በስማቸውና በአገልግሎታቸው መለየት መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- የመስሎ መጫወት ጨዋታ መጫወት

ዓላማ ፡- በመረጡት ቦታና የመረጡትን ሚና ተላብሰው መጫወትን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- ለመስሎ ጨዋታ የሚረዱ ቁሳቁሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- በመስሎ መጫወት ጨዋታ ወቅት የሚረዱ ቁሳቁሶችን እና አስፈላጊውን ቦታ ማደራጀት

- ከሕፃናቱ ጋር አብሮ በመጫወት የአገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን ጠቀሜታ እንዲረዱ ማድረግ

  ለምሳሌ፡- ሱቅ ሱቅ፣ ገዢና ሻጭ፣ ት/ቤት አስተማሪና ተማሪ፣ ሃኪም ሃኪም/ ሃኪምና ታካሚ/ ወዘተ...

ምዘና ፡- በአገልግሎት መስጫ  ቦታዎች ላይ የመረጡትን ሚና ተላብሰው ለመጫወት መሞከራቸውን በማየት መገምገም።

ተግባር ሶስት ፡- በአገልግሎት ሰጪ ቦታዎች የሚገኙ ቁሶችን መለየት

ዓላማ ፡- ሕፃናቱ በአገልግሎት መስጫ ቦታዎች የሚገኙ ቁሶችን ይለያሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- በሱቅ፣ በት/ቤት እና በሃኪም ቤት የሚገኙ ዕቃዎች /ሻማ፣ ክብሪት፣ የምሣ ዕቃ፣ የምሣ ቦርሳ፣ ባዶ የመድኃኒት ዕቃ ወዘተ..../፣ የሱቅ፣ የሃኪም ቤት፣ የት/ቤት ወዘተ...ምስል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናት ፊት ለፊት በሚገኝ ጠረጴዛ ላይ የተለያዩ በሱቅ፣ በት/ቤት እና በሃኪም ቤት የሚገኙ ዕቃዎችን ማስቀመጥ፤ /ሻማ፣ ክብሪት፣ የምሣ ዕቃ፣ የምሣ ቦርሳ፣ ባዶ የመድኃኒት ዕቃ ወዘተ...
- አንድ ሕፃን በማስወጣት በሱቅ ውስጥ የሚገኝ ዕቃ አንስተህ/ሽ ስጠኝ/ስጪኝ በማለት ሕፃኑ/ኗ በጠረጴዛ ላይ ካሉት ዕቃዎች ውስጥ መርጦ እንዲሰጥ ማድረግ
- ሕፃናት ትክክል መሆን አለመሆኑን ሌሎች ሕፃናት እንዲያረጋግጡ በማድረግ የዕቃውን ስምና የሚገኝበትን ቦታ በመንገር ማበረታታት
- የሱቅ፣ የሃኪም ቤትና የት/ቤት ምስልን በየተራ ለሕፃናት በማሳየት በውስጡ ምን ምን ዕቃ ሊገኝ እንደሚችል መጠየቅ
- የተወሰኑ ዕቃዎችን በማሳየት ምን የት ሊገኝ እንደሚችል እንዲረዱ ማድረግ
- በዚህ ዓይነት ሌሎቹም ሕፃናት እንዲሳተፉ ማድረግ

ምዘና ፡- በአገልግሎት መስጫ ቦታዎች የሚገኙ ቁሶችን መለየት መቻላቸውን መገምገም።

ተግባር አራት ፡- አገልግሎት ሰጪ ቦታዎች ቀለም መቀባት

ዓላማ ፡- ሕፃናቱ አገልግሎት መስጫ  ቦታዎች የሚከናወኑ ተግባራትን ይለያሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- አገልግሎት መስጫ ተቋማት ስእሎች፣ የተለያዩ ባለቀለም እርሳሶች

የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ ፡-

- የተለያዩ በአካባቢ የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን ስዕል መስጠት
- ደማቅ ያልሆነ ከለር እንዲቀቡት ማድረግ ምክያቱም ደማቅ ከሆነ በውስጡ የሚገኙት ቁሳቁሶች አይታዩም
- ሲጨርሱም ምን እንደቀቡ በመጠየቅ አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን መጠሪያ እንዲያውቁ ማድረግ
- የአገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን በተመለከተ መዝሙር መዘመር

ምዘና ፡- በአከባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን ቀለም መቀባታቸውንና ስለቀቡት ነገር መናገራቸውን በማየትና በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፡- መዝሙር መዘመርን መለማመድ

ዓላማ ፡- ዜማውን ጠብቀው መዘመርን ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሳሪያዎች ጥቆማ ፡- አገልግሎት መስጫ ተቋማት ስእሎች

የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ ፡-

- አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ሰእልን በማሳየት ምን እንደሆነ መጠየቅና ስለእነሱ የተዘመረውን መዝሙር መስማት እንደሚፈልጉ በመጠየቅ ለማዳመጥ ያላቸውን ፍላጎት መቀስቀስ
- ድምጽን ከፍ አድርጎ ረጋ ብሎ መዘመርና ህጻናቱም መዘመር እንደሚፈልጉ መጠየቅ
- ስንኝ በስንኝ መዝሙሩን በመዘመር ህጻናቱ ከመምህር በኋላ እንዲዘምሩ ማለማመድ
- ቀጥሎም ከመምህር ጋር አብረው እንዲዘምሩ ማድረግ
- የመዝሙሩን ይዘት እንዲረዱ በጥያቄና መልስ ማጠናከር

ምዘና ፡- መዝሙሩን ዜማውን ተከትለው ለመዘመር መሞከራቸውን በማዳመጥ ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 3. አካባቢን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ማወቅ እና መንከባከብ | 3.1. ቤታቸውንና አካባቢያቸውን የማጽጃ መንገዶችን መጠቆም ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፦ የአካባቢ ንጽህና መጠበቂያ ቁሶችን መለየት

ዓላማ ፦ የአካባቢን ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ስማቸውንና አገልግሎታቸውን ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ቅርጫት፣ መጥረጊያ፣ መወልወያ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የአካባቢ ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን በማሳየት ምን እንደሆኑና ለምን እንደሚያገለግሉ በመጠየቅ ማወያየት
- እነዚህ ቁሳቁሶች እቤታቸው እንዳሉና ማን እንደሚጠቀምባቸው በመጠየቅ ማነቃቃት
- ቤታቸውን፣ ግቢያቸውንና መማሪያ ክፍላቸውን ማን እንደሚያፀዳና ለምን እንደሚፀዳ በመጠየቅ ማወያየት
- በአካባቢያቸው የቆሻሻ ማጠራቀሚያ ገንዳ አይተው ያውቁ እንደሆነና ለምን እንደሚጠቅም በመጠየቅ በአካባቢያችን ቁሻሻ የትም መጣል እንደሌለበትና መጣል ያለበት በቁሻሻ ገንዳ ውስጥ ብቻ መሆኑን እንዲገነዘቡ ማድረግ
- አካባቢ ንጹህ ካልሆነ በተለያየ በሽታዎች ሊታመሙ እንደሚችሉ በሚገባቸው ቋንቋ በመግለጽ ንፅህና መጠበቅን አስፈላጊነት በደረጃቸው እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፦ የአካባቢን ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ስማቸውንና አገልግሎታቸውን መናገራቸውን በማዳመጥ መገምገም።

ተግባር ሁለት ፦ የፅዳት መጠበቂያ ቁሶችን ቀለም መቀባትና ማዛመድ

ዓላማ ፦ የፅዳት መጠበቂያ ቁሶችን ቀለም በመቀባት ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የቁሻሻ ገንዳ፣ የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት፣ የመወልወያና የመጥረጊያ ስእሎች፣ደማቅ ባለቀለም እርሳሶች

የአተገባበር ዘዴዎች ጥቆማ ፦

- መምህር ከህጻናቱ ፊት በመቆም የቁሻሻ ገንዳ፣ የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት፣ የመወልወያና የመጥረጊያ ስእሎችን በየተራ ደማቅ ቀለም በመቀባት ምን እንደሆኑ ህፃናቱን በመጠየቅ እንዲናገሩ ማድረግ
- ለህፃናቱም አንድ አንድ ስእል በመስጠት የሚፈልጉትን ከለር እንዲቀቡ ማድረግ

- ቀብተው ሲጨርሱ መምህርጋ በመምጣት ምንን ቀለም እንደቀቡ በመጠየቅ መምህር ከቀቡት ስእል ጋር እንዲያዛምዱ ማድረግ

ምዘና ፦ የፅዳት መጠበቂያ ቁሶችን ቀለም በመቀባት መምህር ከቀቡት ስእል ጋር ማዛመድ መቻላቸውን በማየት መገምገም።

ተግባር ሶስት ፦ የአካባቢን ንጽህና መጠበቅን መለማመድ

ዓላማ ፦ በአቅማቸው የአካባቢያቸውን ንጽህና ይጠብቃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የቆሻሻ መጣያ ቅርጫት፤ ስስ ፌስታል ወዘተ…

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ሕፃናትን ከክፍል ውጪ በማስወጣት እጃቸዉን በስስ ፌስታል በመሸፈን የዛፍ ቅጠሎችን፣ ትናንሽ ወረቀቶችን፣ የብስኩት እና የከረሜላ ልጣጭ የመሳሰሉትን እንዲያነሱ እና ቅርጫት ውስጥ እንዲያስቀምጡ በማድረግ ግቢያቸውን እንዲያፀዱ ማለማመድ
- ይህንን ተግባር በሚያከናውኑበት ወቅት ‹‹ትናንሽ ወረቀቶች›› የሚለውን መዝሙር በመዘመር እየተዝናኑ አካባቢያቸውን እንዲያፀዱ ማድረግ
- ሲጨርሱም እጃቸውን በውሃና በሳሙና እንዲታጠቡ ማድረግ

ማስታወሻ ፦ የአካባቢ ንጽህና ልምድን እንዲያዳብሩ በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው ክትትል በማድረግ እንዲሁም ጥሩ ሞዴል በመሆን ማሳየት።

ምዘና ፦ የአካባቢ ንጽህናን መጠበቅ መጀመራቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፦ ራስን ከበሽታ መጠበቂያ መንገዶችን መተዋወቅ

ዓላማ ፦ ራሳቸዉን ከበሽታ የመጠበቂያ መንገዶችን በመለየት ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የምሳ ዕቃዎች፣ መሸፈኛ ጨርቅ፣ ውሃና ሳሙና

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ታመው ያውቁ እንደሆነና ምናቸውን እሚቸው እንደሚያውቅ በመጠየቅ ማወያየት

- መልሳቸውን ካዳመጡ በኋላ ሕፃናት ሁልጊዜ እጃቸውን ከምግብ በፊትና በኋላ መታጠብ እንዲሁም ከመፀዳጃ ቤት መልስ መታጠብ እንዳለባቸው፣በአፀደ ሕፃናት ሆነ በቤታቸው ምግባቸውን በመሸፈን/መከደን/ከአቧራና ከዝንብ በመከላከል ራሳቸውን ከበሽታ መጠበቅ እንዳለባቸው ማስገንዘብ
- ከንጽህና አጠባበቅ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን ገጠመኞች እና ተረቶችን መንገር

ማስታወሻ ፦ እነዚህን በዕለት ተዕለት ሕይወታቸው እንዲተገብሩ ማድረግ የሚያስፈልግ ሲሆን ወላጆችም ልጆቻቸዉ በቤት ውስጥ ይህንን ልምድ እንዲያዳብሩ እንዲረዷቸው ለወላጆች መረጃ መስጠት ያስፈልጋል።

ምዘና፡- ራሳቸዉን ከበሽታ የመጠበቂያ መንገዶችን መለየትና መናገራቸውን መገምገም።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 4. በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየትና ጥንቃቄ መውሰድ | 4.1. በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችንና ሁኔታዎችን መለየት ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፦ በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፦ በአካባቢያቸው የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን በመለየት ራሳቸውን ይጡብቃሉ።

የመርጃ መሳርያዎች ጥቆማ ፦ የተሰባበሩ ጠርሙሶች፣ አጥንቶች፣ ሽቦ፣ ሚስማር፣ ክብሪት፣ ምላጭ፣ መርፌ ወዘተ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ከላይ የተጠቀሱትን ቁሶች አንድ በአንድ በማሳየት ምን እንደሆኑ? የት አይተዋቸው እንደሚያውቁ ወዘተ በመጠየቅ ማወያየት
- ስለ አደገኛነታቸው ሊረዱ በሚችሉበት መንገድ መንገር
- ከጥንቃቄ ጉድለት ራሳቸውን ከእነዚህ አደገኛ ነገሮች እንዴት መራቅ እና መከላከል እንደሚችሉ ማወያየት
- አደገኛ ነገሮች መንካትም ሆነ በእነርሱ መጫወት እንደሌለባቸው መንገር

ምዘና ፦ በአካባቢያቸው የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየታቸውንና ራሳቸውን እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው መረዳታቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- ራስን ከትራፊክ አደጋ መጠበቅን በጨዋታ መለማመድ

ዓላማ ፡- ህፃናት ከትራፊክ አደጋ ራሳቸውን መጠበቅ ይለማመዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- አረንጓዴ፣ ቢጫ፣ ቀይ ክቦች፣ ነጭ ወረቀት፣ የትራፊክ ፖሊስ ኮፍያ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ከክፍል ውጪ "የመንገድ ትራፊክ ምልክት" ጨዋታን እንደሚከተለው ማጫወት
- ሶስት በክብ የተቆረጡ ካርቶኖችን ቀይ፣ ቢጫ፣ አረንጓዴ መቀባት
- በወፍራም ነጭ ወረቀት የመንገድ ማቋረጫን መሰመርንና የትራፊክ ፖሊስ ኮፍያ መስራት
- ግማሾቹ ሕፃናት የአሽከርካሪዎች፣ ግማሾቹ ሕፃናት ደግሞ የእግረኞችን ገፀባህሪን እንዲላበሱ ማድረግ
- መምህር ደግሞ የትራፊክ ፖሊስ ገጸባህሪን ለብሰው መጫወት
- በመንገድ መካከል እርስዎ ምልክቶችን ይዘው መቆም
- ምልክቶችን እየቀያየሩ እግረኞች ምን ምልክት ሲያዩ መንቀሳቀስ እንዳለባቸው ማስተማር
- ሕፃናቱ ተሽከርካሪዎች ሲሆኑ ደግሞ ምን ምልክት ሲያዩ መቆም እንዳለባቸው ማሳየት
- ጨዋታው ከመጠቃለሉ በፊት የሚከተለውን ለልጆቹ አጽንኦት መስጠት
- የትራፊክ ፖሊስ ቀይ ሲያሳይ መኪናዎች ይቆማሉ እግረኞች ይሻገራሉ፣ የትራፊክ ፖሊስ አረንጓዴ ሲያሳይ ሰዎች ይቆማሉ መኪናዎች ይሄዳሉ፣ የትራፊክ ፖሊስ ቢጫ ሲያሳይ ሰዎች ይቆማሉ መኪና ለመሄድ ይዘጋጃሉ

ማስታወሻ ፡- ይህንን ተግባር በተደጋጋሚ በማጫወት ትምህርቱን ማጠናከር ያስፈልጋል።

ምዘና ፡- መንገድ ሲያቋርጡ ሊያደርጉአቸው ስለሚገቡ ጥንቃቄዎች መገንዘባቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሶስት ፡- "ጎበዙ ተማሪ" መዝሙርን መዘመር

ዓላማ ፡- "ጎበዙ ተማሪ" መዝሙሩን መዘመር ይለማመዳሉ፣ የመዝሙሩን መልእክት ለመረዳት ይሞክራሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ፡-

- መንገድ ሲያቋርጡ በእግረኛ ማቋረጫ መስመር ላይ ማቋረጥ እንዳለባቸው መንገር
- ለዚህም መምህር "ጎበዙ ተማሪ" የሚለውን መዝሙር ማዘመር

- የመዝሙሩን መልእክት በጥያቄና መልስ እንዲሁም በተግባር እንዲረዱት ማድረግ

ምዘና ፦ "ጉብዙ ተማሪ" የሚለውን መዝሙር መዘመር መቻላቸውን እና የመዝሙሩን መልክት መገንዘባቸውን ማረጋገጥ።

**ተግባር አራት ፦ ራስን ከአደገኛ ነፍሳቶች መጠበቅ**

ዓላማ ፦ ራሳቸውን በአካባቢያቸው ከሚገኙ አደገኛ ነፍሳቶች ይጠብቃሉ።

የመርጃ መሳርያዎች ጥቆማ ፦ ሊናደፉ የሚችሉ የተለያዩ አደገኛ የሆኑ ነፍሳትን ወዘተ… የያዘ ስእል

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- መምህር አደጋ ሊያደርሱ /ሊናደፉ፣ሊቆናጠጡ/ የሚችሉ ነፍሳትን ስዕል እንደ ንብ ፣ ሸረሪት ፣ ጉንዳን ወዘተ… ማሳየት
- ልጆቹ በየተራ የእያንዳንዱን ነፍሳት ምንነታቸውን መንገር
- አንድ አንድ ነፍሳት ሊጐዷቸው እንደሚችሉ አንዳንዶቹ ድግሞ ጠቀሜታቸውን መንገር

  ለምሳሌ፦ ንብ ጥቅም የምትሰጥ መሆኗን ግን ጥንቃቄ ማድረግ እንደሚገባ በሚረዱት መልኩ መንገር

ምዘና ፦ ራሳቸውን በአካባቢያቸው ከሚገኙ አደገኛ ነፍሳቶች እንዴት መከላከል እንደሚችሉ ግንዛቤ መጨበጣቸውን መገምገም።

**ተግባር አምስት ፦ "ጃምቦና ኩባያው" ተረትን ማዳመጥ**

ዓላማ ፦ በአካባቢያቸው የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን ይለያሉ፣ በአቅማቸው ራሳቸውን ከአደገኛ ነገሮች እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው ይረዳሉ።

የመርጃ መሳርያዎች ጥቆማ ፦ ጃምቦና ኩባያው ተረት መጽሐፍ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- የህፃናቱን አቀማመጥ በግማሽ ኩብ ማስተካከል
- ተገቢውን የተረት አተራረክ ስልት በመጠቀም ተረቱን ከመጽሐፍ ላይ ማንበብ
- ከንባብ በኋላ ከመፅሐፉ የወጡ ጥያቄዎችን በመጠየቅ የመፅሐፉን መልእክት እንዲረዱ በማድረግ በአካባቢያቸው ከሚገኙ ነገሮች ውስጥ አንዱ እሳት መሆኑን እንዲረዱ ማድረግ

ምዘና ፡- በአካባቢያቸው የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየታቸውንና ራሳቸውን ከአደጋ እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው መገንዘባቸውን በመጠየቅ ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| 5. የእንቅስቃሴን ጽንሰ ሃሳብ መረዳትና ሙከራ ማካሄድ | 5.1. በአካባቢ ስለሚገኙ ነገሮች እንቅስቃሴ መግለጽ ይችላሉ። |

ተግባር አንድ ፡- የሚንከባለሉና የማይንከባለሉ ነገሮችን መለየት

ዓላማ ፡- እቃዎችን በማንከባለል ባህሪያቸውን ይናገራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ትንሽ ኳስ፣ ትንሽ የእንጨት ሳጥን፣ ትንሽ ፕላስቲክ እቃ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ቁሶቹን በማሳየት ምን እንደሆኑ በመጠየቅ ማነቃቃት
- በመቀጠልም የትኛው ቁስ መንከባለል እንደሚችልና የትኛው መንከባለል እንደማይችል በመጠየቅ ምላሽ እንዲሰጡ ማድረግ
- አስቀድሞ መንከባለል ማለት ምን እንደሆነ ሊገባቸው በሚችል ቋንቋ ማስረዳት ያስፈልጋል
- በመቀጠልም ለህጻናቱ በየጠረጴዛቸው ቁሶቹን በመስጠት እንዲያንከባልሉና ውጤቱን እንዲያጤኑና እንዲናገሩ ማነቃቃት

ምዘና ፡- እቃዎችን በማንከባለል ባህሪያቸውን መናገር መቻላቸውን ማረጋገጥ።

ተግባር ሁለት ፡- ፈጣንና ዝግታ እንቅስቃሴን ማከናወን

ዓላማ ፡- ፈጣንና ዝግታ እንቅስቃሴዎችን በድርጊት ያሳያሉ፣ ያዩትን እንቅስቃሴ በመኮረጅ ያሳያሉ።

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ሕፃናትን ከክፍል ውጭ ይዞ በመውጣት በግማሽ ክብ እንዲቆሙ ማድረግ
- ህፃናቱ የመምህርን የእጅና የእግር እንቅስቃሴን በማየት አብረው ከመምህር እኩል እንቅስቃሴውን እንዲሰሩ ማድረግ
- ለምሳሌ መምህር ቀስ እያሉ ባሉበት ሲዘሉ ህፃናቱም ቀስ ብለው መዝለል፣ ሰፈጥኑ መፍጠን፣ መምህር ቀስ ብለው በዝግታ እጃቸውን ሲያንቀሳቅሱ ህጻናቱም እንዲያንቀሳቅሱ ማድረግ

- በመቀጠልም መምህር ቀስ ብላችሁ መኪናችሁን አሽከርክሩ ሲሉ በቀስታ እንዲያሽከረክሩና በፍጥነት አሽከርክሩ ሲሉ በፍጥነት እንዲያሽከረክሩ በማድረግ ፈጣንና ዝግታ እንቅስቃሴን እንዲረዱ ማድረግ
- ትልቁ ጎማ ተሽከረከረ ጨዋታን እንዲጫወቱ በማድረግ ማጠናከር

ምዘና ፦ ፈጣንና ዝግታ እንቅስቃሴዎችን በድርጊት ማሳየታቸውንና ያዩትን እንቅስቃሴ በትክክል መኮረጃቸውን በማየት መገምገም።

ተግባር ሶስት ፡- የእግር ዱካዎችን ማዛመድ

ዓላማ ፡- ተመሳሳይ የእግር ዱካዎችን ያዛምዳሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- ከወፍራም ክላሰር ወይም ካርቶኒ ላይ የተቀረፁ በተለያየ እድሜ ክልል ላይ የሚገኙ የሰዎች የእግር ዱካዎች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ከወፍራም ክላሰር ወይም ካርቶኒ የተሰራ የእግር ዱካዎችን በማሳየት ምን እንደሆነ በመጠየቅ ማወያየት
- በየጠረጴዛቸው የተለያዩ ሰዎችን የእግር ዱካዎችን በመስጠት የሚመሳሰሉትን እንዲያዛምዱ ማድረግ
- አዛምደው ሲጨርሱ ለመምህር እንዲያሳዩ ማድረግ

ምዘና ፡- ተመሳሳይ የእግር ዱካዎችን ማዛመድ መቻላቸውን በማየት ማረጋገጥ።

| የሚጠበቅ ውጤት | ብቃት |
|---|---|
| በስነ ስዕልና ቅርፃ ቅርጽ የተለያዩ ነገሮችን መፍጠር፣ ዱነቅና ራስን መግለጽ | 6.1. የዓይንና የእጆቻቸውን እንቅስቃሴ በማቀናጀት የተለያዩ ነገሮችን መስራት ይለማመዳሉ። |

ተግባር አንድ ፦ ስዕል መሳልና ቀለም መቀባት

ዓላማ ፦ ስእል በመሳል ቀለም ይቀባሉ፣ ለቀቡት ስእል መጠሪያ ስም ይሰጣሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀቶች፣ እርሳሶችና ባለቀለም እርሳሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለእያንዳንዱ ህፃን ስእል መሳያ ወረቀት በመስጠት የሚፈልገውን እንዲስልና ሲጨርስ የእርሳስ ቀለምን በመጠቀም ቀለም እንዲቀቡ ማድረግ
- ቀብተው ሲጨርሱ ለመምህር በማሳየት የሳሉትን ስእል ምንነት እንዲናገሩ ማነቃቃት፤
- ህጻናቱ ሲናገሩ ከስእሉ ስር ስያሜውን መፃፍ
- ሕፃናት ሊታያቸው በሚችል ቦታ ላይ ወረቀቱን መለጠፍ

ምዘና ፦ የፈለጉትን ነገር መሳላቸውንና ቀለም መቀባታቸውንና እንዲሁም ለሳሉት ስእል ስያሜ መስጠታቸውን በማየት መገምገም።


ተግባር ሁለት ፦ መሠረታዊ መስመሮችንና ቅርጾችን መስራት

ዓላማ ፦ መሠረታዊ መስመሮችንና ቅርጾችን ይሰራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ ወረቀትና እርሳሶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለህፃናቱ እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመቆም የተለያዩ መሠረታዊ መስመሮችንና ቅርፆችን እየሰሩ ማሳየት



- ቀጥሎም ለሕፃናት ወረቀትንና ባለቀለም እርሳሶች በማደል ያዩትን እንዲሰሩ ማድረግ፣
- ሲሰሩ እየተዟዟሩ በማየት ማበረታታት

ማስታወሻ ፦ ይህንን ተግባር በተለያየ ጊዜ ማለማመድ ያስፈልጋል።

ምዘና፡- የዓይን እና የእጆቻቸውን እንቅስቃሴ በማቀናጀት መሠረታዊ መስመሮችንና ቅርፆችን መስራታቸውን በማየት መገምገም።

ተግባር ሶስት ፡- ክፍልን ማስዋቢያ መስራት

ዓላማ ፡- ወረቀትን በመጠቅለል ቀለበቶችን በመስራት ክፍልን ማስዋቢያ ያዘጋጃሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፡- በቀጫጭኑ የተቆራረጡ ባለ ቀለም ወረቀቶች

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፡-

- ለህፃናቱ እይታ ቦታ ላይ በመቆም በቀጭኑ የተቆረጠ አንድ ወረቀትን በመውሰድ በጠቋሚ ጣት ላይ በመጠቅለል ጫፉን ማጣበቂያ በመቀባት ቀለበት መስራት
- በመቀጠልም በተሰራው ቀለበት ውስጥ ሌላ የተቆረጠ ወረቀት በመክተትና ጫፉን በማጣበቅ ሁለት የተቀጣጠሉ ቀለበቶችን ማዘጋጀት
- በዚህ አይነት አምስት ቀለበቶችን በመስራት ህጻናት እነሱም መስራት እንደሚፈልጉ በመጠየቅ የመስራት ፍላጎታቸውን ማነሳሳት
- ወረቀቱን እንዴት እንደሚጠቀልሉና ማጣበቂያውን ጠቋሚ ጣታቸውን በመጠቀም እንዴት መቀባት እንዳለባቸው መግለፅ
- ለእያንዳንዱ ህፃን አምስት ቁርጥራጭ ወረቀትን በመስጠት መምህርን በማየት እንዲሰሩ ማድረግ
- ሲሰሩ ድጋፍ ለሚያስፈልጋቸው ድጋፍ ማድረግና ማበረታታት
- ሲጨርሱም በክፍል ውስጥ በመስቀል ክፍላቸውን እንዲያስውቡ ማድረግ

ምዘና ፡- ወረቀትን በመጠቅለልና በማጣበቅ ክፍልን ማስዋቢያ ቀለበቶችን መስራታቸውን በማየት ማረጋገጥ።

ተግባር አራት ፡- በተቦካ ጭቃ ወይም ወረቀት ቅርፃ ቅርፆችን መስራት

ዓላማ ፦ ከተቦካ ጭቃ ወይም ወረቀት የተለያዩ ነገሮችን ይሰራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የተቦካ ጭቃ ወይም የተቦካ ወረቀት፣ ጠረጴዛ መሸፈኛ ላስቲክ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ለህፃናት እይታ አመቺ ቦታ ላይ በመሆን የተቦካ ጭቃ ወይም ወረቀትን በማድቦልቦልና በመጠፍጠፍ ምጣድ፣ ድስት ከነመክደኛው፣ ስኒ ከነማስቀመጫው፣ ብይ ወዘተ በመስራት መስራት ያላቸውን ፍላጎት መቀስቀስ
- የሹራብና የሸሚዛቸውን እጅታ እንዴት እንደሚጠቀልሉ በማሳየት እንዲጠቀልሉ ማድረግ
- ጠረጴዛቸውን በላስቲክ እንዲሸፍኑ በማድረግ የተቦካ ጭቃ ወይም ወረቀት በመስጠት የፈለጉትን እንዲሰሩ ማድረግ
- ሲሰሩ እየተዟዟሩ በማየት ከከበዳቸው ፍንጭ በመስጠት ማበረታታት
- ሰርተው ሲጨርሱ ምን እንደሰሩ በመጠየቅ የሰሩትን በወረቀት ላይ በማድረግ ስማቸውን በመፃፍ እንዲደርቅ ማድረግ

ምዘና ፦ ከተቦካ ጭቃ ወይም ወረቀት የተለያዩ ነገሮችን መስራታቸውን በማየትና የሰሩትን መናገራቸውን በማዳመጥ ማረጋገጥ።

ተግባር አምስት ፦ ከቅጠል መጫወቻን መስራት

ዓላማ ፦ የዓይን እና የእጆችን እንቅስቃሴ በማቀናጀት ከቅጠል መጫወቻ ይሰራሉ።

የመርጃ መሣሪያዎች ጥቆማ ፦ የደረቁ የባህር ዛፍ ቅጠሎች፣ ጥቅም ላይ የዋለ የሞባይል ካርድ

የአተገባበር ዘዴ ጥቆማ ፦

- ህጻናቱን ከክፍል ውጪ ይዘው በመውጣት በግማሽ ክብ እንዲቆሙ በማድረግ ከባህር ዛፍ ቅጠል ሽክርክሪት በመስራት በንፋስ ሀይል እንዴት እንደሚሽከረከር ማሳየትና እነሱም መስራት እንደሚፈልጉ በመጠየቅ ማነቃቃት

- ለእያንዳንዱ ልጅ የባህር ዛፍ ቅጠል በመስጠት መምህርን በመከተል እንዲሰሩ ማድረግና ሲጨርሱም እየሮጡ በማሽከርከር እንዲጫወቱ ማድረግ
- ተጫውተው ሲጨርሱም ምን እንደሰሩ እና የሰሩት መጫወቻ ሲቆሙ ለምን እንደማይሽከረከር በመጠየቅ በቅጠል የሚሰራ እሽክርክሪት የሚሽከረከረው ንፋስ ሲያገኝ ብቻ መሆኑን በደረጃቸው እንዲረዱ ማድረግ

ማስታወሻ ፡- የባህር ዛፍ ቅጠልን በግቢ ባይገኝ ከሌላ አካባቢ ፈልጎ ማግኘት ወይም ጥቅም ላይ የዋለ የሞባይል ካርድን በማጠፍ እሽክርክሪት በመስራት እንዲሰሩና እንዲጫወቱ ማድረግ ይቻላል።

ምዘና፡- የዓይን እና የእጆችን እንቅስቃሴ በማቀናጀት ከቅጠል መጫወቻ በመስራት መጫወታቸውን በማየት ማረጋገጥ።

## 2.5.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ

የቅድመ መደበኛ ት/ቤት ስም ----------------------------------------------------------------------

የህጻኑ ስም --------------------------------------------- ዕድሜ -------------- ጾታ --------

የመምህሩ ስም ----------------------------------------------- ዓመተ ምሕረት -------------

ስለ ህጻኑ ምልከታዉን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅጹ ዉስጥ ምልከታ በሚለዉ ስር ይመዝግቡ

ደረጃዎቹ፡-

1/ መሻሻል የሚያስፈልገዉ -------------------------------------------------------------------

2/ የታለመዉ ብቃት የተገኘበት ------------------------------------------------------------

3/ ከታለመዉ በላይ የተገኘበት --------------------------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በዓመቱ መጀመሪያ፣ በዓመቱ አጋማሽ እና በዓመቱ መጨረሻ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | የዓመቱ መጀመሪያ | የዓመቱ አጋማሽ | የዓመቱ መጨረሻ |
| **1.** የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ | | | |
| 1.1. ስለመኖሪያ ቤታቸውና በቤታቸው ስላሉ ቀሳቁሶች መናገር ይችላሉ | | | |
| 1.2. በቤታቸውና በቅርብ አካባቢያቸው ያሉትን ሰዎች፣ እንስሳቶች፣ አትክልቶች፣ ቁሳቁሶችን ፣ ነፍሳቶችን ሌሎች ነገሮችን መለየት ይችላሉ | | | |
| 1.3. በቅ/መ/ት/ቤት የሚገኙትን ሰዎች መጫወቻዎችና ሌሎች ነገሮች መለየት ይችላሉ | | | |
| **2.** በአካባቢ የሚገኙትን አስፈላጊ ቦታዎች ማወቅና ማድነቅ | | | |
| 2.1. በአካባቢያቸው ስለሚገኙት አስፈላጊ ቦታዎች መናገር ይችላሉ | | | |
| | | | |
| **2.** አካባቢን እንዴት መንከባከብ እንደሚቻል ማወቅና መንከባከብ | | | |
| 3.1. ቤታቸውንና አካባቢያቸውን የማፅጃ መንገዶችን መጠቀም ይችላሉ | | | |
| **4.** በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየትና ጥንቃቄ መውሰድ | | | |
| 4.1. በአካባቢ ያሉ አደገኛ ነገሮችና ሁኔታዎችን መለየት ይችላሉ | | | |
| **5.** የእንቅስቃሴን ጽንሰ ሃሳብ መረዳትና ሙከራ ማካሄድ | | | |
| 5.1. በአካባቢ ስለሚገኙ ነገሮች እንቅስቃሴ መግለጽ ይችላሉ | | | |
| **6.** በስነ ስዕልና ቅርፃ ቅርጽ የተለያዩ ነገሮችን መፍጠር ማድነቅና ራስን መግለጽ | | | |
| 6.1. የዓይንና የእጆቻቸውን እንቅስቃሴ በማቀናጀት የተለያዩ ነገሮች መሥራትን ይለማመዳሉ | | | |

# አባሪ

| መዝሙር | ጨዋታ | ተረት |
|---|---|---|
| 1. እኔ ልጅ ነኝ<br>2. ሉነኝ (እኔ ትንሽ ነኝ)<br>3. ስለመቅመስ<br>4. ትንየሰውነት ክፍሎች<br>5. ሙሿ አፊ<br>6. ጥርስን መፋቅ እንደዚህ ነው<br>7. ንጽህናዬን ጠብቄአለሁ<br>8. ወፊቷን እሆናለሁ<br>9. ጠዋት ተነስቼ<br>10. ፊትን መታጠብ እንደዚህ ነው<br>11. ውሸታሙ እረኛ<br>12. ጥንቸል ጉረኛው<br>13. ተረት ተረት<br>14. ማን ነኝ ማን ነኝ<br>15. ትንሽ ትንሽ ወፎች<br>16. ቤቴ ቤቴ<br>17. አንድ ላይ አንድን ጨምሬ<br>18. የቁጥር ስንኝ<br>19. አስር አረንጓዴ ጠርሙሶች<br>20. ጠዋት ተነስቼ<br>21. የሳምንቱ ቀናት እነማን ናቸው<br>22. ባንዲራችን<br>23. ልጆች ልጆች እንካችሁ<br>24. አደገኛ ነገሮች<br>25. ጎበዙ ተማሪ<br>26. ለወላጆች ቀን | 1. ዱላ ቅብብል<br>2. ማን ቀድሞ ይበጥሳል<br>3. ጭራ ነቀላ<br>4. ትንሹ ጎማ<br>5. ወፊቷን እሆናለሁ<br>6. አያ ጅቦ<br>7. አረንጓዴ<br>8. የወንበር ሽሚያ<br>9. የጠራህን ዕወቅ<br>10. ቀምሰህ ዕወቅ<br>11. ተአምረኛው ከረጢት<br>12. መሃረቤን ያያቹ<br>13. ማነው ቀድሞ የሚለብሰው<br>14. መሪውን ዕወቅ<br>15. ትዕዛዝን ፈጽም<br>16. ልትወጣ ነው ልትወጣ ነው<br>17. ጓደኛህን ፈልግ<br>18. የጎደለውን ሙላ<br>19. ጭብጨባውን በቁጥር አዛምድ<br>20. የመስፈር ጨዋታ<br>21. ምን መቼ ይደረጋል<br>22. ምን የት እንዳለ ዕወቅ<br>23. የመንገድ ትራፊክ መብራት | **1.** ትንሹ ዮናስ<br>**2.** የላሊቱ ሉሊት<br>**3.** በድሉ በረኛው<br>**4.** ማነው የሚበልጠው<br>**5.** ውርዬና ቦቢ<br>**6.** በራሪው አበባ<br>**7.** ጃምቦና ኩባያው |

መዝሙር

1. <u>እጅ ለእጅ ተያይዘን</u>

እጅ ለእጅ ተያይዘን

እጅ ለእጅ ተያይዘን

እንሽከረከራለን

መዘመር እንችላለን

መደነስ እንችላለን

2. <u>ዓይን አለኝ አያለሁ</u>

ዓይን አለኝ አያለሁ ዓይን

አለኝ አያለሁ አካባቢዬን

አስተውላለሁ

ከምንም ጋር አልጋጭም በመንገድ አስተውዬ

እያየሁ ስለምሄድ

3. <u>ሽታን እንደሚገልፁ ስንኞችን</u>

ሽተተን ሽተተን ሎሚው

ሽተተን ሽተተን ማንጎው

ብሉት ብሉት አለን ሽታው

የቆሻሻ ገንዳ ሽታ

ልጆች ያስይዛል በሽታ

እንራቅ እንራቅ ከቆሻሻ ሽታ

እንዳንያዝ በጉንፋን በሽታ

4. <u>የላሊቱ ሉሊት</u>

የላሊቱ ሉሊት በለጠች

ከቲቲ ቡችሊት

ቲቲ ቡችሊት እንዴት ሆነች

ትምህርት ጠልታ በየቆሻሻው ተልከሰከሰች

ባልታጠበ እጇ እየጐረሰች

ታመመች ፣ አስቀመጣት፣ አስታወካት

ደከመች፣ ተዝለፈለፈች፣ ወደቀች

የላሊቱ ሉሊት

በለጠች ከቲቲ ቡችሊት

የላሊቱ ሉሊት

በለጠች ከቲቲ ቡችሊት

ላሊትስ እንዴት ሆነች ?

ከእንቅልፏ ተነሳች

ልብሷን ለባበሰች

በሣሙና ተጣጠበች

ምግቧን ተመገበች

ቦርሳዋን አነገበች

ጉዞዋን ቀጠለች

**5.** <u>ሃሎ ሃሎ</u>

ሃሎ ሃሎ ጓዴ እንደምንድነህ?

ሃሎ ሃሎ እኔ በጣም ደህና ነኝ

አንተስ እንደምንድነህ ?

**6.** <u>ትንሽ ትንሽ ወፎች</u>

አንድ ሁለት ሶስት ትንሽ ትንሽ ወፎች

አራት አምስት ስድስት ትንሽ ትንሽ ወፎች

ሰባት ስምንት ዘጠኝ ትንሽ ትንሽ ወፎች

አሥር ትናንሽ ወፎች

**7.** <u>በአካባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ቦታዎች</u>

እማማ ስንዴ ለማስፈጨት

ሄደች ወፍጮ ቤት

አስፈጭታ ስትመጣ

አባባ ከሥራ መጣ

ከዕለታት አንድ ቀን

ስላመመኝ ሆዴን

ሃኪም ቤት ሄደኩኝ

ሐኪሙም እንዲህ አለኝ

እጅህን ሳትታጠብ

እንዳትበላ ምግብ

እሺ ብዬ ቃል ገባሁኝ እኔም

ሁለተኛ እጄን ሳልታጠብ አልበላም

**2.** <u>የሕብረት ጽዳትን በተመለከተ ግጥምና ስንኝ</u>

ትናንሽ ልጆች በህብረት

ግቢያቸውን ያፀዳሉ በአንድነት

ሲጨርሱም አጽድተው ግቢያቸውን

በሳሙና ይታጠባሉ እጃቸውን

**9.** <u>በምን ምን እናደርጋለን **?**</u>

መምህር እናያለን ሲሉ /በዜማ/

ሕፃናት በዓይናችን ይላሉ /በዜማ/

መምህር እንሮጣለን /በሩጫ መልክ በዜማ/

ሕፃናት በእግራችን

መምህር እንሰማለን

ሕፃናት በጆሮአችን

መምህር እንቀምሳለን

ሕፃናት በምላሳችን እናሽታለን

በአፍንጫችን ወዘተ.....

**10.** <u>ቀስ በቀስ ሸረሪቷ</u>

ቀስ በቀስ ሸረሪቷ ወደ ላይ ወደ ላይ ወጣች

ንፋሱ ነፍሶ ሲያወዛውዛት

ዝናቡ ዘንቦ ወደታች ወደታች ጣላት

**11.** <u>እንደ ዛፍ እወዛወዛለሁ</u>

እንደ ዛፍ እወዛወዛለሁ

እንደ ወፍ እበራለሁ

እንደ ፊንጣ እዘላለሁ ወዘተ.....

**12.** <u>ወፊቷን እሆናለሁ</u>

ወፊቷን እሆናለሁ

በአየር ላይ እበራለሁ

ከዛፎቹም በላይ

ወደ ላይ ወደ ላይ

ቢራቢሮን እሆናለሁ

በአየር ላይ እበራለሁ

ከአበቦቹም በላይ

ወደ ላይ ወደ ላይ

**13.** ጥንቸል ጉረኛው

ጥንቸል ጉረኛው አፈረ

ኤሊ ትጉህ ተከበረ

ጥንቸል ጉረኛው ሲነዛ ጉራ

ኤሊ አሸነፈ ሮጠ በተስፋ

አጨበጨቡ ዳኞች እንሰሳት

በኤሊ ኮሩ ቀሰሙ ትምህርት

**14.** _የቤት እንሰሳት መዘመር ይችላሉ

የቤት እንሰሳት መዘመር ይችላሉ /2/

ሆሆ ምን ምን እያሉ?

ድመት ትዘምራለች ትደንሳለች

ሚያው ሚያው ሚያው ትላለች

የቤት እንሰሳት መዘመር ይችላሉ /2/

ሆሆ ምን ምን እያሉ?

ውሻስ ምን አለ ምን ምን አለ?

ውው አለ አጥንት ቆረጠመ

የቤት እንሰሳት መዘመር ይችላሉ /2/

ሆሆ ምን ምን እያሉ?

ዶሮስ ምን አለ ምን ምን አለ?

ኩኩሉ አለ ከአጥር ላይ ዘለለ

**15.** ደስተኛ የሆነ

ደስተኛ የሆነ ያጨብጭብ

ደስተኛ የሆነ ይዘላል

ደስተኛ የሆነ ደስታውን

ዱብ ዱብ በማለት ይግለፅ

**16.** እጅን መታጠብ እንደዚህ ነው

እጅን መታጠብ እንደዚህ ነው እንደዚህ ነው

ፊትን መታጠብ እንደዚህ ነው እንደዚህ ነው

ፀጉርን ማበጠር እንደዚህ ነው እንደዚህ ነው ወዘተ.....

**17.** <u>አምስት ሙዞች አሉኝ</u>

አምስት ሙዞች አሉኝ

ለማን ልስጣቸው?

ለሃና ሰጠሁ 4 ቀረኝ

ለሄኖክ ሰጠሁ 3 ቀረኝ

ለአስቴር ሰጠሁ 2 ቀረኝ

ለአሹ ሰጠሁ 1 ቀረኝ

ለራሴ አንድ ወሰድኩ ስንት ቀረኝ ?

**18.** <u>ትንሽ ትንሽ ወፎች</u>

አንድ ሁለት ሶስት ትንሽ ትንሽ ወፎች

አራት አምስት ስድስት ትንሽ ትንሽ ወፎች

ሰባት ስምንት ዘጠኝ ትንሽ ትንሽ ወፎች

አሥር ትናንሽ ወፎች

**19.** <u>አምስቱ የስሜት አካላት</u>

አምስቱ አምስቱ

የስሜት ህዋሳት

የስሜት የስሜት

አዝማች ህዋሳት ህዋሳት**×2**

ዓይን አፍንጫ (**×2)**

ምላስ ጆሮና (**×2)**

እጃችን ናቸው (**×2)**

ዓይን አለኝ አያለሁ

ጆሮ አለኝ እሰማለሁ

በአፍንጫዬም አሸታለሁ (**×2)**

በምላሴም እቀምሳለሁ (×2)

መዳሰሻ እጅም አለኝ (×2)

የስሜት ህዋሴን እወቁልኝ!

**20.** <u>ሁልጊዜ ይህን እናደርጋለን</u>

ሁልጊዜ ጠዋት ስንነሳ

ፊታችንን እንታጠባለን  ቁርሳችን እንበላለን                                                    ሁልጊዜ ይህን

እናደርጋለን

**21.** ወደ ሱቅ እሄዳለሁ (የአገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን ማስተዋወቅ)

| | |
|---|---|
| እኔ ወደ ሱቅ ከእናቴ ጋር እሄዳለሁ | እሄዳለሁ |
| እኔ ወደ ሱቅ ከአባቴ ጋር እሄዳለሁ | እሄዳለሁ |
| ሄጄም ብስኩት እገዛለሁ | እገዛለሁ |
| ሄጄም ደብተር እገዛለሁ | እገዛለሁ |
| ተመልሼም ወደ ቤቴ እመጣለሁ | እመጣለሁ |
| እኔ ወደ ሃኪም ቤት ከእናቴ ጋር እሄዳለሁ | እሄዳለሁ |
| ሄጄም ያመመኝን እታከማለሁ | እታከማለሁ |
| ተመልሼ ድኜም ወደ ቤቴ እመጣለሁ | እመጣለሁ |

**22.** ትናንሽ ወረቀቶች

ትናንሽ ወረቀቶች

ትናንሽ ወረቀቶች

መሬት ላይ ወድቀዋል

ወለሉ /ግቢውን /አቆሸሹት

አንሷቸው አንሷቸው

**23.** ጉበዙ ተማሪ

ጉበዙ ተማሪ በጣም ጠንቃቃ ነው

በመንገድ ላይ ሲሄድ እያስተዋለ ነው

መኪና ሲመጣ ከሩቅ እንዲታየው

የመንገዱን ግራ ይዞ ነው የሚጓዘው

**24.** ወፊቷ

ወፊቷ ከየት ይሆን ቤትሽ?

የምትገቢውን ዞረሽ

በሰማይ ስትበሪ

እጥሩን ስትሰብሪ

ቤትሽን ስትሰሪ

መሆኑን አወቅሁኝ

ወፊቱ ልታርፊ ልተኚ

**25.** እኔ ልጅ ነኝ

እኔ ልጅ ነኝ ሰው ሁሉ የሚወደኝ

እኔ የምወደው ጨዋታ ነው በሸርተቴ

በመሰላል በሽክርክሮሽ መውጣት መውረድ

ደስታዬ ነው

**26.** የሰውነት ክፍሎች

በእጆቼ አጨበጭባለሁ /ቸብ ፣ ቸብ/

በእግሮቼ እዘላለሁ /ዝልል፣ ዝልል/

በዓይኖቼ አያለሁ /በሩቅ ዓይንን ከልሎ ማየትን ማስመሰል/

በአንገቴ እጅ እነሳለሁ /እጅ መንሳት/

በአፍንጫዬ አሸታለሁ /እንደማሽተት አየር መሳብ/

**27.** ሙሉ ነኝን

እኔ ትንሽ ነኝ ትንሽ ነኝ

ትንንሽ የአካል ክፍሎች አሉኝ

መራመጃ ትንንሽ እግሮች አሉኝ እኔ

ትንሽ ነኝ ትንሽ ነኝ

መጫወቻ ትንንሽ እጆች አሉኝ

እኔ ትንሽ ነኝ ትንሽ ነኝ

የማይባቸው ዓይኖች አሉኝ

እኔ ትንሽ ነኝ ትንሽ ነኝ

የምሰማበት ትንንሽ ጆሮዎች አሉኝ

እኔ ትንሽ ነኝ ትንሽ ነኝ

**28.** ትንሹ አፊ

ትንሹ አፊ የት ነው ያለሽው ?

እዚህ ነኝ እዚህ ነኝ እንደምንናችሁ

ትናንሽ ጥርሶቼ የት ነው ያላችሁት

እዚህ ነን እዚህ ነን እንደምናችሁ

ቀዩ ምላሴ የት ነው ያለኸው?

እዚህ ነን እዚህ ነን እንደምናችሁ

ትናንሽ ከንፈሮቼ የት ነው ያላችሁት?

እዚህ ነን እዚህ ነን እንደምናችሁ

**29.** <u>የመቅመስ መዝሙር</u>

ስኳር ይጣፍጣል ቃሙኝ ቃሙኝ ይላል

ማርም ይጣፍጣል ላሱኝ ላሱኝ ይላል

ሎሚ ይኮመጥጣል አፍን ምራቅ ይሞላል

**30.** <u>መሃረቤን ያያችሁ</u>

መሐረቤን ያያችሁ? /ሲል/

አላየንም እባካችሁ /ሕፃናት ይላሉ/

ይቺ ምንድን ናት ? /ሕፃኑ/

የውርዬ ኳስ ናት /ሕፃናት/

ማየት የለም፣ /ሕፃኑ/

መዳበስ የለም /ሕፃናት ይላሉ/

**31.** <u>ጠዋት ተነስቼ</u>

ጠዋት ተነስቼ

ፊቴንም ታጥቤ

ቁርሴንም በልቼ

ልሄድ ትምህርት ቤት

ቦርሳዬን አንግቼ

**32.** <u>ውሸታሙ እረኛ</u>

ውሸታሙ እረኛ

ዘወትር ልማደኛ

ቀበሮ መጣብኝ

በጎቼን በላብኝ

እያለ ዘወትር

ሲቀልድ ሲያስቸግር

በዚህ አድራጎቱ

ደግሞም በውሸቱ

ሁሉም ሰው ተማሮ

አንድ ቀን ቀበሮ

መጣና በድንገት

በጎቹን በላበት *2

ውሸታሙ እረኛ

ዘውትር ልማደኛ

ኡኡ እያለ ወጣ

የሚረዳው አጣ*2

## **33.** ተረት ተረት

ተረት ተረት የላም በረት

ከዕለታት አንድ ቀን አንዲት ጦጣ

በስልቻ ያለ ማር ሰርቃ እጇን ከታ

እያላሰች ምንም ምንም አላስቀረች

ሆዷ ተነፍቶ መሄድ አቅቷት የማሩ ጌታ

ድንገት አገኛት እጇን አስሮ ወደኋላ

ገርፎ ገርፎ በያዘው ዱላ ጦጢትም

ታውቋት ያ ጥፋቷ የሰውየውን ማር በመስረቋ

አይለመደኝም ብላ ጮኸች በመስረቋም

ተፀፀተች ተረቴን ተረቴን መልሱ

አፌን በዳቦ አብሱ አብሱ

## **34.** ቤቱ ቤቱ

ቤቱ ቤቱ በምን ያጌጠ ነው ? /አሻንጉሊት/ በልዩ

ልዩ ቀለማት /ሕፃናት/ በምን በምን ዓይነት

ቀለማት? /አሻንጉሊት/ ግድግዳው ቢጫ ነው

ወለሉ ቀይ ነው ጣሪያው አረንጓዴ ነው /ሕፃናት/

ደስ ብሎኛል /2/ አመሰግናለሁ።

**35.** <u>የቀለማት ግጥም</u>

ሰማይ ሰማያዊ - ሳር አረንጓዴ ነው ደምም ቀይ

ሲሆን -- አደይ አበባ ቢጫ ነው በደንብ

እናስተውል ልጆች እንዳንረሳው

**36.** <u>ልጆች ልጆች ስሙኝ እባካችሁ</u>

ልጆች ልጆች እባካችሁ ስሙኝ ልንገራችሁ

ቆሻሻዎችን በየቦታው አትጣሉ በሽታን ያመጣሉ፤ ከተያዝን

በበሽታ

እንቀራለን ከትምህርት ገበታ

አይኖርም ያ ጣፋጭ ጨዋታ

**37.** <u>አደገኛ ነገሮች/ግጥም/</u>

ክብሪትና ምላጭ መጫወቻ አይደሉም

ከአጠገባችን ይጥፉ ለእኛ አይጠቅሙም

ተወዳጆች ለእኛ ጠቃሚያችን

ኳሶቻችንና አሻንጉሊቶቻችን

አምጧቸው ወደእኛ

እንወዳቸዋለን እኛ

**38.** <u>የወላጆች ቀን</u>

እኛን የምትወዱ ሰዎች እባካችሁ ሙብታችን

አስከብሩልን እናንተም አክብራችሁ ስናጠፋ ከመምታት ይልቅ

ምክሩን ከመሳደብ ከመጮህ ይልቅ አስተምሩን

ይገባናል እኮ ምንም ትንሽ ብንሆን ደግሞም

አትከልክሉን እባካችሁ እንጫወት እንዝለል እንቦርቅ

እንደሰት ጊዜያችን ነው መፈንደቂ

መቦረቂ ትፈቅዱልን ነበር እኮ ሙብታችን

መሆኑን ብታወቁ

## 2.1.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ስም ------------------------------------------ ቡድን-----------

የህጻኑ ስም---------------------------------------------እድሜ--------------ፆታ----------

የመምህሩ ስም-----------------------------------------ግምገማው የተካሄደበት ወር----------------

ስለህፃኑ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ምልክት ያድርጉ

ደረጃዎች

1. የታለመው ብቃት ላይ አልደረሰም/ችም------------------------------------------
2. የታለመው ብቃት ላይ በተወሰነ ደረጃ ላይ አልደረሰም/ችም---------------------------------------
3. የታለመው ብቃት ላይ ደርሷል/አልደረሰችም ------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በየወሩ መጨረሻ ላይ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | **2** | 3 |
| **1.** እራስን መገንዘብ፣ በራስ መተማመንና ራስን የማክበር ስሜት መኖር | | | |
| 1.1 ስማቸውን፣ እድሜያቸውንና ጾታቸውን መናገር ይችላሉ<br>• ስማቸውን፣ እድሜያቸውንና ጾታቸውን መናገር መቻል | | | |
| 1.2 አዲስ ጓደኛን ማፍራትና መወዳጀት ይችላሉ<br>• አዲስ ጓደኛን መተዋወቅና መወዳጀት መጀመር | | | |
| **2.** የሰውነት ክፍሎችን መለየትና ጥቅማቸውን መናገር | | | |
| 2.1 የሰውነት ክፍሎቻቸውን መጥራት ይችላሉ<br>• የሰውነት ክፍሎቻቸውን ሲጠየቁ ማሳየትና በስም መጥራት መቻል | | | |
| 2.2 በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው የሚያከናውኑትን ተግባራት መናገር ይችላሉ<br>• በተለያዩ የሰውነት ክፍሎቻቸው የሚያከናውኗቸውን ተግባራት ማወቅ መቻል | | | |
| **3.** ዓይኖችን መንከባከብ | | | |
| 3.1 ዓይኖቻቸውን መንከባከብ ይችላሉ<br>• የዓይንን ጠቀሜታ መረዳትና መናገር መቻል | | | |
| **4.** ጆሮዎችን መንከባከብ | | | |
| 4.1 ጆሮዎቻቸውን መንከባከብ ይችላሉ<br>• የጆሮን ስእል ቀለም መቀባትና የቀቡትን የጆሮ ስእል ምንነት መናገር መቻል | | | |
| **5.** የማሽተት ስሜት ሕዋስን መጠቀምና አፍንጫን መንከባከብ | | | |
| 5.1 በማሽተት የተለያዩ ነገሮችን ሽታ መለየት ይችላሉ<br>• የአፍንጫን ጥቅም መናገር መቻልና ስለተለያዩ ሽታዎች ለመግለፅ መሞከር | | | |
| **6.** የመቅመስ ስሜት ሕዋስን መጠቀምና አፍን መንከባከብ | | | |
| 6.1 የተለያየ ጣእም ያላቸውን ምግቦች መለየትና መናገር ይችላሉ<br>• ምላስ የት እንደሚገኝ መናገር መቻልና የምላስን ስእል ተገቢውን ቀለም መቀባት መቻል | | | |
| 6.2 አፋቸውን በጥንቃቄና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ<br>• የጥርስን ጥቅም መናገር መቻል | | | |
| **7.** በመዳሰስ ነገሮችንና ሁኔታዎችን መግለፅ | | | |

| | | | |
|---|---|---|---|
| 7.1 በመዳሰስ ሙቀትና ቅዝቃዜን መለየት መቻል | | | |
| **8.** ጤናን መጠበቅና የአጠባበቅ ሥርዓቶችን መለማመድ | | | |
| 8.1 የአመጋገብ ሥርዓትን ይለማመዳሉ<br>• ተገቢ የዓመጋገብ ሥርዓቶችን ማወቅ መቻል | | | |
| **9.** አካልን በጥንቃቄ መያዝና መንከባከብ | | | |
| 9.1 አካላቸውን መጠበቅና በእንክብካቤ መያዝ ይችላሉ<br>• በአካላቸው ላይ ጉዳት ሊያስከትሉ የሚችሉ ነገሮችን መለየት መቻል | | | |
| **10.** ጉልህና ረቂቅ /ትላልቅና ትናንሽ/ ጡንቻዎችን መጠቀም | | | |
| 10.1 የሰውነት ክፍሎቻቸውን ለተለያዩ ተግባራት መጠቀም ይችላሉ<br>• የሰውነት ሚዛንን ጠብቆ መራመድ መቻል | | | |
| **11.** በነፃነት ፈጠራን መግለፅ | | | |
| 11.1 አካላቸውን በመጠቀም ሀሳባቸውን ይገልፃሉ<br>• መዝሙርን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት መዘመር መቻል | | | |

### **2.2.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ስም ------------------------------------------- ቡድን-----------

የህጻኑ ስም----------------------------------------------እድሜ--------------ፆታ----------

የመምህሩ ስም-----------------------------------------ግምገማው የተካሄደበት ወር----------------

ስለህፃኑ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ምልክት ያድርጉ

ደረጃዎች

1. የታለመው ብቃት ላይ አልደረሰም/ችም -------------------------------------------

2. የታለመው ብቃት ላይ በተወሰነ ደረጃ ላይ አልደረሰም/ችም----------------------------------------

3. የታለመው ብቃት ላይ ደርሷል/አልደረሰችም -----------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በየወሩ መጨረሻ ላይ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 |
| 1. በአካባቢ ያሉ ሰዎችን መመልከት፣ ለማወቅ ፍላጎት ማሳደርና መለየት | | | |
| 1.1 አብረዋቸው የሚጫወቱትንና በዙሪያቸው የሚያገኟቸውን ሰዎች በስም መጥራት ይችላሉ /ጓደኛን፣ ወላጆችንና የሚንከባከቧቸውን/<br><br>አብረዋቸው የሚጫወተቱትን ህፃናት በመልክና በስም መለየት መቻል | | | |
| 1.2 ተቀባይነት ያለውን ባህሪ ማሳየትና አብረው መጫወት ይችላሉ<br><br>ሀሳባቸውን በሚገልፁበት ወቅት ተገቢ የአነጋገር ስርዓትን ተከትሎ መናገር መልመድ መቻል | | | |
| 1.3 ስለጓደኞቻቸውና አብረው ስለሚውሏቸው ሰዎች መግለፅ ይችላሉ<br><br>የቤተሰብ አባላትን መለየትና መግለፅ መቻል | | | |
| 2. ጥንቃቄና እንክብካቤ የሚያደርጉላቸውን ሰዎች መለየትና እንዴት እንደሚንከባከቧቸው ማወቅ | | | |
| 2.1 ስለሚጠነቀቁላቸውና ስለሚንከባከቧቸው ሰዎች መናገር ይችላሉ<br><br>ወላጆችና መምህራኖቻቸው እንዴት እንደሚንከባከቧቸው መናገር መቻል | | | |
| 3. ሌሎችን መንከባከብና ያለን ነገር ማካፈል | | | |
| 3.1 በቡድን ስራ ውስጥ መሳተፍን ይለማመዳሉ<br><br>ከሌሎች ጋር በጋራ ተስማምቶ መስራት መቻል | | | |

### **2.3.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ስም ------------------------------------------ ቡድን-----------

የህጻኑ ስም----------------------------------------------እድሜ--------------ፆታ----------

የመምህሩ ስም-----------------------------------------ግምገማው የተካሄደበት ወር----------------

ስለህፃኑ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ምልክት ያድርጉ

ደረጃዎች

1. የታለመው ብቃት ላይ አልደረሰም/ችም -----------------------------------------

2. የታለመው ብቃት ላይ በተወሰነ ደረጃ ላይ አልደረሰም/ችም --------------------------------------

3. የታለመው ብቃት ላይ ደርሷል/አልደረሰችም ------------------------------------------

ማሳሰቢያ፡- የክትትል ሠንጠረዡ በየወሩ መጨረሻ ላይ መሞላት ይኖርበታል፡፡

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | **2** | 3 |
| **1.** መረጃዎችን በአግባቡ ማዳመጥና ለተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢውን ምላሽ መስጠት | | | |
| 1.1 ለተለያዩ ድምፆችና ትዕዛዞች ምላሽ መስጠት ይችላሉ<br>• የሰሙትን ድምፅ አስመስለው ማውጣት መቻል | | | |
| 1.2 የተለያዩ ድምፆችን በማዳመጥ መለየትና አቅጣጫዎችን መጠቀም ይችላሉ<br>• የድምፁን አቅጣጫን በመከተል ነገሮችን ፈልጎ ማግኘት መቻል | | | |
| 1.3 አጫጭር ተረቶችንና መዝሙሮችን በማዳመጥ መልሰው መናገርና መዘመር ይችላሉ<br>• ተረትን አዳምጠው ከተረቱ ለወጡ ጥያቄዎች ተገቢውን መልስ መስጠት መቻል | | | |
| **2.** በተለያዩ ሁኔታዎች በራስ በመተማመን በተገቢውና ትርጉም ሊሰጥ በሚችል ንግግር እና የምልክት ቋንቋ መግባባት | | | |
| 2.1 ቀላል ትዕዛዞችንና መመሪያዎችን መከተል ይችላሉ<br>• "ወፊቷን እሆናለሁ" እና "አሻንጉሊቴ" መዝሙርን ከአካላዊ እንቅስቃሴ ጋር በማቀናጀት መዘመር መቻል | | | |
| **3.** በማንበብ መደሰት፤ ዕውቀት ማግኘትና መረዳት | | | |
| 3.1 ስዕሎችንና ቅርፆችን በማየት መለየት ይችላሉ<br>• ተመሳሳይ ነገሮችን መለየትና ማዛመድ መቻል | | | |
| **4.** የዓይንና የእጅ እንቅስቃሴ ቅንጅትን በማዳበር ለጽሁፍ መዘጋጀት | | | |
| 4.1 የዓይንና የእጃቸውን እንቅስቃሴ ማቀናጀትን ይለማመዳሉ<br>• ስእሎችን ቀለም መቀባትና የቀቡትን ስእል ምንነት መናገር መቻል | | | |

## 2.4.5 የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ስም ------------------------------------------ ቡድን-----------

የህጻኑ ስም----------------------------------------------እድሜ--------------ፆታ----------

የመምህሩ ስም-----------------------------------------ግምገማው የተካሄደበት ወር----------------

ስለህፃኑ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ምልክት ያድርጉ

ደረጃዎች

1. የታለመው ብቃት ላይ አልደረሰም/ችም ------------------------------------------

2. የታለመው ብቃት ላይ በተወሰነ ደረጃ ላይ አልደረሰም/ችም --------------------------------------

3. የታለመው ብቃት ላይ ደርሷል/አልደረሰችም ------------------------------------------

ማሳሰቢያ ፦ የክትትል ሠንጠረዡ በየወሩ መጨረሻ ላይ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | **2** | 3 |
| **1.** የቁሳቁሶችን ባህሪ መፈተሽ መረዳትና መለየት | | | |
| 1.1. ነገሮችን በዓይነትና በቅደም ተከተል ማስቀመጥ ይችላሉ<br>• ክብ፣ጎነ ሶስትና ካሬን ቅርፆች መጠሪያ ስምን ማወቅ | | | |
| **2.** ነገሮችን በባህሪያቸው መሠረት ማወዳደር | | | |
| 2.1. በነገሮች መካከል ያለዝምድናን ቅደም ተከተል በጠበቀ መልኩ ማሳየት ይችላሉ<br>• ቁሶችን በመጠናቸው መለየት መቻል | | | |
| **3.** ቁጥሮችን ማስተዋወቅ፣ መግለጽ፣ ዝምድናቸውን መረዳት እና ቀላል ስሌቶችን መስራት | | | |
| 3.1. የአንድ ለአንድ ግንኙነትን ማሳየት ይችላሉ<br>• ተመሳሳይ ነገሮችን ቀለም በመቀባት ማዛመድ መቻል | | | |
| 3.2. ቁሳቁሶችን መቁጠር ይችላሉ<br>• ከ 1-10 ያሉትን ቁጥሮች በቅደም ተከተል መቁጠር መቻል | | | |
| 3.3. ብዛትን መጨመርና መቀነስ ይችላሉ<br>• በደረጃቸው የመጨመርን/ የመደመርን/ ጽንሰ ሀሳብ መረዳት መቻል | | | |
| **4.** በተለያዩ ሁኔታዎች ተገቢ የሆኑ የመለኪያ መስፈርቶችንና መሣሪያዎችን መጠቀም | | | |
| 4.1. በሁለት ቁሶች መካከል የሚታዩ የመጠን ልዩነቶችን መናገር ይችላሉ<br>• የቁሶችን መጠን ረዥምና አጭር በማለት መግለፅ መቻል | | | |
| **5.** የጊዜ ፅንሰ ሐሳብ መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም፣ | | | |
| 5.1. በጊዜ ውስጥ የሚከናወኑ ተግባራትን መለየትና መከተል ይጀምራሉ<br>• ስእልን በማየት በእለት የሚከናወኑ ተግባራትን መናገር መቻል | | | |
| **6.** የቦታ ጽንሰ ሐሳብ መረዳትና መገለጫዎቹን መጠቀም | | | |
| 6.1. ሰዎችንና ነገሮችን መሰረት በማድረግ ቦታንና ርቀትን መግለጽ ይችላሉ<br>• ቦታን ገላጭ ቃላትን ላይና ታችን መለየት መቻል | | | |
| **7.** ገንዘብን መተዋወቅ፣ መለየት፣መግለጽና መጠቀም | | | |
| 7.1. ሳንቲምና ብርን ይለያሉ<br>• ሳንቲምና ብርን መለየት መቻል | | | |

**2.5.5** የምልከታ መከታተያ ቅጽ ናሙና

የቅድመ መደበኛ ትምህርት ቤት ስም ------------------------------------------ ቡድን-----------

የህጻኑ ስም-----------------------------------------------እድሜ--------------ፆታ----------

የመምህሩ ስም------------------------------------------ግምገማው የተካሄደበት ወር----------------

ስለህፃኑ ምልከታውን ከሚከተሉት ደረጃዎች የአንዱን ደረጃ ቁጥር ብቻ በመስጠት በቅፁ ውስጥ ምልከታ በሚለው ስር ምልክት ያድርጉ

ደረጃዎች

1. የታለመው ብቃት ላይ አልደረሰም/ችም -------------------------------------------------------------
2. የታለመው ብቃት ላይ በተወሰነ ደረጃ ላይ አልደረሰም/ችም---------------------------------------
3. የታለመው ብቃት ላይ ደርሷል/አልደረሰችም ------------------------------------------

ማሳሰቢያ፦ የክትትል ሠንጠረዡ በየወሩ መጨረሻ ላይ መሞላት ይኖርበታል።

| መድረሻ/ግብ | ምልከታ | | |
|---|---|---|---|
| | 1 | 2 | 3 |
| **1.** የቅርብ አካባቢን መፈተሽና ማወቅ | | | |
| 1.1 ስለመኖሪያ ቤታቸውና በቤታቸው ስላሉ ቀሳቁሶች መናገር ይችላሉ<br>• የተለያዩ የቤት አይነቶችን በስማቸውና በቅርፃቸው መለየት መቻል | | | |
| 1.2 በቤታቸውና በቅርብ አካባቢያቸው ያሉትን ሰዎች፣ እንስሳቶች፣ አትክልቶች፣ ቁሳቁሶችን ፣ ነፍሳቶችን ሌሎች ነገሮችን መለየት ይችላሉ<br>• በቤታቸው አብረዋቸው የሚኖሩ ሰዎችን በስም መጥራት መቻል | | | |
| 1.3 በቅ/መ/ት/ቤት የሚገኙትን ሰዎች መጫወቻዎችና ሌሎች ነገሮች መለየት ይችላሉ<br>• የሚማሩበትን አፀደ ህጻናትና የመማሪያ ክፍላቸውን በስምና በማየት መለየት መቻል | | | |
| **2.** በአካባቢ የሚገኙትን አስፈላጊ ቦታዎች ማወቅና ማድነቅ | | | |
| 2.1 በአካባቢያቸው ስለሚገኙት አስፈላጊ ቦታዎች መናገር ይችላሉ<br>• በአካባቢያቸው የሚገኙ አገልግሎት ሰጪ ቦታዎችን ስማቸውንና አገልግሎታቸውን መናገር መቻል | | | |
| | | | |
| 3.2 ቤታቸውንና አካባቢያቸውን የማፅጃ መንገዶችን መጠቀም ይችላሉ<br>• የአካባቢን ንፅህና መጠበቂያ ቁሳቁሶችን ስማቸውንና አገልግሎታቸውን መናገር መቻል | | | |
| **4.** በአካባቢ የሚገኙ አደገኛ ነገሮችን መለየትና ጥንቃቄ መውሰድ | | | |
| 4.1 በአካባቢ ያሉ አደገኛ ነገሮችና ሁኔታዎችን መለየት ይችላሉ<br>• በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን መለየታቸውንና ራሳቸውን እንዴት መጠበቅ እንዳለባቸው መረዳት መቻል | | | |
| **5.** የእንቅስቃሴን ጽንሰ ሃሳብ መረዳትና ሙከራ ማካሄድ | | | |
| 5.1 በአካባቢ ስለሚገኙ ነገሮች እንቅስቃሴ መግለጽ ይችላሉ<br>• እቃዎችን በማንከባለል ባህሪያቸውን መናገር መቻል | | | |
| **6.** በስነ ስዕልና ቅርፃ ቅርጽ የተለያዩ ነገሮችን መፍጠር ማድነቅና ራስን መግለጽ | | | |
| 6.1 የዓይንና የእጆቻቸውን እንቅስቃሴ በማቀናጀት የተለያዩ ነገሮች መሥራትን ይለማመዳሉ<br>• የፈለጉትን ነገር መሳልና መቀባት እንዲሁም ለሳሉት ስእል ስያሜ መስጠት መቻል | | | |